

## የአዲስ ዓመት መዝሙር

_አሠርገወ ሰማይን በብሩሃን (ጽዱላን) ከዋክበት (2 X)
ከጥንት ምድርን ያስጌጠ በሥነ ጽጌያት
ዘእምልዑላን ልዑል አማላክ አማልክት (2 X)

ደስ ይበልሽ እመ ብርሃን ዘይብለኪ መልአክ
ካንቺ የሚወለደው አምላክ ወልደ አምላክ
ስሙ የተቀደሰ ለዘለዓለም ቡሩክ ። (2 X);

አዲስ ሕይወት ስንጀምር በዚህ አዲስ ዓመት (2 X)
በምድር እንዲበዛልን ጸጋና በረከት
ስለኢትዮጵያ ሰላም ሰአሊ ለነ ቅድስት ! (2 X)

**መግቢያ**--ጸሎት ብሂል"ተናግሮ-ምስለ ግዚአብሔር= ጸሎት- ከእግዚአብሔር ጋር -መነጋገር ማለት ነው:: ለምሳሌ-ሐና--ስትጸልይ-በልብዋ-ከእግዚአብሔር-ጋር-ትነጋገር ነበር (1 ሳሙ1:12 ):: ነቢዩ ዳንኤልም "በጸሎት ከእግዚአብሔር-ጋር-ስነጋገር-፡ ቀድሞ በራእይ አይቼው የነበረ መልአክ ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ" ይላል (ዳን 9፡ 21) :: በቀን ሦስት ጊዜ መጸለይ እንደሚገባ "ዘወትር ጠዋት፡ዕኩለ ቀንና-ማታ-ችግሬንና-ሐዘኔን በመግለጥ- በጸሎት- ወደ- እግዚአበሔር እጮሃለሁ" ይላል -መዝ. 54፡ 12:: በቀን 7 ጊዜ መጸለይ እንደሚቻል--"ስብዐ ለዕለትየ እሴብሐከ= በቀን-ሰባት-ጊዚ-በጸሎት-አመሰግንሃለሁ"-ይላል (-መዝ 118፡ 164):: አንዳንድ ፈተና ሲያጋጥም ከአንድ ሰዓት በላይ መጸለይ እንደሚገባ "ከእኔ ጋር አንድ-ስዓት- በጸ-ሎት-መትጋት-አቃታችሁን?'ይላል*(ማቴ-26:-40-) ምን_ጊዜምአዛውትሮ_ሳይሰለቹ_መጸለይ እንደሚገባ ቅ/ሉቃስ በጻፈው ክፍለ ወንጌል 11፡9-13 -እና ምዕ.18፡ 1-8 ያስረዳል:: የዚህም መጽሐፈ ጸሎት አቀራረብ ምሳሌነት (ሞዴል) የተወሰደው ከዘጠኙ ኪዳናት ጸሎትና በሐዋርያት ሥራ ምዕ 4፡ 24 -31 የተጻፈውን ትምህርታዊና ልዩ ትርጓሜ የተከተለውን የሐዋርያትን የማኅበር ጸሎት መሠረት በማድረግ ነው:: እያንዳንዱም ክፍለ ጸሎት ከቅዱሳት መጻሕፍ መነሻ ጥቅሶች አሉት:: ስለዚህ ዝግጅቱ እጥር፡ ምጥን፡ ብጥር፡ ንጥር ብሎ የተቀናበረ ፍጹ8ም መጽሐፋዊ እንጂ የልብ ወለድ ድርሰት አይደለም::



www.ethiopianorthodox.org

## ፩ /1 በአዲስ ዘመን መለወጫ ዕለት ቤተሰባዊ ምስጋና

(Thanksgiving)----ፈነወኒ-እስብክ_ዓመተ-እግዚእብሔር-ኅሪተ የተመረጠችውን የጌታን_ዓመተ ምሕረት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል' (ሉቃ-4፡19)።ዘመናትን ሁሉ የምትለውጥ፡ አንተ ግን ለዘለዓለሙ- የማትለወጥ፡ ቀንና ሌሊትን፡ በጋ ክረምትን የምታፈራርቅ፡ የምሕረት አምላክ ሆይ ተቀዳሚ፡- ተከታይ በሌለው በአንድ ውድ ልጅህ -በጌታችን አምላካችን መድኃታችን ኢየሱስ-ክርስቶስ ለደህንታችን የመረጥሃትን ዓመተ ምሕረት በወንጌል-ስላወጅህልን-ቅዱስ-ስምህ ይመስገን- !ባለፈው ዓመት ያንተ ጸጋና በረከት፡ ረድኤትህም ሁሉ ሳይለየን በሰላምና በጤና ጠብቀህ እንደገና ወደዚህ አዲስ ዘመን ስላሸጋገርኸን ለገናናው ስምህ-የምናቀርበውን ጽሎትና ምስጋና እንድትቀበልልን ፈቃድህ ይሁን። በዚህም አዲስ ዓመት- እንደገና አዲስ ሕይወት ስንጀምር እንደ ወዳጅህ እንደ-አብርሃም- አንተን ደስ በሚያሰኝህ ቅን መንፈስ በፊትህ መመላለስ እንድንችል በንስሐ የመታደስን ጸጋ አብዛልን። በዚህ ዓመት የተዘራውን ሰብልና የአትክልቱን ፍራ ሁሉ ባርክልን ። ለሀገሪቱ ሕዝብ ሰላምንና የፍቅር አንድነትን-ስጥልን።የርስ_በርስ-አለመግባባትን-መንፈስ አርቅልን። በመላ ሀገራችን የተጀመረውን የልማት ዕድገት ሁሉ ባርክልን።

_ዝናመ ምሕረት ጠለ በረከት ሰጥተህ ሕዝባችን በልጽጎ ለማየት-አብቃን። የኑሮ ፈተና የበዛበት ይህ ሕዝብ ከዓለም ማኅበረሰብ እርዳታ ተቀባይነት ነጻ መውጣት የሚችልበትን የብልጽግና መንገድ እንድትከፍትለት-ፈቃድህ- ይሁን።- የመንፈስ-ደስታ-የሚገኝበትን-ሰላም-ስጠን። የመፅናናትን-መንፈስ አታርቅብን። የሰላም-አምላክ ሆይ ! እንደ በደላችን፡ -እንደ ኃጢአታችን፡ እንደ ስንፍናችንም ብዛት ሳይሆን እንደቸርነትህ በጸጋህ አስበን። ቤተሰባችንን-ጠብቅልን።ሕፃናቱን-አሳድግ፡ ሽማግሎችን አበርታ።ጤንነታችንን ባርክህ ያለድካምና ያለ ሐኬት እናመሰግንህ ዘንድ ብርታትን ስጠን። በአወጣጣችንና በአገባባችን ሁሉ የአንተ ጥበቃ-አይለየን።ከመከራ-ሥጋ፡-ከመከራ-ነፍስ፡-ጠብቀን። ከቍጥር-ሳጐድል-ለመጪው-ዓመት-በሰላም-



አድርሰን፡-ምንጊዜም-በረድኤትህ-አትለየን-የሰጠኸንን-ሀብት ንብረት ሁሉ ባርክልን፡ አሜን !

## ፪ /2. የግል ሕይወትን የሚመለከት የምስጋና ጸሎት

እምከርሠ-እምየ አንተ-አምላኪየ=ከእናቴ ማሕፀን ጀምሮ ጠባቂዬ የሆንህ አምላኬ እግዚብሔር ሆይ! ከሕፃንነት ጊዜዬ ጀምሮ ተከባክበህ፡ ካደጋም ሁሉ--ጠብቀህ፡ አሳድገህ፡ በሕይወቴ ዘመን ስላደረግህልኝ ድንቅ ነገር ሁሉ ለቅዱስ ስምህ ምስግናን ክብር ይሁን ። በቅዱስ ቃልህ ትእዛዝ በፈጠርህልን በዚህ ግዙፍ ዓለም ከትንሽነትዋ የተነሣ ትንኝን እንኳ ሳትረሳ ፍጥረትህን ሁሉ ከትንሽ 'እስከ ትልቅ የምትጠብቅና የሁሉም መጋቢ አንተ ነህ። ላንተ የሚሳንህ ምንም ነገር የለም።

"አንተ አምላኩ የሆንክለት-ሕዝብ ብፁዕ ነው"-ተብሎ እንደተጻፈ በአንተ አምኜ.-አንተን ተስፋ አድርጌ ባሳለፍሁት ዘመን ሁሉ ከብዙ ችግርና ከፈተናም ጠብቀህ 'ይኸው እዚህ አድርሰኸኛል። የሕይወቴ-ዋስ-ጠበቃ፡-አለንታዬ-አንተ-ነህ።-እናትና-አባት ለልጆ ቻቸው-ከሚያስቡላቸውና ከሚጠነቀቁላቸው በላይ -አንተ-እኔን እንደ በኸር ልጅ አድርገህ ስለጠበቅኸኝ ላመሰግንህ ይገባኛል። ከዚህም ሁሉ በላይ ደግሞ የበደሌን ብዛት- ሁሉ በውድ- ልጅህ ደም-አጥበህ፡--በርሱ-መሥዋዕትነት-የኃጢአትን-ሥርየት ሰጥተኸ ኛል። ምንጊዜም ወደ- ፈተና- ከመግባት- ጠብቀኝ። በሕይወቴ ውስጥ-የሚያስጨናቀኝን- ከንቱ አሳብ ሁሉ አውጥተህ በቅዱስ መንፈስህ ጸጋ የመፅናናትና የመረጋጋትን--ሰላም ስጠኝ፡ ዛሬም ዘወትርም፡-ለዘለዓለሙ አሜን !

## ፫/3.- የንጹሐንን ደም የሚበቀል የፍትሕ አምላክ

(መዝ. 9፡12) እስመ ተዘከረ ዘይትሐሠሥ ደሞሙ፡ ወኢረስአ አውያቶሙ ለነዳያን=ተብሎ_እንደተ ጻፈ፡_የችግረኞችን ጩኸት ቸል-የማትል፡የንጹሐንንም ደም ተመራምረህ የምትበቀል የፍትሕ አምላክ ሆይ ! ያለ ፍትሕ በከንቱ የፈሰሰ የእልፍ፡ አእላፍ ወገኖቻችን ደም: ደመ ከልብ ሆኖ



www.ethiopianorthodox.org

እንዳይቀር ለፍትሕ ዳኞች ሁሉ የማስተዋልን ጥበብ ስጥልን። ከደም አፍሳሽ ወራሪ-ጠላት፡ ካሸባሪ አደጋና ከመቅሠት ሁሉ- ሠውረን ። ፍትሕ- አልባ የሙስና አሠራርን ከምድራችን-ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት ሁሉ-ባርክልን።በሁኑ-አስቸጋሪ-ዘመን ከሌሎች አንዳንድ የአፍሪቃ-አህጉር-በተለየ ሁኔታ እኛን ኢይትዮጵያውያን ሕዝብህን በተረጋጋ ሰላም- ስለጠበቅኸን ቅዱስ ስምህ የተመሰገነ ይሁን። አቤቱ ስለበደላችን ብዛት ለደም አፍሳሽ ጠላት አሳልፈሽህ አትስጠን። ከጦርነት ሥጋት ፡ ከዝናም እጥረት፡ ከምድር መናወጥ፡ ከአባር፡ ከቸነፈር፡ከማይፈወስ ደዌና ከሕመም-ሁሉ-እንድትታደግን-ፈቃድህ-ይሁን። አንተ-በመለኮታዊ ጥበብህ ሁሉን ነገር- እንድታስተካክለውና- የተፈጥሪን ቀውስ ሥርዓት አሲዘህ አገራችንን በረከትና ብልጽግና የመላባት አድርግልን።በመንግሥትህ_የወንጌል-ቃል -ከጻድቁ-ከአቤል ደም- ጀምሮ-በቤተ-መቅደስና-በመሠዊያው--መካከል-በከንቱ እስከተ ገደለው እስከ ዘካርያስ_ወልደ በራክዩ ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰ ንጹሕ ደም የሚያስከትለው ፍዳ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ በቅዱስ ቃልህ ተነግሯ`ል። በሀገራችንም በተለይ በማርክሲስቱ ደርግ ዘመን የፈሰሰ ንጹሕ ደም ከሚያመጣው ፍዳ ጠብቀን። በዓለም ዙሪያ_ከጦርነትና ከሕዝብ_እልቂት ወሬ ይልቅ ሰላምን የሚያበሥር ዜና የምንሰማበትን ዘመነ ሣህል- ወምሕረት-አብዛልን።-ለመሪዎችና-ለፍትሕ-ዳኞችም-ሁሉ-ትክክለ ኛውን የፍትሕ፡ ርትዕ ጥበብ ስጣቸው። ሀገረ-እግዚአብሔር- ኢትዮጵያ እጆችዋን- ወደ አንተ-ስትዘረጋ በምሕረትህ-አስባት።- ሕዝብዋንም ሁሉ ጠብቅልን።የምሕረትህ-በሮች-እንዲከፈቱ- አድርግልን። ገጸ ምሕረረትህንም አብራልን። በዓይነ ምሕረትህ- ተመልከተህ የሕዝብህን በደል ሁሉ ይቅር በል፡ <u>አሜን !</u>

## ፬/4.- <u>በክርስቶስ የተባረከ ቤተሰባዊ ሕይወት</u>

"ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑበት ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው" ( ዮሐ.1፡12 )። ሰውን በአርአያ



ህና- በአምሳልህ ፈጥረህ "ብዙ፡ተባዙ፡ምድርንም ሙሏት" ብለህ- የሰጠኸው- መለኮታዊ- ትእዛዝና ቃለ በረከት ሳይለወጥ-እነሆ ለብዙ ሺህ-ዘመናት እንደፀና የሚኖር ነው። -በአንተ-አምነን በክርስቶስ የጸጋ ልጅነትን አግኝተን፡ የሰማያዊ መንግሥትህ ዜጎችና ቤተሰብ እንድንሆን ፈቅድህልናል። ስለዚህም ሁሉ ስምህ ይመስገን። የበደላችንን ብዛት ሳታስብ በምሕረትህ ስላቀረብኸን-ቅዱስ_ስምህን-እናመሰግንለን።"አንተ--በደሉን የማት ቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው" ተብሎ እንደተጻፈ፡ እኛ ጠላቶችህ ስንሆን በደላችንን ሁሉ በልጅህ ደም አጥበህ በቸርነትህ ስለወደድኸን ድንቅ የፍቅር አምላክ- መሆንህን እናምናለን። "የምድር-አሕዛብ-ሁሉ- በዘርህ- ይባረካሉ"-ብለህ- ለወዳጅህ ለአብርሃም -በሰጠኸው የተስፋ ቃል መሠረት ውድ-ልጅህ ከአብርሃም-ዘርዐ-ትውልድ-የነሣውን-ሥጋ-ተዋሕዶ፡ወደ-ዓለማችን እንዲመጣ-ቅዱስ-ፈቃድህ ሆኖልናል። እርሱም እስከ--መስቀል- ሞት-ድረስ-እኛን የወደደበት ፍቅሩ፡ እጅግ- ድንቅ-ነው።_ስለዚህ- -አገልጋይህ--መስፍን--ኢያሱ--"እኔና-ቤተሰቤ እግዚአብሔርን- እናመልካለን" ብሎ እንደተናገረ፡ የእኛና የቤተሰባችንም ሁሉ ምርጫ ይኸው ብቻ-እንዲሆን-እርዳን። ከሰማይ በታች ከውድ- ልጅህ ከክርስቶስ በቀር እንድንበት-ዘንድ- የተሰጠ ሌላ- ስም እንደሌለ በቅዱስ-ቃልህ -(የሐዋ-ሥ-4፡ 12) በተነገረው እናምናለን። ውድ ልጅህ የከፈለውን የሕይወ -መሥዋዕነት በማሰብ፡ በቅዱስ- ቃልህ እየተመራን በፍቅርህ ፀንተን እንድንቆም በቸርነትህ እርዳን፡ ዛሬም፡ ዘወትርም ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፭ /5. <u>የእግዚአብሔር ቸር ጠባቂነት</u> ( መዝ. 22፡1 -6 )

ቸር-እረኛ (ሊቀ ኖሎት) ሆነህ በጽድቅ መንገድ የምትመራንና የምትጠብቀን ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በጎቼ ድምፄን -ይሰማሉ፡ እኔም አውቃቸዋለሁ፡ እነርሱ ይከተሉኛል፡- እኔም የዘለዓለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ' ብለህ እንደተናገርህ፡ እነሆ እኛ ሁላችን-የመሠማሪያህ በጎች ነን።ቃልህን እንሰማለን። ነገር ግን ይህ የምንኖርበት-ሥጋዊ ዓለም ብዙ ዓመፅና ተንኮል፡ ምቀኝነትና-የክፋት ዘር ሁሉ የሞላበት፡ የፍትሕ ርትዕ መዛበት፡



www.ethiopianorthodox.org

ለቅሶና ዋይታ የበዛበት፡ ድህነትና-ጕሥቍልናም የበረከተበት ከመሆኑ-የተነሣ ሕይወት ራስዋ ምድረ-በዳ መስላ የምትታይበት ጊዜ ይበዛል። _ከሰላም ማጣትና ከፍቅር እንድነት መቀዝቀዝ የተነሣ-ከመንጋህ-ተለይተው እንደባዘኑ በጎች ሆነን እንዳንቀር በፍቅርህ ትሰበስበን ዘንድ እንማፀንሃለን ።

_የእረኞች አለቃ የሆንህ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ! ወደአንተ ወደ ቸር ጠባቂያችን መመለስ እንድንችል፡ የንስሐን ሕይወት ስጠን (1 ጴጥ 2፡ 25 )። የመንጋህ ጠባቂዎች የሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ አንተ የሰጠሃቸውን-አርአያና ምሳሌነት ተከትለው በማስፈራራት ሳይሆን በርኅራኄ ቅዱስ ቃልህን እየመገቡ የነፍስ ረሃብና ጥም፡ የሥጋ ምግባር-መራቆትም- እንዳይደርስባቸው ማድረግ-ይችሉ ዘንድ-የመንፈስ ትጋትን ስጣቸው።_ከመንጋህ-ተለይተው የተበተኑትን-መመለስ፡ የመንፈስ ስብራት፡ የሞራል ውድቀት /ስብራት የደረሰባቸውንም መጠገን እንዲችሉ ያንተ ኃይለ ረዳኤ ያስፈልጋቸዋል። የመለያየትን መንፈስ ከመካከላ ቸው አርቅ። መንጋህን ያለ ርኅራኄ በኃይል አስገዳጅነት ከሚበትኑ ተኵላዎች መጠበቅ እንዲችሉ መንፈሳዊ ኃይልን ስጣቸው። "መንጋውን በትኖ ለሚጠፋ እረኛ- ወዮለት" -ተብሎ- በነቢዩ -ዘካርያስ -የተጻፈ- ቅዱስ- ቃልህን ማስተዋል ካለመቻል የተነሣ ከመንጋህ መሪዎች ብዙዎቹ በቅዱስ ቃልህ መመራትን ቸል እንዳይሉና ሕዝብህን-ለማስተ-ማር-ያለባቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዲችሉ የመንፍስ ብርታትን ስጣቸው። "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል። "ወካህንኒ ከመ ሕዝብ=ካህኑም እንደ-ሕዝብ ሆነ " ተብሎ" በነቢዩ ሆሴዕ 4፡ 9 ) የተነገረ የትንቢት-ቃል አስፈሪ ነው። ስለዚህም ጌታ አምላካችን ሆይ ! "የልቤን ፈቃድ የሚፈጽሙ እረኞችን እሰጣችኊለሁ፡ እነርሱም በማስተዋል ጥበብ-ይጠብቋችኊል"-ብለሃልና፡ መንጋ-ህን በርኅራኄ-የሚጠብቁ-ዕረኖችን በየጊዜው ለማስነሣት የገባኸውን ቃል አስብ ፡ ዛሬም። ዘወትርም፡ ለዘለዓለሙ፡አሜን !

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,



## ፮ /6. ስለ ምድር አበቦች የሚቀርብ የምስጋና ጸሎት

(Thanksgiving)-"ለእግዚአብሔር-ሕዝብ-እንደ-ጠል እሆናለሁ፥ እርሱም እንደ ተክል ያብባል" (ሆሴ14፡ 6 )። የፍጥረት-ሁሉ አስገኝ የሆንህ ሰማያዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ! ሰማይን በከዋክብት፡ ምድርን በአበቦች ( በሥነ ጽጌያት ) ያስጌጥህበት ጥበብ እንዴት ድንቅ ነው ! የፈጠርህልን ዓለም ራሱ "ብርሃን ይሁን" ብለህ በሰጠኸው ትእዛዝ መሠረት በብርሃን የተሞላ ሆኗል። እንጨቱ ከእንጨት ቢፋጭ፡ ድንጋዩ ከድንጋይ ቢጋጭ እሳት ወለደ ብርሃን ይወጣል። ከዚህ ጋር በከርሠ ምድር ያለው እሳተ ገሞራ፡ በዝናም ጊዜ የሚታይ የመብረቅ ብልጭታ፡ የዕንቍ ማዕድናት የሚያስገኙት ልዩ፡ ልዩ ብርሃን የሚደነቅ ነው። ቶፓዝዮንና ቢረሌ" ከተሰኙት አዕናቍ የሚያብረቀርቅ-አንጸባራቂ ብርሃን ይወጣል። መረግድ ከሚባለው ዕንቍ አረንጓዴ ብርሃን መገኘቱ ዓለማችን በብርሃን የተሞላ መሆኑን-ይመሰክራል።የብርሃን-አምላክ ሆይ! የእኛንም አእምሮ የዕቀት-ብርሃን-የሞላበት-አድርገህ-የማስተዋልን ጥበብ አብዛልን። በአገልጋይህ ነቢይ ዕንባቆም እንደተነገረ፡ ውቅያኖስ በውኃ እንደተ ሞላ፡ ምድርም የአንተን ክብር በማወቅ_ጥበብ የተሞላች ትሁን። አንተ_አማናዊ_ ብርሃን መሆንህን ዓለም_ሁሉ ማወቅ ይችል ዘንድ ቃልህን_ለሚያስተምሩ-አገልጋዮችህ ሁሉ የዕውቀትን ልዩ ብርሃን- ሣልባቸው፡ አማኞችንም ሁሉ የጸጋህ ብርሃን እንዲጕበኛቸው አድርግ። ሁላችንንም በረድኤት-አስበን። -የልጅነት-በደላችንንና፡-የሠራነውን-ኃጢአትና ስንፍናች ንን_ሁሉ ይቅር ብለህ የንስሐ ሕይወት እንዲኖረን የመንፈስን ብርታት ስጠን ።"የኃጢአታቸውን ብዛት ሳላስብ እንዲሁ በነጻ እወዳቸዋለሁ ብለህ የተናገርህ የምሕረትና የርኅራኄ አባት ነህና። አሁንም በጸጋህና በምሕርትህ፡- በረድኤትህ -አስበን። አበቦችን ተከትሎ የሚመጣውን የምድር ፍሮ አዝርዕቱንና አትክልቱን ባርክልን። የልዩ። ልዩ አበቦች መልክ ያለው ሕዝባችን-ምን-ያህል-ታጋሽና -መከራ- ቻይ -ሆኖ እንደ ሌሎች



www.ethiopianorthodox.org

አንዳንድ አህጉር አንድነቱን ሳያፈርስ ያሳለፈውን የብዙ መከራና-የእልቂት ዘመን አስበህ እንድትረዳው ቅዱስ ፈቃድህ ይሁንልን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፯ /7.. ከሐዘን የምንፅናናበት የሕይወት ተስፋ

_ተዘከር እግዚኦ ከመ መሬት ንሕነ =የአባቶቻችን አምላክ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ! የተፈጥሮ ደካማነታችንን ታውቃለህ። አቤቱ እኛ ከመሬት የተገኘን አፈር፡ትቢያ መሆናችንን አስብ። በዘለዓለለማዊ- ሕያው ቃልህ እንደተነገረ፡ የሰው ዘር ሕይወት በዘመኑ ሁሉ እንደ ሣር ነው። እንደ ዱር አበባ ለጊዜው አምሮ፡ ደምቆ ይታያል። ዘግየት ብሎ ግን እንደ ቅጠል ፈጥኖ ይጠወልጋል ። "ሣሩ ይጠወልጋል፡ አበባውም ይረግፋል የጌታ ቃል ግን ለዘለዓለም ይኖራል" ተብሎ ተጽፏልና። መፅናናትን ማግኘት የምንችለው ከቅዱስ ቃልህ በሚገኝ በአንተ ጸጋና ምሕረት ተደግፈን ስንኖር ብቻ ነው። በቅዱስ ቃልህ እንደተነገረ፡ ብንሞትም፡ ብንኖርም-የአንተ ነን።ሞትም ቢሆን ለእኛ ማስፈራሪያ ሆኖ የተሠራ አይደለም። ከሞት ወደ ሕይወት የምንሸጋገርበት-ድልድይ-ነው እንጂ፡ ወይም ወደ አንተ ወደ ሰማያዊ አባታችን የምናርግበት መሰላል መሆኑን መረዳት የምንችልበትን እውቀት አብዛልን። ከሞት በኋላ ሌላ ሐዲስ ሕይወት መኖሩን አምነን፡ ዛሬ ከመካከላችን-በሞት-የተነጠቁ-ወገኖቻችን ሁሉ በክርስቶስ እምነት ፀንተው የኖሩና አሁንም በአንተ ዘንድ ሕያዋን መሆናቸውን አምነን ፡ በዓለም መጨረሻም ከሞት ተነሥተው፡ -በአንተ- ፊት- እንደምናያቸው- በቅዱስ ቃልህ በግልጥ-የተነረውን-የተስፋ ቃል ኪዳን የምናስተ ውልበትን አእምሮ አስፋልንስ። የነፍስ ከሥጋ መለየት ጉዳይ ሳይሆን ዘውእቱ ዳግም ሞት= 2ኛ ሞት" ተብሎ የተጠራው ከአንተ የመራቅ አደጋ እንዳይደርስብን ፡በረድኤትህ ጠብቀን "ክርስቶስ-ለቤዛ-ዓለም-እንደሞተና-እንደተነሣ-ካመንን፡ በክርስቶስ፡ አምነው_የሞቱትን ሁሉ እግዚአብሔር ከሞት አስነሥቶ ከክርስቶስ ጋር-ያመጣቸዋልና-ተስፋ ትንሣኤ እንደሌላቸው- አረማውያን-ሆናችሁ-ልታዝኑ፡-አይገባም"-ተብሎ-የተጻፈ አስተማ



ማኝ የተስፋ ቃልህን ማስተዋል እንድንችል እርዳን። በቀናች-ሃይማኖት-ፀንተን፡ በመልካም ሥነ ምግባር ታንፀን፡ የአንተ ቅዱስ ስም በሕይወታችን እንዲከብርና የአንተ ፍቅር በልባችን ነግሦ እንዲኖር ፈቃድህ ይሁንልን። ከአረማዊ ሥርዓተ ሐዘን ሁሉ ነጻ አድርገን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ..........

## ፰ /8. አምላካዊ ጠለ ምሕረት የሚገኝበት በረከት

_"የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ሕይወት ዛፍ ዕድሜ ይሆናል። እኔም የመረጥኋቸው ቡሩካን ሕዝብ በእጃቸው ሥራ ደስ ብሏቸው ረጅም ዘመን ይኖራሉ" (ኢሳ. 65፡ 22 -23 )። የጽድቅ ባለቤት የሆንህ የአባቶቻችን አምላክ ሆይ ! "ጻድቅ ሰው እንደ ዘንባባ ይለመልማል፡ እንደ ቴምርም ያፈራል፡ እንደ ሊባኖስ-ዝግባም-ያድጋል።ደጋግ-ስዎች-በእግዚአብሔር-ቤት-ተተክለው-በአምላካችን አደባባይ-ይበቅላሉ፡ ያንጊዜም በለመለመ ሽምግልና ፍሬ ምግባር የሚገኝባቸው ይሆናሉ፡ ደስተኞች ሆነው ይኖራሉ፡ፈጣሪዬ እግዚአብሔር እውነተኛ መሆኑን ይመሰክራሉ" ተብሎ እንደተጻፈ፡ ይህን-ለቅዱሳን ጻድቃን የገባኸውን የተስፋ-ቃል ለእኛም እንድትፈጽምልን እንማፀንሃለን። ሕያው ቃልህ ለእኛ ሕይወትን የሚያለመልም ጠለ በረከት ነውና። ምን ጊዜም ቅዱስ ቃልህ ከሚነገርበት ጉባኤና ቅዱስ ስምህ ከሚመሰገንበት ቤተ መቅደስህም ሳይለዩ መኖር እንዴት ድንቅ-ነው! በዘመናችን-ሁሉ ጸጋ የሞላበትን ሕይወት ለማግኘት የሚያስችል የቅዱስ ቃልህን ፍቅር-አጽናልን-ሕይወታችንነ ባርክርህ በአንተ-ጸጋ-የተሞላና እንደ ዘንባባ የሚለመመልም እንደ ቴምር ፍሬ ምግባር ወሃይማኖት የሚገኝበት አድርግ፡ በሽምግልና ዘመናችኝ አትተወን፡-ድንቅ ሥራህን ለመጪው-ተተኪ ትውልድ እስክንነግር ድረስ የንስሓን ጊዜ አስረዝምልን። በሕያው-ቃልህ- የልጆቻችንንን አስተዳደግ ባርከህ፡-የወጣቶችንና የጐልማሶችን አካሂድ አቅና፡ ልዩ፡ ልዩ ፈተና በበዛበት በዚህ ክፉ አስቸጋሪ ዘመን ያንተን ሕግና ሥርዓት የሚጠብቅ ዘርዐ ትውልድ-ማትረፍ-እንድንችል በቸርነትህ እርዳን። የቤተሰባችንም አመራር የተቃና ይሆን ዘንድ ሰላምንና የፍቅር አንድነትን



www.ethiopianorthodox.org

ስጥተህ በጤንነት እንድትጠብቀን ፈቃድህ ይሁን። የዕለት ሥራችንንም ሁሉ ባርክልን። አካሄዳችን ሁሉ በቅዱስ ቃልህ ትእዛዝ በቅን መንፈስ የተቃኘ፡ በቅዱስ ቃልህ ላይ የተመሠረተ ሆኖ እንደወዳጅህ እንደ አብርሃም አንተን ደስ በሚያሰኝህ ሕይወት- በፊትህ_እንድንመላለስ በቸርነትህ ርዳን። ሰይጣን የሚያመጣው ፈተና ሁሉ ወጥመድ እንዳይሆንብንና በሥነ - ምግባር- ጉድለት፡ የልብ- ትዕቢት፡ ግብዝነትም ሁሉ ነፍሳችንንም ሥጋችንንም ለጥፋት የሚዳርግ እንዳይሆን ፡በስዎች ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት ተጠብቀን መኖር እንችል ዘንድ እንደ አገልጋይህ እንደ ነቢዩ ሙሴ የልብን የዋሃት ስጠን። እንደ ልበ አምላክ ዳዊትም ለንስሓ ሕይወት-የሚያበቃ-ንጹሕ-ልብ-ፍጠርልን፡-በቸርነትህም ማረን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን!

## ፱/9 <u>የእግዚአብሔርን ቃል፡ ሁልጊዜ ማንበብና በማሰላሰል</u>

"የዚህ- ሕግ- መጽሐፍ ቃል- ከአንደበትህ -አይለይ" ተብሎ የተጻፈውን ለመፈጸም ዕለት በዕለት፡ ቀንና ሌሊት በማንበብ አሰላስለው፡- ይህን ብታደርግ መንገድህ ሁሉ የተቃና ይሆንልሃል፡ አስተዋይም ትሆናለህ ( መጽሐፈ ኢያሱ 18 ) _ጌታ-እግዚአብሔር-ሆይ! በአገልጋይህም ነቢዩ-ንጉሥ- ዳዊት "በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የሚለውና ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብና የሚያሰላስለው ሰው ብፁዕ ነው። እንደዚህ ያለውም ሰው በፈሳሽ-ውኃ ዳር እንደተተከለችና-ፍሬዋንም በየወቅቱ እንደምትሰጥ፡-ቅጠልዋም-እንደማይረግፍ-ዛፍ- ይሆናል፡የሚሠራውም ሁሉ- ይከናወንለታል" ተብሎ- እንደተጻፈ-ሕወይትን የሚያለመልምና የመንፈስ ፍሬዎች የሚገኙበትን ቅዱስ ቃልህን-የሕይወት-ዋስትና-አድርገህ-ስለሰጠኸን--ስምህ-ይመስገን። ሕይወትን ከሚያጠወልግ ኃጢአትና-ከሞራል ስብራት ጠብቀን ፡፡ሥር-መሠረትንም-ከሚያደርቅ-ከክፉ-አሳብና-ሰይጣን ከሚያመጣው ፈተና ሁሉ ሰውረን። ትእዛዛትህን-ጠብቀን_ቅዱስ ቃልህ፥ _ሕግህን በቀንና በሌሊት ማሰላሰል ማሰብ የምንችልበትን ብርታት ስጠን። በቅዱስ መንፈስህም_ኃይል_አፅናን፡፡-"ጐልማሳ-መንገዱን-በምን ያቀናል?" ቢሉ_የአንደበትህን-ቃል-በመጠበቅ--



ስለሆነ ከትእዛዝህ አታርቀን። በቅዱስ ቃልህ ሕያዋን እንድንሆን የማስተዋልን ጥበብ አብዛልን። ሕያው ቃልህ ሁሉ ከማር ወለላ ይበልጥ ጣፋጭ ስለሆነልን እናመሰግንሃለን ። ቃልህ ከዕንቁ ባሕርይና ከወርቅ የሚበልጥ ዋጋ ያለው መሆኑን በይበልጥ እንድናስተውል እርዳን። ሕይወታችንን የመንፈስ ፍሬ የሞላበት አድርገህ ትባርከው ዘንድ ቅዱስ_ ፈቃድህን _የምንጠይቅበትን-የሃይማኖት- ጸሎት እንደተወደደ ዕጣን መዓዛ አድርገህ ተቀበልልን። በሕያው ቃልህ የእውቀትን መንገድ አስተምረን፡ አንተ ያስተማርከው ሰው ብፁዕ ነው" <u>ተብሎ ተጽፏልና፡ ስለ ስምህ ስትል ስማን፡ አሜን!</u>

## ፲ /10. ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚገኝ የ<u>ሀገር ብልጽግና</u> --

(ዘሌ 26 10 ) በሕጌና በሥርዓቴ ብትመሩና ትእዛዛቴን ብትጠብቁ ምድራችሁ በእህል ሰብል፤ዛፎቻችሁም-ሁሉ-በፍሬ- የተሞሉ-እንዲሆኑ-ዝናምን--በወቅቱ-እሰጣችኋለሁ፡፡-ሰብላችሁ ከመብዛቱ የተነሣ፤የእህል መከር ሰብስባችሁ ሳትጨርሱ፤ የወይን ዘለላ የምትቈርጡበት-ጊዜ ይደርሳል። የወይኑም ዘለላ ተሰብስቦ ሳያልቅ-እህል-የምትዘሩበት-ጊዜ ይደርሳል_። ክፉዎችን አራዊት ከምድራችሁ_ አስወግዳለሁ ። ሰይፍ በምድራችሁ-አያልፍም፡ የሚያስፈራና የሚያስደነግጣችሁ ሳይኖር ያለምንም ሥጋት ትኖራላችሁ። ለምግብ የሚያስፈልጋ ችሁን ሁሉ እያገኛችሁ፣ በምድራችሁ ለዘላለም-በሰላም-ትኖራላችሁ፡-( አሞፅ 9፡ 13 )። እባርካችኋለሁ፤ብዙ ልጆችን እሰጣችኋለሁ። ከዓመት እስከ ዓመት የሚቈይ ሰብል ሰብስባችሁ ለማኖር ባለፈው የመከር ስብሰባ የተትረፈረፈውን አውጥታችሁ ለመጣል ትገደዳላችሁ። _ስንፍናችንንና፣ በደላችን ሁሉ ይቅር ለማለት፡ምሕረት የባሕርይ-ገንዘብህ የሆነ እግዚአብሔር-አምላክ ሆይ ! በቸርነትህ ማረን ። ምድረ ገነት የሆነች አገር ሰጥተኸን ሳለ፡ በመግባባትና በመቻቻል ተደጋግፈንና ተረዳድተን ማልማት አቅቶን፣ የነበራት የተፈጥሮ ጫካ /ደን ተቃጥሎና ተመንጥሮ አልቆ፣ አፈርዋ በውኃ ተጠራርጎ ሲወሰድ ዝም ብለን መመልከታችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለድህነት ስለዳረገን ለጐረቤት አገሮች መዘባበቻ ሆነናል ። ይህን-አስነዋሪ--ስድብ_ለመገደብ-ተባብረን--ስልማት-ሥራ በመነ



www.ethiopianorthodox.org

ሣሣት-ገዳማትና አድባራት -ወደገነትነት-እንዲለወጡ ለማድረግ በፍቅር አንድነትና በመቻቻል የመተሳሰብን መንፈስ_ስጠን ::- "እኔን አምላካችሁን ብቻ በመከተል-ፀንታቹ-ብትኖሩ፡-እኔ- የምትበሉትን-እህልና-የምትጠጡትን-ውኃ--እባርካለሁ፡ ዕድሜያ ችሁን-አረዝማለሁ፡ የበሽታ- ዘሮችንም-ሁሉ-ከመካከላችሁ አርቃ ለሁ" ስትል የተናገርኸውን የተስፋ ቃል ፈጽምልን (ዘፀ 23: 25 -26):: ምሕረትህ ፈጥኖ ይጐብኘን ፡ የቀድሞ በደላችንን አታስብብን:: ስለ ስምህ ስትል በምሕረትህ አስበህ የኃጢአትን ስርየት ስጠን:: ከኑሮ ችግር፡ ከማይፈወስ ደዌና ከአባር ከቸነፈር ሁሉ ጠብቀን፡ አገራችንን የሚቀናቀኑና ሕዝባችንን የሚጠሉ አንዳንድ የቅኝ ግዛት ርዝራዦች እንዲጓደዱብንና- እንዲዘባበቱብ ንም አታድርግ:: በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፡ በሞላ የአፍሪቃ አገሮች የተቸገሩ ወገኖችህን ሁሉ አስብ:: ጌታ አምላካችን ሆይ! ከአፍሪቃ ሕዝቦች መካከል አብዛኞቹ ለኑሮ ችግር፡ ለበሽታና ለጕሥቍልና ተጋልጠው የሚኖሩ እስከ መቼ ነው ? ኢትዮጵያ ውያን ሕዝብህ ምን ያህል ታጋሶችና መከራ ቻዮች እንደሆኑ አስብ:: ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"- ተብሎ እንደተጻፈ፡ የአንተን-ምሕረት-ለማግኘት በጸሎት የሚማፀኑ -ወገኖችህን አትርሳ:: አገራችንንና ሕዝባችንን በዓይነ ምሕረት ተመልከት:: ሰማይ ዝናም ለዘር ፡ ጠል ለመከር ከመስጠት እንዳይገታ አድርገህ የእርሻውን ሰብልና የዛፉን ፍሬ ሁሉ ባርክልን:: ይህ የድህ-ነትና የጕሥቍልና ዘመን አልፎ-ስለ ስምህ ክብር-እልል-እያልን ወደምንዘምርበት ዘመነ ሣህል ወምሕረት እንድታሸጋግረን ፈቃድህ ይሁን:: መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆን ቅዱስ ስምህ ስትል ማረን፡ ጸጋህንም አብዛልን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፲፩/11. አምላካዊ ጸጋና ረድኤት በሽምግልና ዘመን --

"ለነዋኅ መዋዕል አጸግቦ፡ ወአርእዮ አድኅኖትየ=ረጅም ዕድሜን አጠግበዋለሁ:: ማዳኔንም አሳየዋለሁ (መዝ 90:13 ):: አቤቱ አምላኬ ሆይ በአንተ-ታምኛለሁና ከሐፍረት ሁሉ ጠብቀኝ፡ በጽድቅህ ከክፉ- ነገር- ሁሉ አድነኝ:: መሸሸጊያዬና ጋሻ መከታዬ



አንተ ነህ ከዓመፀኞችና ከግፈኞች_አድነኝ:: አንተን_ተስፋ አድርጌአለሁና አምባ መጠጊያ ሁነኝ::በሽምግልና ዘመኔም አትጣለኝ፡ ጉልበቴ-ባለቀ ጊዜ አትተወኝ፡ አቤቱ ጌታ አምላኬ ሆይ ! ከእኔ አትራቅ:: ነፍሴን የሚቃወሟት የሰይጣን ዘሮች ሁሉ-ይፈሩ:: አምላኬ ሆይ ! ከታናሽነቴ ጀምረህ ያስተማርከኝና ያሳደግኸኝ- አንተ ነህ :: ስለዚህም በአገልጋይህ ነቢይ ኢሳይያስ አንደበት" እነሆ እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ፡ እስከ ሽበትም ድረስ እደግፋችኋለሁ" ስትል ያናገርከውን የተስፋ-ቃል-አስብ:: ያለማወቅን-ዘመን-አሳልፈህ_እነሆ_ሁሉ-ከእግዚአብሔር_የተማሩ-ይሆናሉ፡ሕጌን-በኅሊናቸው-አኖራለሁ፡ በልባቸው-ጽላት፡እጽፈዋ ለሁ-እኔ_አምላካቸው-እሆናለሁ፡እነርሱ-ሕዝቤ ይሆናሉ" ስትል ያናገርኸውን የተስፋ ቃል አስበህ- ሽምግልናችንን- ከሚያስነውር ተግባር ሁሉ ጠብቀን:: ጸጋ--በተሞላበት- ሁኔታ-በመልካም-ሽምግልና-ያንተ-ቅዱስ ስም የሚከብርበትን-ተግባር-ማከናወን-እንድችል እርዳን:: በሽምግልና ዘመን ከፉ ነገር ከማየትና ከመስማት ጠብቀን::_ክፉ ቃል-ተናግረን ሰውን ከማሳዘን እንድንጠበቅ-ሕግህንና፡ ሥርዓትህን አስተምረን::"ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል"-_ተብሎ-በአገልጋይህ ነቢይ ሆሴዕ ያናግርኸው አስፈሪ- ትንቢት በእኛ- ላይ- ተፈጻሚ እንዳይሆን የልብህን ፈቃድ የሚፈጽሙ ዕረኞችን፡ የመካሪዎችንና የአስተማሪዎችን፡ የቅን አመራር ሰጪዎች ቍጥር አብዛልን:: _በዕውቀትና በማስተዋል መምራት ይችሉ ዘንድ- የመከፋፈልን-መንፈስ ከመካከላቸው-አርቅ::መንጋህን የሚጠብቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን- በቅዱስ መንፈስህ=እርዳ::ሕዝብህን ለማስተማርና ለማፅናናት እንዲችሉ የማስተዋልን ጥበብ አብዛላቸው:: በሕይወታችን ዘመን--ሁሉ- ቅዱስ ቃልህን በማስተዋል ጥበብ የተሞላ ሕይወት_እንዲኖረን_ ታደርግ ዘንድ-በጸሎት እንማፀንሃለን የጸጋ ምሕረትህን አብዛልን ፡ አሜን !

## ፲፪/12.. አንደበትን ከክፉ ንግግር የመጠበቅ-ጥበብ

_"ወኵሉ ነገር ሕሡም ኢይፃእ እምአፋክሙ=ክፉ ነገር ሁሉ ከአንደበታችሁ-አይውጣ "(ኤፌ-4፡-29):: የባሕርይ ትዕግሥትህና

www.ethiopianorthodox.org

የቸርነትህ ብዛት-ከውቅያኖስ ባሕር ይልቅ የሰፋ፡ የርኅራኄ አባት ጌታችንና አምላካችን መድኃኔ-ዓለም ክርስቶስ ሆይ ! እኛን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት እስከ ቀራንዮ መስቀል በተጓዝህበት የመከራ ዕለት ያን ሁሉ የስድብ ቃል ሲነገሩና በሐሰት ሲመሰክሩብህ፡ ሲዘብቱብህም፡ሁሉን ነገር-ታግሠህ ያን በዚህች-የሕይወት ፈተና በፍጹም ትዕግሥት-እንዳሸነፍህ ቅጽበት-እናስባለን። ይህን ያህል- ትሕትና፡ ይህን ያህልስ ትዕግሥት ፍጹምነቱ እንዴት የሚያስደንቅ ነው ! ይህን ያህልስ ሰውን መውደድና ማፍቀር እንደምን ያለ ፍቅር ነ! "የሰው ፍቅር የእግዚአብሔርን ልጅ ከሰማይ ዙፋኑ-ሳበው፡እስከ ሞትም አደረሰው" ተብሎ እንደተነገረ ለሚያምንብህ የሰው ዘር-ሁሉ ትምህርት የሚሆን ይህን ሁሉ የማይረሳ የተቀደሰ አርአያና ምሳሌነትን ስለሰጠኸን ቅዱስ ስምህ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን።እኛም-ባንደበታችን-ክፉ-ቃል-ተናግረን ማንንም ከማሳዘንና ከማስቀየም፡ የመታገሥን ጥበብ ስጠን። የትዕግሥትንም ልጓም በአንደበታችን አኑር። አንደበታችን በሕዋሳችን ክፉ ዓለም-ሆኖብናል።አገልጋይህ-ሐዋርያ-ያዕቆብ -በመልእክቱ እንደጻፈልን፡ "ምላስ ትንሽ የአካል ክፍል ስትሆን፡ ዓለምን እንደሚያቃጥል የእሳት-ነበልባል ናት። ስለዚህ በሁሉ ነገር የመታገሥንና ከሰውም ሁሉ ጋር በሰላምና በፍቅር አንድነት አብሮ የመኖርን ጥባብ አብዛልን። "ሕይወትን የሚወድና፡መልካም ዘመናትን ማየት የሚፈልግ አንደበቱን ከክፉ ነገር፡ ከንፈሮቹንም ከሽንገላ ቃል ከመናገር ይጠብቅ፡ ሰላምን ይሻት፡ ይከተላትም "ተብሎ የተጻፈ-ቅዱስ-ቃልህን-ማስተዋል-እንድንችል-እርዳን! ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ::

## ፲፫/13.እግዚአብሔር-አምላኩ የሆነለት ሕዝብ <u>ብልጽግና</u>

_"ብፁዕ ብእሲ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር=እግዚአብሔርን የሚፈራ /የሚያከብር ሰው ብፁዕ ነው (መዝ. 33 -0 12 )። ክብር ወብዕል ውስተ ቤቱ= ቤቱም በብልጽግና የተሞላ ነው (መዝ 111:3 )።አንተን የሚወዱ ሰዎች በጉልማሳነታቸው እንደ አዲስ ተክል ናቸው። ሴቶች- ልጆቻቸውም- እንዳጌጠ



እልፍኝ ያማሩና የተወደዱ ናቸው።ግምጃ ቤታቸው ዓይነቱ በበዛ ዕቃ የተሞላ ነው። የበግ መንጋዎቻቸው ብዙ የሚወልዱና- በየመሠማሪያቸውም በአመራባት የሚበዙ-ናቸው። ከብቶቻቸው-የሚሰቡ፡-አጥር- ቅጥራቸው- ስጠላት የማይደፈርና-መውጫ፡-መግቢያውም የማይታወቅ ነው።አደባባያቸው የለቅሶና የዋይታ-ጩኸት ድምፅ የማይሰማበት-ነው"-ተብሎ የተጻፈ ቅዱስ ቃልህን እናስታውሳለን። አንተ አምላኩ የሆንህለት ሕዝብ እንዴት የተባረከ ነው ! ጌታ- አምላካችን ሆይ !-ይህን የመሰለውን የብልጽግና ጸጋና በረከት ሁሉ በተፈጥሮ አስጊጠህና አሣምረህ_በሠራሃት አገራችን ኢትዮጵያ-ላይ እንድታፈስው በጸሎት_እንማፀንሃለን ። ዝናመ ምሕረትን፡ ጠለ በረከን ሰጥተህ ምድሬቱ ፍሬ_በረከት-የሞላባት-እንድትሆን፡ ለእንስሳትና-አራዊት ለሰማይ አዕዋፍም የሚያስፈልጋቸውን ምግብ እንድትሰጣቸው ቅዱስ ፈቃድህ ይሁን። አደባባያችን-ሁሉ-ደስታ የሞላበት፡ እልልታ-የሚሰማበት-እንዲሆን-ከብልጽግና-ጋር-ሰላምን-አብዛልን።

_ያላንተ-መለኮታዊ-ኃይል-ታዳጊ-የሌለንን-ሕዝብህን-ከፈተና ሁሉ እንድትጠብቀን-እንማፀንሃለን።-የርስ_በርስ-አለመግባባት ተወግዶ አንዱ የሌላውን ወገኑን ሀብት፡ ንብረት የመመኘትኛ አንዱ በሌለው ላይ የከንቱ ቅናት _መንፈስ አድሮበት እርስ በርስ ከመባላትና ከመካሠሥ ይልቅ ሁሉም ተባብሮ ሠርቶ በመበልጸግ የነፍስ ወከፍ ድርሻውን በሥራው መጠን አግኝቶ በሰላምና በመቻቻል ተማምኖ በፍቅር አንድነት ለመኖር አብቃው፡ ጸጋና ረድአድኤትህ አይለየው። ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፲፬ /14. በእግዚአብሔር ላይ መተማመኛ ጸሎት

_"እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው የሚያስደነግጠኝና ፡ የሚያስፈራኝስ ማነው ? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛ-ነው። ክፉዎችና-አስጨንማቂዎች የሆኑ ጠላቶቼ-ሥጋዬን-ይበሉ ዘንድ በቀረቡ-ጊዜ በአንተ ኃይል ተሰናክለው ወደቁ። የጠላት ሠራዊት በዙሪያዬ ቢሠፍር፡በአምላኬ-ታዳጊነት-ተማምኛለሁና ልቤ ከቶ አይፈራም። ሠልፍም ቢነሣብኝ



www.ethiopianorthodox.org

እርስዋንም አልደነግጥም። አንዲት ነገር ብቻ ለምንሁት፡ ይፈጽልኝ ዘንድ በብርቱ እሻለሁ። ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ከልቼ ጋር በእግዚአብሔር ቤት ፀንቼ መኖርን እወዳለሁ። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ አይ ዘንድ እሻለሁ። አቤቱ አምላኬ ሁይ ! የምሕረት ገጽሕን ከእኔ አትሰውር። በፅኑ ዐለት ላይ ከፍ፡ከፍ አድርገኸኛልና። በዙሪያዬ በከበቡኝ-ጠላቶቼም ላይ አሠልጥነኸኛል። አቤቱ አምላኬ ሆይ ! ወደ አንተ ያቀረብሁትን ጩኸቴን ስማ፡ ማረኝ፡ በጸጋህም-አስበኝ። በደሌንም ሁሉ ይቅር ብለህ በረድኤትህ አትለየኝ።

_ፊትህን እሻለሁ፡ አቤቱ የምሕረት ገጽህን ከእኔ አትሰውር፡ ተቈጥተህም ከእኔ አትራቅ፡ ረዳት ሁነኝ አትጣለኝ፡ ለጠላቶቼም ፍላጎት አሳልፈህ አትስጠኝ።-በሕያውን_ምድር-የአንተን ቸርነት ማየት እፈልጋለሁና በአንተም_ተስፋ አደርጋለሁ። ልቤን በማፅናት የመንፈስን ብርታት ስጠኝ። ምን ጊዜም አለኝታዬ አንተ ነህና ። የሰጠኸኝንም- ልጆች- የአንተን- ሕግና-ሥርዓት-ጠብቀው-እስከ ሕይወታቸ- ዘመን-የሚኀዙ አድርግልኝ። ቤተሰቤን_ሁሉ_በሰላም ጠብቅልኝ። በቅዱስ ቃልህ-ታንፀው-የአንተን ቅዱስ ስም-የሚያከብሩ አድርጋቸው አካሂዳቸውንም በቅዱስ-ቃልህ-የተቃና-አድርግ።-አቤቱ--አምላኬ--ሆይ! ከሕፃንነት ጊዜዬ-ጀምሮ-በስንቱ-አስጨናቂ_ዘመን-ሁሉ-በረድኤትህ እንዳልተለየኸኝ አውቃለሁ። በብዙ አስጨናቂ ፈተና ውስጥ መከታ-ሆነህ-ያሳለፍሃት-ነፍሴ-ሁልጊዜ ስምህን-ታከብራለች።- ከከንቱ-ጭንቀትና፡ ከመሸበር ጠብቀኝ፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፲፭/15 በደልን በመናዘዝ የሚቀርብ ጸሎት (ዳን፡9፡ 4-14)።

ትእዛዛትህን-ከሚጠብቁ-አማኞች ጌታ_አምላኬ-ሆይ!_ከሚወዱህና-ትእዛዛትህን-ከሚጠብቁ-አማኞች ጋር ቃል ኪዳንና ምሕረትን ጠብቀህ የምትኖር ስለሆንህ በታላቅነትህ ምስጋናና ክብር የሚገባህ ኃያል ነህ። በርግጥ እኛ በፊትህ_በሠራነው-ኃጢአት-ሁሉ-አሳዝነንሃል-ከዕውነተኛ ፍርድህና_ከትእዛዛትህ--ርቀናል ፡-ቅን ታዛዥነትም-ጎድሎን፡_በስምህ ለመሪዎቻችን፡ ለአለቆቻችንና -ለአባቶቻችንም- ሁሉ -በግልጥ የተናገሩ-/ያስተማሩ-የነቢያትህን ቃል ከመስማት ቸል ብለናል።



ጌታ ሆይ ! ይህም ሁሉ ሆኖ፡ ምሕረት የባሕርይ ገንዘብህ ስለሆነ በቸርነትህ ታግሠኸናል። አንተን የሚያሳዝን በደል መሥራታችን ለእኛና-ለአባቶቻችን ማፈሪያ ሆነ እንጂ-እንተማ-በዕውነተኛነትህ ፀንተህ-የምትኖር-ሕያው-ነህ።

_ታዲያ አሁንም በአንተ ላይ ያመፅን ብንሆንም እንኳ በጸጋህ ብዛት_/በቸርነትህ_የበደልን_ይቅርታና_ምሕረት እንድታደርግልን በጸሎት እንማፀንሃለን ። በምንም ዓይነት ሁኔታ ከዚህ ዓይነቱ በደል ነጻ ነን ለማለት አንደፍርም። በነቢያትህ የተጻፈውን ትምህርትና በውድ ልጅህ ደም ታትሞ የተሰጠንን የሕገ ወንጌል ቃል ቸል ብለን ቃል ኪዳን አፍራሾች ሆነናል። ይኸውም አንተ የምትጠላውን-የጥንቆላ-መተትና-የቃልቻ-ድቤ ድምፅ በየመንደሩ መስማት ለውርደትና ለቅሌት- የሚዳርገን እንጂ ለምንም የማይበጀን መሆኑ በተግባር እየተየ እንኳ-ከዚህ ስሕተት-ነጻ-ለመሆን ውሳኔ ያላደረገ ሕዝባችን ቍጥሩ እጅግ ብዙ ነው። ከዚየተነሣ- ህም- የደረሰብን የዝናም እጥረትና፡ አባር ቸነፈር፡ ፍትሕ-አልባ የሕዝብ እልቂት፡ ስደትና ውርደት በዓለም ዙሪያ ከታየው ሁሉ እጅግ የከፋ ነው። ያም ሁሉ ሆኖ ግን አሁንም ከከፉ ሥራችን ሁሉ ገና አልተመለስንም። የአንተ ጸጋና ምሕረት ብቻ ዋልታና-ምሰሶ ሆኖ ደግፎን በመኖሩ እንጂ እንደ እኛ አካህድ ቢሆን ኖሮ እስካህን ጠፍተን ነበር። በዚህም ሁሉ ቅዱስ ስምህ የተመሰገነ ይሁን፤ለዘለዓለሙ፡አሜን !

## ፲፮ /16. '''''''' የንስሐ ጸሎት ''''''' (ዳን 9 ፡15-18)

_በምደረ-ገብጽ ባረነት-ላይ የነበረ-ሕዝብህን ከባርነት-የታደግህና ነጻ ያወጣህ ኃያል-አምላካችን ሆይ! ለእኛና ለአባቶቻችን ያሳየኸው ድንቅ ነገር-ሁሉ-እጅግ-ብዙ ነው። በተለይ ለእኛ በምሥራቅ አፍሪቃ ቀንድ ላይ በተፈጥሮ-የተዋበች አገር (ኢትዮጵያን) ሰጥተኸናል። የቀድሞ አባቶታችን በአንተ አምነው፡ በዚህች ምድር ከብረው፡ ገንነው፡ በተድላና በደስታ ዘመን ያንተ ጸጋና በረከት የነበረበት መሆኑን በዚህች ቅጽበት እናስባለን። ከጊዜ በኋላ ግን ዓለማትን በረሃብ የቀጣ የኮምዩንስት ርእዮተ ዓለም ወደ ሀገራችን መግባት ሲጀምር



www.ethiopianorthodox.org

ከአንተ የሚያርቅና ወደ ሁለተኛው ዳግም-ሞት የሚመራ ሕይወት በመከተል መንጋዳችን የተጣመም በምሆኑ ምክንያት አሳፋሪ በደል ሠርተን-በመገኘታችን በመካከላችን የፍቅር አንድነትና የመቻቻል መንፈስ ጠፍቶ ራሳችንንም፡አገራችንንም አደጋ ላይ-መጣላችን ታሪክ የማይረሳው ዓመፅ ነው ። በእውነት አሳዛኞች ፍጥረቶች ነን ። ነገር ግን አንተ መሐሪና በደልን ሁሉ ይቅር-ባይ በመሆንህ ብቻ በጸጋህ ስላሰብከን እንደ ሌሎች አንዳንድ አህጉር ህልውናችን ሳይጠፋ በመኖሩ ስምህ ይመስገን። አሁንም- የአንተ ጸጋና ረድኤት እንደተለየን እንዳን ቀር የጸጋ ምሕረትህ ያስፈልገናል። ስለዚህም በቸርነትህ የመረጋጋትንና የመፅናናትን ሰላም ስጠን። ይህ ለልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራና-ለከባድ የኑሮ ፈተና የተዳረገ ሕዝብህ ባንተ የመተማመን ተስፋ እንዳይለየው -በቅዱስ መንፈስህ-ጸጋ እንድትደግፈው- በጸሎት-እንማፀንሃለን። ·

_በቀድሞ አባቶቻችን ዘመን እንደተለመደ በሁሉ ነገር ተሳሰበን በመረዳዳትና በመደጋገፍ፡ በመተጋገዝ ኑሮዋንን ማሸነፍ እንድችል እርስ በርስ የመቀናናትንና የፀብ ክርክርን-መንፈስ-አርቀህ በሰላም አብሮ የመኖርን ጸጋ እንድታበዛለት ቅዱስ ፈቃድህ-ይሁን። ሁሉም ሠርቶ ለመበልጸግና በሚያገኘው የነፍስ ወከፍ ድርሻ ኑሮውን ማሸነፍ እንዲችል ያንተ ረድኤት ያስፈልገዋል ። የአባቶቻችን- አምላክ-ሆይ ! አሁንም እንደ በደላችን-ብዛት ሳይሆን እንደ ቸርነትህ በጸጋህ አስበን። ያለፈ በደላችንን ሁሉ ይቅር ብለህ ምሕረትህን አብዛልን።ለንስሐ የሚያበቃ ፍሬ እንድናፈራ በቅዱስ መንፈስህ እርዳን። እኛን ለማዳን እስከ ቀራንዮ መስቀል ስለተጓዘ ውድ ልጅህ ስትል ጸሎታችንን እንድትቀበልልን ፈቃድህ ይሁን፡ አሜን !

## ፲፯/17. የቤተስብ መሪዎች ጸሎት ፣

_ነፍስየኒ ሎቱ ተሐዩ፡ ወዘርዕየኒ ሎቱ ይትቀነይ= ነፍሴ በርሱ-ሕያዊት -ሆና ትኖራለች፡ ዘሬም ሁሉ ለርሱ ይገዛለታል (መዝ 22፡ 29--30)_የሠራዊት ጌታ የሆንህ አዶናይ-እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! አገልጋይህ ሐና "እኔን አገልጋይህን በበረከት



አስበህ ወንድ ልጅ ብትስጠኝ መልሼ-ላንተ በማስረከብ ለገልግሎትህ እንድመደብ አደርጋለሁ' ስትል ያቀረበችውን ጸሎት ተቀብለህ የፈጸምህላትን ድንቅ ነገር በዚህች ቅጽበት እናስባለን (1-ሳሙ-1፡11) ።"የነገሩህን የማትረሳ፡ የጠየቁህን የማትነሣ፡ ሁሉን አዋቂ የሆንህ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! በአንተ አምነን የምንሠራውን ሁሉ ስለባረክህልን ቅዱስ ስምህ የተመስገነ ይሁን። ከሁሉ ይበልጥ የተባረከ ቤተሰብ ለመመሥረትና የአንተን ቅዱስ- ስም የሚያከብሩ-ልጆችን ለማፍራት ስላበቃኸን ለገናናው ቅዱስ ስምህ ምስጋና እናቀርባለን። "ዘርህን እንደ-ሰማይ ኮከብ፡ እንደ-ምድር አሸዋ አባዛለሁ" ስትል ለወዳጅህ-ለአብርሃም የሰጠኸውን ተስፋ በመፈጸም- ሬገድ-የታመንህ ነህ። ለአንተ-የሚሣንህ ምንም-ነገር የለም።ይህኑ-ዓይነት -ተስፋ ለእኛም-ለገልጋዮችህ ትፈጽመው ዘንድ ይቻልሃልና ቸል አትበለን! በጠቢቡ ሲራክ መጽሐፍ "ታላቅ- ቤተሰብ በማግኘትህ-ብቻ ደስ- አይበልህ እምነት-ከጎደላቸው ሽህ ልጆች ይልቅ የእግዚአብሔርን ስም የሚያከብር አንድ ልጅ ይበልጣል" ተብሎ ተጽፏልና በአንተ ሕግና ሥርዓት የማይመሩ ልጆችን ሕይወት አንተ በቅዱስ ቃልህ እንድትታስተ ካክለው-ፈቃድህ-ይሁን።አሁንም-ቢተሰባችንን ባርከህ- ልጆቻችንን ከከፉ ፈተና ሁሉ ጠብቀህ- የሰማያዊት- መንግሥትህ--ዜጎች-እንዲሆኑ- አድርግልን፡ ለዘላለሙ፡ አሜን! """""""""""""""""

## ፲፰/18.- ከፈተና-ተጠብቆ በድል አድራጊነት መኖር

_እግዚአብሔር-አምላክ ሆይ! አንተ የሁላችን-እምባ መጠጊያ ዐለት ነህ። የምትታደገንና- ከጠላት- የምታድነን -አንተ- ነህ። በአንተ-ታምነን በሰላም የመኖርን ጸጋ አብዝተህልናል። መሸሸጊያችንና እምባ መጠጊያችን አንተ ነህ። ለጠላት ከመሸነፍ ጠብቀን። ምስጋናና ክብር- የሚገባውን ቅዱስ ስምህን በጸሎት- እንጠራለን፡ ጠላቶቻችን የሆኑትን ሠራዊተ-አጋንንት በኃያሉ ስምህ ድል የምንነሣበትን የመንፈስ ብርታት ስጠን ። ሰማያዊ አባት እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! አሁንም የአንተ ረድኤትና ፈጥኖ የማዳን ኃይልህ ያስፈልገናል። የጸጋ



www.ethiopianorthodox.org

ምሕረትህን አታርቅብን:: የአንተ-ኃይል እንደ ጋሻ መከታ ሆኖልን -ስንቱን-አሸባ--ፈተና-ሁሉ -አልፈን ዛሬ ድንቅ ሥራህን ለመመስከር አብቅተኸናል:: የአንተ ኃይል ለእኛ መከላከያ ምሽግ ሆኖልን፡ ጠላቶቻችን ሁሉ የተመኙትን ያህል በእኛ ላይ ክፉ ነገር ለማድረስ አልተቻላቸውም:: ይህማ ባይሆን ኖሮ ፍላጎታቸው እኛን ከገጸ ምድር ለመደምሰስ ነበር:: ታዲያ አሁንም የአንተ የማዳን ኃይልና የአንተም ትክክለኛ ፍትሕ፡ ለዘለቄታ ያንተ የሕይወት ዋስትና- ያስፈልገናል:: ማንንም ሳንበድል በከንቱ ለሚጠሉን_ሁሉ-አስተዋይ ልቡና ስጣቸው:: _ክፉ ምክራቸውንም እንደምክረ አኪጦፌል በማምከን_መና ስላስቀረረኸው ድንቅ ሥራህን ሁሉ ስናስታውስ እንኖራለን:: መላ ቤተሰባችንን፡ ልጆቻችንንና የልጅ ጤንነታችንን ባርክልን:: ምን ጊዜም የአንተን ልጆቻችንንም ሁሉ በረድኤትህ ጠብቅልን:: የቅዱስ መንፈስህን ቅ/ ስም በጸሎት ከመጥራት እንዳንገታ (ሥግው ሆኖ ብርታት ስጠን:: በተለይም ሰይጣን በስዎች-አድሮ ) ከሚያመጣው ፈተና ሁሉ ጠብቀን:: ከልጅነት ጀምሮ የሠራነውን በደል ሁሉ ሳታስብ በቸርነትህ ማረን፡ ይቅርም በለን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን ፣

## ፲፱/19. የእግዚአብሔር ሰላም በልባችን ይንገሥ—

አቤቱ የሰላም አምላክ ሆይ! ምሕረትህ በምድር ሁሉ ሞላች:: ለእኛ ላገልጋዪችህ ሕግና ሥርዓትህን ሁሉ አስተምረን:: በትእዛዛትህ ያደረግኸው ድንቅ ነገር ሁሉ እጅግ ብዙ ነው:: ታምነናልና መልካም-ምክርና ሰላም-የሞላበትን-ዕውቀት ስጠን:: የትዕቢትን ዓመፅ ሁሉ አርቅልን:: ከአእላፍ ወርቅና ብር ይልቅ ከአንተ አንደበት የሚፈልቅ ሕያው ቃልህ የተሻለና ከሁሉ ነገር የሚበልጥ ሆኖልናል:: የአንተ ሰላም በልባችን ነግሦ እንዲኖር "በደላችንንና-መተላለፋችንንም-ሁሉ-ደምስስልን::-የአሳብ መለያየ ትን አርቅልን:: ከዲያብሎስ ገዢነት፡ ነጻ ለማውጣት ወደ ዓለማችን የመጣ ውድ ልጅህ "እነሆ እኔ አዲስ ሕግ /ትእዛዝ- እሰጣችኋለሁ፡ ይኸውም-እርስ-በርሳችሁ-ትፋቀሩ-ዘንድ -ነው:: ዓለም ፍቅር ቢኖራችሁ የእኔ ደቀ ማዛሙርት መሆናችሁን



ሁሉ-ያውቃል"-ብሎ-እንዳስ--ተማረን፡--በወንጌሉ-ቃል-ሰላምን ሰብኮልናል::-እኛን-ለማዳን-የከፈለውን-የሕይወት-መሥዋዕትነት- በዚህች-ቅጽበት-እናስባለን::በመስቀሉ-የሞትን-ኃይል-ድል- ነሥቶ- በእግዚአብሔርና በሰው ዘር መካከል፣ በሕዝብና-አሕዛብ-መካከል- የነበረውን-የጥል-ግድግዳ-አፍርሶ፡ሁሉን-አንድ-አድርጓልን::

_በትንሣኤውም ከሞት በኋላ ሌላ አዲስ ሕይወት መኖሩን አረጋግጦልናል:: ስለዚህም በርሱ ያገኘነው ሰላምና ፍቅር- ለዘለዓለም ፀንቶ እንዲኖር አድርግልን፡ ሕግህን በቀንና በሌሊት እንድናስብ የመንፈስን ትጋት ስጠን:: የሕያው ቃልህን ፍቅር አፅናልን:: አቤቱ አምላካችን ሆይ! በዙሪያችን የሚኖሩ- ጎረቤቶቻችንም-ሁሉ ለሰላምና ለፍቅር አንድነት፡ በቅን- መንፈስ ለትክክለኛ ማኅበራዊ ሕይወት የተዘጋጁ አድርገህ ባርካቸው:: የሞትን ኃይል ድል ነሥቶ፡ከሙታን- ተለይቶ በሚነሣት ለእኛ ተስፋ ትንሣኤ በኵር ስለሆነልን ስለውድ ልጅህ ስትል ጸሎታችንን-ተቀብለህ የምሕረትህ- በር እንዲከፈት አድርግልን፡ ስለ ቅዱስ ስምህ --ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፳ /20. የእግዚአብሔርን ምሕረትና ትዕግሥት

( ዕንባ 1፡ 1- 4) አቤቱ የምሕረት አምላክ ሆይ ! አገልጋይህ ነቢይ ዕንባቆም -"አቤቱ አምላክ ሆይ ! ወደ አንተ ስጮህ ዝም የምትለኝ እስከ መቼ ነው ? በምድር ላይ ስለሚፈጸመው የግፍ ሥራ ሁሉ ወደ አንተ እጮሃለሁ:: ይህን ሁሉ ግፍና በደል ስለ_ምን አሳየኸኝ ? የስዎችንስ የልብ ጠማማነት ሁሉ ስለምን ትመለከታለህ ? እነሆ ጥፋትና የግፍ ሥራ ሁሉ ዘወትር በፊቴ ነው:: ፀብና ክርክር ይነሣል:: ነገር ግን ትክክለኛ ፍትሕ ድል ነሥቶ፡ አይወጣም:: ሕግም ሁሉ ተፈጻሚነት አጥቷል:: ከዚህም የተነሣ ኃጢአተኛው የዓመፅ ሰው ዕውነትን የሚከተለውን ደግ ሰው ከብቦ ያስጨንቀዋል" ሲል የተናገረውን ቃል አስብ:: መዓትህ የራቀ መሐሪና በደልን ሁሉ ይቅር ባይ አምላክ ሆይ! እነሆ ይህ የአገልጋይህ ነቢይ ዕንባቆም የትንቢት ቃል በየአህጉሩ ሲፈጸም የሚታይ ነው:: እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ የሰው ልጆች-ስንባል ምን ጊዜም ከበደልና



www.ethiopianorthodox.org

ፍትሕን ከማጣመም የተቆጠብንበት ጊዜ የለም። ስለዚህም በማዕከለ ዘመን የእኛ ዕዳ፡ በደል ከፋይ ባደረግኸው በውድ-ልጅህ የሕይወት-መሥዋዕትነት በደላችንን ሁሉ ይቅር ብለህ ትምረን ዘንድ እንማፀንሃለን።አቤቱ የምሕረት- አምላክ- ሆይ ! ለሀገር- መሪዎችና- ለፍትሕ ዳኞች ሁሉ የማስተዋልን ጥበብ ስጣቸው። ሕግህንና ሥርዓትህን ጠብቀው በፍጹም ቅንነት፡ በዕውነት ለዕውነት መፍረድ የሚችሉበትን ጥበብ አስተምራቸው። ባጠቃላይ ሕገ ወጥነትን፡ሥርዓት አልባነትና፡ የሙስና አሠራርን ሁሉ ከምድራችን አስወግድልን። ወንድም በወንድሙ ላይ መጨከንና ነፍስ ማጥፋት ታላቅ በደል መሆኑን የሚያስተውልና ሰብአዊ ርኅራኄ የሚላበትን ንጹህ ልብ ፍጠርልን። ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ፡ ነመንፈስ ቅዱስም፡ ዘለዓለም ሥላሴ፡ አሜን ! """"""""""""

## ፳፩/21፡ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ( ዕንባ 3 )

የአማልክት-አምላክ፡-የነገሥታት-ንጉሥ-ጌታ-እግዚአብሔር ሆይ! በቅዱስ ስምህ የሚያምንብህ-የሰው ዘር ለትውልደ ትውልድ ያለህን ዘለዐለማዊ ፅኑ ፍቅርህንና ድንቅ ሥራህን ያውቅ ዘንድ "በመዓት ጊዜ ምሕረትን አስብ። በዕውነት አንተ በእኛ ላይ ለዘላለም-ተቆጥተሃልን?-የኤትዮጵያ-ድንኳኖች-(ሕዝብ) ሲጨነቁ-አየሁ" ተብሎ በአገልጋይህ ነቢይ ዕንባቆ እንደበት እንደተነገረ ሰላምና የፍቅር አንድነት ከዚህች አገርና ከሕዝብዋ እንዳይርቅ ምሕረትህን አብዛላት።_የተፈጥሮ ቀውስም ሆነ ሰው ሠራሽ ችግር ከሚያስከትለው መከራና ሐዘን ጠብቀን። ሰብሳቢ ያጡ የሙት ልጆችን ጩኸት መስማት አሰቃቂ ሆኖብን እንዳይቀር-ዝናመ-ምሕረትና-እክለ-በረከት--ሰጥትህ--በረድኤትህ እንድትጐበኘን-እንማፀንሃለን።-አንተን የሚያሳዝን ክፉ በደል መሥራታችንን-እናውቃለን። ነገር ግን ምሕረትና ይቅር-ባይነት-የባሕርይ ገንዘቦችህ ስለሆኑ በቸርነትህ ብቻ ማረን። በአገልጋዮችህ ነቢያት አንደበት "እንዲሁ በነጻ እወዳችኋለሁ፡ በደላችሁንም ሁሉ ደግሜ አላስብም" ስትል ያናገርኸውን የተስፋ ቃል አስበህ የጸጋ-ምሕረትህን-አብዛልን። እኛን- ክፉ እድራጊዎችን /ኃጥአንን



ብትምረን በደልን ሁሉ-ይቅርባይ መሆንህን ዓለም ሁሉ ያውቃል። አቤቱ ምሕረትህና ይቅርታህ ፈጥነው ይጐብኙን ። "ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐና እምኵሉ ኃጣውኢነ" ተብሎ እንደ_ተጻፈ ፡ በማወቅም-ሆነ ባለማወቅ ከሠራነው በደል ሁሉ ያነጻን ዘንድ በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈሰሰ የውድ ልጅህን ክቡር ደም አስብ። እንደ ስንፍናችንና እንደ በደላችንና እንደ-ኃጢአታችንም ብዛት- ሳይሆን በቸርነትህ ማረን፡ ይቅርም በለን፡ ለዘለዓለሙ፡አሜን !

## ፳፪/22፡ ለመላው ዓለም የክርስቶስ ሰላም-አስፈላጊነት

(ኢሳ 2፡ 3=-4) "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ይፈርዳል፡ ስለዚህ ሰይፋቸውን ለውጠው ማረሻ፡ ጦራቸውንም ለውጠው-ማጭድ፡ አድርገው-ይሠሩታል ። ሕዝብ በሕዝብ ላይ ጦርነት ማንሣቱ-ይቀራል።"ከዚያ በኋላ የጦር ትምህርት መማር አያስፈልጋቸውም-" ስትል- የሰጠኸውን የተስፋ ቃል አስበህ-በሥራ አጥነትና፡ በተፈጥሮም ቀውስ ማለት-በውኃ ሙላትና ባማዕበል ሞገድ መነሣት፡ በእሳተ ገሞራና በጦርነት ለተናወጠው ለዓለም ሰላም የመረጋጋትን መንፈስ እንድትሰጥ እንማፀንሃለን። የሰላም አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ! ብጥብጥና ሁከት ሽብርና የኑሮ ምስቅልቅል በዝቶበት የተናወጠውን- ይህን ግዙፍ ዓለም ያላንተ መለኮታዊ ኃይል ማረጋጋት የሚችል የለም ። ብዙ ችግር ማዕበል ሞገድ ሆኖ በሚያናውጠው ዓለም የሚኖሩና አንተን የሚወዱ ብዙ ደጋግ ሰዎችም አሉ። ሃምሳም ሆነ ዐርባ አምስት፡ ወይም ሠላሳ አምስት፡ሠላሳና ሐያ አምስት፡ ዐሥራ አምስትና ዐሥር ጻድቃን በውስጣቸው ቢኖሩ የሰዶምና ገሞራውን ከተሞች ሕዝብ-እንደምትምራቸው-የሰጠኸውን-የተስፋ-ቃል እናስታውሳለን። ስለዚህ በዘላለማዊ ፍቅርህ መርጠህ የጠራሃቸውንና-ያከበርካቸውን የቅዱሳን ጸሎትና እንዲሁም ስለስምህና ስለ ቅዱስ ወንጌልህ ቃል ደማቸውን ያፈሰሱ የሰማዕታትን ተጋድሎ በማሰብ፡- በልዩ፡ ልዩ- አሸባሪ ጦርነት የተናወጠውን ይህን አስቸጋሪ ዓለም እንድታረጋጋው ቅዱስ ፈቃድህ ይሁን።

www.ethiopianorthodox.org

_ጦርነትና ማናቸውም የተፈጥሮ ቀውስ የምድርና የባሕር መናወጥ ባስከተለው-ችግር በዓለም ዙሪያ ግራ የገባቸውንና ከኑሮ ተፈናቅለው በየአህጉሩ ሁሉ የሚንከራተቱ ስደተኞችን ሁሉ ከረሃብና ከኑሮ ጕሥቍልና እንድትታደግ እንማፀንሃለን። በዓለም ዙሪያ የተቸገሩና በሁሉ ነገር ግራ ተጋብተው ታዳጊ አጥተው በግዞት የሚኖሩ ወገኖችህ ሁሉ በርኅራኄ ዓይን- እንዲታዩ አድርግ። በዓለም ዙሪያ የጦርነትን ወሬ ሳይሆን የሰላምን የምሥራች ቃል እንድታሰማን ፈቃድህ ይሁን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## ፳፫/23፡ ከጠላት የምንጠበቅበት ጸሎት (መዝ. 30)

_ዘለዓለማዊ ሕያው የሆንህ አምላካችን ሆይ ! አቤቱ አንተን ታምነናልና ለዘለዓለሙ እንዳናፍር ከአደጋ ሁኩ በጽድቅህ አድነን። ስለ ሕያው ስምህ ስትል የምንጓዝበትን የድል ጎዳና አቅና።-ጠላት-ከዘረጋው-ወጥመድ_ሁሉ-ትጠብቀን_ዘንድ ሕይወ ታችንን ለአንተ አስረክበናል። የደረሰብንን ችግርና ዕብሪተኞች ስዎች በእኛ ላይ የቃጡትን ቀስት ሰብረህ በምህረትህ ስለታደግኸን ቅዱስ ስምህ የተመሰገነ ይሁን። አሁንም ለጠላት አሳልፈህ አትስጠን። ሐሰተኛ የሆነ ሰው-ሠራሽ- ተንኮል እየሸረቡ-ከሚያሳድዱንና ሁልጊዜ ክፉ ከሚመክሩብን ጠላቶቻችን ሁሉ ጠብቀን። ገጸ ምሕረትህን በእኛ ላይ አብራ። ስለምሕረትህ ስትል አድነን፡ ቅዱስ ስምህም በጸሎት ስንጠራ አታሳፍረን። በአንተ ቅዱስ ስም ለሚታማመኑ ሁሉ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀሃትና ለሚፈሩህ ሁሉ የሠወርካት ቸርነት እንዴት በዛች ! ለሰው ዘር ሁሉ ያለህን የማይናወጥ ዘለዓለማዊ ፍቅር በአንድ ውድ ልጅህ በጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ስለገለጥህልን ምስጋናና ክብር ለቅዱስ ስምህ ይሁን ። እነሆ በርሱ የማዳን ኃይል ከጥንተ ጠላታችን ከሰይጣን ፈተና ሁሉ ታድገኸናል። ቤተሰባችንን ባርከህ፡ ጤንነታችውን ጠብቀህ ለቁምነገር ስላበቃህልን ቅዱስ ስምህ ይመስገን። በከንቱ ለሚጠሉን ሁሉ አስተዋይ ልቡና ሰጥተህ ሰላማዊ-ሕይወት-እንዲኖራቸው-አድርግልን። በዙሪያችን ከሚኖሩ



ስዎች ሁሉ ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችል ጥበብን ስጠን። "የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፡ ከጠላቶቹ ጋር እንኳ በሰላም እንዲኖር ይረዳዋል' ተብሎ በአገልጋይህ ጠቢብ ንጉሥ። ሶሎሞን የተነገረውን መሪ ቃል ማስተዋል-እንድንችል-እርዳን በከንቱ የሚጠሉንን ሁሉ የበደልን ይቅርታ ማወቅ ይችሉ ዘንድ ሕይወታቸውን በቅዱስ ቃልህ- እንዲለወጥ አድርግህ አስተዋይ ልቡና ስጣቸው።ለእኛም ለነርሱም--የንስሐን ሕይወት ሰጥተህ ለዕርቀ ስላም በማዘጋጀት አንተን ደስ በሚያሰኝህ ሕወት ምራን። ሁላችን የአንተ ልጆችና የማያዊት መንግሥትህ ዜጎች እንድንሆን እርዳን፡ አሜን ! """

## ፳፬ /24. የወንድሞችና እኅቶች በኅብረት መኖር

ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዩ አኃው ኅቡረ =ወንድ ሞች በኅብረት ቢኖሩ እንዴት-መልካም ነው! (መዝ 122፡1)

_ወንድሞቻችንና--እኅቶቻችንን--ሁሉ--እንደራሳችን--አድርገን የምናፈቅር እንድንሆን እርዳን። በደልንም ሁሉ ይቅር ባዮችም እንድንሆን ንጹሕ ልብ ፍጠርልን። በማንኛውም የተፈጥሮ ወንድማችን ላይ የበቀል እርምጃ ከመውሰድ እንድንቆጠብ ትዕግሥትን ስጠን። በያዕቆብ- ላይ የነደደውን የወንድሙን- የዔሳውን ቍጣ በማብረድ ሁለቱም ወንድማማቾች እንደ-ገና አዲስ ሰላማዊ ኑሮ እንዲጀምሩ-ማድረግህ-ተጽፏል። በአገልጋይህ ንጉሥ ሶሎሞን ምሳሌ 16፡7 የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ በርሱና በጠላቶቹ መካከል ሰላምን ያደርጋል ተብሎ የተጻፈ ቅዱስ ቃልህን እናስባለን። በዙሪያችን የሚገኙ የአፍሪቃ እህጉር- ሕዝቦች በሰላም አብሮ የመኖርን ጥበብ አውቀው በመቻቻል ተደጋግፎና ተሳስቦ በፍቅር አብሮ የመኖር ዋስትና እንዲኖራቸው አድርግ። ባጠቃላይ ክፍለ ዓለማችን አፍሪቃን እንድትባርካት ፈቃድህ ይሆን ዘንድ እንማፀንሃለን። የመለያየትን መንፈስ አስወግድልን ። ክፍለ-ዓለማችን-የፍቅር- አንድነትና-ሰላም- የሰፈነባት- እንድትሆን ረድኤትህን-አብዛላት፡ በፍጹም መግባባትና በመቻቻል ታሳስቦ- የመኖርን ጥበብ አስተምረን። የሰላም አለቃ፡-የፍቅር አንድነት- መሥራች-



www.ethiopianorthodox.org

በሆነው- በአንድ- ውድ ልጅህ ቅዱስ- ስም ስትል ጸሎታችንን ተቀበልልን፡ በቸርነትህ ማረን፡ ለዘላለሙ፡ አሜን_!

**፳፭/25.ስለ ዝናመ ምሕረትና ጠለ በረከት** <u>መማፀኛ-ጸሎት</u>

-_ሰማያዊ_አባታችሁ_እግዚአብሔር በጻድቃንና ኃጥአን መካከል ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም እኩል ዝናምን ያዘንማል (ማቴ.5፡ 45) "በዚያን ጊዜ በበረሃ ውስጥ የጅረት- ውኃ ይፈልቃል::- የሚቃጠለው-በረሃና-ስፍራ ሁሉ ለምለም ሣርና ቄጠማ የሚበቅልበት ጨፌ ይሆናል" ተብሎ በአገልጋይህ ነቢይ ኢሳይያስ (ኢሳ 35፡ 5 -8 ) የተነገረውን የትንቤት ቃል በምድራችን እንዲፈጸም አድርገው:: ለአንተ የሚሳንህ ምንም ነገር የለምና የተዛባውን የተፈጥሮ ሚዛን አስተካክለህ ሰማይ ዝናም ለዘር፡ ጠል ለመከር እንዲሰጥ በማድረግ ከደን የተራቆቱ የሀገራችንና የክፍለ ዓለማችን የአፍሪቃ ተራሮችና ኮረብቶች ሁሉ በልምላሜ እንዲሸፈኑ ዝናመ ምሕረትና ጠለ በረከትህን አውርድላቸው:: በቀድሞ ዘመን ታይቶ የማይታወቅ የዝናም እጥረት በተፈጥሮ የባረክሃትን አገራችን ኢትዮኣጵያንና ክፍለ ዓለማችን አፍሪቃን- ወደ- በረሃነት- እየለወጣቸው- በመምጠቱ- የመንፈስ ጭንቀት ፈጥሮብናል :: በእኛ በደል ምክንያት በምድሪቱ የሚገኙ እንስሳት፡ አራዊትና አዕዋፈ ሰማይ እንኳ እየታወኩ ወደ ጐረብየት አገሮች በመፍለስና በመሰደድ ላይ ይገኛሉ::_በጥንቱ ዘመን በዚህች ምድረ ካም -በአፍሪቃ ሰሜናዊ-ክፍል የፈጸምኸውን ድንቅ ሥራ ሁሉ እናስታውሳለን::

_ከሁሉ ይበልጥ ተቀዳሚ-ተከታይ የሌለው-አንድ ውድ ልጅህ ከርጉም_ንጉሥ-ሄሮድስ-ዛቻ-የተነሣ-በቅዱስ_ፈቃድህ_ወደ_ክፍለ-ዓላምችን እስከ_መሰደድ ደርሶ አፍሪቃን እንዲባርካት ያደረግህበትን ቸርነት አስብ:: አሁንም ጌታ ሆይ ! እንደ በደላችን፡ እንደ ኃጢአታችን ብዛትና እንደ ስንፍናችን ሳይሆን፡ ቢቸርነትህ ማረን:: አገራችንን ኢትዮጵያንና_ክፍለ_ዓለማችን-አፍሪቃን ባርከህ-ወንዞች- ከውሃ- ሙላት- እንዳይጎድሉ-ዝናመ-ምሕረትና- ጠለ በረከትን አውርድላቸው፡ ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘለዓለሙ አሜን!



**፳፮/26.. መንፈሳዊ ኃይልና ብርታት የሚገኝበት ጸሎት** (Thanksgiving) ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ= ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና እቅርቡለት፡ በየቀኑ ይማዳንና ሥራው እጅግ ድንቅ ነው (መዝ 97፡ 1 ):: _የሰማይና የምድር ሁሉ ጌታ የሆንህ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ቅዱስ -ስምህ -የተመሰገና ይሁን::አንተ ከሁሉም በላይ ከፍ፡ ከፍ ብለህ የምትመሰገን ልዑለ ባሕርይ ነህ፡ ገናንነትና ድል አድራጊነት ኃይልና-የአሸናፊነት-ግርማ-ውዳሴና-ክብር-ያንተ ነው:: ለስዎች የሚሰጥ ባለጸጋነትና ክብር ሁሉ የሚገኝ-ካንተ ነው:: ስለዚህም ለአንተ -ሕይወታችንን እናስገዛለን:: ለቅዱስ ስምህም ክብርና ልዕልና ውዳሴ እናቀርባለን :: ከእጅህ የተቀበልነውንም በረከት ለአንተ መባ አድርገን እናቀርባለን ::

_እኛ በዚህች ምድራዊት ዓለም ስደተኞችና እንደ አልፎ ሒያጅ መንገደኖች ነን:: ዘመናችንም እንደ ጥላ የሚያልፍ ነው:: ሕይወታችን እንደ አበባ የሚረግፍ ነው:: ይህኑ የሰውን ሕይወት ደካማነት አይተህ ሕያዋን የሚያደርገንን ቅዱስ ቃልህን ስለሰጠኸን ስምህ ይመስገን:: በዚህም በቅዱስ ቃልህ ፍቅር ፀንተን መቆም እንድንችል እርዳን::ወደ-ዕውቀትና ማስተዋል የሚመራ ቅዱስ መንፈስህን አታርቅብን :: አቤቱ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪና አስገኝ የሆንህ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! የአንተን ቅዱስ ስም ማክበር የጥበብ-ሁሉ-መጀመሪያ-መሆኑን-እንድንገናዘብ-ዓይነ ልቡናችንን አብራ፡ አእምርውችንን ክፍትለን::ስለ አንተ ታማንነትና የማዳን ኃይል ድንቅ ሥራህን ሁሉ እንድንመሰክር መንፈሳዊ ጥበብን አስተምረን:: ከፍርሐት በማንጻ መንፈስ ኃይልና ብርታትን ስጠን፡ የልባችንንም አሳብ ፈጽምልን መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነ ቅዱስ ስምህ ስትል ጸለታችንን ስማ፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !' ''''''''''''''''''''''''''''''

**፳፯/27 በሞት ለተለዩ አማኞች ምሕረትን** <u>መማፀኛ ጸሎት</u>

_ሮቤል በሕይወት ይኑር፡ አይሙትም " ( ዘዳ. 33፡ 6 ) ሲል ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ ስለሮቤል ነፍስ በሕይወት መኖር፡



www.ethiopianorthodox.org

ማለት በነፍስ ዳግም ሞት እንዳያገኘው መማፀኑን እናያለን። እኛም ሁላችን ከዚህች ምድራዊት ዓለም በሞት በምንለይበት ጊዜ ጉዞዋችን ወደ አንተ-ስለሆነ፡ ብንሞትም፡ ወይም በሕይወት ብንኖርም ያንተው ነን (ሮሜ 14፡ 7-8 ) ። _ወደ አንተ በምንቀርብበትም ጊዜ በፊትህ- እንዳናፍር፡ከበደል ሁሉ የሚያነጻ የንስሐ ሕይወት-እንዲኖረን እርዳን። "ንስሐ ባትገቡ- ሁላችሁም እንዲሁ ትጠፋላችሁ" ተብሎ እንደተነገረ፡ የጥፋት-ልጆች ሆነን ከመቅረት-ጠብቀን ፡ ንስሐ-ገብቶ-ወደ እግዚአብሔር በሚመለስ በአንድ ኃጢአተኛ-ምክንያት በእግዚአብሔር መላእክት ዘንድ-በሰማይ ደስታ (እልልታ) ይሆናል" ተብሎ በተጻፈ ቃልህ እናምናለን። የእኛንም-ሕይወት በንስሓ መታደስ ለመላእክት ደስታ ምክንያት አድርገው ። በሞት_የተለየች የአገልጋይህን የ------------ነፍስ ካስፈሪ ዳግም ሞት-ጠብቅልን።-እስመ እሙንቱ ሕያዋን በኀቤሁ=እነርሱ በርሱ ዘንድ ሕያዋን ናቸው" ተብሎ እንደተጻፈ ፡ በአንተ አምነው ከዚህ ዓለም በሞት-የተለዩ ቅዱሳን ሁሉ በአንተ ዘንድ በአካለ ነፍስ ሕያዋን- ሆነው እንደሚኖሩ ሕያው-ቃልህ ይነግረናል። ኋላም ለመጨረሻ ፍርድ እንደገና ተመልሰህ በምትመጣበት ጊዜ፡ አሜሃ ይበርሁ ጻድቃል እምብርሃነ ፀሐይ= ያን ጊዜ ጻድቃን በትንሣኤ ዘለሕይወት በአባታቸው መግሥት በአዲስ አካል -ከሞት ተንሥተው በአዲስ ሕይወት ከፀሐይ ብርሃን ይበልጥ-የሚያበሩ-ሆነው እንደምናያ ቸው የሰጠኸውን ዘለዓለማዊ የተስፋ ቃል (ማቴ 13፡ 43) በማሰብ ቤተሰባቸው ሁሉ በቅዱስ መንፈስህ እንዲፅናና አድርግ፡ ስለ ስምህ ስትል፡ አሜን !

## ፳፰/28.-የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ስለመሻት

"እናንተስ-አስቀድማችሁ-የእግዚአብሔርን-መንግሥት፡ ጽድቁንም ሹ /ፈልጉ፡ ሌላውም ነገር ሁሉ ተጨማሪ ሆኖ ይሰጣችኋል"። (ማቴ 6፡ 33)። የሕዝቦች ሁሉ አባት የሆንህ ሕያው አምላካችን ሆይ! ምን-ጊዜም-ለእኛ የሚያስፈልገንን ማናቸውንም ነገር እኛ-ከመጠየቃችን-በፊት-ታውቀዋለህ።-በረድኤትህ-የጉበኘሃቸው የቀ



ድሞ- አባቶቻችን -ድንቅ- ሥራህንና፡ የበረከት-ሁሉ ባለቤት መሆንህን ነግረውናል። በዓለም ማኅበረሰብ መካከል የማዳንህን ኃይልና በምድርም የሕግህን መንገድ እናውቅ ዘንድ በቅዱስ መንፈስህ ምራን።' እኛ ልጆችህ ከሁሉ በፊት የአንተን መንግሥትና ጽድቅህን የምንሻ እንድንሆን በጸሎት የመጠየቅን ጥበብ አስተምረን። አሁንም ለእኛ የሚያስፈልገን ተቀዳሚ ነገር ምድር ሁልጊዜ ፍሬዋን እንድትሰጥና ሕዝባችንን ከኑሮ ችግር እንድታደግልን-ነው። አቤቱ የምሕረት-አምላክ ሆይ! አገራችንን ባርከህ ሕዝብዋን ከኑሮ ችግር እንድትታደግልን ቅዱስ ፈቃድህ ይሁን።-አንተ ለእኛ የቅርብ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለህም ።

_ከጥንት_ጀምሮ_ለቀድሞ_አባቶቻችን የገለጥኸውን ያን ሁሉ ድንቅ ሥራ በእኛም ዘመን እንዲደገም አድርግልን። ሰማያዊ አባታችን ሆይ! እንደ በደላችንና እንደ ስንፍናችን ሳይሆን በጸጋህ-አስበህ-እንድትምረን-እንማፀንሃለን።-የአባቶቻችንና የእናቶ ቻችን አምላክ ሆይ ! ከሁሉም ነገር ይበልጥ እኛን ልጆችህን እስከሞት ስለወደድኸን ቅዱስ ስምህ የተመሰገነ ይሁን። ከጥንት ከመሠረተ ዓለምን ከፈጠርህበት ጥበብ ይልቅ በውድ ልጅህ ከቡር-ደም-ዓለምን-የዋጀህበት-ጥበብ-ይበልጣል"ተብሎ እንደተነገረ ውድ ልጅህ እኛን ከዘለዓለም ጥፋት -ለማዳን በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለከፈለው ውድ የሕይወት መሥዋትነት ቅዱስ ስምህ ይክበር፡ይመስገን፡ለዘለዓለሙ፡አሜን !

## ፳፱/29. የወንድሞችንና የእኅቶችን በደል ይቅር ባይነት

"እነሆ እኔ አዲስ ሕግ ሰጥቻችኋለሁ፡ ይኸውም እኔ እንደወደድ ኋችሁ እናንተም እርስበርሳችሁ ተዋደዱ"(ዮሐ-13፡-34)። "ወዳጄ ፊልሞና-ሆይ!-በእስራቴ ዘመኔ ስለወልድሁት (በወንጌል ማመን እንዲችል -ስላደረግሁት )-ስለአገልይህ-ስለ-አናሲሞስ እማልድሃ ለሁ፡ ምናልባት በቀድሞው አገልግሎቱ አልጠቀመህ ይሆናል። አሁን ግን ለአንተም ለእኔም እጅግ የሚጠቅም ሰው ሆኗል። ስለዚህም ወደ አንተ መልሼ ልኬዋለሁና ልጄ እንደመሆንህ መጠን በፍቅር ተቀበለው፡ ከእንግዲህ ውዲህ እንደ አገልጋይ ሳይሆን እንደ ወንድም የሚታይ ነው" በማለት ሐዋርያ



www.ethiopianorthodox.org

ጳውሎስ አናሲሞስ የተባለውን አገልጋይ ካሳዳሪው ከፊልሞና ጋር ለማስማማት የጻፈውን መልእክት ስናስብ እኛም ሁላችን፡ አገልግሎት እንዲሰጡን የምንቀጥራቸው ሰዎች ቢኖሩ እንኳ እንደ ወንድሞችና እኅቶች አድርገን እንድናፈቅራቸው የታዘዝን- መሆናችንን በግልጥ ያመለክታል፡፡_ጌታ አምላካችን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ሆይ ! እኛ ጠላቶችህ ስንሆን አንተ ማንንም ከማን ሳትለይ ሁላችንንም በማፍቀር በቅዱስ ቃልህ እንድንድን ፈቃድህ ስለሆነ ስምህ ይመስገን፡፡ አንተ እንደወደድኸን፡ እኛም ሁሉን-እንድንወድ ንጹሕ ልብ ፍጠርልን፡፡ እነሆ ኢትዮጵያውያን ሕዝብህ ከባዕድ አገር በመጣ ኮምዩኒስታዊ ዓመፅ የተፈጸመውን የብዙ ሕዝብ እልቂት በማስመልከት ሆድ ለሆድ ተባብሰው መኖር-ከጀመሩ-ብዙ-ዓመታት-አልፈዋል፡፡አንተ ግን ቂመኛነትንና በቀልን የማትወድ የርኅራኄ አባት ነህ፡፡ ስለዚህ ይህ ሕዝብ - ብሔራዊ ዕርቀ ሰላም-ካላወረድለት በቀር በሰላም- አብሮ- የመኖር- ዋስትናው አስተማማኝ መሆን-አይችልም፡፡ ስለዚህ የዔሳውና የያዕቆብ የወንድማማችነት ዕርቀ ሰላም ምሳሌነቱ አንድ ቀን ለኢትዮጵያም ሕዝብ እንዲሆንለትና ፍጹም ሰላማዊ የሆነ አዲስ ሕይወት ለመጀመር-እንዲበቃ ታደርገው ዘንድ- ፈቃድህ ይሁን፡ ስለ ስምህ ስትል ማረን፡ይቅርም በለን አሜን!–

## ፴ /30. የመዳን ተስፋ በክርስቶስ ስም

_ቅዱስ ስምህ በበረከትና በምስጋና ክሁሉ በላይ ከፍ፡ ከፍ ያለበትን ድንቅ ሥራ የገለጥህልን ልዑል አምላካችን ሆይ ! የሃይማኖት አባታችን አብርሃምን ከኡር ከላውዴዎን ጠርተህ በበረከት-ያከበርከው-አንተ-ነህ፡፡ የመላው-ዓለም ቤተሰብ-ሁሉ- የአብርሃምን ዘርዐ ትውልድ ሥጋ በተዋሐደ ውድ ልጅህ እንዲባረክበት ፈቃድህ ስለሆነ እናመሰግንሃለን፡፡ ከሰማይ በታች እንድንበት ዘንድ የተሰጠ ሌላ ቅዱስ- ስም የለምና፡፡ ይህም ተቀዳሚ፡ተከታይ-የሌለው ውድ ልጅህ በሥጋ ወደ -ለማችን የመጣ፡ ከሁሉ በላይ የሆነና-ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ መሆኑን-እናምናለን፡፡-ጉልበት-ሁሉ-ለርሱ-ይንበረከካል፡፡በሰማይና- በምድር-ያሉት፡-የሚታዩትና-የማይታዩት-የሰማይ-ኃይላትና-ገገር



ዎች-ሁሉ፡-አለቆችና-ባለሥል-ኖችም የተፈጠሩት በርሱና ለርሱ ነው፡፡ እርሱም -ከሁሉ በፊት የነበረ፡ ያለና የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው፡፡ ዘይእኀዝ ኵሎ በኃይለ ቃሉ= ሁሉም ነገር ተያይዞ የቆመ በርሱ ቃል ነው፡፡ እርሱ በሰማይም በምድርም ያሉትን ሁሉ ከራሱ-ጋር-አስታረቀ፡፡"በመስቀል-ላይ-በፈሰሰ-ደሙ-ሰላምን አደረገ" ተብሎ እንደተጻፈ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ! ለእኛ የሚገባውን መከራ መስቀል በመቀበል እስከ ሞት ድረስ ስለወደድኸን ቅዱስ ስምህ የተመሰገነ ይሁን፡፡ አሁንም የአንተ ቸርነትና ምሕረት የሰው ልጆች ሁሉ ከሚፈጽሙት በደል ሁሉ በላይ ነው፡፡ የሰው ዘር ሁሉ በዕድሜው መጠን የሚፈጽመው በደል /ኀጢአት ሁሉ ተደምሮ ካንተ የጸጋ ምሕረት ጋር በማነጻጸር ሲታይ በውቅያኖስ ውስጥ አንድ አንዲት የውኃ ጠብታ ሲሆን ያንተ የጸጋ ምሕረት ግን ክውቅያንስ ባሕር ይልቅ እጅግ የሰፋ ነው፡፡ ስለዚህም የልጅነት በደላችንን ሁሉ ደምስሰህ በዘለለማዊ ፍቅርህ የሰማያዊት መንግሥትህ ወራሾች የቤተሰብ አባላት ለመሆን አብቃን፡፡ በዚህች ምድር በምንኖርበት ዘመን ሁሉ አንተን ደስ በሚያሰኝህ በቅን መንፈስ በፊትህ መመላለስ እንድንችል በረድኤትህ አትለየን፡ ለዘለዓለሙ አሜን ! ---------

## ፴፩ /31. በደልን በመናዘዝ የሚቀርብ የንስሓ ጸሎት

(ነህምያ ምዕ 9፡1-15 ) ጌታ-እግዚአብሔር አማላካችን ሆይ ! በላይ- በሰማይ፡ በታችስ-በምድር-አንተን የሚመስል-ማን ነው?-ሁሉን የፈጠርህና ለሁሉ ሕይወትን የሰጠህ አንተ ነህ፡፡ ስለዚህም የሰማይ ኃይላት ሁሉ ይሰግዱልሃል፡፡ ከሃይማኖት አባታችን ከአብርሃም ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን በመፈጸም የታመንህና፡- ዘሩን-እንደ-ሰማይ--ኮከብ፣እንደ_ባሕር-አሸዋ-ያበዝህለት ማርና ወተት-የሚፈስባትን ምድረ ርስት ለዝርያዎቹ ያወረስህ አንተ ነህ፡፡ በምድረ ግብጽ በባርነት ቀንበር ሥር የወደቁ የሕዝብህን ጩኸት ሰምተህ ነጻ በማውጣት የታደግሃቸው ቸር አምላክ ሆይ ! ያ የማዳን ኃይልህ ዛሬም ለእኛ የሚያስፈልግበት-ዘመን ነው፡፡ምን-ጊዜም-የማትለወጥ-ሕያው-አማላካችን-ሆይ! ከበደላችን



www.ethiopianorthodox.org

ብዛት የየነሣ ብናሳዝንህም እንኳ እስከ መጨርሻው አትተወን። _የዝናም ጠብታና የሣር፡ ቅጠል ምልክት በማይታይበት በዓረብ ምድረ ብዳ መና ከደመና በማውረድና ውኃም ከጢንጫ (ከዐለት ድንጋት) በማፍለቅ ሕዝብህን መመገብ የቻልህ ፡ ዛሬስ ያ ሁሉ ድንቅ ሥራህ እንድፈጸምልን-ታደርግ ዘንድ ላንተ-የሚሳንህ ነገር አለ እንዴ? ምን ጊዜም ያንተ_አባታዊ- መሪነት፡ መጋቢነትና-በረከትህም ሁሉ ያስፈልገናል። የምንኖርባትን ምድር ባርከህ፡ የበሽታን ዘር ሁሉ ከሕዝባችን አርቅ። ለሀገራችን የልምላሜ ጸጋህን አብዛላት። የተጀመረውንም_የሀገር ልማት እቅድ ለማራመድ-ለሀገራችንና-ለሕዝባችን-የተረጋጋ-ሰላምን ስለሰጠህ ልን ስምህ ይመስገን። በሁሉም_ነገር እንደበደላችን ብዛት ሳይሆን በቸርነትህ የምሕረት ጸጋህን_ አብዛልን። ለምድሪቱ-ዝናሙ- ምሕረትን ስላወረድህላት ቅዱስ ስምህን እናመሰግናለን። አሁንም የተዘራውን የእርሻውን ሰብልና የምድሬቱን ዛፍ ፍሬ ሁሉ ባርከህ ሕዝባችንን ከኑሮ ችግር ጠብቅልን፡ አሜን !

## ፴፪/32 <u>ለመንፈሳዊ ድል የሚያበቃ ኃይለ ጸሎት</u> (ኤፌ 6፡ 10-18)

እውነተኛ ፍትሕ ተጠብቆ እንዲኖር የምትወድና ለሰው ዘር-ሁሉ-እንደ-ሥራው-መጠን-ዋጋውን-የምትከፍል፡ ፡ እድልዎ ንና የዘር ልዩነትን፡ ግብዝነትንና የዓመፅን ሥራ ሁሉ የምትጠላ የሰላም-አምላክ ሆይ! የአብርሃም- ዘሮች የሆኑ የቀድም- አበው ልባቸውን እልኸኛ በማድረግ ትእዛዛትህን ለመከተል እምቢ ባሉ ጊዜ እንደገና ወደ ባርነት ቀንበር እንዲገቡ ፈርደህባቸው ነበር። ነግር ግን እስክ መጨሳ ይጠፉ-ዘንድ አልተውሃቸውም። ያስተምራቸው-ዘንድ-ቅዱስ-መንፈስህን-ስጠሃቸው፡ ዐርባ ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ መገብሃቸው። ምንም ያሳጣሃቸው ነግር-አልነበረም።-ልብስቸውና-ጫማቸው-ሳያልቅ-ወደ-ተስፋዪቱ ምድር መርተህ ለማስግባት ጠላቶቻቸውን ተዋጋህላቸው። ዛሬም እኛ ልጆችህ የጨለማውን ዓለም ከሚገዙ ሠራዊተ አጋንንት ጋር ያለብን የመንፈስ ጦርነት እጅግ የከፋ ነው። ከዚህም የተነሣ የሰይጣን-ዲያብሎስን-የተንኮል-ሥራ ሁሉ መቋቋም እንድንችል



የእግዚአብሔርን ጦር-ማሣሪያ ሁሉ እንድንለብስ በቅዱስ ቃልህ ታዘናል ። ይኸውም ዕውነትን እንደ- ዝናር ታጥቀን፡ ጽድቅን እንደ-ጥሩር-ደፍተን፡ የሰላምን የምሥራች የሚያበሥር ወንጌልን እንደ-ጫማ-አድርገን-በመዘ_ጋጅት-በጠጠንቅቅ-መቆም እንደሚ ገባን-ተነግሮናል። ነገር_ግን ይህ የመንፈስ ተጋድሎ ከአቅማችን በላይ ሆኖ እንዳንሸነፍ ያንተ ኃይለ ረድኤት ያስፈልገናል። የእምነትን ጋሻ መክተን፡ የምንፈስ ቅዱስ ሰይፍ የተባለ ቅዱስ ቃልህን አፅንተን ይዘን-ለመጨረሻ ድል በሚያበቃን መንፈሳዊ ኃይል እየተመራን አዘውትረን የመጸለይን ጥበብ አስተምረን ። የጸሎታችንም ኃይለ ረድኤትን እንደ ኢያሪኮ ግንብ የጠነከረውን የስይጣን ዲያብሎስን ምሽግ ሁሉ የሚያፈራርስ አድርገው። ሀገራችንን ከወራሪ ጠላት። ሕዝባችንንም ከጦርነት ሥጋት ፡ ከአባር ከቸነፈር፡ ከበሽታ ዘርና በተለይም ከድህነት ኑሮ ነጻ አድርግልን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፴፫ /33. <u>ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት ነው</u>

(ሰቈቃ ኤር 3፡ 22 ) የአብርሃም፡ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ሆይ ! በዓለማት ዙሪያ ታይቶና ተሰምቶ የማያታውቅ ያን ሁሉ ድንቅ ሥራ በመፈጸም ከባርነት ቀንበር ነጻ ያወጣሃቸው ሕዝብህ የሰጠሃቸውን-መመሪያ ሕግና እእዛ ረስተው ለባዕዳን አማልክት በመስግድ ባሳዘኑህ፡ ጊዜ ከዚያ በድል እንዲመለሱ አስምክረህ፡ ባይመለሱ ግን ከሰጠሃችው ምድረ ርስት ተነቃቅለው-እንደሚጠፉ-በቅዱስ-ቃልህ-በማስጥንቀቅ ያስተማሯ ችውን ነብያትህን ገድሉ። በክፉ ሥራቸው ባስቈጡህም ጊዜ ለጠላት አሳልፈህ ሰጠሃቸው። እነርሱም በባዕዳን አገሮች ተበትነው በባርነት እገዛዝ ሥር ወድቀው ከተዋረዱ በኋላ መከራ ሲጠናባቸው ተፀፅተው ወደ አንተ ተመልሰው በጸሎት መጮህ ጅመሩ። አንተም መዋረዳቸውን አይተህ፡ ጩኸታችውን ሰምተህ፡እንደ ቸርንትህ ብዛት ምሕረት አደረግህላቸው። የእኛም በደል ከዚህ ያነሰ አይደለም። ከባዕድ አገር ተጎትቶ የመጣውን አደገኛ ርእዮተ_ዓለም ተስፋ በማድረግና እንደ ጣዖት አድርገን በማምለክ አንተን እስከ መካድ የሚያደርስ ተግባር በሀገራችን



www.ethiopianorthodox.org

ተፈጽሟል። ይህም ትውልድን ሁሉ ሲያስረግም የሚኖር በደል ነው። እንግዲህ በቸርነትህ ክምትምረን በቀር ለተጸመው ኃጢአት ሁሉ በቂ ምክንያት ማቅረብ አይቻለንም። ከዚህም በደል የተነሣ ብዙ-ውርደትና መንገላታት የደረሰበትን ሕዝብህን እንደገና በረድኤት እንድትጐበኘው እንማፀንሃለን። ያንተ ጥበቃ አይለየን፡" የሀገሪቱን ዕድገትና ብልጽግና ባርከህ ሕዝባችንን ከኑሮ ችግር በመታደግ ያንተን ቅዱስ ስም የሚያከብር ዘርዐ ትውልድ ለማትረፍ የበቃ አድርገው። አቤቱ ሕዝብህን አድን፡ ርስትህንም ባርክ። ይቅር ባዩ ስለሆነ ቅድስ ስምህ ስትል ጸሎታችንን ተቀብለህ፡ በደላችንን ሳታስብ የቅርም በለን አሜን !

## ፴፬ /34 <u>የማኅበር ጾምና ጸሎት</u> (ኢዮኤል 2፡-12-13)

በነቢዩ-ኢዮኤል ትንቢት- እግዚአብሔር- እንዲህ አለ፡ "በፍጹም ልባችሁን ልባችሁ በጾም፡ በለቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ፡ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ። አምላካችሁ እግዚአብሔር ቸር ነውና፡ ቍጣው የዘገየ፡ ምሕረቱም የበዛ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ። የመለከትን ድምፅ አሰሙ፡የጾምን-ጊዜ አውጁ፡ሕዝቡን ሰብስቡ። ስብስቡ፡ ሽማግሎችንና ጡት የሚጠቡ ሕፃናትንም ሰብስቡ። የእግዚአብሔር ሙሽራውና ሙሽሪቱ ከእልፍኛቸው ይውጡ። የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ ካህናቱም በቅኔ ማኅሌቱና በመንበረ ምሥዋዑ መካከል ቆመው በማልቀስ ጭምር "አቤቱ ለሕዝብህ ራራለት፡ አሕዛብ መዘባበቻ እንዳያድርጓቸው ርስትህን ለባዕዳን ሕዝብ መሣለቂያ አሳልፈህ አትስጥ" በማለት ይጸልዩ። የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና"" ተጽፏል። በዚህም የማኅበር ጾምና ጸሎት የእግዚአብሔር ምሕረት ስለቀረበ፡ እንደገና አንድህ_የሚል የተስፋ-ቃል ተነገረ፡ "ምድር ሆይ! እግዚአብሔር ታላቅ ድንቅ ነገር አድርጓልና ከቶ አትፍሪ፡ ደስ ይበልሽ፡ የምድረ በዳው ከብት መሠማሪያ ለምልሟል፡ ዛፍና ተክልም ሁሉ ፍሬ መስጠት ጀምሯል። ዓውድማዎችም በእህል-ምርት-የተመሉ ሆነዋል"።ቅዱስ--አምላክ-ሆይ! ለመሪጥሃ



ቸው--ሕዝብህ--የተነገረ--ይህ--ተስፋ_ለሀገራችን-ለኢትዮጵያም-እንዲፈጸምላት-አድርግ። የምሕረት አምላክ ሆይ ! ራራልን። ንስሓ ገብተን በጾምና በጸሎት-ወደ-አንተ መመለስ እንድንችል፡ የመንፈስን ብርታት ስጠን። የርኅራኄ ሥራህ አያልቅምና። ድንቅ ሥራህም ሁሉ ከዕለት ወደ ዕለት ምን ጊዜም አዲስ ነው። ነፍሳችን አንተን ተስፋ በማድረግ የፀናች ናት። በጸሎት ደጅ ለሚጠኑህ ሁሉ በጐ አድራጊ-ነህና።_ጌታ-እግዚአብሔር--ለዘለዓለም-አይጥልም፡ቢያሳዝንም እንደ ምሕረቱ ብዛት ይራራልናል። ታዲያ ሕያው ሰው ሁሉ ለምን ያጕረመርማል? በኀጢአት ብዛት ምክንያት ስለደረሰብን ቅጣት ከማጕረምረም ይልቅስ መንገዳችንን እንምርምር። ሁሉን ነገር ፈትነን ወደ አምላካችን እንመለስ። አቤቱ አምላካችን ሆይ ጸሎት ሁሉ ወደ አንተ እንዳያርግ ፊትህን በደመና ሸፈንህን? በቸርነትህ ብዛት ታድነን ዘንድ ቅዱስ ፈቃድህ ይሁን፡ አሜን !

## ፴፭ /35 ብንወድቅም በእግዚአብሔር <u>ኃይል እንነሣለን</u>

(ሚክ 7፡ 7- 20 ) "እኔ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመለከትሁ፡ የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ። አምላኬም ጩኸቴን እንደሚሰማ አምናለሁ።ስለዚህ ጠላቴ ሆይ ! ደስ አይበልህ ! ብወድቅ እንኳ በእግዚአብሔር ኃይለ ረድኤት እነሣለሁ ። በጨለማ ውስጥ ብቀመጥ እንኳ አምላኬ እግዚአብሔር ያበራልኛል።በርግጥ-እኔ-በእግዚአብሔር-ፊት በደልን ሠርቻለሁ። በዚህም ምክንያት ከሚከሠኝ ከጥንተ ጠላት ክሰይጣን ዲያብሎስ እስክሚገትልኝና ፍርዱን ለእኔ እስክሚያ ድርግ ድረስ፡-ቍጣውን-እታገሣለሁ።እርሱም-ወደ-ብርሃን-ያወጣኛል። የጽድቅ ንም መንገድ አያለሁ፡ በደልን ይቅር የሚል፡ የርስቱንም ተረፍ አበሳ ኃጢአትን ሁሉ የሚያሳልፍ አንተን የሚመስል አምላክ ማነው? ምሕርት ማድረግን ትውዳለህ። ቍጣህም እንኳ ለዘለዓለም ፀንቶ እንዲኖር አትፈቅድም ከመዓት ወደ ምሕረት ተመልሰህ-በረድኤት-ትጐበኘናለህ፡-ክፋታችንን-ሁሉ-ታስወግዳለህ፡ ክቀድሞ-ዘመን_ጀምሮ-ለአባቶቻችን የሰጠሃቸውን የተስፋ ቃል ሁሉ_ በመፈጸም _የታመንህ_ ነህ"። ስለዚህ አንተን_ ተስፋ-



www.ethiopianorthodox.org

አድርገን-ለምንኖር-ልጆችህ_ሁሉ አሁንም የጸጋ ምሕረትህን አብዛልንል:: ዛሬም ዘወትርም፡ አሜን !

## ፴፮ /36. በእግዚአብሔር ኃይል ከድል ወደ ድል

_ሰውን_የምትወድ_የሰላም_አምላክ_ሆይ!_አቤቱ_ስላንተ_ድንቅ--ሥራ_ሁሉ_በጆሮአችን_ሰማን::-የቀድሞ--አባቶቻችን በዘማናቸው የፈጸምኸውን_ድንቅ ሥራ ሁሉ ነግረውናል:: ከድል ወደ- ደል የምትመራቸው- ንጉሣቸው አንተ እንደነበርህ ቅዱስ--ቃልህ ይነግረናል:: እኛ_በሰይፋችን ብቻ የምንታመን_አይደለንም:: ዘመናዊ_የጦር መሣሪያም ሁሉ ብቻውን ያድነናል ብለን አንተማመንበትም:: ሁልጊዜ በአንተ ኃይል እንኰራለን::

_ቅዱስ_ ስምህም_እኛ የምንተማመንበት-ታላቅ ዐለት ( ምሽግ ) ነው:: ያንተ ኃይለ ረድኤት ከተለየንና ከሠራዊታችንም ጋር አብረህ ካልወጣህ ግን-በጠላታችን_ፊት_ለሐፍረት-የተጋለጥን-እንዳንሆን- እርዳን:: ስለዚህም የአባቶቻችን አምላክ_ሆይ! ይህችን ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት አስፋፊ ጠላት-በተፈታተናት ቍጥር በየዐረፍተ ዘመኑ ሁሉ ለአባቶቻችን ያስገኘህላቸውን ብዙ ዓይነት የታላላቅ ድል ምዕራፎች፡ በዚህች ቅጽበት እናስባለን:: ሌላው አስደናቂ ቸርነትህ ደግሞ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪቃ ቀንድ ላይ ቅኝ ገዢዎች የቀሰቀሱትን አሥጊ-ጦርነት -ሁሉ በመፋለም ስትኖር እንደ ሌሎች አንዳንድ የጐረቤት አገሮች ሳትጠፋና መንግሥትዋም ሳይፈርስ የአፍሪቃ ውያን-አህጉር-ዋና-መዲና-መሆንዋ-ሳይለወጥ-ህልውናዋ ተጠብቆ ላት እንድትኖር አድርገሃል:: በዚህም ቸርነትህ ዘለዓለማዊ ሕያው-ስምህን-እናመሰግናለን::-የሀገሪቱን-መሪዎች ከሠራዊታ ቸው ጋር፡ እንዲሁም በዱር በገደል ተሠማርተው የነበሩትን እልፍ አእላፋት ተጋዳዮች ዐርባኞቻችን ያንተ ኃይለ ረድኤት "ሳይለያቸው ለሀገሪቱ ነጻነትና ሉዓላዊነት-ክብር፡- የሕዝቡን ሕይወትና ንብረት ከወራሪ ጠላት ለመጠበቅ በየክፍለ ሀግሩ የከፈሉትን ውድ የሕይወት መሥዋዕትነት ሁሉ በዚህች ቅጽበት በጸሎት እናስባለን:: በውጭ ወራሪ ጠላት ላይ ስላጐናፀፍሃቸው ታላቅ_ድል አድራጊነት ሁሉ ቅዱስ ስምህ



የተመሰገነ ይሁን:: በዚህም ሁሉ የዐርበኝነት ሙያ በየክፍለ ህገሩ በሞት፡ ሽረት ትግልና ትንቅንቅ ላይ ሳሉ፡ ከወራሪ ጠላት ጋር በመዋደቅ፡ በየጦሩ ግንባር ደማቸው የፈሰሰ:: አጥንታቸው የተከሠከሠ፡ ሕይወታቸው ያለፈ፡ ዐፅማቸው የረገፈ፡ የጀግኖች ዐርኞቻችንን ነፍስ ሁሉ ከዳግም ሞት ጠብቅልን:: አሜን !

## ፴፯/37፡ የእግዚአብሔርን ቃል የመስማት ጥበብ

_በጸሎት-ስምህን_በምንጠራበት_ጊዜ_ሁሉ_ፈጥነህ የምትሰማንና የልባችንን አሳብ_ሁሉ የምትፈጽንልን ጌታ አምላካችን ሆይ ! !በልብ የዋህነት ይመራ በነበረው በቅን አገልጋይህ ነቢይ ሙሴ-አንደበት-ለሕዝብህ-የተነገርኸውን-ሕያው-ቃል እናስታውሳ ለን-፡ እርሱም እንዲህ የሚል ነው፡- "አምላካችሁን እግዚአብሔ ርን የተከተላችሁ እናንተ እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት አላችሁ፡ አምላኬ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ሕጉንና ሥርዓቱን አስተምሬአችኋለሁ፡ የተማራችኋትንም ሕግ ጠብቋት:: ትእዛዛቱ ንም ፈጽሙ:: ይህች ቅድስት ትእዛዝ ስትነገር ሰምተው 'በእውነት ይህን ቃል የሚሰማ የእግዚአብሔር ሕዝብ ብልህና አስትዋይ ነው' በለው በሚያደንቁ አሕዛብ ፊት ጥበበኞችና-አስተዋዮች -መሆናችሁ--የሚታወቅበት ምልክት እግዚአብሔር ራሱ-የተናገረውን ቃል ሰምታችሁ ለመፈጸም መቻላችሁ ነውና::

ለምላካችን-እግዚአብሔር በምንጠራው ጊዜ ሁሉ እንደሚሰማንና እንደሚቀርበን-ታውቃላችሁ፡-በምድር ላይ አምላኩ እግዚአብሔር እንደዚህ የሚቀርበው ታላቅ ሕዝብ ከናንተ ሌላ ማነው"::_ይህን ሁሉ ስንመለከት በእውነት የዘነጋነው ታላቅ ጥበብ ቅዱስ ቃልህን ዘወትር ማንበብ፡ መስማትና ማጥናት፡ በቀንና በሌሊት ማሰላሰል አለመቻላችን ነው:: እንግዲህ ምን እናመክኛለን ? እንጠብቀው ዘንድ የተሰጠን የሕያው ቃልህ መጽሐፍ በእጃችን ነው:: በየጊዜው የሚነገር ቃልህ በልብችን ሲወጣ፡ ሲወርድ፡ በአእምሮአችንም ሲመላለስ የሚኖር ነው:: ምን ጊዜም ቃልህ ከእኛ ሩቅ አይደለም::አሁንም-ቃልህን ሁልጊዜ ሰሚዎች ብቻ ሳንሆን ተግብራዊ አድርገን እንድንመራበት በቅዱስ-መንፈስህ-የማስተዋልን ጥብብ አብዛልን::_"ቃሉን ሰምቶ ተግባራዊ



www.ethiopianorthodox.org

የማያደርገው ሰው ፊቱን በመስታወት አይቶ ዘወር ሲል የሚረሳውን ሰው ይመስላል" ሲል አገልጋይህ ሐዋርያ ያዕቆብ በጻፈው መልእክቱ ነግሮናል (ምዕ 1፡ 22-24)። በቀድሞ አባቶቻችን- የመታዘዝ ሕይወት ደስ እንደተሰኘህ፡ የእኛም ሕይወት አንተን ደስ በሚያሰኝህ ቅን መንፈስ እንዲመራ ቅዱስ ቃልህን በመስማት የሚገኝ ያንተ ረድኤት ያስፈልገናል። ለቅዱስ ቃልህ ታዛዦች በሆንን መጠን የእጃችንን ሥራ ሁሉ ባርከህ በከብታችን ርቢ፡ በምድራችን ፍሬ ሁሉ እንድታከብረን ፈቃድህ ይሁንልን፡ ስለ ሕያው ስምህ በምሕረትህ ጐብኘን፡ አሜን ! """""""""""""""""""""""""""""""

## ፴፰ /38. <u>መኑ ይክለነ ለእመ እግዚአብሔር ምስሌነ</u>

_እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ያሸንፈናል? ሮሜ 8፡ 32 ፦ አቤቱ ዘለዓለማዊ የሠራዊት ጌታ ሕይው አምላካችን 'ሆይ ! አንተ አምባ መጠጊያችንና ኃይላችን ነህ። ባገኘን መከራ ጊዜ ሁሉ ረዳታችን ስለሆንህ፡ ምድር ብትነዋወጥ፡ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም፡ ከቶም አንደነግጥም። የሠራዊት ጌታ አንተ አማኑኤል ምን ጊዜም ከእኛ ጋር ነህና። በምድር ላይ ያደረግኸን ታላላቅ ድንቅ ሥራ ሁሉ አይተናል።

_በዓለማት ዙሪያ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ጦርነትን የምትሽር ፡ ቀስትንም ሁሉ የምትሰብር ፡ ሰይፍና ጌራዴን ማስወገድ የሚቻልህ ፡ ሠርገላንም በእሳት የአምታጋይ ፍጹም የሰላም አምላክ ነህ ። ይህንም ሁሉ ማድረግ የሚቻልህ የሰላም አምላክ ሆይ! እርስ በርስ የሚያፋጅ የሰይጣን ፈተና እንዳይበረታብን በጸሎት ኃይል የመከላከልን ብቻ ሳይሆን የጥንተ ጠላትችን የሰይጣን ዲያብሎስን ምሽግ የማፈራረስን ኃይል_ስጠን። እንዴት መጸለይም እንደሚገባን በቅዱስ መንፈስህ አስተምረን። ,ጌታ እግዚአብሔር አምላካችንሆይ_! እኛን ልጆችህን ለመታደግ ተነሥ፡ ጠላቶችህም ይበተኑ። ሁሉን የማድረግ ሥልጣን ያለህ የንገሥታት ንጉሥ፡ የጌቶችም ጌታ የሆንህ ቸር መድኃኔ ዓልም ክርስቶስ ሆይ ! አንተ የጻድቃን ምርኩዛቸው። ለተስደዱም



ሁሉ ተስፋቸው፡ በባሕር ጕዞ ለሚታወኩም ሁሉ ማረፊያ ወደባቸው ነህ። የፍጹማን ብርሃን ጌታ አምላካችን ቸር መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ሆይ ! ባንተ መታመንንና የማያዘነብል የሃይማኖትን ኃይል- የማይለወጥና የማይናወጥ ተስፋንም አፅናልን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፴፱/39. በአደጋ ጊዜ እግዚአብሔር መልአክ ተራዳኢነት

_<u>(ኢዮብ 33፡ 23 -24)</u> ዘለዓለማዊ አምላክ ሆይ! አገልጋይህ ያዕቆብ የልጁን የዮሴፍን ልጆች ሲመርቅ የተናገረውን ቃለ በረከት እናስታውሳለን። እርሱም ፦"አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ በቅንነት ፀንተው የኖሩ የክብር ባልቤት እግዚአብሔር፡ ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የመገበኝ እግዚአብሔር፡ እንዲሁም ከክፉ አደጋ ሁሉ የታደገኝ የእግዚአብሔር መልአክ እነዚህን ልጆች ይባርክ ፡ ዘራቸውም ይብዛ" የሚል ነው።

_እኛም እንደዚሁ ይህን አርአያና ምሳሌነት ተከትለን፡ አማኞችን ለመርዳት ያንተን ቅዱስ ትእዛዝ ይፈጽሙ ዘንድ በምትልካቸው ቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት ተድግፈን እንድንኖር ፈቃድህ ስለሆነ ስምህ ይመስገን። "እነሆ በመንገድህ ሁሉ እንድጠብቅህና እኔ ወደማዘጋጃት ምድር በሰላም ያስገባህ ዘንድ በፊትህ የሚሄድ መልአኬን እልካለሁ፡ እርሱም የሚነግርህን ስማ፡ ለቃሉም ታዘዝ፡ በርሱ ላይ እንዳታምፅ ተጠንቀቅ፡ ስሜ በርስ ስለሆን፡ የምትፈጽመውን ዓመፅና በደል አይቶ ምሕረት አያደርግልህም። ለርሱ ብትታዘዙና እኔ የምንግራችህንም ቃል ብትፈጽሙ ግን ጠላቶቻችሁን ሁሉ እኔ ራሴ እዋጋልችኋለሁ" ስትል የተናገኸውንም ቃል እናስታውሳ ለን። ያንተን ቅዱስ ፈቃድ መፈጸምና አማኞችን መርዳት ተግባራቸው የሆነ፡ ሊቃነ መላእክት ለሰው ዘር ደኅንነት ምሕረትን በመለመንም የሚማልዱ ናቸው። ስለዚህም የስአሴ ምሕረት ሊቀ መላእክት- ቅዱስ ሚክኤልን፡ የጌታን ልደት ያበሠረ የመጋቤ ሐዲስ ቅ/ ገብርኤልን፡" የጦቢትን፡ የሣራ ወለተ ራጉኤልንና የጦቢያን ጸሎት ተቀብሎ ወደ አንተ በማሳረግ የረዳቸውን የቅ/ ሩፋኤልን፡ የመገብተ ብርሃናት ቅ/



www.ethiopianorthodox.org

ራጉኤልንና የቅ/ ኡራኤልን :የቅ/ ሱርያልንም ታራዳኢነት አታርቅብን:: በትንቢተ ዘካርያስ (1፡ 12 -13) ተጽፎ እንደሚገኝ፡ አንተ የላክኸው አንድ ቅዱስ መልአክ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች ህሉ በቍጣና መዓትህ ከፈረድህባቸው እነሆ ሰባ ዓመት ሆኗል፡ የማትምራቸው እስከ መቼ ነው?" ሲል ላቀረበው የምልጃ ጥይቄ-የሚያፅናና ቃል እንደ መለስህለት ተጽፏል:: የሰጠኸውም የተስፋ ቃል "የምሕረት ፊቴን ወደ ኢየሩስሌም እመልሳለሁ፡ ቤተ መቅደሴም እንደገና በርስዋ ይሠራል" የሚል ነው:: ጌታ ሆይ ! ይህ የተስፋ ቃል ለእኛም አገር እንዲፈጸምላት ፈድህ ይሁን:: ለሀገሪቱ የታቀደውን የልማት ዕድገት ሁሉ ባርክህ በኑሮ ችግር የተፈተነ ሕዝብህ የሚበለጽግበት ምክንያት እንድታደርገው እንማፀንሃለን፡ ለዘላለሙ፡አሜን ! ''''''''''

## ፵ /40. <u>የበደልን ይቅርታ-መጠያቂያ ጸሎተ</u>

_አቤቱ የምሕረት አምላክ ሆይ ! እንደቸርነትህ ማረኝ፡ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ፡ ከበደሌም ሁሉ አጥበህ በፍጹም አንጻኝ:: እኔ ራሴ ሕግህን በመጣስ ትእዛዝትህን በማፍረስ መተልለፌን አውቃለህ፡ የሠራሁትም በደል ሁሉ ምን ጊዜም ከፊቴ ሊሠውር አይችልም:: በተለይ አንተን ብቻ በደልሁ፡ ክፉ ነገርንም በማረግ አሳዝናሃለሁ:: አቢቱ እንደገና ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፡ የቀናውንም መንፈስ በፊቴ አድስ፡ ከፊትህ አትጣለኝ፡ ከባለሟልነትህም አታውጣኝ:: ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ አትውሰድብኝ፡ የማዳንህንም ደስታ ስጠኝ:: ያንተ መሥዋዕት ትሑት ልብ ነው፡ በሐዘን የተሰበረውንም ልብ አትንቅምና :: አቤቱ የጽድቅ ሁሉ ባለቤት የሆንህ ፈጠሪ አምላኬ ሆይ ! ጸሎቴን ስማ:: ንስሓዬንም ተቀበል፡ ምሕረትህ ፈጥኖ ይጐብኘኝ፡ ገጸ ምሕረትህን በእኔ ላይ አብራ:: ከሹሕተትም ሁሉ ተጠብቄ አንተን ድስ በሚታሰኝህ መንፍስዊ ሕይወት መኖር የምችልብትን የመንፈስ ኀይልና ብርታትን ስጠኝ:: አቤቱ መሐሪና ኃጢአትን ሁሉ ይቅር ባይ አምላካችን ሆይ ! በውድ ልጅህ ክቡር ደም የተዋጀን እኛ ልጆችህ እንደገና ተመልሰን ወደ ኃጢአት ባርነት እንዳንገባ በሃይማኖት ኃይል እርዳን:: ለዘርዐ አዳም /ለዓለም ሁሉ የገባኸውን ቃልና የገለጥኸውንም ፅኑ ፍቅር አይተን አምነንብሃልና::

_እኛ ጠላቶችህ ሆነን ሳለን፡ እስክ ምት የወደደንን አንድ ልጅህን ወደ ዓለማችን ስመላክ ቅዱስ ፈቅድህ ስልሆነ ስምህ ይመስገን:: በርሱም ክቡር ደም የተዋጅን ልጅችህን እንድገና ለሰይጣን ከመሸነፍ ጠብቃን፡ አድነንም :: እንደ ወዳጅህ እንደ አብርሃም ለቅዱስ ቃልህ ታዛገዮች በመሆን፡ በቀና መንፈስ በፊትህ መመላለስ እንድንችል የልብ የዋሃትንና የትሕትናን ሕይወት ስጠን:: እንደ ዐለት ድንጋይ የጠጠረውን ልብ አውጥተህ ለቅዱስ ቃልህ ታዛኘ የሆነ አድስ ልብ ስጠን:: በተልይም ሰይጣን ምንጊዜም ከክፋት የምይገታ ጥንት ጠላት ስለህነ ከሚያመጣው-ትዕቢት ተጠብቀን እንድንኖር በረዳኢኤህ አትለየን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ''''''''''

## ፵፩ /41. ለኢዮሳፍጥ ታላቅ ድልን ያቀዳጀ <u>ኃይለ ጸሎት</u>2

2 ዜና 20፡ 3-12) "የቀድሞ አባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ! ልዩ ግርማ ሞገስ ባለው ስማይዊ ዙፋንህ ፀንተህ በዓለማት ዙሪያ ያሉ መንግሥታትን ሁሉ የምትመራ አንተ ነህ:: ሥልጣንም ሁሉ በአንተ እጅ ነው:: ያንተን አሳብ ማስለወጥና ያንተን ኃይል መቋቋም የሚችል ምንም ዓይነት ምድራዊ ኀይል የለም:: ወዳጅህ ለነብረው ልአብርሃም የተናገርኸውን ተስፋ በመፈጸም ለዝርያዎቹ ርስት አድርገህ በስጠኸው በዚህች የተስፋ ምድር እንድንኖር ፈቃድህ ሆኖ ይኸው እስካሁን በሰላም ቆይተናል:: ሕዝብህም ያንተን ኃይል መከታ በማድረግ ጦርነትም ሆነ አባር፡ ቸነፈር በደረሰ ቍጥር በቢተ መቅደስህ በፊትህ ተሰብስበው ወደ አንተ ይጮኻሉ:: አንምተም ሳታሳፍራቸው፡ ጸሎታቸውን ሰምትህ ከብዙ ወራሪ ጠላት ሁሉ በኃያሉ ክንድህ ስትታድጋቸው መኖርህን እናምናለ:: እነሆ አሁንም እንደገና ያነተ ኃይለ ረድኤት በሚያስፈልግበት ፍጹም አስጨናቂ ወቅት ላይ እንገኛለን::


www.ethiopianorthodox.org

እነሆ የሞአብና የኤዶም ሕዝቦች በአድማ ተማምለው ያልተጠበቀ አደጋ ሊጥሉብን በእኛ ላይ ዘምተውብናል። የነዚህን አገሮች ሠራዊት ሁሉ ለመቋቋም ከአቅማችን በላይ ሆኖብናል። አንተ ራስህ ካልቀጣሀቸው በቀር በእኛ አቅም የሚገኝ ድል ይኖራል ብለን በራሳችን የመተማመን ተስፋ የለንም። በአንተ ዘንድ ግን እነርሱ ኢምንት ናቸው። እኛ ያንተን እርዳታ ለማግኘት እጃችንን ወደ አንተ በጸሎት ከመዘርጋትና ዓይናችንንም ወደ አንተ ከማንሣት በቀር ምንም ነገር ማድረግ እንደማንችል-አቅማችንን-ታውቀዋለህ"።-

የሠራዊት-ጌታ አምላካችን ሆይ ! ይህን የንጉሥ ኢዮሳፍጥን ጸሎት ሰምተህ፡ ከአገልጋዮችህ ከነቢያት አንዱ የሆነውን ያሕዝኤልን ልከህለት የተናገረው አስተማምኝ የተስፋ ቃልህ እንዲህ የሚል ነበር፡--"ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ሆይ ! እናንተም የይሁዳና የኢየሩስሌም ኑዋሪዎች ሕዝብ ሁሉ እግዚአብሔር ስለ እናንተ የተናገረውን ቃል ስሙ፡ "ይህን የታላቅ ሕዝብ ሠራዊት-ለመቋቋም-አትፍሩ፡-የምዋጋላችሁ-እኔ--ራሴ እግዚአብ ሔር ነኝ እንጂ እናንተ አይደልችሁም። እናንተ በየረድፉ ስፍራ፡ ስፍራችሁን-ይዛችሁ-በመቆም-ጠብቁ፡-እኔ-ድልን እንደማጐንጽፋ ችሁ ዛሬውኑ በዓይናችሁ ታያላችሁ"።

ይህንም የተስፋ ቃል በመፈጸም እነርሱ ተሠልፈው ለቅዱስ ስምህ በሚዘምሩበት ጊዜ የጠላቶቻቸውን ምሽግ በማፈራረስ ያን ሁሉ የጠላት ሠራዊት በማይዳግም ሁኔታ እንደመታህላቸው ከቅዱስ ቃልህ እንረዳለን። የዚያን ሁሉ ሠራዊት ምርኮ ለመሰብሰብ ብቻ ሦስት ቀን ፈጀባቸው" የብሎ ተጽፏልና። ይህኑ ዓይነት ድል እኛም በጠላታችን ሰይጣን ዲያብሎስ ሠራዊት ላይ መቀዳጀት እንድንችል ያንተ ኃይለ ረድኤት ያስፈልገናል፡-ባንተ ኃይል -መንፈሳዊ ድልን ተቀዳጅተን "ኃይል የእግዚአብሔር-ነው፡-ማዳን- የእግዚአብሔር፡- ጥበብ የእግዚአብ ሔር።አንመካም-በጉልበታችን፡-እግዚአብሔር-ነው-የእኛ ኀይላችን" እያልን ለመዘመር አብቃን፡ ስለ ስምህ ስትል፡ አሜን !

''''''''''''''



## ፵፪ /42. ንጉሥ ሕዝቅያስን ከሞት አፋፍ የመለሰ ጸሎት

_"በኪሩቤላዊ ዙፋን የምትኖርና ሠራዊተ መላእክት በየነገዳቸው የሚያመሰግኑህ አሸናፊ፡ ኃያል ባለግርማ የሆንህ ዘለዓለማዊ አምላክ ሆይ ! የሕይወቴ አለኝታ አንተ ብቻ ነህ። የሕይወቴ ዘመን አክትሞ ወደ መቃብር በር የምገባበት ጊዜ ደረሰ' ብዬ ነበር። ከእንግዲህ ወዲህ በሕያዋን ምድር እግዚአብሔርን የማየት ተስፋ አይኖረኝም ብዬ በአሳብ ተጨንቅሁ። የነፍሴ ማረፊያ የሆነው ሥጋዬ እንደ መከራ ድንኳን ተነቅሎ የተጠቀለለና ከእኔ የተወገደ መስሎኝ ነበር። ሕይወቴ እንደ ሸማኔ ዕቃ ተጠቅሎ ወደቀ፡ አለቀለት በቃ" አልሁ። እንደ ርግብም ማጕረምረም ጀመርሁ። ዓይኖቼ ወደ ላይ ከማየት ደከሙ፤ ጌታዬ ሆይ ! ተጨንቄአለሁና-መከታ-/ጥላ፡- ከለላ ሁነኝ" አልሁ። አንተም ጩኸቴን ሰምተህ ከሕመም ፈውስኸኝ፤ ወደ ሕይውትም መልሰህ ዕድሜ ጨመርህልኝ፤ ንፍሴን ከምት ጕድጓድ አድንኃታል። የሠራሁትን በደል ሁሉ ወደ ኃላ ጣልህ። አቤቱ ጌታ ሆይ ! ለእኔ ይህን ሁሉ ምሕረት ነገር ማድረግህ እጅግ ድንቅ ነው። መቀብር ላንተ ምስጋና የለውምና፤ ሞትም ላንተ ክብርን አይስጥም "። ጌታ አምላካችን ሆይ ! ይህን ጸሎት ተቀብለህለት ንጉሥ ሕዝቅያስን ከሕመም ፈውሰህ በጊዜ ላይ ጊዜን በመጨመር ዕድሜ በ15 ዓመት እንዲራዘም አድርገህለታል። እኛም ያለ ዕድሜአችን በሞት ከመነጠቅ ጠብቀን። ሰውነታችንን ከሚያድክም ደዌና ሕመም በጸጋህ እንድትፈውሰን በጸሎት እንምፀንሃለን አሁንም በሕመም ላይ የሚገኙ የአገልጋህን /የአገልጋዮችህን የ------------------------ ሕይወት-በመፈወስ፡ ከዚህ ብርቱ ሕመም በማዳን- ለመታደግ ፈቃድህ ይሁን። የሕመም ዓይነቶች ሁሉ ባንተ ዘንድ ኢምንት ናቸውና ለመፈወስ እጅህን ዘርጋ፡ የማዳን ኃይልህንም ግለጥ። ላንተ የሚሳንህ ምንም ነገር የለምና አባት ሆይ ! አታሳፍረን። ለዚህ ሕመም ኃይል የሆነ የሰይጣን ማሰሪያ ሁሉ እንዲፈታ አድርግልን። ለመፈወስ ኃይል ያለውን ቅዱስ ስምህን አክብረው። ለዝዘአኣለሙ፡ አሜን 1።



www.ethiopianorthodox.org

## ፵፫/43. የሥራ አጥነት ችግር የሚቀርብ ጸሎት

_ሁሉን ማድረግ የምትችል የዓለማት ሁሉ ፈጣሪና አስገኝ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! የመጀመሪያውን ሰው ፈጥረህ በገነት ባኖርኸው ጊዜ እንኳ በሥራፈትነት /ቦዝኖ እንዲኖር አልፈቀድህም ። በልዩ፡ ልዩ ተክል ያስጌጥሃትን ምድረ ገነት በመከባከብ ይጠብቃት ዘንድ አዘኸዋል። ይህም አስደናቂ ትእዛዝ ሰውን በሥራ ለሥራ እንደፈጠርኸውና ሥራም ራሱ ክቡር መሆኑን ያመለክታል። በሐዲስ ኪዳን ትምህርትም "ቅንነት የሞላበት-አገሎትችሁን-ለእግዝ|አሔር- እንደተቀደሰ መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ" (ሮሜ 12፡ 1) ተብሎ በአገልጋይህ ሐዋርያ ጳውሎስ ያናገርኸውን ሕያው ቃልህን እናስታውሳለን። ስለዚህ በሰጠኸን ጤናማ ሕይወትና እውቀት መጠን እየሠራን ራሳችንንና ቤተሰባችንን በመርዳት፡ ያስተማረንንንም ሕዝብ ውለታ መመለስ እንድንችል የሥራ አጥነትን ችግር አስወግድ ልን።--አገሪቱን-የሚያለሙና፡ የሚያበለጽጉ አገር-በቀል የሆኑና ሕዝብህን የሚወዱ ሰባአዊ ርኅራኄም ያላቸውን የባለሀብቶችን (Investors) ቍጥር እንድታበዛልን ፈቃድህ ይሁን ። ለግል ጥቅም ብቻ የመስገብገብን ጠባይ አርቅልን፡ እኛም ሐኬትን /ስንፍናን ሁሉ አስወግደን ሀገራችንንና ሕዝባችንን ማገልገል እንድንችል ፍትሕ፡ ርትዕ፡ የፍቅር አንድነትና ሰላም በሰፈነበት የሥራ መስክ እንድታሠልፈን ፈቃድህ ይሁን። በተለይም ያንተ ቅዱስ ስም በሚከብርበት የሥራ መስክ ተመድበን የምንሰጠው ቅን አገልግሎት ሁሉ ለበረከት እንዲሆን እርዳን። የማንም ሸክም ከመሆን ይልቅ ራሳችን ሠርተን በሥርዓት የመኖርን ጥበብ አስተምረን። ለሥራ በምንሠማራበትም ጊዜ ሁሉ ከሥራ አለቆቻችንና መሪዎቻችን፡ እንዲሁም ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር በጥሩ ሥነ ምግባር የመግባባትና የመቻቻል፡ የመደጋገፍም መንፈስ እንዲኖረን ሕይወታችንን ምራ። በቅዱስ መጽሐፍ እንደምናነበው ከዮሴፍ ጋር በረድኤት ሆነህ የሚሠራውን ሁሉ እንደባረክህለትና ለርሱ ስትል ያሳዳሪውን ግብጻዊ ሀብት እንዳበዛህለት-የተጸፈውን-ድንቅ-ታሪክ-በቅዱስ-ቃልህ እናስታው



ሳለን (ዘፍጥ 39፡ 1 -6)። በያዕቆብም አድረህ ያጎቱን የላባን ቤት እንዳበለጸግህ ተጽፏል። እኛም እንደዚሁ በመንግሥትም ሆነ በግል-ድርጅት-በምንመደብበት-የሥራ አሠላለፍ የምናበረክተው አገልግሎት-ሁሉ-ፍሬያማ-ሆኖ ያንተንም ቅዱስ ስም የሚያስመ ሰግን እንዲሆን አድርግልን። በሁሉም የሥራ መስክ በፍጹም ጤናማ ሕይወት ማገልገል እንድንችል ጸጋህን አብዛልን፡ ለዘላለሙ፡ አሜን ! ..........

## ፵፬ /44. መሐኖች በእምነት የሚያቀርቡት ጸሎት(1ሳሙ.1፡9-11)

_የምድር ዕፀዋትና አትክልት ሁሉ ከባሕርያቸው አበባና ፍሬ ማስገኘት እንዲችሉ አድርገህ የፈጠርሃቸው፡ የምድር እንስሳትና አዕዋፈ ሰማይንም ሁሉ ጥንድ፡ ጥንድ አድርገህ በመፍጠር ያለ ተተኪ ዘር እንዲቀሩ የማትፈቅድ ርኅሩኅ አምላክ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ! የአገልጋዮችህን የነቢዩት ሐና እመ ስሙኢልን፡ የይስሐቅን፡ በዘመነ ሐዲስም የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ-እናት-የነበረችውን-የኤልሳቤጥንና የዘካርያስን ፡ የቅድስት ሐና እና የኢያቄምን ጸሎት ተቀብለህ የተባረኩ ልጆችን በመስጠት የፈጸምህላቸውን ድንቅ ሥራ ሁሉ፡ በዚህች ቅጽበት አስብለሁ።_እኔም አገልጋይህ (እከሌ /ሊት-) የዚህ ሁሉ በረከት ተካፋይ እንድሆን ላንተ የሚሳንህ ነገር እንደሌለ አምናለሁ።

_የአገልጋይህ የያዕቆብ ሚስት ልያ መልክ በባልዋ ዘንድ የሚያስወድድ ባለመሆኑ ምክንያት የተጠላችውን ያህል እንድትወደድ ለማድረግ ማሕፀንዋን ከፍተህላት በተከታታይ ዐራት ልጆችን የመውለድ ጸጋህን አብዝተህላት እንድነበር በቅዱስ ቃልህ ተነግሯል ( ዘፍጥ-30፡ 31 -35)። አቤቱ የምሕረት አምላክ ሆይ ! እኔስ አገልጋይህ ( -------- ) ልጅ ከማጣት የተነነሣ የደረሰብኝን ሐዘንና ተስፋ መቍረጥ አይተህ ለመርዳት የሚሳንህ ነገር አለ እንዴ ? እነሆ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረታትን ሁል ጥንድ፡ ጥንድ (ተባትና እንስት) ሆነው እንዲፍጠሩ አድርገህ ተተክ ዘር ሰጥተሃቸዋል። እኔስ ከፍጥረትህ ሁሉ ተለይቼ ያለተተኪ ዘር- እንድቀር ፈቃድህ ነውን? አቤቱ ጌታ ሆይ ! ወደ እኔ ወደ አገልጋይህ ጸሎት



www.ethiopianorthodox.org

ተመልከት። ለልብ ተስፋ፡ ላይን ማረፊያ። _ለሕይወት ታሪክም ማዘከሪያ የሚሆኑና በተለይም ያንተን ቅዱስ ስም የሚይከብሩ ቡሩካን ልጆችን ብትሰጠኝ በቅዱስ ቃልህ ታንፀው ማደግ እንዲችሉና መንፍሳዊ ሕይወት እንዲኖራችው ለማስተማር ቃል እገባለሁ። "ቅንና ትክክል የሆነውን መልካም ነገር ሁሉ በማድረግ የእግዚአብሔርን ቅን መንገድ እንዲከተሉ ልጆቹንና ቤተሰቡን በመምከርና በማስተማር ይመራቸው ዘንድ እኔ እርሱን መርጨዋለሁ" ስትል በዘፍጥ 18፡19 እንደተጻፈ ለወዳጅህ ለአብርሃም ከሰጠኸው ተስፋ ተካፋይ ለመሆን እንድትረዳኝ ፈቃድህ ይሆን ዘንድ በጸሎት እማፀንሃለሁ።

_ነፍስየኒ ለከ ተሐዩ፡ ወዘርዕየኒ ለከ ይትቀነይ= ነፍሴ ባንተ ሕያዊት ሆና ትኖረለች፡ ዘሬም ሁሉ ላንተ ይገዛልሃል (መዝ 22፡ 29 -30)። የጠየቁህን የማትነሣ፡ የነገሩህንም የማትረሳ ርኅሩኅ ሰማያዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ ! መሐንነትን ከእኔ አርቀህ የተባረኩ ልጆችን በመስጠት የልቤን አሳብ ፈጽምልኝ። መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነው ሕያው ስምህ ስትል ጸሎቴን ተቀብለህ እኔን ለመርዳት ፈቃድህ ይሁን። ርኅሩኅ አባት ሆይ ! እንደበደሌ ብዛት ሳይሆን፡ እንደ ቸርነትህ ማረኝ፡ ጸጋህንም አብዛልኝ፡ አሜን !

## ፵፭ /45. <u>የተማሪዎች አእምሮ መክፈቻ ጸሎት</u>

_ሰብአዊ አእምሮ ተመራምሮ ሊደርስበት የመይችል የጥበባት መዝገብ ያለህና ሁሉን የምታውቅ ጌታ አምላካችን ሆይ ! አገልጋይህ ንጉሥ ሰሎሞን ከሌላው ምድራዊ ሀብትና ብልጽግና ይልቅ ክፉና ደጉን ለይቶ ማወቅ የሚችልበትን ልዩ የማስተዋል ጥበብ እንድትገልጥለት በጸሎት ያቀረበውን ጥያቄ ተቀብለህ የፍትሐዊ ጥበብንና የዕውቀትን ጸጋ እንዳበዛህለት ቅዱስ ቋልህ ይነግረናል። እኛ ሁላችን ያለንበት ይህ ዘመን ያለ ትምህርት መኖር የማይቻልበትና ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ስለምታውቅ፡ ለእኛ ለልጆችህ የሚጠቅመንን ዕውቀትና



የማስተዋልን ጥበብ አብዛልን። በዓለማች ያለውን ክፉውንም፡ ደጉንም ነገር ሁሉ ለይተን ለማወቅ በጥልቀት የምንመረምርበትን ብርቱ ኃይል ያለውን መጠነ ሰፊ የሆነ አእምሮ ስለፈጥርህልን-ስምህ-ይመስገን።-በርቀትና በጥልቀት ከሚካሄደው ከጊዜአችን-የምርምር-ጥናት-መብዛት የተነሣ ሰብአዊ አእምሯችን ሲሸከመው- ከሚችለው በላይ ሆኖበት በከንቱ እንዳይዝልና እንዳይደክም በቅዱስ መንፈስህ ኃይለ ርድኤት-ልዩ-የማስተዋል-ጥበብ-የመሳበት-እንዲሆን -አድርግልን።

_አእምሮአችን ይበልጥ አስተዋይና ብሩህ መሆን እንዲችል የእውቀትን ብርሃን ሣልበት። "ወለእመ ቦ ዘኃጥአ ለጥበብ በመካከላችሁ ጥበብ የጎደለው ሰው ቢኖር በጸሎት ይጠይቅ ፡ እግዚአብሔር ይሰጠዋል" ተብሎ በተነገረ ሕያው ቃልህ እናምናለን። የፍትሕና የሕገ ርትዕን ምሥጢር ለሙሴ፡ የእጅ-ጥበባትን-ሙያ-ለባስልኤልና ለኤልያብ፡ ለባዊነትን ለዳዊት፡ ጥበብን ለሶሎሞን የሰጠህ፡ የጥበባት ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ! ለእኛ ለልጆችህ የሚያስፈልገንን የማስተዋል ጥበብ ስጠን። የምንማረውንና የምናነበውን-የመጻሕፍት-ምሥጢር-በመገንዘብ--ለሚቀርብልን-የችሎታን-መመዘኛ /ፈተና ሁሉ ተፈላጊውን ፈጣን መልስ የመስጠት ችሎታ እንዲኖረን እርዳን። ከዚህ ሁሉ ጋር ዋና ጥበብ ማለት በቅዱስ ቃልህ አንተን ማወቅ ስለሆነ ወደ ፍጹም ዕውቀት ሁሉ የሚመራ የቅዱስ-መንፈስህ ኃይለ ረድኤት አይለየን፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

## ፵፮/46፡ <u>የምልጃ ጥያቄ፡</u>

<u>_ወወሀበነ</u> መልእክተ ሣህሉ=በእኛም ላይ የማስታረቅን ቃል አኖረ። ንሕነሰ ንተነብል በአምሳለ ክርስቶስ=እኛስ በክርስቶስ አምሳል እንማልዳለን-2 ቆሮ 5፡19 )። አምላከ አበው ቀደምት፡ አምላከ ነቢያት ወሐዋርያት፡ አምላከ ጻድቃን ወሰማዕት፡ አንተ ተማላጅ የባሕርይ አምላክ ሆነህ ሳለ፡ ለሰዎች አርአያና ምስሌነትን ለመስጠት በተውዋሐድኸው ሥጋ ሰብእ እስከ መስቀል ሞት ድረስ "አባ ስረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ



www.ethiopianorthodox.org

ይገብሩ= የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ ! ይቅር በላቸው" በማለት በመስቀል ላይ ለቸነከሩህ ጠላቶችህ እንኳ ሳይቀር ምሕረትን ጠይቀህላቸውል። ከዚህ ጋር ደግሞ "ስለእግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸውን ጃንደረባ አድርገው የሚኖሩ አሉ" ተብሎ በመንግሥትህ ወንጌል እንደተነገረ፡ ከዓለማዊ ተድላ ደስታ ተለይተው፡ ዓለምን ንቀው፡ መንነው፡ ገዳም ገብተው፡ የፍየል ሌጦ ለብሰው፡ ዳዋ ጥሰው፡ ድንግይ ተንተርሰው፡ ጤዛ ልሰው፡ በጾምና በጸሎት ተወስነው፡ ያንተን ቅዱስ ፈቃድ ለመፈጸም፡ በተለይም የሰው ድምፅ በማይሰማበት በረሃ ቅዱስ ቃልህን በማንበብና በማጥናት ራሳቸውን ካዘጋጁ በኋላ፡ ዓለምን ዞረው ያስተማሩ ቅድሳን ጻድቃን፡ ሰምዕታት ባንተ ዘንድ ሕያዋን ስለሆኑ ወደ አንተ ይማልዱልን ዘንድ ፈቃድህ ስለሆነ ስምህ ይመገን። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! በታላቅ ኃይል፡ በተዘረጋች ክንድ ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣሃቸው ሕዝብህ ዐምፀው ባሳዘኑህም ጊዜ ልትደመስሳቸው ተቃርበህ ነበር። ነገር ግን አገልጋይህ ነቢይ ሙሴ በአንተና በሕዝብህ መክከል ቆሞ "ተዘክር አብርሃምሃ ፍቁረከ= ወደጅህን አብርህምን አስብ፡ ከርሱም ጋር ለይስሐቅና ያዕቆብን የገባህላቸውን ቃል ኪዳን አስበህ የሕዝብህን በደል ይቅር በል" ብሎ እንደማደላቸውና አንተም የበደልን ይቅርታ እንዳድረግህላቸው ቅድስ ቃልህ ይነግረናል ( ዘፀ 32፡ 11 -19 )።

_ሌሎችም ነቢያትና ካህናት እንደዚሁ በምድር ላይ አባር፡ ቸነፈር፡ የዝናም እጥረትና የብሽታ ወረርሽኝ ወይም የጠላት ወረራ አስጊ በሚሆንበት ዘመን ሁሉ አንተ በአባታዊ ርኅራኄ ሕዝብህን እንድታደግ ሲማልዱና ሲያማልዱ መኖራቸው ተጽፏል።-በዚህ ዓለም ሳሉ ሕያዋን ለሕያዋን መማለድና ማማለድም ከቻሉ፡ ስለአንተ መንግሥት የተጋዳሉ፡ በንፍር ውኃ የተቀቀሉ፡ በመጋዝ የተተረተሩ፡ በሰይፍ ስለት የተመተሩ ቅዱሳን፡ ጻድቃን፡ ሰማዕታትም ሁሉ በዐጸደ ነፍስ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ሕያዋን ሆነው በሕይወተ ሥጋ ላለነው ለእኛ እንዲማልዱልን ፈቃድህ ስለሆነ እናመስግንሃለን። _በተለይም ደግሞ ከሴቶች መሐል መርጠህ ውድ ልጅህ መድኃኔ ዓለም



ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋን፡ ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ በመዋሐድ ያከበራት ቡርክት" ቅድስት፡ ሰአሊተ ምሕረት ድንግል ማርያም በልጅዋ በወዳጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ምሕረትን በመለመን ለኃጥአንን በመማለድ ምሕረትና ይቅርታን ለማስገኘት ባለሟልንትን ስጥተሃታል። ስለዚህም አዘክሪ ድንግል ንግደቶ ዘምስሌኪ= ድንግል ሆይ ! ርጉም በሆን በሔርድስ ዘመን በስደት ከአገር ወደ አገር ስትሸሺ፡ ካንቺ ጋር አብሮ መሰደዱን አሳስቢ፡ ድንግል ሆይ ! ክዓይኖችሽ የፈስሰውንና በልጅሽ ፊት ላይ የወረደውን መሪር እንባ አሳስቢ፡ ስለጻድቃን ሳይሆን ስለ ኃጥአን አሳስቢ" ተብሎ-በተጻፈው መሠረት ይህን ምልጃ እንድትቀበልልን-እንማፀንሃለን።-ወይእዜኒ-ንሰብሖ-ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለመ ዓለም=አሁንም- ስለዚህ ሁሉ የጸጋ ስጦታው ብዛት አብን፡ ወልድልን፡መንፈስ ቅዱስንም እናመስግነው፡ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## ፵፯ /47፡ የማዕድ ጸሎትና ምስጋና

_"ከነዚያም ደቀ መዛሙርት ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፡ ኅብስቱን አንሥቶ ባረከው፡ ቆርሶም ሰጣቸው" ( ሉቃስ 24፡ 30) "እኔን አምላካችሁን በማመን ፀንታችሁ ትኖራላችሁ፡እኔም የምትበሉትን እህልና የምትጠጡትን ውኃ እባርካለሁ፡ የበሽታ ዘሮችንም ሁሉ ከመካከልችሁ አርቃለሁ /አስውግዳለሁ ( ዘፀአት 23፡-25_28 )። በልተህ ስትጠግብና ጠጥተህም ስትረካ፡ ይህችን ለምለም ምድር የሰጠህን እመላክህን እግዚአሽብሔርን አመስግን። ጥሩ ቤቶች ሠርተህ፡ የከብትህና የበጎችህ መንጋ ርቢ ሲበዛልህ፡ ወርቅና ብር እንዲሁም ሀብት ሁሉ ሲሞላልህ አይተህ ልብህ እንድይታብይና አምላክህን ኣግዚአብሔርን ማመስገን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ" (ዘዳግም 8፡ 10+ መዝ 61፡ 10 ) ተብሎ እንደተጻፈ ይህን በፊታችን የቀረበ ማዕድ ባርክልን። ይህንም ተመግብን ኀይልና ፅንዓትን አግኝተን በቅዱስ ውንጌልህ ትምህርት ሕዝብህን ለማገልገል ብርታትን ስጠን። ይህንም ምግብ በማዘጋጀት የደከሙትን ሁሉ ባርካቸው። ምግብ አጥተው የተቸገሩ ወገኖቻችን ሁሉ አስበህ በረድኤት-



www.ethiopianorthodox.org

ጉብኘልን:: ሀገራችንን ለዘለዓለሙ ባርከህ ምግብ የሞላባት የሀብት መገኛ እንድትሆን ጸጋህን አብዛላት:: በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ዝናመ ምሕረትና ጠለ በረከት እንዳይለያት አድርግ:: ከዚህም ሁሉ ጋር "ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም "ተብሎ ተጽፏልና "ሲሲተ ልብ ቃላቲሁ ለእግዝአብሔር= ከአንደበትህ የሚወጣ ሕያው ቃልህ አማናዊ የልብ ምግበ ነፍስ መሆኑን እንድናስተውል እርዳን::"ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተባረከ ይሆናል" (1 ጢሞ 4፡ 3 -5 ) ተብሎ በቅዱስ ቃልህ እንደተጻፈ ለእኛ ለልጆችህ ይህን ምግብ ባርከህ ፡ ቀድስህ ስጠን:: አብሮ መብላትም ራሱ የፍቅር ምልክት (አጋፔ) ስለሆነ በዚህ ማዕድ ዙሪያ የተገኘነውን ሁሉ ባርከህ የፍቅር አንድነትንና ቤተስብዊ ሕይወትን ስጠን:: በአሐዱ ወልድከ= ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ፡ ካንተና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ዕሪና ባለው ( በክብር በሚተካከል) በአንድ ውድ ልጅህ ስም፡ በረከትን አውርድልን፡ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም፡ አሜን ! ........................................

## ፵፰ /48. በባዕድ አገር ከችግር የምንጠበቅበት ጸሎት

_ለእግዚአብሔር ምድር በምልአ፡ ዓለምኒ ወከሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ= =ምድር በመላው የእግዚአብሔር ናት፡ ዓለምና በውስጧም የሚኖሩት ሁሉ የርሱ ናቸው" ( መዝ 23፡ 1) ተብሎ በቅዱስ ቃልህ እንደተጻፈ የአገሮች ሁሉ ወሰንና ዳር ድንበር ሁሉ ሰው ሠራሽ እንጂ ባንተ ፈቃድ የተወሰነ አይደለም:: ያንዱ አገር ኑዋሪ ሕዝብ ለሌላው ባዕድ ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት ባንተ አባትነት ያለማመን ጉዳይ እንጂ ባንተ ቢያምን ኖሮ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ከአንድ ዘርዐ አዳም የተገኘ ስለሆነ በአርአያ ሥልሴ የተፈጠረ የሰው ዘር በሙሉ ውንድማምችና እኅትማማች በመሆን አብሮ መኖር በተቻለው ነበር:: ከዚህ የተነሣ ከአንደ አገር ወደሌላው መዘዋወር ሲጀመር ያልተጠበቀ ችግርና ፈተና የሚደቀንበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: ብዙዎች-ወገኖቻችን ሰብአዊ መብት በማይጠበቅባቸው በአንዳንድ አህጉር ብዙ ተፈትነዋል::አንዳንዱ ፈተና የሚመጣ ደግሞ በገዛ



ወገኖችን የሙስና አሠራር ጭምር መሆኑ ታውቋል:: የገዛ ወገናቸውን ለጉቦ ገንዘብ በመሸጥና በመለወጥ ያለ ሰብአዊ ርኅራኄ እንዲንገላቱና ለእስራት እንዲዳረጉ ከማድረግም አልፎ ካገር እንድባረሩ ማድረግ በብርቱ ያሳዝናል:: ስለዚህም ሰማያዊ አባት እግዚኣአብሔር አምልክ ሆይ ! ይህን ሁሉ ግፍና በደል ተመክልተህ አንተ ራስህ ፍረድ ! በፍትሕ አልባ አሠራርና ዓይነ ልቡናን በሚያሳውር ጉቦ ወገን በውገን ላይ እንደዚህ መጨከኑን ተመልከት:: በሌላ በኩል ደግሞ ያንተ ረድኤት ያልተለያቸው ብዙዎች ወገኖቻችን በአንዳንድ የስደት አገር ኑሮ ተመቻችቶላቸው፡ ሠርተው በሚያገኙት ሀብት በሀገር ቤት የሚኖሩ ቤተሰቦቻቸውን በመርዳት ብቻ ሳይወሰኑ በሀገሪቱም ለተጀመረው ልማት አስተዋፅኦ በማድረግና እንዳንዶቹም ብዙ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ ለሥራ አጥ ወገኖችን የሥራ መስክ ለመፍጠር እንዲችሉ ስለረዳሃቸው ስምህ ይመስገን::

_የአንዳንድ ባዕዳን አህጉር ሕዝቦችና መንግሥታት ደግሞ አገራችን ኢትዮጵያ የወጠነችው የልማት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ግቡን እንዳይመታ በገንዘብም ሆነ በቁሳቊስ እርዳታ እንዳይለግሡ የሚሸርቡትንም ሴራና ሰውሠራሽ ግድብ ሁሉ እንዲደርመስ አድርገው:: ሕዝብችን ለዚህ ሁሉ ስደት የተዳረገው በጊዜያዊ የኑሮ ችግር እንጂ ኢትዮጵያን የመሰለች ለምለም አገር በሌሎች አገሮች የምትለወጥ ሆና አልነበረም::

_አሁንም አገሪቱ ክለማችና ክበለጽገች ለሕዝባችን ስደት ምኑ ነው ? ስለዚህም ሰማያዊ አባት እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! አብዛኛው ሕዝባችን ለልማት ሥራ ታታሪና በቀላሉ ሠርቶ መበልጸግ የሚችል ስለሆነ ከስደት ኑሮ ይልቅ አገሩን በማበልጸግ ተግባር ላይ ትኩረት ማድረግ እንዲችል ያንተ ረድኤት-ያስፈልገዋል::-ከሕዝብዋ-ስደት- መልስ- ቅድስት አገር ኢየሩሳሌምን ለማበልጸግ ፈቃድህ በሆነ ጊዜ" የዓለምን ሕዝብና መግሥታትን ሁሉ እንደገና አናውጣለሁ፡ የዓለም መንግሥታት ሀብት ሁሉ ወደ አንቺ ይመጣል፡ ወርቁም ሆነ ብሩ ሁሉ የእኔ ነው:: እንደገና ለዚህች አገር የማይናወጥ ሰላምንና ብልጽግናን



www.ethiopianorthodox.org

እሰጣለሁ" ስትል አገልጋዮችህ በሆኑት በነቢዩ እሳይያስና በነቢዩ ሐጌ አንደበት ያናገርኸው ተስፋ ትንቢት አሁን ደግሞ-ለእናት_አገራችን_ኢትዮጵያ-እንዲፈጸምላት-ፈቃድህ ይሁን።" ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርከ ርስተከ = አቤቱ ሕዝብህን አድን፡ ርስትህንም ባርክ ! ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ''''''''''''''''''''''''''

## ፵፱/49. ከማናቸውም ደዌና ሕመም የምንጠበቅበት ጸሎት

_ነሥአ ደዌነ ወፆረ ሕማመነ= ለእኛ የሚገባውን ደዌ እርሱ ተቀበለ፡ ሕመማችንንም ሁሉ እርሱ ተሸከመ፡ በርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን (ኢሳ 53፡ 4 -5 )። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚያ አልፎ ወደ ገሊላ ባሕር ደረሰ። ወደ ተራራም ውጥቶ ተቀመጠ። ብዙ ሕዝብም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ከዚያም ሁሉ ሕዝብ ጋር ብዝዎች አንክሶች፥ ማየትና መስማት የተስናቸው፥ እጅና እግራቸውም የሰለሉ፥ በሌላም ልዩ፡ ልይ ዓይነት ደዌ የሚሠቃዩ ነበሩ። ሁሉንም ፈወሳቸው፡ ሕዝቡም ይህን ሁሉ አይተው በመደነቅ እግዝአብሔርን አመሰገኑ ( ማቴ 15 )።

_"በእኔ የሚያምኑ ሁሉ እነዚህን ታምራት የማድረግ ሥልጣን ይኖራቸዋል። በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ። እጃችውን በበሽተኖች ላይ-ይጭናሉ።ሕመምትኖች-ሁሉ-ይፈወሳሉ"-ስትል የተናገርኸው የወንጌል ቃል የማይታበል ነው። ይህኑ ዓይነት ሕሙማንን የመፈወስ ሥልጣን ለሚያምኑብህ ስዎችም ጭምር የሰጠህ ሰማያዊ አባታችን እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! ምንም ዓይነት ይሁን፡" ደዌና ሕመም ሁሉ ባንተ ዘንድ ኢምንት ነው። ሳንተ የሚሳንህ ምንም ነገር የለምና ማንችውንም ሕመም በቅዱስ ቃልህ እንዲወገድ እርዳን። በእኔ የሚያምኑ እኔ የምሠራውን ሁሉ፡ ከዚያም በላይ መሥራት ይችላሉ" ስትል በገባህልን ቃል መሠረት ስለታመሙ አባቶችና እናቶች፡ ወንድሞችና እኅቶች ሁሉ የምናቀርበውን ጽሎት እንድትቀበልልን ፈቃድህ ይሁን። የበሽታ ዘሮች ሁሉ ከዚህ ቤት እንዲወጡና ርኵስን መናፍስትም-በኃያሉ-ስምህ እዲገሠፁ አድርግንልን።የአገልጋይህን /ዮችህን የ-------------------ን ሕይወት የሚያሠቃይ ደዌን ሁሉ_ አርቀህ ፍጹም ጤንነትን በመስጠት ድንቅ ሥራህን ግለጥ ! ቅዱስ ስምህንም አክብረው። ሳንተ የሚሳንህ ምንም ነገር ስለሌለ በዚህ /ች አገልጋይህ በ -------------------ሕይወት ላይ የመፈወስ ኃይል ያለውን እጅህን ዘርጋ ! ድንቅ ሥራህም ሲፈጸም በዓይናችን ለማየት አብቃን።- አቤቱ--የሥጋችንም፡ የነፍሳችንም አስገኝ የሆንህ አምላካችን ሆይ ! አንተ በውድ ፈቃድህ /በሥምረትህ ለሰማያዊ -መንግሥትህ የመረጥሃትን (የ-----------ን ሕይወት ክደዌ ሥጋ ወነፍስ እስራት እንድትፈ ታና እንድትፈወስ፡ ከአልጋ ተነሥታ በፍጹም ጤናማ ሕይወት በፊትህ መመላለስ እንድትችል አድርግልን። ለዘለዓለሙ፡አሜን!



## ፶/50፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ-የምትመራ ሕይወት

_ከመ እንግር ፈቃደከ መከርኩ አምላኪየ፡ ወሕግከኒ በማዕከለ ክርሥየ =ፈቃድህን_በመፈጸም እኖር ዘንድ መከሬ ወሰንሁ፡ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው -መዝ 39 ፡8። ጌታ አምላኬ ሆይ ! ባንተ ታምኛለሁና ለጠላት ከመሸነፍ አድነኝ፡ ሕይወቴንም አንተ ምራ። አንተን ተስፋ አድርገው በቅዱስ ፈቃድህ የሚመሩ ሁሉ ከቶ እንደማያፍሩ በቅዱስ ቃልህ ተመልክቻለሁ። አቤቱ አምላክ ሆይ ! ቅን መንገድህን አመልክተኝ፡ በቀናች መንገድ ምራኝ። አቤቱ ለዘለዓለም በቅዱስ ቃልህ ያፀናኸውን ምሕረትህንና ቸርነትህን አስብ። የልጅነት መተላለፌንና በደሌን ሁሉ ሳታስብ እንደ ቸርነትህ ማርኝ። "እመሰ ኃጢአተን ትትዐቀብ እግዚኦ፡ እግዚኦ መኑ ይቀውም ?' አንተ በደልን ሁሉ የምትቈጣጠር-ቢሆንማ ኖሮ በፊትህ መቆም የሚቻለው ማነበር ?" (መዝ 129፡1 -8 ) ። "ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ /አመስግኚ፡ ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፡ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፡ ሕይወትሽን ክጥፋት የሚያድን፡ በምሕረትና በቸርነቱ እንደ ጋሻ መከታ ሆኖ የሚጋርድሽ፡ ፍላጎትሽንም ከበረከቱ_የሚያጠግብ እርሱ-ነውና።-ጐልማሳነትሽንም-እንደ-ንሥር-ያድሳል። እግዚአብ ሔር ይቅር ባይ ነውና ለተበደሉም ሁሉ ፍርድን ይሰጣል። ሁልጊዜ-ለመቅሠፍ- አይቸኩልም፡ ለዘለዓለምም አይቈጣም። እንደ ኃጢአታችንም ብዛት መጠን ፍዳ አላመጣብንም። ሰማይ ክምድር ከፍ እንድሚል፡ እንዲሁም እግዚአብሔር በደላችንን

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ከእኛ አራቀ:: አባት ለልጁ እንደሚራራ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚፍሩትና በፈቃዱ ለሚመሩ ሁሉ ፍጹም ርኅሩኅ ነው:: እርሱ የተፈጥሮ ደካማነታችንን ሁሉ ያውቃልና:: ለሚፈሩትና ስሙን ለሚይከብሩም ሁሉ ቃል ኪዳኑን በማሰብ ትእዛዝቱን በሚጠብቁ ስዎች ላይ የእግዝአብሔር ምሕረት ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ነው:: የጽድቅ ሥራውም ሁሉ ለትውልደ ትውልድ፣ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ነው (መዝ 102፡1 -17):: አቤቱ እኔ ብቸኛና በብዙ ችግርም የተከበብሁ መሆኔን አስበህ፡ ገጸ ምሕረትህን ወደ እኔ መልስ:: በልቤ ውስጥ የሚጉላላ ችግርና ሐዘን ብዙ ነው::

_ስለዚህም ከሚያስጨንቀኝ መከራና ከፈተንም ሁሉ ጠብቀኝ፡ አገልጋዮችህን ሁሉ እንድሚከሥ እንደ እኵይ ፍልስጣ (ሰይጣን ሆነው በእኔ ላይ ደባና ተንኮል የሚያስቡትን ህሉ አስታግሠህ የዕውነትን መንገድ አስትምራቸው:: እኔም እራሴን ክነርሱ የባስሁ በደለኛ ስለሆንሁ እነርሱን እጥፋልኝ ብዬ በጸሎት እንድክሥ ያንተ ፈቃድ አይደለም:: ያንተ ፈቃድ የሚጠሉንን ሁሉ እንድንወድ ነውና :: በርግጥ አገልጋይህ ሐዋርያ ጳውሎስ "እመሰ- ይትክሀለክሙ- ምስለ-ኵሉ-ሰብእ-ተአኀዉ የሚቻላሁስ ቢሆን ከሰው ሁሉ ጋር በወንድማማችነትና በእኅትማማችነት ኑሩ" (ሮሜ 12፡18) ብሎ እንደጻፈ፡ "የሚቻላችሁ ቢሆንስ" ከሚለው ቃል አንጻር ሲታይ፡ አንዳንድ ጊዜ ጠላትን ሁሉ ስመውደድ /ለማፍቀር ከተፈጥሮ አቅም በላይ የሚሆንበት ወቅት መኖሩን እንገነዘባለን:: ያንተ ፈቃድ ግን አሁንም እስከ መጨረሻው ጠላትን መውደድ ስለሆነ ፍጹም ትዕግሥትንና የልብን ፅናት ስጠን:: የፍቅር አምላክ ሆይ ! አንተ ራስህ ፍቅር ስለሆንህ በክፋትና በተንኮል ተመርዘው የሚመጡብንን ሁሉ በጠብ /በክርክር ብዛትና በክፋትም ሳይሆን በበጐ ሥነ ምግባርና በልብ የዋሀት፡ በይቅር ባይነት፡ በትሕትና ማሸነፍ እንድንችል እርዳን:: ነገር ግን ያንተ ቅዱስ ቃል ለሌሎች እንዳይዳረስ፡ ብዙዎች በስምህ ማመን እንዳይችሉ የሥራ እንቅፋት የሚፈጥሩ ስዎችን ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት እንደሚገባ በሐዋርያትህ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ አማካይነት



በቅሥፈት የተፈጸመውን የሞት ቅጣት ክቅዱስ ቃልህ ተመልክተናል:: አሁንም እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! እንደነዚህ ያሉትን አዕራራ ወንጌል በሚመልክት "መጥውዎ ለሰይጣን ከመ ይሥርዎ ሥጋሁ፡ ወትድኃን መንፈሱ በዕለተ እግዚእነ= _እንደዚህ--ያለውን-ሰው-በሥጋው-እንዲቀጣ-ለሰይጣን አሳልፋ ችሁ ስጡት፡ ነፍሱ ግን በጌታ ምጽአት ቀን ከዳግም ሞት እንድትድን ይሁን" ሲል አገልጋይህ ሐዋርያ ጳውሎስ የጻፈው ቃል በዘምናችንም ለውንጌል ሥራ እንቅፋት በሚፈጥሩ ሁሉ ላይ ቢድርስባቸው ኃጢአታቸው በነርስ ራስ ላይ መውረዱ የማይቀር ነው:: እዚህ ደረጃ ከመድረስቸው በፊት ግን አጽራረ ወንጌል ንስሓ እንዲገቡና ክክፉ ሥራቸው እንዲታቀቡ አድርግ፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን 1 """""""""""""""""""""""""""""""""""""""""

## ፶፩ /51. ጻድቅ ብእሲ ይምሕር ነፍሰ እንስሳሁ

<u>ጻድቅ /ደግ ሰው ለእንስሳው ነፍስ ይራራል፡</u> (ምሳሌ 12፡ 10 )። ኃጥእ ሰው ግን የጭካኔን ሥራ እንደ ርኅራኄ አድርጎ ይቈጥራል። ጌታ አምልክችን ሆይ! በሀገራችን ኢትዮጵያና በመላው ክፍለ ዓለማችን አፍርቃ በቤት ለማዳ እንስሳት ላይ ያለምንም ርኅራኄ የሚፈጸም ጭካኔ የመላበት አሠራር ገድብ ካጣ በሺህ የሚቈጠሩ ዘመናት አልፈዋል:: ከሦስት እስከ ዐራትናእስከ አምስት ኵንታል የሚመዝን ክብደት ያለውን ጭነት፡ እንድሁም ከሦስት እስከ ዐራት ሰው ጭነው በአንድ ትንሽ-ፈረስ-በማስጐተት-በጅራፍ-እየጠበጠቡ-መንዳት-ተለምዷል:: ከዚህም ሁሉ ጋር በቀን ጭብጥ ሙሉ ሣርና ጥርኝ ውኃ እንኳ ሳያገኙ የሚኖሩ እንስሳት ቍጥራቸው እልፍ አእላፍ ነው:: እንደዚህ ያለውም የጭካኔ አሠራር አገርንና ትውልድን ሁሉ የሚያስረግም ስለሆነ ገደብ እንዲኖረው ማሰብ ይገባል:: ሰብአዊ ቋንቋ ቢያውቁማ ኖሮ ዕብራተኛው የሰው ዘር በአረመኔያዊ ጭካኔ የሚፈጽምባቸውን ስንቱን በደል ዘርዝረው በተነገሩት ነበር:: "እህል የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር" ስትል በዘዳግም የሕግ መጽሐፍ ምዕ 25፡-4. ያናገርህ የርኅራኄ አምላክ_ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ! የመላው ዓለም ሕዝቦችም



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ለነዚህ አሳዛኞች እንስሳት ሕይወት ጥንቃቄ የሞላበት ክብካቤ ለማድረግ በርኅራኄ መንፈስ ማየት የሚችሉበትን ዓይነ_ልቡናቸውን እንድከፍትላቸውና መንግሥታትም ሁሉ ለዚህ አሳሳቢ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የመስጠት ልምድ እንዲኖራ ቸው ታደርግ ዘንድ እንማፀንሃለን።

_ምንጮችን ወደ ቆላ አገሮች ትልካለህ፡ ውኃዎች በተራራዎች መካከል ያልፋሉ፡ የተጠሙ የምድረ በዳ አህዮችንና ሌሎችንም እንስሳት ሁሉ ያረካሉ፡ በደንጊያ /ዐለት ሽለቆ ውስጥ ተሠውረው -የሚኖሩ ሽኮኮዎች እንኳ_የሚጠቱት_ውኃ እንዲደርስላቸው-ታደርጋለህ። በዚያም የሰማይ ውፎች ህሉ ተጠልለው ይኖራሉ። በየዋሻው መሐል ሲጮሁም ድምፃቸውን ሰምተህ በተራራዎች ሥር ውኃ ማለፍ እንዲችልና ምድርን ፍሬ የመላባት አደረገህ። ለእንስስትም ለምለም ሣር እንዲበቅልላቸው ታደርጋለህ" ተብሎ በቅዱስ ቃልህ (መዝ 103፡ 10 -14) እንደተጻፈ አንተ ይህን ያህል የምትጠነቀቅላቸውን እንስሳት፡ አራዊትና አዕዋፈ ሰማይ እኛም ለራሳችን ጥቅም -ልንጠነቀቅላ ቸው ሲገባ ይህን ያህል መጨከናችን እንደሚያሳዝንህ ይሰማናል። ስለዚህም ርኅሩኅ አምላካችን ሆይ! በቍርባን እንኳ ሊሰረይ የማይችል ይህን ሁሉ ከባድ በደል በችርነትህ ይቅር በለን፡ የቤት እንስሳትን አገልግሎት መጠቀም የሚሹ ስዎች ሁሉ ስብአዊ ርኅራኄ እንዲኖራቸውና-በእንስሳት-ሕይወት በአግባቡ_የመጠቀምን_ጥበብ እንድታስተምራቸው ፈቃድህ ይሁን ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## ፶፪ /52. የስደት አገርን ፈተና በማስብ የቀረበ ጸሎት

_ከዓለማት መንግሥታት ሁሉ በላይ ነግሠህ የምትኖር ያባቶቻችን አምላክ ሆይ ! ልመናችንን ሰምተህ በደላችንን ይቅር በለን።ከፍቅርህ የተራብችና የተጠማች ነፍሳችን ስለሠራችው ክፉ በደል በማዘንና በመፀፀት በትካዜ ወደ አንተ ትጮሃለች። በእርግጥ በፊትህ በደልን ሁሉ ሠርተናል። እኛ በሠራነው በደል ጠፊዎችና ኃላፊዎች ነን፡ አንተ ግን ዘላዓለማዊ ኗሪ ነህ። በሁሉ ነግሠህ የምትኖር ፈጣሪያችን ሆይ ! በፊትህ በደልን



የሠሩ፡ ለቅዱስ ቃልህም ታዛገሮች ሆነው ያልተገኙ አባቶቻችን አንተን ለቍጣና ለመቅሠፍት በማነሣሣታቸው ምክንያት በወራሪ-ጠላት እጅ ተምርከው ውርደትና ሐፍርት ደርሶባቸዋል (መጽሀፈ ባሮክ 3፥ 1-12) ። ከዚያም ህሉ ውርድትና ሐፍረት በኋላ ተፀፅተው ወደ አንተ በንስሓ የተመለሱ የሕዝብህን ጸሎት ሰማ። ጩኸታቸውንም ሁሉ አድምጥ። ከፉ ነገርን ሁሉ የተከተልን፡ የአባቶቻችንንም ኃጢአት ሁሉ ያላሰብን እኛ ሁላችን አካሂዳችን ሁሉ በፊትህ የቀና እንዳልነበረ እናውቃለን።

አንተ ግን መሐሪና በደልንም ሁሉ ይቅር ብይ ስለሆንህ በቸርነትህ እንድትራራልን ያንተን ቸርነት ከምንለምን በቀር ለሠራነው በደል ሁሉ የምናቀርበው መከላከያ ምክንያት የለንም። ስለዚህም በጠላት እጅ ተመርከው የተወሰዱ ሕዝብህ በእስራትና በከባድ ሥራ ብዛት ሕይወታቸው ምን ያህል እንደተፈተነ ታውቃለህ። ሰብአዊ ርኅራኄ በጎደለው ጭካኔ የተሠቃዩ ወገኖችን ሁሉ አስብ። በቅዱስ ቃልህ እንደተጻፈ-ሕግህንና ሥርዓትህን ጠብቀን በትእዛዛትህ ተመርተን ቢሆን ኖሮ ለዘለዓለም በተድላና በደስታ ለመኖር በበቃን ነበር። ኃይልና ብርታት፡ ዕውቀትና ጥበብ፡ ለረጅም ዘመን በሕይወት የመኖር-ጸጋ-የሚገኝ ካንተ ዘንድ መሆኑን ማስተዋል እንድንችል እርዳን ። ለአንተ የሚሳንህ ምንም ነገር የለምና በቸርንትህ ማረን።አምባ-መጠጊያችን፡-ጋሻ መከታችን፡-ኃይላችንና መመኪ ያችን ስለሆንህ በይቅር ባይነትህ ብቻ ታስበን ዘንድ እንማፀን ሃለን። እንዲህም እያልን በመዘመር-ቅዱስ-ስምህን እናከብራለን፡-

"ኃይል-የእግዚአብሔር-ነው፡-
ማዳን-የእግዚአብሔር፡-ጥበብ የእግዚ አሔር (2 ጊዜ)
አንመካም በጉልበታችን፡
እግዚአብሔር ነው የእኛ ኃይላችን" ( 2 ጊዜ)

ምስጋና ይሁን ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስም ዘለዓለም ሥላሴ፡ አንድ አምላክ፡ አሜን !
''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''



www.ethiopianorthodox.org

**ክፍል-ሁለት**፡ከጸሎተ ቅዳሴያት መደምደሚ/ ሐዳፌ ነፍስ

## ፶፫ /53. ከቅዱስ ጎርጎሬዎስ ቀዳማዊ መጽሐፈ ቅዳሴ

_ዳግመኛ ሁሉን የሚይዝ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔር አብን እንማልዳለን:: ከሊቃነ መላእክት ገናንነት ይልቅ የሰውን ትሕትና የመረጥህ፡ ከአብርሃም ነገድ ሕዝብ መዛግብት ( ሀብት ሁልሉ ) ይልቅ የአዳምን ድህነት የወደድህ የፍቅር አምላክ ሆይ ! የስውን አፍአዊ /ውጪያዊ መልክና ደም ግባትን ሳይሆን ውስጣዊ የልብ ቅንንነትን የምትወድ አቤቱ ለእኛ ለልጆችህ ያለህ መውደድ /ፍቅር እንዴት ድንቅ ነው:: በቸርነትህ ሁሉን ማንጻት የሚቻልህ ጌታ ሆይ ! ሥጋችንንም ነፍሳችንንም ከኃጢአት ሁሉ አንጻ፡ በደልን ይቅር ባይና መሐሪ አምላክ ሆይ ! ውኃን ከወይን ጋር ቀላቅለህ፡ ነፋስንም ከእሳት ጋር ውኃንም ክመሬት ጋር እንዳዋሐድህ፡ እንዲሁም የእኛን ድካም ከመለኮትህ ፅንዕ /ብርታት ጋር አዋሕደህ፡ የእኛንም መከራ ከመከራ መስቀልህ ጋር አንድ አድርገህ በመመልከት ልትታደገን ፈቃድህ ስለሆነ ስምህ ይመስገን::

_ብልጽግና ወደሞላበት ቤተ መቅደስህ የመጣን እኛን አገልጋዮችህን ሁሉ ባርከን:: ወንዶችንም ሴቶችንም፡ ሽማግሎችና ሕፃነቱንም ሁሉ በምሕረት ዓይንህ ተመልከት:: በብርሃንህ መጋረጃ ሸፍነን:: በክንፈ-ረድኤትህ ሠውረህ ከክፍ ሥራም ሁሉ እንድንርቅ እርዳን:: በየጊዜውና በየሰዓቱ ጸሎትን ከሚያሳርጉ ትጉሃን መላእክት ማኅበር ጨምረን:: የበላነው ሥጋህ፡ የጠጣነው ደምህ ለቅሥፈት ሳይሆን ለኃጢአት ማስተስረያ እንዲሆንልን በቅዱስ መንፈስህ-አንጻን::-ለዘለዓለም-ሕይወቷና-ለማስተዋልም እንዲሆንልን አድርግ" ብለን በጸሎት እንማፀንሃለን:: ምስጋና ይሁን ለአብ፡ ለወልድ፡ ለመንፈስ ቅዱስም ፡ዘለዓለም ሥላሴ አንድ አምላክ፡ አሜን !



## ፶፬ /54. የቅ/ ጎርጎሬዎስ ካልእ ቅዳሴ ሐዳፌ ነፍስ

_በሥልጣንህ ሁሉን የያዝህ ጌታ አምላካችን ሆይ ! በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ታከብረን ዘንድ ፈቃድህ ይሁን:: ሁሉን ለበረከት አድርግልን:: በየጊዜውና- በየሰዓቱ- ስላደረግህልን ድንቅ ነገር ሁሉ ልቅዱስ ስምህ ምስጋና ከመቅረብ እንዳንገታ የልብን ትጋት ስጠን:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ! በጸጋህ ባርክርን ቀድሰንም:: ያለ ኃጢአትና ያለ ነውር አንተን ደስ በሚያሰኝህ ሕይወት በፊትህ ያለ ነውር መመላለስ እንድንችል ከሰይጣን ፈተና ሁሉ ጠብቀን:: ከክብርት ማዕድህ የተቀብልነው ቅዱስ ሥጋህና ክቡር ደምህ ለምዳን ይሁንልን:: ወደ ሕይወት መንገድም ይመራን ዘንድ ቅዱስ መንፈስ ህን ላክልን:: ዘለዓለማዊ ሕያው የሆነ ውድ ልጅህ ለዓለም ቤዛ ሆኖ ቅዱስ ሥጋውንና ክብር ደሙን አዘጋጅቶልናል::ሥጋውን በልተን፡ ደሙንም ጠጥተን ከርሱ ጋር ሕያዋን ሆነን እንኖር ዘንድ እስከሞት ስለወደደን ቅዱስ ስሙ ይመስገን::

_በጸጋው-ስቦ:-በምሕረቱም-አቅርቦ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና የርሱ ማደሪያዎችም እንሆን ዘንድ ወዶአልና ስሙ ይክበር፡ ይመስገን:: ጸሎትን ከሚያሳርጉ አገልጋዮቹ እጅ የተቀበልነው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ለኃጢአት ማስተስረያና ለዘለዓለም ሕይወት፡ እንዲሁም ከሞት ለመነሣት፡ ለደህንነት፡ ለፈውስና ለማስትዋልም ጥበብን የሚገልጥ እንዲሆንልን ሥምረትህና ፈቃድህም ስለሆነልን ስምህ ይመስገን:: አንተ እንደወደድኸን እኛም ሰውን ሁሉ የማፍቀርና የመውደድ፡ ከሁሉም ጋር አብረን በሰላምና በፍቅር አንድነት የመኖር ጸጋ እንዲበዛልን ፈቃድህ ይሁንልን፡ አሜን !

## ፶፭ /55. የቅዱስ ባስልዮስ ቅዳሴ ሐዳፌ ነፍስ

_መዓትህ የራቀ፡ ምሕረትህ የበዛ የክብር ባለቤት ልዑለ ባሕርይ የሆንህ አምላክ ሆይ! ለቅዱስ ስምህ መክበሪያና ለምስጋናህ ማደሪያ ይሆን ዘንድ በመረጥኸው በዚሕ ቅዱስ ቦታ በፊትህ እንቆም ዘንድ በጸጋህ ስላከበርኸን እጃችንን ወደ ላይ



www.ethiopianorthodox.org

አንሥተን ለመጸለይ የተዘጋጀን እንድንሆን እርዳን። ቅዱስ ስምህ ገናና፡ ጌትነትህ ለዘለዓለም የፀና፡ ምስጋናህ በሰማይም በምድርም የሞላ ነው። በፍጹም ልባቸው ለሚያምኑብህ ሁሉ ቃል ኪዳንን የምትጠብቅ ታማኝ አምላክ ነህ። ተቀዳሚ፡ ተከታይ በሌለው በአንድ ውድ ልጅህ በጌታችን አምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የመዳንን ጸጋ አብዝተልናል። የቊጥራቸው ብዛት እልፍ አእላፋትና ትእልፊት አእላፋት የሆነ ትጉሃን መላእክት፡ ቅዱሳን ስራፌልና ኪርቤል ከሌሎች ሰማያውያን ኃይላት ጋር ሆነው ሥፍር፡ ቅጥር የሌለው ጉብኤ በፊቱ የሚቆምለት ውድ ልጁህ እኛን ለማዳን ወዶ /ሠምሮ እስከ ቀራንዮ መስቀል ድረስ እንዲጓዝ ቅዱስ ፈቃድህ የሆነ ቸር አምላካችን ሆይ ! ስላደረግህልን ድንቅ ነገር ሁሉ ለገናናው ቅዱስ ስምህ የምንቀርበውን ምስጋና ተቀበልልን። ኃጢአታችንና በደላችንን ሁሉ በልጅህ ደም አንጻ። ክፉ ኀሊናን ሁሉ ከእኛ አርቅልን፥ ነፍስችንንና ልቡናችንንም አንጻ። በንጹሕ ልብና በብርሀት ነፍስ ደስ እንድናሰኝህ በቅዱስ ቃልህ ሕይወታችንን ለውጠህ ያንተ ማድሪያ ቤተ መቅደስ አድርግልን፥ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፥ አሜን ፣ ''''''''''''''''

**<u>ክፍል ሦስት፡</u>** በዚህ መጽሐፍ ለሚገኙት የጸሎት ዓይነቶች አቀራረብ ሁሉ-መሠረት-(ሞዴል) የሆነ መጽሐፋዊ ቃል ከዚህ የሚከተለው ነው ፡ - - -

## ፶፮ /56. <u>የዘመነ ሐዋርያት ጸሎተ ማኅበር</u> -የሐዋ ሥ 4 24 -32

"ጌታ ሆይ ! አንተ ሰማይንና ምድርን፡ ባሕሩንና በርሱም ውስጥ የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ፥ የባሕርይ ሕይወትህ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአገልጋይህ በአባታችን ዳዊት አንደበት "አሕዛብ ለምን ተሰብሰቡ? ሕዝቡስ ብላሽ የሆን ከንቱ "ነገርን ስለምን ተናገሩ? የምድር ነገሥትት ተነሡ፥ አለቆችም በጌታና በመሲሑ /ክርስትስ ላይ አብረው ለመዶለት ተሰበሰቡ" ብለህ ይህን መሲሐዊ ትንቢት አስቀድመህ የተናገርህ አምላክ ነህ። መሲሕ አድርገህ በላክኸው በቅዱሱ ልጅህ በኢየሱስ



ክርስቶስ ላይ ሄሮድስና ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ተባብረው በቅዱስ ፈቃድህና አሳብህ ቀድሞ የወስንኸውን ሊፈጽሙ በዚህች ከተማ በእውነት ተሰብስበዋልና። አሁንም ጌታ ሆይ ! ወደ ዛቻቸው ተመልከት። ለመፈወስም እጅህን ዘርጋ። በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ድንቅ ምልክት /ታምር ሲደረግ ሕዝቡ ማየት እንዲችሉና አገልጋዮችህም የሆኑት ደቀ መዛሙርት ሁሉ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን መናገር ይችሉ ዘንድ ኃይልን ስጣቸው" አሜን ፣

**<u>አጭር-ትርጓሜ፡</u>** እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደገለጥነው-ለቀረበው-ኃይለ-ጸሎት ሁሉ በምሳሌነት (ሞዴል) ሆኖ የተቀመረበት ስልት ይህኑ የሐዋርያትን የማኅበር ጸሎት መሠረት በማድረግ ነው። በዘመነ ሐዋርያት የነበሩ አማኞች ከሐዋርያት ጋር አብረው ያቀረቡት ይህ የማኅበር ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ መሆኑን የሚገልጥ ልዩ ተአምር /ድንቅ ነገር ተከትሎታል። ይኸውም በጸሎቱ ፍጻሜ ላይ ተሰብስበው የነበርበት ቤት ተናወጠ፡ በሁሉም መንፈቅዱስ ሞላባቸው።የእግዚአBሔርን ቃል በግልጥ ለመነገርም ድፍረትን አገኙ" ይላል። አቤቱ ጌታ አምላካችን ሆይ ያ ኃይል ለእኛም እንዲስጠን ፈቃድህ ይሁን ! ለዘለዓለሙ ፡አሜን።

**<u>የጸሎቱ አቀራረብ ስልት፡</u>** ይህ ጸሎት ልመናን ብቻ የሚገልጥ አይደለም። ፍጹም ትምህርታዊ የሆነ የአንድምታ ትርጉም ያለው ነው። ለምሳሌ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ስም ሲያነሡ ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው ያለውንም ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ገልጠው ስሙን በማክበር አመስግነዋል። ለምሳሌ፡ በሁለተኛ መዝሙረ ዳዊት ያለውንም መሲሐዊ የትንቢት ቃል ሲጠቅሱ ትምህርታዊ የሆነ ልዩ ትርጓሜ ሰጥተውታል። ይኸውም ያን ትንቢት የተናገረው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በደፈናው <u>"የምድር ነገሥታት ተሰበሰቡ"</u> አለ እንጂ የሔሮድስንና የጲላጦስን ስም አላነሣም ነበር። የዚህ ጸሎት ተነጋሪዎች ግን በትርጒም መነጽርነት አጕልተው ነግሥታቱን በስም ጠርተው፡ ድርጊታቸውን ገልጠዋል። ይህ

www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ ጸሎት ሲዘጋጅ ትምህርትዊ ትርጉም እንዲኖረው ያስፈለገበት ምክንያት በዚሁ መሻነት ነው። _ከዚህም ሁሉ በላይ ግን ቀደም ሲል ጌታችን ራሱ ያስተማረው "አባታችን ሆይ!" -የሚለው ጸሎት አምስት ዋና፡ ዋና አርእስት አሉት። እነርስም፡ -1. ሃይማኖት፥ 2. ተስፋ፥.3. ፍቅር፡ 4. ትሕትና፥ 5./ ጸሎት ተብለው ይጠራሉ። ይኸውም-1-የማያዩትን አምላክ እግዚአብሔርን አባታችን ሆይ ብሎ መጥራት ራሱ ሃይማኖት ነው። 2. መንግሥትህ ትምጣ ብሎ መጸለይም ተስፋ ነው። 3. እኛ ብሎ አንዱ ለሌላው /ለሌሎች መጸለይ ፍቅር ነው። 4. የበደሉንን ይቅር እንደምንል በማለት ተበድሎ ማሩኝታን፡ በድሎ ይቅርታን ማወቅ ታላቅ ትሕትና ነው። 5. ቃሉ በሙሉ ጸሎት ነው። ሌላውም_የዚሁ_ተከታይ፡ ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው የጌታችን ክፍለ ወንጌል ምዕራፍ 1፡ 46 -55- ተጽፎ የሚገኝ የቡርክት ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት ነው።"ተዐብዮ-ነፍስየ-ለእግዚአብሔር-ነፍሴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች፡ ከፍ፡ ከፍ ታደርገዋለች" በማለት ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብር በመስጠት ትጀምርና እርስዋንም እንዴት እንደመረጣትና እንዳከበራት በመመስከር በታልቅ ትሕትና ታመስግነዋለች። ድንቅ ሥራውንና ኃያልነቱንም ክተናገረች በኋላ ለቀድሞ አባቶች የሰጠውን የተስፋ ቃል እንዴት እንደ ፈጸመው በመግለጥ-ትደመድማለች።- ወስብሐት ለእግዚአብሔር !

## ክፍል-ሦስት፡ሊጦን (Litany=የምስጋና ጸሎት

_ሊጦን /ምልጣን በሚል ርእስ ከሰኞ እስከ እሑድ ባሉት ሰባቱ ዕለታት የሚቀርበውን ተማሕፅኖ መሠረት በማድረግ የሚቀርብ የምስጋና ጸሎት ነው። ,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

### ፩ /1. ከሰኞ ሊጦን ጋር የቀረበ የምስጋና ጸሎት፥

"በስመ-አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ=አሜን ! ወይቤ እግዝዚአብሔር ለይኩን ጠፈር ማዕከለ ማይ= እግዚአ ብሔር አምላክ በዚህ ዕለተ ሰኑይ (ሰኞ) ጠፈርን ፈጥሮ ሰማይ ብሎ ጠራው ( ዘፍ 1፡ 7 -8 ) ። ሁሉን--የሚይዝ- የጌታችንና -የመድኃኒታችን -የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔርን ዳግመኛ-እናመሰግናለን። ሌሊቱን ሁሉ ጠብቆ ከጨለማ ወደ ብርሃን አሸጋግሮናልና። ከጥፋት ወደ ሕይወት፡" ካለማወቅ ወደ ፍጹም እውቀትና-ማስተዋል ያደረሰን-እርሱ ነው። በሕይወት እንድንኖር በመላእክት ኃይለ ረድኤት ሕዝቡን ይጠብቅ ዘንድ ወድዶ፡ ሠምሮ ለበረከት ሥራ ሁሉ የማይዳሰስ ሥልጣን ያለው ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ብቻ ነው። አሁንም ሁሉን የምትይዝ ጌታ አምላካችን ሆይ ! ቀኑን ሁሉ በፍጹም ሰላምና በተረጋጋ ሕይወት እንድንውል አድርገህ የዕለት ሥራችንን ባርክልን። ሌሊቱን ሁሉ ጠብቀህ ወደዚህ አዲስ ዕለት አሸጋግረኸናልና። ሁሉን ማድረግ የሚቻልህ አምላካችን ሆይ ! በወዳጅህ ጻድቅ ኢዮብ መጽሐፍ (ምዕ. 33፡ 23 -26) እንደተነገረ ከጥፋት የሚታደግና የጽድቅን መንገድ እንድንከተል ቀናውን መንገድ እየመራ በአንተና በእኛ መካከል እንደ አስታራቂ ሆኖ-የሚማልድልንን ርኅሩኀ መልአክህን ስደድልን። እንደ በደላችን ብዛት ሳይሆን እንደ ቸርነትህ ማረን፡ ይቅርም በለን። ከእኛ ወገን ማንንም ከባለሟልነትህ አታውጣ። ምስጉን የሆነ ቅዱስ ስምህ በእኛ ላይ ስለተጠራ ከበደል ሁሉ ነጻ ለመሆን እንድንበቃ በቅዱስ ቃልህ የተነገረውን የተስፋ ቃል ፈጽምልን፡" ለዘለዓለሙ አትተወን።- በአንተና በውድ ልጅህም ፊት ባለሟልነትን እንድናገኝ በቅዱስ መንፈስህ እርዳን። ከውድ-ልጅህና ከባሕርይ ሕይወትህ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ክብር፡ ምስጋና ላንተ ይገባል። ዛሬም ዘወትርም፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን !

### ፪ /2.. የማክሰኞ ሊጦን /ምልጣን

_በሦስተኛው ቀን ማክሰኞ እግዚአብሔር አምላክ አዝርዕትን፡ አትክልትንና ዕፀዋትን /ዛፎችን ፈጠረ ( (ዘፍ 1፡ 11 -13 ): በዚህች ዕለት ምድርን በአዝርዕትና በአትክልት በሥነ ጽጌያትና በልዩ፡ልዩ ዕፀዋትም እንዳስጌጥህ የእኛንም ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የለመለመ እንድታደርገው ፈቃድህ ይሁን ! ስምህ-ለዘለዓለም-ሕያው-ነው፡የማታንቀላፋ--ትጉህ፡ በባሕርይህ ድክመት የሌለብህ፡ ብርቱ፡ ኃያል ፈጣሪ አምላክ ነህ። በሁሉ ነገር ላይ


www.ethiopianorthodox.org

ሥልጣን ያለህና፡ የማትሰወጥ ጌታ ነህ። በሰማይም በምድርም የሚገኙ ፍጥርታተ ሁሉ ለስምህ ምስጋና ያቀርቡ ዘንድ በአንቃዕድዎ ወደ አንተ ይመለከታሉ። ዓለምን የያዝህ አንተ አምላካችን ነህ። አንተ የደስታና የሐሴት ሁሉ መገኛ አምላክ ነህ ። የምስጋናህ ኃይል ወደሚደርበት ወደ ቤተ መቅደስህ መጥተው የሚማፀኑ ሴቶችም፡ ወንዶችም ውገኖቸሀ ሁሉ በፊትህ የሚያቅቀርቡትን ጸሎት-እንደ በጐ መዓዛ አድርገህ ተቀበለህ በደላቸውን ይቅር በል ። የእኔንም -የአገልጋይህን-(የ--------)-ልመና-ለመቀበል ፈቃድህ ይሁን፡ የእኔን የአገልጋይ ህን በደል ሁሉ ይቅር በል። አቤቱ አምላካችን ሆይ ! በሰብአዊ ዓይን የማትታይ፡ አንተ ግን ሁሉን የምታይ የቅርብ አምላክ ነህ ( ኤር. 23፡ 23--24) ። ሕዝብህ የሠሩትን በደል ሳታስብ ኃጢአታቸውን ተቀበል። መሐሪ አምላክ ሆይ ! ገጸ ምሕረትህን ወደ እኛ መልስ። በርኅራኄም ዓይን ተመልከተን። በዚህ ዓለምና፡ በመጪውም ዓለም በፊትህ እንሰግድልህ ዘንድ የበቃን አድርገን። ክቡር ስምህንም ከፍ፡ ከፍ በማድረግ እንድናመሰግንህ የመንፈስን ብርታት ስጠን። በአንድ ልጅህ ያለ ክብር፡ዕንዕ ላንተ ይገባል። ከርሱ ጋራ ከባሕርይ ሕይወትህ ከመንፈስ_ቅዱስ-ጋር፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## ፫ /3. ከረቡዕ ሊጦን ጋር የሚቀርብ የምስጋና ጸሎት

_አቤቱ መሐሪ አምላክ ሆይ ! በምሕረትህ ጐብኘን። ገጸ ምሕረትህን በእኛ ላይ አብራ። በራሳችን ስሕተት ከሚመጣብን-ጥፋት ሁሉ ጠብቀን። ደስ የሚያሰኘን ቸርነትህ-ይገለጥ። በውድ ልጅህ የሕይወት መሥዋዕትነት በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያወረድኸውን ዕርቀ ሰላም አይተናል። በደል የሠራውን ኃጥእ ወአባሲ ሁሉ ወደ አንተ መመለስ ይቻልሃልና። ስፍር ቊጥር "የሌለውን-ይቅርታህን-አታርቅብን። ድክመታችንንና የስንፍናችንን ብዛት አታስብብን። አቤቱ አምላካችን ሆይ ! በደላችንን- ሁሉ ታግሠህ ኃጢአታችንን ሁሉ-ደምስሰህ በምሕረት-ስላቀረብከንና ስላደረግህልን ድንቅ ነገር ሁሉ ስምህ ይመስገን። ቸር መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ሆይ ! የአብ የባሕርይ ልጁ አንተ ነህ።



የሰውን ልጅ በጸጋህ ከፍ፡ ከፍ ማድረግን የወደድህ እኛንም አገልጋዮችህን ከውድቀት በማንሣት ከኑሮ ችግርና ከሥራ አጥነት ፈተና ጠብቀን። ለመረጥሃቸው አገልጋዮችህ በጐ ነገርን ማድረግ የማይሳንህ ቸር ሰማያዊ አባት ነህና። የፍቅርህን ምልአት፡ ስፋት ለመግለጥ ወደህ በሥጋ ሰብእ ተገለጥህ። አሁንም እንደ ይቅርታህ ብዛት ይቅር በለን። እንደ ቸርነትህም ብዛት ለዘለዓልም በደላችንን ደምስስልን። በዚህችም ዕለተ ረቡዕ ፀሐይን፡ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጥረህ ጠፈረ ሰማይን በብርሃን ያስጌጥህ የብርሃን አምላክ ሆይ ! ስምህ ይመስገን። የእኛን አእምሮ በእውቀት ብርሃን የተሞላ አድርግልን። ቅዱስ ቃልህን ማስተዋል እንድንችል ወደ እውቀት ሁሉ የሚመራ ቅዱስ መንፈስህን አሳድርብን። በቅዱስ መጽሐፍ የምናነበውን ቃል በብሩህ ልብ ማስተዋል እንድንችል እርዳን። ልጆቻችንም ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት በምልአት-እንዲኖራቸውና-አንተን የማክበር ጥበብ እንዲበዛላቸው አድርግ። አንተ ያስተማርኸው ሰው ብፁዕ ነው፡ እነሆ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ"-ተብሎ-እንደተጻፈ ያስተምራ ቸው ዘንድ ቅዱስ- መንፈስህን እንድትልክላቸው ፈቃድህ ይሁን። ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑበት ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው" ተብሎ ተጽፏልና ( ዮሐ 1፡ 12 -13 ) አሜን።

## ፬ /4. ከሐሙስ ሊጦን /ምልጣን ጋር የሚቀርብ ጸሎት

_አቤቱ መሐሪ አምላክ ሆይ ! ከዕለት እኪት፡ ከዘመነ መንሱት (ከክፉ ቀንና ከጥፋት ዘመን )። ከክፉ ሰዎች ተንኮልና ከሐኬት /ከስንፍና ብዛት ፡ ድንገት ከሚመጣ መከራ ሁሉ ጠብቀን ። ዓለምን ሁሉ የያዝህ አምላካችን ሆይ ! የተመሰቃቀለውን ሕይወት ሁሉ እንድታስተካክለው እንማፀንሃለን። አቤቱ አምላካችን ሆይ! ረድኤትና የደኅንነት ዋስትና የሚገኝ ካንተ ነውና ጌትነትህን የተማፀነ ዳዊትን ከጠላት ጦር ያዳንኸው፡ ሶስናን ከረበናት ተንኮልና ዓድማ፡ ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ፡ አናንያ፡ አዛርያና ሚሳኤልን ከባቢሎን የደመራ እሳት ያዳሃቸው



www.ethiopianorthodox.org

አንተ ነህ። አቤቱ እኛንም ከአሉባልተኛና ከስም አጥፊ ትውልድ ጠብቀን። ነፍሳችንን፡ ሥጋችንንም በቸርነትህ ጠብቅ። በውድ ልጅህ ደም የተዋጀች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ጠብቀህ በጸሎት-ኃይል ምእመናንን በመጠበቅ ለጸሎት የሚተጉ መሪዎችን ስጣት። አቤቱ አምላካችን ሁላችንንም ማረን፡ ይቅርም በለን። ለሰይጣን ከመሸነፍ አድነን። ከውርደትና ከሚያሳፍር ነገር ሁሉ ጠብቀን። በየጊዜውና በየሰዓቱ ሁሉ የአንተ ጥበቃ አይለየን። ያለ ድካምና ያለ ሐኬት /ያለ ስንፍና እናገለግልህ ዘንድ የመንፈስን ብርታት ስጠን። ባንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ፅንዕ ላንተ ይገባል። ከርሱ ጋራ፡ የባሕርይ ሕይወትህ -ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ። _የሁሉ ፈጣሪ የሆንህ እምላካችን ሆይ በዚህች ዕለተ-ሐሙስ "ለታውፅእ-ማይ= ውኃ-ሕይወት-ያላቸውን-ፍጥረታትን ታስገኝ ብለህ በሰጠኸው መለኮታዊ ትእዛዝ ብቻ አዞ-ጕማሬውን፡ ዓሣውንና-ዓሣ-አንበሪውን፡-ሌሎችንም-ተንቀሳቃሽ-ነገሮች እንደፈጠርህ ተጽፏል። ይኸውም-ለመጀመሪያ-ጊዜ ሕይወት-ያላቸው ፍጥረታት ከውኃ አንደተገኙ-የክርስትና-እምነት-አዲስ ሕይወትም- በውኃ ጥምቀት እንዲጀመር-ቅዱስ-ፈቃድህ መሆኑን ያመለክታል። እንዲሁም ቅዱስ ሥጋህን በኅብስት። ክቡር ደምህንም በወይን አምሳል አማናዊ ምግብና መጠጥ አድርገህ የሰጠህባት ይህችው ዕለተ ሐሙስ ናትና ስለባረክሃት ስምህ ይመስገን። በዚህችም ዕለት-የምንሠራውን-ሁሉ-ባርከህ በሰላም-አውለን፡ አሜን።"""""""""""""""""

## ፭/5.——ከዓርብ-ሊጦን-ጋርየሚቀርብ-የምስጋና-ጸሎት

(Thanksgiving ) ዓለምን የያዝህ የሰላም አምላክ ሆይ ! እያንዳንዱን ሰብአዊ ፍጥረትህን ሁሉ ከእናቱ ማሕፀን ጀምረህ አስብ። በጸሎት የሚጠይቀውን ሁሉ ተቀበልለት። በቀናች ሃይማኖት የሚመሩ ሕዝብና አሕዛብን አስብ። ልጆቻቸውን ባርክ፡ የጕጕማሶቻቸውን አካሂድ አቅና።ሴቶችንና ወንዶች ጕልማሶችን፡ ሽማግሎችንም ሁሉ ጠብቅ፡ ጥቃት የደረሰባቸውን-ፈጥናህ ታደጋቸው። ስደት ደርሶባቸው የተበተኑ ትን-ሰብስብ።መንገድ-ከሚሄዱት-ጋር-አብረሃቸው-ሁን። የተጨቆ



ኑትን አድን። በፅኑ አገዛዝ ተጨቁናው የሚኖሩትን ፈጥነህ እንድትታደጋቸው ፈቃድህ ይሁን። አቤቱ አምላካችን ሆይ! ባል የሞተባትን መበለትና አባት፡ እናት የሞቱባቸውን ልጆች መታደግ የሚቻልህ የርኅራኄ አባት ነህ። ለታመሙትም ባለመድኃኒት/ሐኪም ነህ ።በባሕር ለሚጋዙት ማረፊያ ወደብ ነህ ። አንተ የያንዳንዱን ልመናውን፡ እኗኗሩንና የልቡንም አሳብ መርምረህ-ታውቃለህ። አቤቱ ይህችን ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሌሎችንም የአፍሪቃ አገሮች ሁሉ አንተን በማመን አፅንተህ ጠብቃቸው። መናፍቅነትን ከቤተ ክርስቲያንህ አርቅ። ምስጋናህ ከበራላቸው ልጆችህ ጋር አንድ አድርገን። እንደ አንድ ልብ መካሪ፡ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን አብን፡ ወልድን፡ መንፈስ ቅዱስንም እናመስግን፡ ዛሬም፡ ዘውውትርም፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን ! """""""""""

## ፮ /6. በቀዳሚት ሊጦን ላይ የተመሠረተ የምስጋና ጸሎት

_የጸጋ ስጦታ ሁሉ ጀማሪ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ! የአብ ኃይሉና የጥበቡም መገለጫ አንተ ነህ። የዓለምን ኃጢአት የምታርቅ የእግዚአብሔር ልጅ አንተ ነህና ማረን፡ ይቅርም በለን። ሊቈጠርና ሊሠፈር በማይችል ጥበብ ከሰማይ ወርደሃልና። አንተ የፈጠርኸውን በሞት ተለዋጭ ሰውን ታድን ዘንድ ከነፋስ ኃይል ይልቅ ፍጥነት ያላቸውን መላእክትህን የእሳት ነበልባል ያደረግሃቸው አምላክ ሆይ ! ምድርን አይተህ-እንድትናወጥ-ማድረግ-ይቻልሃል።-ተራራዎችን ትዳስሳ ለህ፡ እነርሱም ይጤሳሉ። ስለዚህ ዓለምን የያዝህ አምላካችን ሆይ ! በጸጋ ስጦታህ መሥፈርት መጠን ሕዝብህን አድን። አንተ የፈጠርከውን በሞት ተለዋጭ ሰውን ታድን ዘንድ የእያንዳንዱን ሰው ጸሎት ተቀብለህ፡ በኑሮ የሚገጥመውንም ችግር ሁሉ ስለምታውቅ መርዳት ይቻልሃል።-አቤቱ-ይህችን-አገር-ኢትዮጵያንና-ሌሎችን-ሀገሮች፡-አውራጃዎቻቸውን ጠብቅ። አማኞች ቅዱሳንን ሁሉ በአሳብ ከመናወጥ ፡ ከኑሮ ችግርና ከወራሪ ጠላት አድን ። የጥርጣሬን መንፈስ ከቤተ ክርስቲያን አርቅ። የብርሃን ልጆች ተብለው ከሚጠሩ ቅዱሳን ቤተሰቦች



www.ethiopianorthodox.org

ጋር አንድ አድርገን። እንደ አንድ ልብ መካሪ፡ ኣንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን ዛሬም ዘወትርም አብን፡ ወልድን፡ መንፈስ ቅዱስንም-እናመሰግናለን።-በዚህች ዕለተ ዓርብ በደረቅ ምድር የሚገኙ እንስሳት፡ አራዊትን፡ የሰማይ ወፎችንና ፡ በልብ-የሚሳቡ-ተንቀሳቃሽ-ፍጥረታትን-አስገኝተሃል ። በመጨረሻም ሰውን-በአርአያህና--በአምሳልህ -ፈጥረህ በፍጥረታት ሁሉ-ላይ ላይ ገዢ-አድርገህ ሥልጣን ሰጥተኸዋል። ትእዛዝህን በማፍረስ ካንተ ርቆ የነበረውን የሰው ዘር ከስይጣን ዲያብሎስ ተገዢነትና ከኃጢአት ባርነት ነጻ ያወጣባትም ይህቺው ዕለተ ዓርብ መሆንዋን በዚህ ቅጽበት እያሳብን የምሕረትህ ብርሃን እንዲጕበኘን ፈቃድህ፡ ይሁን። ከነፋስ ኃይል ይልቅ ፍጥነት ያላቸውን መላእክትህን የእሳት ነበልባል ያደረግሃቸው አምላክ ሆይ! ምድርን አይተህ እንድትናወጥ ማድረግ ይቻልሃል።

_ተራራዎችን ትዳስሳለህ፡ እነርሱም ይጤሳሉ።ስለዚህ ዓለምን የያዝህ አምላካችን ሆይ ! በጸጋ ስጦታህ መሥፈርት መጠን ሕዝብህን አድን። አቤቱ የምሕረት አምላክ ሆይ! በስጦታህ መንፈስ ወገኖችህን ሁሉ ደስ አሰኛቸው። አስጨናቂውን ነገር ሁሉ የማቅለል ችሎታ ያለህ አንተ ብቻ ነህና ለነዳያን ገንዘባቸው፡ ተስፋ ላጡ ስዎችም ተስፋቸው አንተ ናህ። ሙታንን -ማስነሣት የምትችል ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! የአብ ኃይሉና ጥበቡ በመሆንህ የምናቀርብልህን ምስጋን ለመቀበል ቅዱስ ፈቃድህ ይሁንልን።

_ይህችን ዕለት መርጠህ፡ ባርከህ፡ ቀድሰህ የአምልኮት መፈጸሚያ በማድረግ በነቢዩ ኢሳይያስ አንደበት "እነሆ በዕለተ ሰንበት በየሳምንቱ ሥጋ ለባሽ የሆነ ሰብአዊ ፍጥረት ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ወደ እኔ ይመጣል" ስትል የተናገርኸውን ቃል በዚህች ቅጽበት እናስባለን ( ኢሳ 66፡ 23 ) ። ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመሄድ ቅዱስ ቃልህን የማንሰማባቸው የሰንበት ቀኖች ሁሉ ከዕድሚያችን ላይ ኣንደሚቀነሱ በቅዱስ ቃልህ ተነግሯል ( 2 ዜና መዋዕል 36፡21-23 )። ስለዚህም በዕለተ ሰንበት



በየሳምንቱ-በቤተ-መቅደስህ ተገኝተን በፊትህ መስገድ እንድንችል የልብን ትጋት ስጠን። ዛሬም፡ ዘወትርም፡ ለዘለዓለሙ፡ አሜን።

## ፯ /7. ከእሑድ ሊጦን ጋር የሚቀርብ <u>የምስጋና ጸሎት</u>

<u>( Thanksgiving )</u> የምሕረት አምላክን ዳግማኛ እንማልዳለን፡ ኖኅን በመርከብ ያሻገርከው፡ 4ቱን ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ለመውጋት 318 የቤት አገልጋ_ዮቹን አሠልፎ በዘመተ ጊዜ አብርሃምን የረዳኸውና ከጠላት ያዳንኸው፡ ለመሥዋዕትነት ቀርቦ የነበረ ይሥሐቅን ከሚሠዋበት መጥባህት የታደግኸው፡ ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ፊት ሸሽቶ በሄደ ጊዜ በሚጓዝበት መንገድ ሁሉ የረዳኸው፡ የመራኸውና ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ባቆመበት ቦታ ሌሊት በራእይ ተገልጠህለት ያፅናናኸው፡ ዮሴፍን በባዕድ አገር ከፍ፡ ከፍ አድርገህ ጠቅላይ አገረ ገዢ ኣንዲሆን ሁሉን ነገር ያመቻቸህለት፡ ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ፡ ሶስናን ከረበናት ተንኮል ፡ ያዳንህ፡ ሙሴን ከታላቅ ረድኤት ጋር ልከህ ሕዝብህን ከባርነት ቀንበር ነጻ አድርገህ ቀን በደመና፡ ሌሊት በእሳት ብርሃን የመራሃቸው አንተ ነህ። በነቢያት አድረህ ቅዱስ ቃልህን ያናገርህና በሐዋርያትም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ያሳደርህባቸው እነተ ነህ ።

_በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ሳሉ፡ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ከሰማይ ወርዶ በነርሱ ላይ ባረፈ ጊዜ በየሀገሩ ሁሉ ቋንቋ፡ ተናገሩ ተብሎ ተጽፏልና። ሰማይና ምድርን የፈጠርህ አንተ አምላካችን ሆይ ! ለእኛም ያን መፈስህን ላክልን። በየጊዜውና በየሰዓቱ አንድነታችንን ባርክልን። በዚህችው ዕለተ እሑድ-መሬትና-ውኃን፡ እሳትና ነፋስን፡ እንዲሁም ብርሃንን፡ ጨለማን ፡ ሰማያትንና መላእክትን የፈጠርህ አምላከ ብርሃን ገናንነትና ክብር፡ ምስጋና ለቅዱስ ስምህ ይሁን ። ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ! በዚህች ዕለተ እሑድ የሞትን ኃይል ድል ነሥተህ ከሙታን ተለይተህ በአንተ አምነው በሞት ለተለዩ ሁሉ በኵር ሆነህ መነሣትህን በክብር፡- በምስጋና- እናስባለን፡ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፡አሜን ! 77



www.ethiopianorthodox.org

# መዝሙር ዘዳዊት

''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## መዝ 1/1፡ <u>የጻድቃን /የደጋግና የክፉ ሰዎች አካሂድ</u>

1 ፍካሬ ዘጻድቃን ወዘኃጥአን፡ መዝሙር ዘዳዊት ሃሌ ሉያ !
በክፉዎች ምክር የማይሄድ ፡ በኃጢአተኞችም መንገድ የማይ
ቆም፡ በዋዘኞችም ወንበር የማይቀመጥ ሰው ብፁዕ (ምስጉን)
ነው 2 በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የሚለው፡ ሕጉንም በቀንና
በሌሊት የሚያነብና የሚያስብ፡ 3 እርሱ በፈሳሽ ውኃ ዳር እንደ
ተተከለችና፣ ፍሬዋን በየወቅቱ እንደምትሰጥ፣ ቅጠሏም
እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል ፡ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለ
ታል። 4 ኃጥአን (ክፉዎች) እንደህ አይደሉም። ነፋስ ከምድር
ገጽ ላይ ጠራርጎ እንደሚወስደው ትቢያ ናቸው። 5 ስለዚህም
ክፉዎች በፍርድ፡-ኃጢአተኖችም በጻድቃል ማኅበር አይቆሙም።
6 እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልና፡ የክፉዎች
መንገድ ግን ትጠፋለች።''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## መዝ ፪ /2፡ መሲሐዊ ትንቢት *(ክርስቶስን የሚመለከት)*

1--ለምንት-አንገለጉ-አሕዛብ-ወሕዝብኒ-ነበቡ ከንቶ=አሕዛብ ለምን
ዶለቱ? ወገኖችስ -ለምን ከንቱ -ነገርን ይናገራሉ? 2 የምድር
ነገሥታት ተነሡ፡ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ
እንዲህ ሲሉ በአንድነት ተሰበሰቡ፡-3 "ማሰሪያቸውን እንበጥስ
ቀንበራቸውንም ከእኛ ላይ አንጣል"። 4 በሰማይ የሚኖር እርሱ
ይሥቅባቸዋል፡ እግዚአብሔርም ይሣለቅባቸዋል። 5 በዚያን ጊዜ
በቍጣው ይናገራቸዋል፡ በመዓቱም ያውካቸዋ። 6 እኔ ግን
በተቀደሰ ተራራው በጽዮን በነርሱ ላይ ንጉሥ ሆንሁ። 7 የእግ
ዚአብሔርን ትእዛዝ እናገር ዘንድ፡ እግዚእብሔር እንዲህ አለኝ፡
እንተ ልጄ ነህ፡ እኔም ዛሬ ወለድሁህ። 8 ለምነኝ፡ አሕዛብን
ለርስትህ፡-የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ- እሰጥሃለሁ"። 9--በብረት-
በትር- ትጠብቃቸዋለህ፣ እንደ- ሸክላ--ሠሪ--ዕቃም ትቀጠቅጣቸዋለህ"



10 አሁንም እናንተ ነገሥታት ልብ አድርጉ፡ እናንተ የምድር
ፈራጆችም *(ዳኞችም)* ተገሠፁ) ። 11 ለእግዚአብሔር በፍርሃት
ተገዙ፡-በመራድም-ደስ-ይበላችሁ።12 እግዚአብሔር እንዳይቈጣና፡
ቁጣውም-ፈጥና-በነደደች-ጊዜ-እናንተም-ከጽድቅ-መንገድ ወጥታ
ችሁ እንዳትጠፉ፣ ጥበብን አፅኑአት፡ በእርሱ የታመኑ ሁሉ
ብፁዓን ናቸውና ።

## ፫ /3፡ <u>የስደት ጊዜ ጸሎት፡</u> *<u>(ዳዊት ከልጁ ከአቤሴሎም ፊት በሸሸ ጊዜ)</u>*

1 እግዚኦ ሚ በዝኁ እለ ይሣቅዩኒ ? አቤቱ የሚያስጨንቁኝ
ምንኛ በዙ! በእኔ ላይ የሚቆሙ ብዙ ናቸው። 2 ብዙ ሰዎች
ነፍሴን "አምላክሽ አያድንሽም " ይሏታል ። 3 አንተ ግን አቤቱ
መጠጊያዬ ነህ፡ ራሴን ከፍ፡ ከፍ የምታደርገው ክብሬ አንተ
ነህ። 4 በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፡ ከተቀደሰው ተራራው
ሆኖ-ሰማኝ። 5እኔ-ተኛሁ፡ አንቀላፋሁም፡-እግዚአብሔር-አስነሥቶ
ኛልና-ተነሣሁ፡ 6 ከሚከቡኝና በእኔ ላይ ከሚነሡ ከአእላፍ
አሕዛብ አልፈራም። 7 ተነሥ አቤቱ አምላኬ ሆይ ! አድነኝ፡-
አንተ-በከንቱ-የሚጠሉኝን-ሁሉ=-መተሃልና የኃጥአንንም ጥርስ
ሰብረሃልና፡8 ማዳን የእግዚአብሔር ነው፤ በረከትህም በሕዝብህ
ላይ ነው። ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## መዝ ፬ /4፡ <u>የእግዚአብሔርን ምሕረት መማፀኛ ጸሎት</u>

1 ሶበ ጸዋዕክዎ ለእግዚአብሔር ሰምዐኒ ጽድቅየ=እግዚአብሔር
በጠራሁት ጊዜ ጽድቄን ሰማኝ ፡ ከጭንቀቴም መውጫውን
አሰፋልኝ፡ ጸሎቴንም ሰምቶ ይቅር አለኝ። 2 እናንተ የሰው
ልጆች ሆይ እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን እልኸኛ ታደርጋላችሁ?
ከንቱ ነገርንስ ለምን ትወድዳላችሁ) ሐሰትን ለምን ትሻላችሁ)
3 እግዚአብሔር በጻድቁ እንደተገለጠ ዕወቁ፡ እግዚአብሔር ወደ
እርሱ-በጮኽሁ-ጊዜ-ይሰማኛል።-4ጠተቁጡ፣-ነገር-ግን አትበድሉ፡
በመኝታችሁ-ሳላችሁ-በልባችሁ-የምታስቡት-ይታወቃችሁ።5 የጽ
ድቅን መሥዋዕት ሠው፣-በእግዚአብሔርም-ታመኑ። 6 "በጐውን
ማን-ያሳየናል?" የሚሉ ብዙዎች ናቸው። አቤቱ የፊትህ ብርሃን
በላያችን ታወቀ። 7 በልባችን ደስታን ጨመርህ። ከስንዴ ፍሬና

www.ethiopianorthodox.org

ከወይን፡ ከዘይትም ይልቅ በዛ። 8 በእርሱ በሰላም እተኛለሁ፡
አንቀላፋለሁም። አቤቱ አንተ ብቻህን በተስፋ አሳድረኸኛልና።

### መዝ ፭/5፡ የእግዚአብሔር አዳኝነት የሚገልጥ ጸሎት

1 ቃልየ አፅምዕ እግዚኦ ወለቡ ጽራሕየ= አቤቱ ቃሌን አድምጥ
ጩኸቴንም አስተውል። 2 የልመናዬን ቃል አድምጥ፡ ንጉሤና
አምላኬ ሆይ! አቤቱ ወደ አንተ እጸልያለሁና። 3 በማለዳ ቃሌን
ስማኝ፣ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፣እገለጥልሃለሁም። 4 አንተ
በደልን የማትወድ አምላክ ስለሆንህ ክፉዎች ከአንተ ጋር
አያድሩም። 5 ዓመፀኞችም በዓይኖችህ ፊት አይኖሩም፣ ዓመፅን
የሚያደርጉትንም-ሁሉ-ጠላህ። 6-ሐሰት-የሚናገሩትን ትጥላቸዋ
ለህ፡ ደም አፍሳሹንና ሽንጋዩን ሰው እግዚአብሔር ይጸየፈዋል።
_7 እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ፡አንተን
በመፍራት በቤተ መቅደስህ እሰግዳለሁ። 8 አቤቱ በጽድቅህ
ምራኝ፣ ስለ ጠላቶቼም መንገዴን በፊትህ አቅና። 9 ባፋቸው
እውነት የለምና፣ ልባቸውም ከንቱ ነው። ጉሮሮአቸው እንደ
ተከፈተ-መቃብር-ነው።-በምላሳቸው-ይሸነግላሉ።10-አቤቱ ፍረድባ
ቸው፣-በነገረ ሠሪነታቸውም ይውደቁ። እንደ ሐሰታቸውም
ብዛት አሳድዳቸው፣-አቤቱ እነርሱ አሳዝነውሃል።11--በአንተ
የሚታመኑ ሁሉ ግን ለዘለዓለሙ ደስ ይላቸዋል። በእነርሱም
ታድራለህ። ስምህንም የሚወድዱ ሁሉ በአንተ ይመካሉ። 12
አንተ ጻድቁን ትባርከዋለህና። አቤቱ እንደ ጋሻ ከለልኸን። '

### መዝ ፮ /6፡ የጭንቀትና መከራ ጊዜ ጸሎት

1 እግዚኦ በመዓትከ ኢትቅሥፈኒ=አቤቱ በቁጣህ አትቅሠፈኝ፡
በመቅሠፍትህም አትገሥፀኝ። 2 ደካማ ነኝና አቤቱ ይቅር-በለኝ!
አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ። 3 ነፍሴም እጅግ ታወከች፡
አንተስ እስከ መቼ ድረስ ነው? 4 አቤቱ ተመለስ፣ ነፍሴንም
አድናት። ስለ ቸርነትህም አድነኝ። 5 በሞት የሚያስብህ
የለምና። በሲኦልስ የሚያመሰግንህ ማን ነው? 6 በጭንቀቴ
ደከሜአለሁ። ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፡ በዕንባዬም
መኝታዬን አርሳለሁ። 7 ዓይኔ ከቁጣ የተነሣ ታወከች፡ ከጠላቶቼ
የተነሣ አረጀሁ ። 8 ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ ከእኔ ራቁ ።
እግዚአብሔር-የልቅሶዬን-ቃል ሰምቶአልና። 9 እግዚአብሔር
ልመናዬን ሰማኝ። እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ። 10 ጠላቶቼ
ሁሉ ይፈሩ፣ ይጐስቁሉም። ወደ ኋላቸው ይመለሱ፡ በፍጥነትም
ሐፍረትን ይልበሱ ።

### መዝ ፯/7፡ ስለ ትክክለኛ ፍትሕ የሚቀርብ ጸሎት

1 እግዚኦ አምላኪየ ብከ ተወከልኩ ኢትግድፈኒ =አቤቱ አምላኬ
ሆይ! በአንተ ታመንሁ፣ አትጣለኝም። ከሚከቡኝ ሁሉ አድነኝና
አውጣኝ፤ 2 የሚያድንና የሚታደግ ሳይኖር፡ ነፍሴን እንደ
አንበሳ እንዳይነጥቋት። 3 አቤቱ አምላኬ እንዲህስ ካደረግሁ፡
ዓመፃም በእጄ ቢኖር ፣ 4 ክፉ ላደረጉብኝ ክፉን የመልሼላቸው
ብሆን፣ ጠላቶቼ ዕራቁቴን ይጣሉኝ። 5 ጠላቴ ነብፍሴን
አሳድዶ ያግኛት። ሕይወቴን በምድር ላይ ይርገጣት፡ ክብሬንም
በትቢያ ላይ ያዋርደው ። 6 አቤቱ በመዓትህ ተነሥ ! በጠላቶቼ
ላይ ተነሣባቸው። አቤቱ አምላኬ ባዘዝኸው ሥርዓት ተነሥ።
7-የአሕዛብ-ጉባኤ ይከብብሃል። ስለዚህም ወደ አርያም ተመለስ፡
8 እግዚአብሔር በሕዝብ ላይ ይፈርዳል። አቤቱ አምላኬ እንደ
ጽድቅህ ፍረድልኝ፡ እንደ የዋህነቴም ይሁንልኝ ። 9 የኃጥአን
ክፋት ያልቃል። ጻድቃንን ግን ታቀናቸዋለህ። እግዚአብሔር
ልብንና ኩላሊትን ይመረምራል። 10 እግዚአብሔር በእውነት
ይረዳኛል። ልበ ቅኖችን የሚያድናቸው እርሱ ነው። 11 እግዚአ
ብሔር የእውነት ዳኛ ነው፡ ኃያልም፡ ታጋሽም ነው። ሆኖም
ሁልጊዜ-ጥፋትን-አያመጣም።12--ባትመለሱ-ግን-ሰይፉን ይመዝ
ዛል።-ቀስቱን-ገተረ፣-አዘጋጀም።13--የሚገድል--መርዝንም አዘጋጀ
በት። ፍላጻዎቹንም የሚቃጠሉ አደረገ። 14 እነሆ ዐመፀኛ
በዓመፁ ተጨነቀ። ጭንቀትን ፀነሶ። ኃጢያትን ወለደ። 15
ጉድጓድ ምሶ አፈሩን የሚያወጣ፣ ባዘጋጀው ጉድጓድ ራሱ
ይገባበታል። 16 ጉድጓድን ማሰ፣ ቈፈረም። ባዘጋጀውም ጉድጓድ
እርሱ ራሱ ይገባበታል። 17 እግዚአብሔርን እንደ ጽድቁ መጠን
አመሰግናለሁ። ለልዑል እግዚአብሔር ስም እዘምራለሁ ።



www.ethiopianorthodox.org

## መዝ ፰ /8፡ ለሰው የተሰጠ የገዢነት ሥልጣን

1 እግዚኦ እግዚአነ ጥቀ ተሰብሐ ስምከ በኵሉ ምድር= አቤቱ
ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ። ምስጋናህም
በሰማዮች ላይ ከፍ፡ ከፍ ብሎአልና ። 2 ስለ ጠላት ከሕፃናትና
ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ። ጠላትንና ግፈኛን
ታጠፋው-ዘንድ።-3-የጣቶችህን--ሥራ-ሰማዮችን፡-አንተ የሠራሃቸ
ውን ጨረቃንና ከዋክብትን እናያለንና፣ 4 አቤቱ ታስበው ዘንድ
ሰው ምንድን ነው? ትጐበኘውስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?
5 ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ
ከለልኸው ። 6 በእጆችህ ሥራ ላይ ሁሉ ሾምኸው ፤ ሁሉንም
ከእግሩ በታች አስገዛህለት።7 በጎችንም፣ በሬዎችንም ሁሉ
ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፣8 የሰማይንም ወፎች፣
የባሕርን-ዓሣዎች፣-በባሕር-መንገድ-የሚሄደውንም-ሁሉ አስገዛህ
ለት። 9 አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ።

## መዝ ፱ /9፡ የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍትሕ

1 እገኒ ለከ እግዚኦ በኵሉ ልብየ= አቤቱ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፡ ታምራትህንም ሁሉ እናገራለሁ። 2 በአንተ
ደስ ይለኛል፡ ሐሤትም አደርጋለሁ፡ ልዑል ሆይ! ለስምህ
እዘምራለሁ። 3 ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው በተመለሱ ጊዜ
ይታመሙ፡ ከፊትህም ይጥፉ። 4 ፍርዴንና በቀሌን አድርገህልኛ
ልና። የጽድቁ ፈራጅ ሆይ! በዙፋንህ ላይ ተቀመጥህ። 5-አሕዛ
ብን-ገሠፅህ፡-ዝንጉዎችም-ጠፉ።ስማቸውንም ለዘላለም ደመሰስህ።
6 ጠላቶች-በጦር ለዘለዓለም ጠፉ፡ ከተሞቻቸውንም አፈረስህ፡-
መታሰቢያችትውንም-ባንድነት-ታጠፋለህ።-7 እግዚአብሔር ግን
ለዘለዓለም ይኖራል፡ ዙፋኑንም ለፍርድ አዘጋጀ፡ እርሱም
ዓለምን በጽድቅ ይዳኛታል። ለአሕዛብም በቅንነት ይፈርድል።
9--እግዚአብሔር-ለድሆች-መጠጊያ-ሆናቸው፡-እርሱም በመከራ
ቸው ጊዜ ረዳታቸው ነው። 10 ስምህን የሚወዱ ሁሉ በአንተ
ይታመናሉ፡-አቤቱ-የሚሹህን-አንተ-አትተዋቸውምና። 11 በጽዮን
ለሚኖር ለእግዚአብ-ብሔር ዘምሩ። ለአሕዛብም ሥራውን ንገሩ



12--ደማቸውን- የሚመራመር- እርሱ- አስቦአልና ። የድሆችን
ጩኸት አልረሳምና።13ጠአቤቱ-ይቅር-በለኝ።-ጠላቶቼም የሚያመ
ጡብኝን መከራ እይ። ከሞት ደጆች ከፍ፡ ከፍ የሚያደርገኝን ፤
14 ምስጋናህን ሁሉ እንናገር ዘንድ በጽዮን ልጆች፡ በደጆችዋም
በማዳንህ ደስ ይለናል።-15 አሕዛብ በሠሩት በደላቸው-ጠፉ።-
በዚያም፡በሸሸጓት-ወጥመድ-እግራቸው-ተጠመደ።

16 እግዚአብሔር ፍርድን ማድረግ ያውቃል። ኃጢአተኞች
በእጆቹ ሥር ተጠመዱ ። 17 ኃጢያተኞችና እግዚአብሔርን
የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ። ወደ ሲኦል ይመለሱ። 18 ድሃ
ለዘለዓለም የሚረሳ አይደለምና። ችግረኞችም ተስፋቸውን
ለዘለዓለም አያጡም። 19 አቤቱ ተነሥ፡ ሰውም አይበርታ ።
አሕዛብ በፊትህ ይፈረድባቸው። 20 አቤቱ የሕግን መምህር
በላያቸው ላይ ሹም። አሕዛብም ሰዎች መሆናቸውን ይወቁ ።
(ተከታዩ መዝ በዕብራይስጡ 10ኛ ነው)

21 አቤቱ ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራየ ጊዜስ ለምን ቸል
ትላለህ? 22 በኃጢያተኛ ትዕቢት ድሃ ይናደዳል። ባሰቡት
ተንኮላቸው ይጠመዳሉ፡ ኃጢያተኛ በነፍሱ ፈቃድ ይወደሳል
ዓመፀኛም ይባረካል።-23-ኃጢአተኛ -እግዚአብሔርን አበሳጨው፡
24 እንደቁጣው ብዛት ግን አይመራመረውም። በእርሱ ፊት
እግዚአብሔር-የለም። 25 መንገዱ ሁሉ የረከሰ ነው። ፍርድህም
በፊቱ የፈረሰ ነው። ጠላቶቹንም ሁሉ ይገዛቸዋል።

_26 በልቡም "ለልጅ ልጅ አልታወክም ክፉም አያገኘኝም" ይላል
27 አፉ መርገምንና ሽንገላን የተመላ ነው። ከምላሱ በታች
ድካምና-መከራ-ነው-።-28-ለማደን ከባለጸጎች ጋር ይሸምቃል፡
ንጹሑንም ሰው በስውር ይገድል ዘንድ ዓይኖቹ ወደ ድሃ
ይመለከታሉ። 29 እንደ አንበሳ በጉድጓድ ተሰውሮ ይሸምቃል፡
ድሃውን ለመንጠቅ ያደባል፡ ድሃውንም ይነጥቀዋል፡
ይስበዋልም። 30 በጠጥመዱም ስለሚያጐስቍለው ይጐብጣል።
በተቈጣጠርው ድሃውንም ይወድቃል፡ 31 ድሃውም በልቡ
"እግዚአብሔር እረስቶኛል፡ ፈጽሞም እንዳያይ ፊቱን መለሰ"
ይላል። 32 አቤቱ አምላኬ ሆይ ተመለስ ፡ እጅህም ከፍ ፡ ከፍ

www.ethiopianorthodox.org

ትበል፡-ድሆችንም-አትርሳ።33 ኃጢአተኛ ስለምን እግዚአብሔርን
አስቆጣው ? በልቡ "አይመራመረኝም" ይላልና። 34 አንተ
ድካምንና ቁጣን በመመልከት ታያለህ። እንግዲህ አሳልፈህ
ትሰጠው ዘንድ ድሃው በአንተ ላይ ተጣለን? ለድሃ አደግም
ረዳቱ አንተ ነህ። 35 ኃጢአተኛን በኃያል ክንድህ ስበር።
ስለእርሱ ኃጢአቱ ተመርምራ አትገኝም። 36 እግዚአብሔር
ለዘለዓለም ይነግሣል። አሕዛብም ከምድር ይጠፋሉ። 37 እግዚአ
ብሔር የድሆችን ምኞች ሰማ።ጆሮውም የልባቸውን ሐሳብ
አደመጠች። 38 ፍርድ ለድሀ-አደግና ለችግረኛ ይደረግ ዘንድ
ክፉ ሰዎች በምድር ላይ አፋቸውን ከፍ፡ ከፍ ማድረግን
እንዳይደግሙ አድርግ ።

መዝ ፤ /10፡ <u>ስለፍትሕ አምላክ የቀረበ ተማሕፅኖ</u>

1 በእግዚአብሔር ተወከልኩ እፎ ትብልዋ ለነፍስየ ?=በእግዚአ
ብሔር ታመንሁ፡ ነፍሴን እንደወፍ ወደ ተራሮች ብረሪ
እንዴት ትላላችሁ? 2 ኃጢያተኞች እነሆ ቀስታቸውን
ገትረዋልና ። ፍላፃቸውንም በአውታር አዘጋጅተዋልና። ልበ
ቅኖችን በስውር ይነድፉ ዘንድ ። 3 አንተ የሠራኸውን እነሆ
እነርሱ አፍርሰዋልና። ጻድቅ ግን ምን አደረገ። 4 እግዚአብሔር
በቤተ መቅደሱ ነው። እግዚአብሔር በዙፋኑ በሰማይ ሆኖ፡
ዓይኖቹ ወደ ድሃ ይመለከታሉ። ቅንድቦቹ የሰው ልጆችን
ይመረምራሉ፤ 5 እግዚአብሔር ጻድቁንና ኃጥኡን ይመረምራል።
ዓመፅን የወደዳት ግን ነፍሱን ጠልቶአል።6 ወጥመድ በኃጥአን
ላይ ይዘንባል።እሳትና ዲን አውሎ ነፋስም የጽዋቸው ዕድል
ፈንታ ነው። 7 እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና ጽድቅን ይወዳል።
ቅንነት ግን ፊቱን ታየዋለች።

መዝ-፲፩/11<u>፡ደግ-ሰው-በጠፋበት-ጊዜ-የእግዚአብሔር ጠባቂነት</u>

1 አድኅነኒ እግዚኦ እስመ ኀልቀ ኄር=ደግ ሰው አልቋና አቤቱ
አድነኝ ። ከሰው ልጆችም መተማመን-ጎድሎአልና። 2 እርስ
በርሳቸውም ከንቱ ነገርን ይናገራሉ። በሽንገላ ከንፈር ሁለት
ልብ ሆነው ይናገራሉ። 3 የሽንገላ ከንፈሮችን ሁሉ
እግዚአብሔር ይቈርጣቸዋል። ታላቅ ነገርን የምትናገረውንም



ምላስ ይቆርጣል። 4 ምላሳችን እናበረታለን፡ ከንፈሮቻችን የእኛ
ናቸው። ጌታችን ማን ነው?" ይላሉ። 5 ስለድሆች መከራና
ስለእስረኞችም--ጩኸት--እግዚአብሔር--"አሁን-እነሣለሁ፥ መድኃ
ኒትንም አደርጋለሁ"። በእርሱም እገለጣለሁ" ይላል። 6 በምድር
ላይ እንደተፈተነና ሰባት ጊዜም እንደተጣራ ብር የእግዚአብሔር
ቃል ንጹሕ ቃል ነው። 7 አቤቱ አንተ ጠብቀን፡ ከዚችም
ትውልድ ለዘለዓለም ታደገን። 8 ዝንጉዎች በዙሪያችን
ይመላለሳሉ።እንደ-ገናናነትህ መጠን የሰው ልጆችን አፀናሃቸው።

መዝ ፲፪/12= <u>የእግዚአብሔርን ረድኤት መማፀኛ ጸሎት</u>

1 እስከ ማእዜኑ እግዚኦ ትረሥአኒ ለግሙራ?= አቤቱ
እስከመቼ ፈጽመህ--ትረሳኛለህ? እስከመቼስ ፊትህን ከእኔ ወደ
ሌላ ትመልሳለህ? 2 እስከመቼ በነፍሴ ሐዘንን አኖራለሁ?
እስከመቼ ልቤ ሁልጊዜ ትጨነቅብኛለች? እስከመቼ ጠላቶች
በላዬ ይታበያሉ? 13 አቤቱ አምላኬ ተመልከተኝ፡ ስማኝም
ለሞትም እንዳያንቀላፉ ዓይኖቼን አብራቸው። ጠላቶቼ
"አሸነፍነው" እንዳይሉ፡- 4 የሚያስጨንቁኝም እኔ ብናወጥ ደስ
እንዳይላቸው አድርግ ። 5 እኔ ግን በቸርነትህ ታመንሁ፡ ልቤ-
በማዳንህ- ደስ--ይለዋል ። 6-የረዳኝን-እግዚአብሔርን አመሰግነዋ
ለሁ፡ ለልዑል እግዚአብሔር ስም እዘምራለሁ ።

መዝ ፲፫/13፡ <u>ከክሕደት የሚመጣ የሰዎች ክፋት</u>

1 ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር=ሰነፍ በልቡ "እግዚ
አብሔር የለም" ይላል። በሥራቸው ረከሱ፡ ጐሰቆሉ። በጐ ነገርን
የሚሠራት አንድም እንኳ የለም። 2 የሚያስተውልና እግዚአ
ብሔርንም የሚፈልግ መኖሩን ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ
የሰው ልጆችን ተመለከተ። 3 ሁሉም ተስተካክለው በአንድነት
ዐመፀ። በጐ ነገርን የሚሠራት አንድም እንኳ አልተገኘም ።
4-ጉሮሮአቸው እንደ መቃብር የተከፈተ ነው። በምላሳቸው
ሸነገሉ። 5 ከከንፈራቸው በታች የእባብ መርዝ አለ። አፋቸውም
መራራ መርገምን የተመላ ነው። 6 ደምን ለማፍሰስ እግራቸው
ፈጣን ነው። ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳቸው አለ። የሰላምንም
መንገድ-አለወቋትምና-እግዚአብሔርን መፍራት በዓይናቸው ፊት

www.ethiopianorthodox.org

የለም። 7 ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉና ኃጢአትን የሚሠሩ
ሁሉ አያውቁም። እግዚአብሔርንም አይጠሩትም።-8-በዚያም-
ፈሩ፡-የማያስፈራ እርሱ አስፈራራቸው። እግዚአብሔር በጻድቃን
ትውልድ-ዘንድ-ነውና።9-የድሆችን-ምክር-አሳፈራችሁ። እግዚአብ
ሔር ግን ተስፋቸው ነው። 10 ከጽዮን መድኃኒትን ለእስራኤል-
ማን-ይሰጣል?-እግዚአብሔር-የሕዝቡን-ምርኮ በመለሰ-ጊዜ-ያዕቆብ
ደስ ይለዋል።እስራኤልም ሐሤትን ያደርጋል።

## መዝ ፲፬ /14፡ <u>በእግዚአብሔር ቤት የሚኖር</u>

1 እግዚአ መኑ የኀድር ውስተ ጽላሎትከ=አቤቱ በድንኳንህ
ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራ ማን ይኖራል? 2
በቅንንነት የሚሄድ፡ ጽድቅንም የሚያደርግ፡ በልቡም እውነትን
የሚናገር፡3 በአንደበቱም የማይሸነግል፡ በባልጀራው ላይ ክፋትን
የማያደርግ፡ ዘመዶቹንም የማያሰድብ፡4 ኃጢአተኛ በፊቱ የተናቀ፡
እግዚአብሔርንም-የሚፈሩትን-የሚያከብር፡-ከማለ-በኋላ ባልንጀራ
ውን-የማይከዳ፡ 5 ገንዘቡን በአራጣ *(በወለድ)* የማያበድር፡ በንጹሕ
ሰው ላይ መማለጃን የማይቀበል። እንዲህ የሚያደርግ ሰው
ለዘለዓለም አይታወክም ።

## መዝጠ፲፭/15፡ <u>እግዚአብሔርን አለኝታ የማድረግ ጸሎት</u>

1 ዕቀበኒ እግዚኦ እስመ ኪያከ ተወከልኩ= አቤቱ በአንተ
ታምኛለሁና ጠብቀኝ። 2 እግዚአብሔርን አልሁት "አንተ ጌታዬ
ነህ፡ በጎነቴን አትሻትምና፡ 3 ፈቃድህ ሁሉ በምድር ባሉት
ቅዱሳን ላይ ተገለጠ ፤ 4 ደዌአቸው በዛ ፡ ከዚያም ከኋላ
ለጥፋት ተፋጠኑ። በደም ማኅበራቸው አልተባበርም። ስማቸው
ንም በአፌ አልጠራም 5 እግዚአብሔር የርስቴ ዕድል ፋንታ
ጽዋዬ ነው። ርስቴን የምትመልስ አንተ ነህ ፤ 6 ይይዙኝ ዘንድ
ገመድ ጣሉብኝ፡ ርዕስቴ ግን ተጠበቀችልኝ፤ 7 እንዳስተውል
„ያደረገኝን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ደግሞም በሌሊት
ኩላሊቶች ይገስፁኛል። 8 እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በፊቴ
አየዋለሁ፡ እንዳልታወክ በቀኜ ነውና። 9 ስለዚህ ልቤ ደስ አለው
ምላሴም-ሐሤት አደረገ፡ ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ያድራል።10 ነፍ



ሴን በሲኦል አትተዋትምና። ጻድቅህንም መበስበስን ያይ ዘንድ-
አትተወውም-(የሐዋ.2፡-27)።11-የሕይወትን-መንገድ-አሳየኸኝ። ከፊ
ትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ። በቀኝህ የዘለዓለም ፍሥሐ አለ።

## መዝ ፲፮ /16፡ <u>በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው ጸሎት</u>

1 እግዚአ ስምዐኒ ጽድቅየ=አቤቱ ጽድቄን ስማኝ፡ ልመናዬንም
አድምጠኝ።በተንኮለኛ ከንፈር ያልሆነውን ጸሎቴን አድምጠኝ ።
2 ፍርዴ ከፊትህ ይወጣል፥ ዓይኖቼም ጽድቅህን አዩ። 3 በሌሊ
ትም ጐበኘኸኝ፡ ልቤንም ፈተንኸው። ፈተንኸኝ ዓመፅም
አልተገኘብኝም። 4 የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር፡ ስለ
ከንፈሮችህ ቃል ጭንቅ የሆኑ መንገዶችን ጠበቅሁ፤ 5 ስኰናዬ
እንዳይናወጥ አረማመዴን በመንገድህ አፅና ። 6 እግዚአብ
ሔር ሆይ! ሰምተኸኛልና እኔ ጮኽሁ፡ ጆሮህን ወደ እኔ
አዘንብል፡ ቃሌንም ስማ ። 7 የሚያምኑብህ ሰዎች ቀኝህን
ከሚቃወሟት የሚያድናቸውን ቸርነትህን ግለጠው ።
8 እንደ ዓይንህ ብሌን ጠብቀኝ፡ በከንፈሮችህም ጥላ ሰውረኝ ።
9 በሚያሳቁሉኝ ኃጥአን ፊት ጠላቶቼ ነፍሴን ተመለከትዋት፤
10-አንጀታቸውን-ቋጠሩ፡-አፋቸው-ትዕቢትን-ተናገረ።11 አሁንም
አባረሩኝ፡ ከበቡኝም። ዓይናቸውንም ወደ ምድር ዝቅ፡ ዝቅ
አደረጉ። 12 እነርሱም ለንጥቂያ እንደሚሸምቅ አንበሳ
ተሰውሮም- እንደሚደፍጥ እንደ አንበሳ ደቦል ተቀበሉኝ ።
13 አቤቱ ተነሥ፡ ደርሰህም አሰናክላቸውና ነፍሴን ከጦር
አድናት። 14 ሰይፍህ በእጅህ ጠላቶች ላይ ናት። አቤቱ በምድር
ካነሱ ሰዎች በሕይወታቸው ከፋፍላቸው። ከሰወርኸው ነገር
ሆዳቸው ጠገበች፡ ልጆቻቸውም ጠግበው የተረፋቸውን
ለሕፃናቶቻቸው ትተዋል። 15 እኔ ግን በጽድቅህ ፊትህን
አያለሁ ክብርህን በማየትም እጠግባለሁ። ''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## መዝ ፲፯/17፡ <u>እግዚአብሔርን የሚያፈቅር ሰው ጸሎት</u>

1አፈቅረከ-እግዚኦ-በኃይልየ=አቤቱ-በፍጹም ኃይሌ እወድሃለሁ።
2 እግዚአብሔር ኀይሌ፡ አምባባ መጠጊያዬ፡ መድኃኒቴ፡ አምላኬ
በእርሱ የምተማመንበት ረዳቴ፡ መታመኛዬና የድኅንነቴ ቀንድ ፡
መጠጊያዬም ነው። 3 እግዚአብሔርን በጠራሁት ጊዜ ከጠላቶቼ

www.ethiopianorthodox.org

እድናለሁ። 4 የሞት ጣር ያዘኝ፡ የአመፀኛ ፈሳሽም አወከኝ ።
5 የሲኦል ጣር ከበበኝ፡ የሞት ወጥመድ ደረሰብኝ ። 6 በጨነቀኝ
ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፡ ወደ አምላኬም ጮህኹ፡ በቤተ
መቅደሱ ቃሌን ሰማኝ፡ ጩኸቴም በፊቱ ወደ ጆሮው ገባ።
7-ምድርም-ተንቀጠቀጠች፡ ተናወጠችም፡ የተራሮችም መሠረቶች
ተነቃነቁ፡ እግዚአብሔርም ተቆጥቶአልና ተንቀጠቀጡ።

8 ከቁጣው ጢስ ወጣ፡ በፊቱም እሳት ነደደ፡ ፍምም ከእርሱ
በራ። 9--ሰማዮችን ዝቅ፡ ዝቅ አደረገ ወረደም፡ ጭጋግ ከእግሩ
በታች ነበር። 10 በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፡ በነፋስም ክንፍ
በረረ። 11 በድንኳኑ ዙሪያ መሰወሪያውን ጨለማ አደረገ፡
ውኃዎች በደመናዎች ውስጥ ጠቈሩ። 12 በፊቱ ካለው ብርሃን
የተነሣ ደመናትና በረዶ፡ የእሳት- ፍም በፊቱ አለፉ።13 እግዚአ
ብሔር-በሰማያት-አንጐደጐደ፡ ልዑልም ቃሉን ሰጠ።14 ፍላፃውን
ላከ፡ በተናቸውም፡-መብረቆችንም-በማብዛት-አወካቸው።15 አቤቱ
ከተግሣፅህና ከመዓትህም መንፈስ እስትንፋስ የተነሣ የውኖች
ምንጮች ታዩ። የዓለም መሠረቶችም ተገለጡ። 16 ከአርያም
ላይ ወሰደኝም፡ ከብዙ ውኖችም አወጣኝ። 17 ከብርቱዎች
ጠላቶቼና ከሚጠሉኝም አዳነኝ፡ በርትተውብኝ ነበርና።

18--በመከራዬ ቀን ደረሱብኝ፡ እግዚአብሔር ግን መጠጊያዬ
ሆነ።19-ወደ-ሰፊ-ስፍራም-አወጣኝ፡-ወዶኛልና-አዳነኝ።-20 እግዚ
አብሔር እንደ ጽድቄ ይሰጠኛል፡ እንደ እጆቼ ንጽሕና
ይከፍለኛል። 21 የእግዚአብሔር መንገድ-ጠብቄአለሁና፡አምላኬን
አልበደልኩም።22-ፍርዱ ሁሉ ሁልጊዜ በፊቴ ነበርና ጽድቁን
ከእኔ-አላራቀም። 23 ከእርሱ ጋር ንጹሕ እሆናለሁ፡ ከኃጢአቴም
እጠበቃለሁ። 24 እግዚአብሔርም እንደ ጽድቄ ይሰጠኛል፡ እንደ
እጆቼም ንጽሕና በዓይኖቹ ፊት ይከፍለኛል። 25 ከጻድቅ ሰው
ጋር ጻድቅ ትሆናለህ፡ ከቅን ሰው ጋርም ቅን ትሆናለህ። 26
ከንጹሕም ሰው ጋር ንጹህ ትሆናለህ፡ ከጠማማም ጋር ጠማማ
ትሆናለህ። 27 አንተ የተዋረደውን ሕዝብ ታድናለህና።
የትዕቢተኞችን ዓይኖች ግን ታዋርዳለህ። 28 አቤቱ አንተ
መብራቴን ታበራለህና አምላኬ ጨለማዬን ያበራል። 29 በአንተ



ከጥፋት-እድናለሁና፡ በአምላኬም-ቅጥሩን-እዘላለሁ።30 የአምላኬ
መንገዱ ንጹህ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፡ በእርሱ-
ለሚመኩበት-ሁሉ-መታመኛቸው-ነው።31 -ከእግዚአብሔር በቀር
አምላክ ማን ነው? ከአምላካችንስ ሌላ እግዚአብሔር ማን ነው?
32 ኃይልን የሚያስታጥቀኝ እግዚአብሔር ነው፡ መንገዴንም
ንጹሕ የሚያደርጋት፡ 33 እግሮቼን እንደ ዋልያ እግሮች
የሚያበረታ፡ በከፍታ ቦታ የሚያቆመኝ፡ 34 እጆቼን ሠልፍ
የሚያስተምር ፡ እርሱ ነው ። በክንዴም የናስ ቀስት አደረገ ።
35-ለደኅንነቴም-መታመኛ-ሰጠኝ፡-ቀኝህም-ተቀበለኝ።ትምህርትህ
ለዘለዓለም ያፀናኛል ። የሚያስተምረኝም -ሁሉ- ተግሣፅ ነው።
36-አረማመዴን-በበታቼ-አሰፋህ፡-ስኰናዬ-አልደከመም።37-ጠላቶ
ቼን-አሳድዳቸዋለሁ፡-አይዛቸዋለሁ፡-እስካጠፋቸውም-ድረስ አልመ
ለስም። 38 አስጨንቃቸዋለሁ፡ መቆም አይችሉም፡ ከእግሬም
በታች ይወድቃሉ። 39 በሠልፍም ኃይልን- ታስታጥቀኛለህ፡-
በበላዬ-የቆሙትን-በበታቼ ትጥላቸዋለህ።

_40 የጠላቶቼን ጀርባ ሰጠኸኝ፡ የሚጥሉኝንም አጠፋሃቸው ፡
41 ጮኹ፡ የሚራራላቸውም አጡ። ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ
አልሰማቸውም። 42 በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ እፈጫቸወለሁ፡
እንደ አደባባይም ጭቃ እረግጣቸዋለሁ። 43 ከሕዝብ ክርክር
አድነኝ፡ የአሕዛብም ራስ አድርገህ ትሾመኛለህ፡ የማላውቀው
ሕዝብ ይገዛልኛል። 44 በጆሮ ሰምተው ተገዙልኝ። የባዕድ
ልጆች-አረጁ፡ በመንገዳቸውም ተሰናከሉ። 45 46 እግዚአብሔር
ሕያው ነው፡ አምላኬም ቡሩክ ነው። የመድኀኒቴም አምላክ
ከፍ፡ ከፍ አለ። 47 አምላኬ በቀሌን ይመልስልኛል፡ አሕዛብን
በበታቼ ያስገዛልኛል። 48 ከጠላቶቼ የሚታደገኝ እርሱ ነው።
ከግፈኛ ሰው አድነኝ። 49 አቤቱ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ
አመሰግንሃለሁ፡ ለስምህም እዘምራለሁ። 50 የንጉሡን
መድኀኒት ታላቅ ያደርጋታል፡ ቸርነቱንም ለቀባው ለዳዊት፡
ለዘሩም እስከ ዘለህለም ያደርጋል።

www.ethiopianorthodox.org

## መዝ-፲8/18፤ ፍጥረታት-የእግዚአብብሔርን-ክብር ይገልጣሉ

1 ሰማያት--ይነግራ--ስብሐተ--እግዚአብሔር--ሰማያት የእግዚአብ
ሔርን ክብር ይናገራሉ፡የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።
2 ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፡ ሌሊትም ለሌሊት ጥበብን
ትናገራለች ። 3 ቃላቸው ያልተሰማበት ነገር የለም፡ መናገርም
የለም። 4 ቃላቸውም ወደ ምድር ሁሉ ወጣ፡ ነገራቸውም እስከ
ዓለም ዳርቻ ደረሰ። 5 በፀሐይ ውስጥ ድንኳኑን አደረገ፡
እርሱም-እንደ- ሙሽራ- ከእልፍኙ-ይወጣል፡-በመንገዱ እንደሚራ
መድ ዐርበኛ ደስ ይለዋል ። 6 አወጣጡ ከሰማያት ዳርቻ ነው።
መግቢያውም እስከ ዓለም ዳርቻ ነው። ከትኩሳቱም የሚሰወር-
የለም።7 የእግዚአብሔርን ሕግ ንጹሕ ነው፡ ነፍስንም
ይመልሳል። የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፥ ሕፃናትንም
ጠቢባን ያደርጋል ። 8 የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፥
ልብንም ደስ ያሰኛል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፡
ዓይኖችንም ያበራል ። 9 እግዚአብሔርን መፈራት ንጹሕ ነው፡
ለዘለዓለምም ይኖራል። የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት
በአንድነት ነው ። 10 ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፡
ከማርና ከማር ወለላም ይልቅ ይጣፍጣል።11 አገልጋይህ ደግሞ
ይጠብቀዋል፡ በመጠበቁም-ብዙ ዋጋ ይቀበላል። 12 ስሕተትን
ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኀጢአት አንጻኝ ፡ 13 ከልዩ ሰው
አገልጋይህን አድነው።፡ ካልገዙኝ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ።
ከታላቁም ኀጢአት እነጻለሁ።14 የአንደበቴ ቃል ያማረ ይሁን፡
የልቤ-አሳብም ሁልጊዜ በፊቴ ነው፡ አቤቱ ረድኤቴ፡ መድኀኒቴም
አንተ ነህ።

## መዝ ፲፱/19. ስእለትና መባ ይዞ ለሚቀርብ ሰው የሚጸለይ ቃል

1 ይስማዕከ እግዚአብሔር በዕለተ ምንዳቤከ =በመከራህ ቀን
እግዚአብሔ ር ይስማህ ፡ የያዕቆብ አምላክ ስም ይቁምልህ ።
2 ከመቅደሱ ረድኤትን ይላክልህ፡ ከጽዮንም ይቀበልህ ።
3--መሥዋዕትህን ያስብልህ፡ ቁርባንህንም ያለምልምልህ ።
4 እግዚአብሔር የልብህን ፍላጎት ይስጥህ፡ እንደልብህ ይስጥህ፡
ፈቃድህንም ሁሉ ይፈጽምልህ። 5 በማዳንህ ደስ ይለናል



በእግዚአብሔር በአምላካችን ስም ከፍ፡ ከፍ እንላለን። ልመናህን
ሁሉ እግዚአብሔር ይፈጽምልህ። 6 እግዚአብሔር የቀባውን
እንዳዳነው-ዛሬ-ዐወቅሁ።ከሰማይ መቅደሱ ይመልስለታል። በቀኙ
የማዳን-ኃይል-አለ።7 እነዚያ በፈረሶችና በሠረገሎች ይታመናሉ፡
እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ፡ ከፍ እንላለን።
8-እነርሱ፡-ተሰነካክለው ወደቁ፤-እኛ--ግን ተነሣን፤ ፀንተንም
ቆምን።9አቤቱ-ንጉሥን-አድነው፡-በጸሎት-በምንጠራህ-ቀን-ስማን፡

## መዝ-፳-/20፡ የድል-ባለቤት-እግዚአብሔር

1-እግዚአ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ=አቤቱ በኃይልህ ንጉሥ
ደስ ይለዋል፡ በማዳንህም እጅግ ሐሤትን ያደርጋል። 2 የልቡን
ፈቃድ-ሰጠኸው፡-የከንፈሮቹን ልመና አለከለከልኸውም። 3 በበጐ
በረከት ደርሰህለታልና። ከክቡር ዕንቍ የሆነ ዘውድንም-በራሱ-
ላይ-አኖርህ።-4-ሕይወትን-ለመነህ፡ ሰጠኸውም። ለረጅም-ዘመን-
ለዘለዐለሙ።5--በማደንህ--ክብሩ-ታላቅ -ነው፡- ክብርና-ምስጋናን
ጨመርህለት። 6 የዘለዓለም በረከትን ሰጥተኸዋልና፡ በፊትህ-
ደስታ-ደስ- ታሰኘዋለህ።-7-ንጉሥ-በእግዚአብሔር-ተማምኗልና፡-
በልዑል-ምሕረት-አይናወጥም።8-እጅህ-ጠላቶችህን-ሁሉ-ታግኛ
ቸው፡ቀኝህም-የሚጠሉህን-ሁሉ-ታግኛቸው።-9--ፊትህ--በተቈጣ
ጊዜ-እንደ- እሳት-አቶን-አድርጋቸው።10--ፍሬያቸውን-ከምድር፡-
ዘራቸውንም- ከሰው- ልጆች-አጥፋ።11--ክፋትን-በአንተ--ላይ ዘር
ግተዋልና፡-መወሰን -የማቻላቸውን-ምክር-ዐሰቡ ። 12-ወደ ኋላ
ቸው ትመልሳቸዋለህ ፡-ፊታቸውን-ለመዓትህ-ጊዜ ታዘጋጃለህ።
13--ታላቅነትህንና-የኃይልህን-ብርታት-በማመስገን እንዘምራለን፡

## መዝ ፳፩ /21፡ የሐዘንና የመከራ ጊዜ ጸሎት

1 አምላኪየ፡-አምላኬ-ነጽረኒ-ወለምንት-ኀደገኒ?-አምላኬ፡ አምላኬ
ተመልከተኝ፡ ለምንስ ተውኸኝ? የኃጢአቴ ቃል እኔን ከማዳን
የራቀ ነው።2 አምላኬ ሆይ! በቀን ወደ አንተ እጮኻለሁ።
አልሰማኸኝም፡ በሌሊትም በፊትህ አላሰብከኝም። 3-በእስራኤል
የተመሰገንህ-አንተ-ግን- በቅዱሳንህ- አድረህ-ትኖራለህ።4 አባቶቻ
ችን አንተን ተማምነው-ኖሩ፡-ተማመኑብህ አንተም አዳንኃቸው።
5 ወደ አንተ ጮኹ ዳኑም ፡ ባንተም ተማምነው አላፈሩም ።

www.ethiopianorthodox.org

6 እኔ ግን እንደ ትል ነኝ፡ ሰውም አይደለሁም። በሰው ዘንድ
የተናቅሁ በሕዝብም ዘንድ የተዋረድሁ-ነኝ። የሚያዩኝ-ሁሉ-
ይጠቃቀሱብኛል፡ ራሳቸውንም እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ
ይላሉ።8-"በእግዚአብሔር-ታምኗልና -እርሱም -ሊያድነው ከወደ
ደው ያድነው"። 9 አንተ ከሆድ አውጥተኸኛልና ፡ በእናቴ ጡት
ሳለሁም በአንተ ታመንሁ ። 10 ከማሕፀን ጀምሮ በአንተ ላይ
ተጣልሁ፡ከእናቴ ማሕፀን ጀምረህ አንተ-አምላኬ ነህ 11-ለመጨ
ነቅ ተቃርቤአለሁ፡ የሚረዳኝ የለምና ከእኔ አትራቅ፤ 12 ብዙ
በሬዎች ከበቡኝ፡ የሰቡትም ፍሪዳዎች ያዙኝ። 13 ለመንጠቅ
እንደሚያሽምቅ አንበሳ በላዬ አፋቸውን ከፈቱ። 14 እንደ ውሃ
ፈሰስሁ። አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ፡ ልቤ እንደ ሠም ሆኖ
በሆዴ መካከል ቀለጠ። 15 ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ። ምላሴም
በጉሮሮዬ ተጣጋ፡ ወደ ሞትም አፈር አወረድከኝ።

16-ብዙ-ውሾችም-ከበቡኝ፡-የክፉዎች-ማኅበርም -ያዙኝ እጆቼንና
እግሮቼን ቸነከሩኝ ። 17-አጥንቶቼንም ሁሉ ቈጠሩ። እነርሱም
አውቀው ቸል አሉኝ። 18 ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፡
በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ። 19 አንተ ግን አቤቱ ከእኔ
አትራቅ፡ እኔን ለመርዳት ተመልከት። 20 ነፍሴን አድናት፡
ብቸኝነቴንም ከውሾች እጅ። 21 ከአንበሳ አፍ አድነኝ፡
ብቸኝነቴንም-አንድ-ቀንድ-ካለው።21-ስምህን-ለወንድሞቼ እነግራ
ለሁ፡ በጉባዔ መካከል አመሰግንሃለሁ። 23 እግዙአብሔርን
የምትፈሩት አመስግኑት፡ የያዕቆብ ዘር ሁላችሁም አክብሩት፡
የእስራኤል ዘር ሁላችሁም ፍሩት። 24 የድሃውን ልመና
አልናቀምና፡ ቸልም አላለምና። ፊቱንም ከእኔ አልመለሰምና።
እኔ ግን በጮኹህ ጊዜ ሰማኝ። 25 በታላቅ ጉባኤ ክብሬ ከአንተ
ዘንደ ነው ። እርሱንም በሚፈሩት ፊት ስእለቴን እሰጣለሁ ።
26 ችግረኞች ይበላሉ፡ ይጠግባሉም። እግዚአብሔርን የሚሹት
ሁሉ ያመሰግኑታል ። ልባቸው ለዘለዓለም ሕያው ይሆናል።
27 የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስቡ፡ ወደ እግዚአብሔርም
ይመለሱ።የአሕዛብ-ነገዶች-ሁሉ-በፊቱ-ይሰግዳሉ። 28 መንግሥት
ለእግዚአብሔር ነውና እርሱ አሕዛብን ይገዛል። 29 የምድር



ደንዳኖች ሁሉ ይበላሉ፡ ይሰግዳሉ፡ ወደ መሬት የሚወርዱት
ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ፡ ነፍሴ ስለ እርሱ በሕይወት ትኖራለች ።
30- ዘሬም-ሁሉ- ለርሱ- ይገዛለታል። የምትመጣው-ትውልድ-
ለእግዚአብሔር-ትነግራዋለች፡31-የሚወለደው ሕዝብ ልጆቹ
እግዚአብሔር ያደረገውን የጽድቅ ሥራውን ይናገራሉ።

## መዝ ፳፪ /22. <u>የእግዚአብሔር ጠባቂነት</u>

1 እግዚአብሔር ይሬእየኒ ወአልቦ ዘየኀጥአኒ፡ ውስተ ብሔር
ሥዑር ህየ ያኀድረኒ= እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፡ የሚያሳጣ
ኝም የለም። 2 በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፡ በዕርፍት ውሃ
ዘንድ አሳደገኝ። 3 ነፍሴን መለሳት። ስለ ስሙ በጽድቅ መንገድ
መራኝ።4 በሞት ጥላ መካከል ባልፍ እንኳ አንተ ከእኔ ጋር
ነህና-ክፉውን-አልፈራም። በትርህና- ምርኩዝህ -እነርሱ ያጽናኑ
ኛል። 5 በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ። በሚያስቃዩኝ ሰዎች ፊት
ለፊት እራሴን በዘይት ቀባህ።-ጽዋህም-የተትረፈረፈ-ስለሆነ-
ያረካል። 6 በእግዚአብሔር ቤት ለረጅም ዘመን እኖር ዘንድ፡
ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተለኝ።

## መዝ ፳፫ /23፡ <u>የልበ ንጹሕ ሰው ጸሎት</u>

1 ለእግዚአብሔር ምድር በምልኣ=ምድር በመላዋ የእግዚአብ
ሔር ናት፡ ዓለምና በእርሷም የሚኖሩ ሁሉ።2 እርሱ በባሕሮች
መሥርቷታልና፡-በፈሳሾችም አጽንቷታል። 3 ወደ እግዚአብሔር
ተራራ ማን ይወጣል? በተቀደሰ ስፍራውስ ውስጥ ማን
ይቆማል? 4 ልቡ ንጹሕ የሆነ፡ እጆቹም የነጹና ለግል ጥቅሙ
ከንቱን ነገርን (ጉቦን፤) ያልተቀበለ ፡ ለባልጀራውም በሽንገላ
ያልማለ። 5 እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን ይቀበላል፡
ምሕረቱም ከአምላኩ ከእግዚአብሐር ዘንድ ነው ። 6 ይህቺ
ትውልድ-እርሱን-ትሻለች።-የያዕቆብን-አምላክ ፊት ትፈልጋለች ።
7 እናንተ መኳንንት በሮችን ክፈቱ፡ የዘለዓለም ደጆችም
ይከፈቱ፡ የክብር ንጉሥም ይግባ፡ 8 ይህ የክብር ንጉሥ ማን
ነው? ብርቱና ኀያል እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር
በጦርነት ኃያል ነው። 9 እናንተ መኳንንት በሮችን ክፈቱ፡
የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ፡ የክብርም ንጉሥ ይግባ ። 10 ይህ

www.ethiopianorthodox.org

የክብር ንጉሥ ማን ነው? ኃያል የሆነ አምላክ እግዚአብሔር
እርሱ የክብር ንጉሥ ነው ።

## መዝ ፳፬ /24፣ ከአደጋ ተጠብቆ ስለመኖር

1-ኀቤከ አንቃእዶኩ ነፍስየ አምላኪየ=አቤቱ አምላኬ ወደ አንተ
ነፍሴን አነሣለሁ።2 አቤቱ አንተን ታመንሁ፡ ለዘለዓለም
አልፈር፡-ጠላቶቼም-በእኔ-አይሳቁብኝ።3-አንተን ተስፋ የሚያደርጉ
አያፍሩምና፡ በከንቱ የሚበድሉኝ ሁሉ ዘወትር ይፈሩ።-4 አቤቱ
መንገድህን አመልክተኝ፡ ፍለጋህንም አስተምረኝ። 5 በእውነት
ምራኝ፡-አስተምረኝም።-አንተ-አምላኬና መድሃኒቴ ነህና ዘወትር
አንተን-ተስፋ-አድርጌአለሁና።-፩ አቤቱ ቸርነትህን አስብ፡
ምሕረትህ- ለዘለዓለም ነውና።7-የልጅነቴን ኃጢአትና ስንፍናዬን
አታስብብኝ። አቤቱ ስለቸርነትህ ብዛት እንደምሕረትህ አስበኝ።
8 እግዚአብሔር ቸር፡ ጻድቅም ነው።ስለዚህ የሚሳሳቱትን
በመንገዱ ይመራቸዋል። 9--ለየዋሃን ፍርድን ያስተምራቸዋል።
10 ቃል ኪዳኑንና ምስክሩን ለሚፈልጉ የእግዚአብሔር መንገድ
ሁሉ ይቅርታና እውነት ነው። 11 አቤቱ ስለ ስምህ ስትል
ብዙ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ ። 12 እግዚአብሔርን
የሚፈራ ሰው ማነው? እርሱ በሚመርጠው መንገድ
ይመራዋል። 13 ነፍሱ በመልካም ታድራለች፡ ዘሩም ምድርን
ይወርሳል። 14 እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው።
የእግዚአብሔር ስም ለሚጠሩት-ሁሉ ነው።ሕጉንም ያስተምራቸ
ዋል። 15 ዓይኖቼ ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር ናቸው። እርሱ
እግሮቼን ከወጥመድ ያወጣቸዋልና። 16 ፊትህን ወደ እኔ
አድርግ፡ ማረኝም። እኔ ብቸና ድሃ ነኝና። 17 የልቤ ሐዘን ብዙ
ነውና ከጭንቀቴ አውጣኝ ። 18 ድካሜንና መከራዬን እይ፡
ኃጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ። 19 ጠላቶቼ እንደበዙ እይ፡
በግፍም ጥልን ተጣልተውኛል። 20 ነፍሴን ጠብቃት፡
አድናትም። አንተን ታምኛለሁና አልፈር። 21 አቤቱ አንተን-
ተስፋ-አድርጌአለሁና-የዋሃንና-ቅንኖች-ተከትለውኛል።-22 እግዚአ
ብሔር እስራኤልን ከመከራ ሁሉ ያድነዋል።-



## መዝ ፳፭ /25፡ የዋህ የሆነ የትሑት ሰው ጸሎት

1 ፍታሕ ሊተ እግዚኦ እስመ አንሰ በየዋሃትየ አሐውር=አቤቱ
እኔ በየዋህነቴ እኖራለሁና ፍረድልኝ፡ እንዳልደክም በእግዚአብ
ሔር አመንኩ። 2 አቤቱ ፈትነኝ፡ መርምረኝም። ኩላሊቴንና
ልቤን ፈትን። 3 ምሕረትሕ በዓይኔ ፊት ነው። በማዳንህ ደስ
አለኝ። 4 በከንቱ ሸንጎ አልተቀመጥሁም፡ ከዓመፀኞችም ጋር
አልገባሁም። 5 የክፉዎችን ማኅበር ጠላሁ። ከከዳተኞችም ጋር
አልቀመጥሁም። 6-እጆቼን-በንጽሕና-አጥባለሁ፡-አቤቱ መሠዊያ
ህን-እዞራለሁ። 7 የምስጋናህን ቃል እሰማ ዘንድ፡ ተአምራትህ
ንም ሁሉ እነግር ዘንድ።8 አቤቱ የቤትህን ጌጥ፡የክብርህንም
ማደሪያ-ቦታ-ወደድሁ።9-ከኃጢአተኞች-ጋር-ነፍሴን፡ ከደም ሰዎች
ጋር ሕይወቴን አትጣላት። 10 በእጃቸው ተንኮል አለባቸው፡
ቀኝ እጃቸውም መማለጃን (ጉቦን) ተሞልታለች።11-እኔ ግን
በየዋህነቴ እኖራለሁ።አቤቱ-አድነኝ፡ ይቅርም በለኝ።12-እግሮቼ-
በቅንነት-ቆመዋልና-አቤቱ-በማኅበር አመሰግንሃለሁ።

## መዝ ፳፮ /26፣ እግዚአብሔር ከአደጋ አዳኝ ስለመሆኑ

1--እግዚአብሔር-ያበርህ-ሊተ -ወያድኅነኒ፡ ምንትኑ ያፈርሃኒ=
እግዚአብሔር-ያበራልኛል፡-ያድነኛልም።ምን-ያስፈራኛል? እግዚአ
ብሔር-የሕይወቴ-መታመኛዋ-ነውና-ምን-ያስደነግጠኛል?-2 ክፉ
ዎች ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ፡ የሚያስቃዩኝ እነዚያ
ጠላቶቼ-ደከመው-ወደቁ። 3 -ሠሪዊትም-ቢጣላኝ፡-ልቤ አይፈራብ
ኝም፡ ሠራዊትም-ቢከቡኝ፡ በእርሱ-እተማመናለሁ። 4-እግዚአ
አብሔርን-አንዲት-ነገር-ለመንሁት ፡-ያችንም-አሻለሁ፡-ይኸውም
በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ።
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፡ በቤተ መቅደሱ
አገለግል-ዘንድ--እወዳለሁ።-5-በመከራዬ-ቀን-በድንኳኑ ሸሸጎኛልና፡
በድንኳኑም መሸሸጊያ ሰውሮኛልና። በዓለትም ላይ ከፍ፡ ከፍ
አድርጎኛልና። 6 አነሆ አሁን እግዚአብሔር በጠላቶቼ ላይ
ራሴን ከፍ፡ ከፍ አደረገ። ድንኳኑን እየዞርሁ መሥዋዕትን
ሠዋሁ። እልልም እልሁለት፡ እግዚአብሔርን አመስግናለሁ፡
እዘምርለታለሁም። 7 አቤቱ ወደ አንተ የጮኹትን ቃሌን

www.ethiopianorthodox.org

ሰማኝ፡ ማረኝ፡ አድምፀኝም፡፡ 8 ልቤ አንተን አለ፡ ፊትህን ፈለግሁ፡ አቤቱ ፊትህን እሻለሁ፡፡ 9 ፊትህን ከእኔ አትመልስ፡ ተቆጥተህ ከአገልጋይህ ፈቀቅ አትበል፡ ረዳት ሁነኝ፡ አትጣለኝ፡፡ አምላኬና--መድኀኒቴ -ሆይ! -ቸል-አትበለኝ፡፡ 10 -አባቴና እናቴ ጥለውኛልና ፡ እግዚአብሔር ግን ተቀበለኝ ፡፡ 11-አቤቱ መንገድ ህን-አስተምረኝ፡-ስለጠላቶቼ መንገድህን ምራኝ፡፡ 12 ለሚያስጨ ንቁኝ-ፈቃድ-አሳልፈህ አትስጠኝ፡፡ የሐሰት ምስክሮች በዓመፅ ተነሥተውብኛልና፡-ሐሰትም--የዓመፅ-ራስ-ነው፡፡13 የእግዚአብሔ ርን-ቸርነት-በሕያዋን-ምድር-አይ-ዘንድ-አምናለሁ፡፡14 እግዚአብ ሔርን-ተስፋ-አድርግ፡-በርታ፡-ልብህንም-አፅንተህ-እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ ፡፡

**መዝ ፳፯/27፡ የእግዚአብሔርን እርዳታ ስለማግኘት**

1 ኀቤከ እግዚኦ ጸራሕኩ አምላኬየ ወኢትጸመመኒ= አቤቱ አምላኬ ሆይ! ወደአንተ እጮሃለሁ፡ ቸልም አትበለኝ፡፡ ቸል ብትለኝ ግን ወደ ጉድጓድ እንደሚወርዱት እሆናለሁ፡፡ 2 በቤተ መቅደስህ እጆቼን ባነሣሁ ጊዜ ወደ አንተ የጮኹትን የልመናዬን ቃል ሰማ፡፡ 3 ከኀጥአን ጋር-ነፍሴን አትውሰዳት፡ ክፋት በልባቸው እያለ ከባልጀራቸው ጋር ሰላምን ከሚናገሩ ክፉ አድራጊዎች ጋር አትጣለኝ፡፡ 4 እንደ ሥራቸውና እንደ ሐሳባቸው ክፋት የእጃቸውን ስጣቸው፡ እንደ እጃቸውም ሥራ ክፈላቸው፡ ፍርዳቸውን በራሳቸው ላይ መልስ፡፡ 5 የእግዚአብ ሔርን ሥራ፡ የእጆቹንም ተግባር አላሰቡምና፡፡ አፍርሳቸው እንጂ-አትሥራቸው ፡፡-6-የልመናዬን-ቃል-ሰምቶኛልና እግዚአብ ሔር ይመስገን! 7 እግዚአብሔር እረዳቴና መታመኛዬ ነው፡፡ ልቤ በእርሱ ታመነ፡፡ እርሱ ስለሚረዳኝ፡ ሥጋዬ ለመለመ፡፡ በፈቃዴም አምነዋለሁ፡፡ 8 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይላቸው ነውና፡፡ ለመሲሑም የመድኃኒቱ መታመኛ ነው፡፡ 9 ሕዝብህን ኣድን፡ ርስትህንም ባርክ፡ ጠብቃቸውም፡ ለዘለዓለሙም ከፍ፡ ከፍ አድርጋቸው፡፡ ''''''''''''''''''''''''



**መዝ-፳8/28፡ ብርቱ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል /ድምፅ**

1-አምጽኡ-ለእግዙአብሔር ውሉደ አማልክት=የአማልክት ልጆች ሆይ! ለእግዚአብሔር አምጡ፡ የጊደሮችን ጥጃ ለእግዚአብሔር አምጡ፡ ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር ስጡ፡2 የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር ስጡ፡ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ፡፡ 3 የእግዚአብሐር ቃል በውኆች ላይ ነው፡፡ የክብር አምላክ አንጐዳጐደ፡፡ እግዚአብሔር በብዙ ውኆች ላይ ነው፡፡ 4 የእግዚ አብሔር ቃል በኃይል ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል በታላቅ ክብር ነው፡፡ 5 የእግዚአብሔር ቃል ዝግባን ይሰብራል፡፡እግዚአብሔር-የሊባኖስን-ዝግባ ይቀጠቅጣል፡፡ 6-እንደ ሊባኖስ ሳም ያከሳዋል፡፡ ተወዳጅ ግን አንድ ቀንድ እንዳለው ርኤም ልጅ ነው፡፡ 7-የእግዚ አብሔር-ቃል-የእሳቱን-ነበልባል-ይቆርጣል ፡፡ 8 የእግዚአብሔር ቃል ምድረበዳውን-ያናውጣል፡፡ እግዚአብሔር-የቃዴስን-ምድረ-በዳ-ያናውጣል፡፡9-የእግዚአብሔር-ቃል-ዋልያዎችን-ያጠነክራቸ ዋል፡፡ ዛሮችን *(ጫካውን)* ይገልጣል፡፡ ሁሉም በመቅደሱ ምስጋናን ይላል፡፡ 10 እግዚአብሔር የጥፋት ውሃን-ሰብስቦአል፡-እግዚአብሔር-ለዘላለም ይነግሣል፡፡ 11-እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይልን ይሰጣል፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካቸዋል፡፡

**መዝ ፳፱/29፡ በእግዚአብሔር አዳኝነት መተማመን**

1 አአኵተከ እግዚኦ እስመ ተወከፍከኒ=አቤቱ ተቀብለኸኛልና የጠላቶቼም መዘባበቻ አላደረግኸኝምና አመሰግንሃለትሁ ፡፡ 2 አቤቱ አምላኬ ፡ ወደ አንተ ጨኽሁ፡ ይቅርም አልኸኝ፡ 3 አቤቱ ነፍሴን ከሲኦል አወጣሃት፡ ወደ ጕድጓድም ከሚወርዱ ለይተህ አዳንኸኝ፡፡ 4 ጻድቃን ሆይ ! ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡ ለቅድስናውም መታሰቢይ ምስጋና አቅርቡ፡፡ መቅሠፍቱ የሚነሣ ከቍጣው ነውና፡ መዳንም ከፈቃዱ የሚገኝ ነውና፡፡ ማታ ለቅሶ ይሰማል፡ ጥዋት ግን ደስታ ይሆናል፡፡ 6 እኔም በደስታዬ “ለዘለዓለም አልታወክም አልሁ”፡፡ 7 አቤቱ በፈቃድህ ለሕይወቴ ኃይልን ስጣት፡፡ ፊትህን መለስህ፡ እኔም ደነገጥሁ፡፡ አቤቱ ወደ አንተ ጮኽሁ፡ወደ አምላኬም ለመንሁ፡፡ 9 ወደ ሲኦል ብወርድ



www.ethiopianorthodox.org

በደሜ ምን ጥቅም ይገኛል? አፈር ያመሰግንሃልን? ጽድቅህንስ
ይናገራልን?-10--እግዚአብሔር-ሰማ፡-ይቅርም-አለኝ። እግዚአብ
ሔር ረዳቴ ሆነኝ። ክብሬ እንዲዘምርልህና እንዳልደነግጥም
እርዳኝ፡ ለዘለዓለም አመሰግንሃለሁ።
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

## መዝ-፴/30፡ <u>በእግዚአብሔር የመታመን መዝሙር</u>

ክያከ ተወከልኩ እግዚኦ ወኢይትሐፍር ለዓለም=አቤቱ ባአንተ
1_ክያከ ተወከልኩ እግዚኦ ወኢይትሐፍር ለዓለም=አቤቱ ባአንተ
ታምኛለሁና፡-የጠላቶቼም-መዘባበቻ-አላደረከኝምና-አመሰግሃለሁ።
2 አቤቱ-አምላኬ ሆይ! ወደ አንተ ጮኽሁ፡-ይቅርም አልኸኝ። 3
አቤቱ ነፍሴን ከሲኦል አወጣሃት፡ ወደ ጉድጓድም ከሚወርዱት
ለይተህ አዳንኸኝ ። 4 ጻድቃን ሆይ! ለእግዚአብሔር-ዘምሩ።
ለቅድስናው-መታሰቢያ--ምስጋና አቅርቡ።5 መቅሠፍቱ ከቁጣው
የመጣ ነውና። መዳንም ከፈቃዱ ነው። ማታ ለቅሶ ይሰማል፡
ጠዋት ግን ደስታ ይሆናል። 6 እኔም በደስታዬ "ለዘለዓለም
አልታወክም" አልሁ። 7 አቤቱ በፈቃድህ ለሕይወቴ ኃይልን
ስጣት። ፊትህን መለስህ፡ እኔም ደነገጥሁ። 8 አቤቱ ወደ አንተ
ጮኽሁ፡ ወደ አምላኬም ለመንሁ። 9 ወደ ጥፋት ብወርድ
በደሜ ምን ጥቅም ይገኛል? አፈር ያመሰግንሃልን? ጽድቅህንስ
ይናገራልን? 10 እግዚአብሔር ሰማ፡ ይቅርም አለኝ።
እግዚአብሔር ረዳቴ ሆነልኝ። 11 ልቅሶዬን መልስህ ደስ
አሰኘኸኝ። ማቄን ቀደህ፡ ደስታን አስታጠቅኸኝ። 12 ክብሬ
እንዲዘምርልህ-፡--እንዳልደነግጥም- አድርገሃልና ፡-አቤቱ-አምላኬ
ሆይ!-ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።

## መዝ ፴ /30፡ የእግዚአብሔር ፍትሕና ቸርነት

1 ኪያከ ተወከልኩ እግዚኦ ወኢይትሐፈር ለዓለም=አቤቱ
አንተን ታመንሁ፡ ለዘለዓለም አልፈር፡ በጽድቅህም አስጥለኝ፡
አድነኝም። 2 ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፡ ፈጥነህም አድነኝ።
ታድነኝም ዘንድ አምላኬ መድኀኒቴና የመጠጊያዬ ቤት ሁነኝ።
3 ኃይሌና መጠጊያዬ አንተ ነህና ስለ ስምህ ምራኝ፡ መግበኝም።
4 አቤቱ አንተ ረዳቴ ነህና፡ ከሰወሩብኝ ካዚያች ወጥመድ
አውጣኝ። 5 በእጅህ ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፡ የጽድቅ አምላክ



እግዚአብሔር ተቤዠኸኝ። 6 ከንቱን ነገር የሚጠብቀውን ሁሉ
ሁልጊዜ ጠላህ፡ እኔ ግን በእግዚአብሔር ታመንሁ። 7 በትድግ
ናህ ደስ ይለኛል፡ ሐሤትም አደርጋለሁ። መከራዬን አይተሃልና፡
ነፍሴንም ከጭንቀት አድናሃታልና ። 8 በጠላቴ እጅ አልዘጋኸ
ኝም፡ በሰፊም ስፍራ እግሬቼን አቆምህ። 9 ተቸግሬአለሁና
አቤቱ ይቅር በለኝ። ዓይኔም ከቁጣህ የተነሣ ታወከች። ነፍሴም
ሆዴም እንደዚሁ። 10 ሕይወቴ በመከራ አልቋልና፡ ዘመኔም
በጩኸት፡ ኃይሌም በችግር ደከመ፡ አጥንቶቼም ሁሉ ተናወጡ።
11 በጠላቶቼ ሁሉ ዘንድ ተሰደብሁ። ይልቁንም በጐረቤቶቼ
ዘንድ፡ ለዘመዶቼም አስፈሪ ሆንሁ። በሜዳ ያዩኝም ከእኔ ሸሹ።
12 እንደ ሞተ ሰው ከልብ ረሱኝ። እንደጠፋ ዕቃ ሆንኩ።
13 በዙሪያዬ የከበቡኝን ድምፅ ሰምቼአለሁና፡ በላዬ በአንድነት
በተሰበሰቡ ጊዜ፡ ነፍሴንም ለመንጠቅ በተማከሩ ጊዜ። 14 አቤቱ
እኔ-ግን-በአንተ-ታመንሁ፡"አንተ አምላኬ ነህና" አልሁ።15-ርስቴ
በእጅህ ነው፡ ከጠላቶቼ እጅና ከከበቡኝ አድነኝ። 16 ፊትህን
በአገልጋይህ ላይ አብራ፡ ስለምሕረትህም አድናኝ። 17 አቤቱ
አንተን ጠርቼአለሁና አልፈር፡ ሽንጋዮችም ይፈሩ። ወደ
ሲኦልም ይወረዱ። 18 በትዕቢትና በንቀት በጻድቅ ሰው ላይ
ዓመፃን የሚናገሩ የሸንገላ ከንፈሮች ወዮላቸው። 19-አቤቱ እንደ
ቸርነትህ ብዛት የሚፈሩህን ሰወርሃቸው። በሰው ልጆች ፊት
የሚታመኑብህንም አዳንሃቸው። 20 በፊትህም ጥላ ከሰው
ክርክር-ትታዳጋቸዋለህ። በመጋረጃህ ካንደበት ሽንገላ ትሸፍንላቸ
ዋለህ።21 በመከራዬ ጊዜ ምሕረቱን በእኔ ላይ የገለጠ እግዚአ
ብሔር ይመስገን። 22 እኔስ "ከዓይኖችህ ፊት ተጣልሁ" ብዬ
ነበር። ስለዚህ ወደ እርሱ የጮኹትን የልመናዬን ቃል ሰማ።
13 ጻድቃን ሆይ! ሁላችሁም እግዚአብሔርን ውደዱት።
እግዚአብሔር ጽድቅን ይሻልና ። ትዕቢትንም የሚሹትን
ፈጽሞ ይበቀላቸዋል ። 24-በእግዚአብሔር-የምትታመኑ-ሁሉ-
ታገሡ፡-ልባችሁንም አፅኑ፡



www.ethiopianorthodox.org

### መዝ ፴፩ /31፡ በደልን በመናዘዝ የሚቀርብ ጸሎት---

1 ብፁዓን እለ ተኀድገ ሎሙ-ኃጢአቶሙ=ኃጢአታቸው የተተወላቸውና እግዚአብሔር በደላቸውን ሁሉ ያልቆጠረባቸው ሰዎች ብፁዓን ናቸው። 2 እግዚአብሔር በደሉን የማይቆጥር በትና በልቡም ሽንገላ የሌለበት ሰው ብፁዕ ነው። 3 ሁልጊዜ ከመጮሄ የተነሣ ዝም ስል አጥንቶቼ አረጁ፡ 4 በቀንና በሌሊት እጅህ ከብዳብኛለችና እሾህ በወጋኝ ጊዜ ወደ ጉስቁልና ተመለስኩ። 5 ኃጢያቴን ነገርኩህ፡ በደሌንም አልሸሸኩህም፡ "ስለ ኃጢአቴ ወደ እግዚአብሔር እራሴን እከሥሣለሁ" አልሁ። አንተም የልቤን ሽንገላ ተውልኝ። 6 ስለዚህ ጻድቅ ሁሉ በምቹ ጊዜ ወዳንተ ይጸልያል፡ ነገር ግን ብዙ የጥፋት ውሃ ወደ አንተ አይቀርብም። 7 አንተ በዚህ ካገኙችኝ መከራዬ መሸሸጊያዬ ነህ። ከከበቡኝም ታድነኝ ዘንድ ደስታዬ ነህ። 8 "አስተምርሃለሁ፡ በምትሄድባትም በዚያች መንገድ አፀናሃለሁ። ዓይኖቼን በአንተ ላይ አፀናለሁ" ብለሃልና። 9 በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጉሟቸውና ልብ እንደሌላቸው እንደፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ። 10 የኃጥአን መቅሠፍታቸው ብዙ ነው፡ በእግዚአብ ሔር የሚታመኑትን ግን ይቅርታ /ምሕረት ይከባቸዋል ። 11 ጻድቃን ሆይ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፡ ሐሤትም አድርጉ፡ ልባችሁም የቀና ሁላችሁ መመኪያችሁ እርሱ ይሁን።

### መዝ ፴፪/32፡ የእግዚአብሔር ቸርነት

1 ተፈሥሑ ጻድቃን በእግዚአብሔር =ጻድቃን ሆይ! በእግዚአብ ሔር ደስ ይበላችሁ፡ ለቅኖችም ክብር ይገባል።2 እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት፡ ዐሥር አውታርም ባለውም በበገና ዘምሩለት። 3 አዲስ ምስጋናንም አመስግኑት፡ በእልልታም መልካም ዝማሬ ዘምሩለት። 4 የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነውና ሥራውም ሁሉ በእምነት ነውና። 5 እግዚአብሔር ጽድቅንና-ምጽዋት-መስጠትን ይወዳል። የእግዚአብሔር ምሕረት ምድርን ሞላ። 6 በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ፡ ሠራዊታቸ ውም--በአፉ-እስትንፋስ።7 በባሕሩ ውሃ እንደ አቁማዳ የሚሰበስበው፡ በቀላዮችም መዝገቦች የሚየያኖረው እርሱ ነው። 8 ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፈራዋለች። በዓለም የሚኖሩ ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ይደነግጣሉ። 9 እርሱ ተናግሮአልና ሆኑ፡ እርሱ አዘዘ ተፈጠሩም። 10 እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ይመልሳል። የሕዝቡንም ሐሳብ ይመልሳል። የአለቆችንም ምክራቸውን-ያስረሳቸዋል።11-የእግዚአብሔር-ምክር-ግን ለዘላለም ፀንቶ ይኖራል ፡ የልቡም -ሐሳብ ለልጅ ልጅ ነው። 12 እግዚአ ብሔር አምላኩ የሆነለት ሕዝብ ብፁዕ ነው። እርሱ ለርስቱ የመረጠውም ሕዝብ የተባረከ ነው። 13 እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፡ የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ። 14 ከተዘጋጀው የመቅደሱ አዳራሽ ሆኖ በምድር ወደሚኖሩት ሁሉ ተመለከተ። 15 እርሱ ብቻውን ልባቸውን የሠራ፡ ሥራቸውንም ሁሉ የሚያውቅ እርሱ ነው። 16 ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም፡ ኃያል ሰውም በኃይሉ ብዛት አይድንም፡ ፈረስም ከንቱ ነው፡ አያድንም፡ በኃይሉ ብዛት አያመልጥም። 18 እነሆ የእግዚአብ ሔር--ዓይኖች-ወደሚፈሩት-ናቸው። በምሕረቱም ወደሚታመኑ። 19-ነፍሳቸውን-ከሞት-ያድናታል፡-በረኃብም-ጊዜ-ይመግባቸዋል። 20 ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ ታደርገዋለች፡ ረዳታችንና መጠጊያችን እርሱ ነውና። 21 ልባችንም በእርሱ ደስ ይለዋልና፡ በቅዱስ ስሙም ታምነናል። 22 አቤቱ በአንተ እንደታመንን ምሕረትህ በእኛ ላይ ትሁን !

### መዝ ፴፫ /33፡ ስለፍትሕና አምላካዊ ቸርነት መማፀኛ

1. እባርኮ ለእግዚአብሔር በኵሉ ጊዜ=እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አመሰግነዋለሁ።ምስጋናውም ሁሉ ከአፌ አይለይም። 2 ነፍሴም በእግዚአብሔር ትከብራለች፤ ደጋግ ሰዎችም ሰምተው ደስ ይበላቸው። 3 እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ከፍ፡ ከፍ አድርጉት፡ በአንድነትም ስሙን ከፍ፡ ከፍ እናድርግ። 4 እግዚአብሔርን ፈለግሁት፡ መለሰልኝም። ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ። 5 ወደ እርሱ ቅረቡ ፡ እርሱም ያበራላችሁልና ፊታችሁ አያፍርም ። 6 ይህ ችግረኛ ጮኸ፡ እግዚአብሔርም ሰማው፡ ከመከራውም ሁሉ አዳነው። 7 የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች



www.ethiopianorthodox.org

ዙሪያ-ይሠፍራል፡-ያድናቸውማል፡፡8 እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ
ቀምሳችሁ ዕወቁ ፡ በእርሱም የሚታመን ሰው ብፁዕ ነው፡፡
9-እግዚአብሔርን የሚፈሩት ችግር የለባቸውምና፡ ቅዱሳን ሁሉ
እግዚአብሔርን ፍሩት፡፡ 10 ባለጠጎች ደኸዩ፡ ተራቡም
እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሰዎች ግን ከመልካም ነገር ሁሉ
ተቸግረው አያውቁም፡፡ 11 እግዚአብሔርን መፍራት ምን
እንደሆነ አስተምራችሁ ዘንድ ልጆቼ ኑ፡ ስሙኝ፡፡12 ሕይወትን
የሚወድ ሰው ማን ነው? በጐ ዘመንንም ለማየት የሚወድድ
ማን ነው? 13 አንደበትህን ከክፉ ከልክል፡ ከንፈሮችህም
ሽንገላን እንዳይናገሩ አድርግ፡፡ ከክፉ ሽሽ፡ መልካምንም አድርግ፡
ሰላምን ሻት፡ ተከተላትም፡፡ 15 የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ
ጻድቃኑ፡ ጆሮዎቹም ወደ ልመናቸው ናቸውና፡፡16--መታሰቢያቸ
ውን-ከምድር-ያጠፋ-ዘንድ የእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሚያደርጉ
ሰዎች ላይ ነው፡፡ 17-ጻድቃን ጮኹ፡ እግዚአብሔርም ሰማቸው፡
ከመከራቸውም ሁሉ አዳናቸው፡፡ 18 እግዚአብሔር በልባቸው
የዋሃን ለሆኑ ሁሉ ቅርብ ነው፡፡ በመንፈስ ትሑታን
የሆኑትንም ያድናቸዋል፡፡ 19 የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፡
እግዚአብሔር ግን አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል፡ ከእነርሱም
አንድ እንኳ አይሰበርም፡፡ 21 የኃጥእ ሞት ክፉ ነው *(ዓፀር-
ይበዛበታል)*፡፡ ጽድቅን የሚጠሉ ይጸጸታሉ፡፡ የአገልጋዮቹን ነፍስ
እግዚአብሔር-ይታደጋል፡-በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ አይጸጸቱም፡፡

## መዝ ፴፬ /34፥ የግፈኞች ጭቆና የሚገታበት ጸሎት

1 ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ፡ አቤቱ የሚገፉኝን
ግፋቸው፡ የሚጣሉኝንም አንተ ተዋጋቸው፡፡ 2 ጋሻና ጦር ይዘህ
እኔን ለመርዳት ተነሥ፡፡ ሰይፍህን ምዘዝ፡ የሚከቡኝንም
ክበባቸው፡፡ ነፍሴንም "እረዳትሽ እኔ ነኝ" በላት፡፡ 4 ነፍሴንም
የሚሿት ሁሉ ይጐስቊሉ፡፡ ክፋትን በእኔ ላይ የሚመክሩ
ይፋሩ፡ ወደ ኋላቸውም ይመለሱ፡፡ 5 በነፋስ ፊት እንደሚበተን
ትቢያ ይሁኑ ፡ የእግዚአብሔርም መልአክ ያስጨንቃቸው፡
6 መንገዳቸው ድጥና ጨለማ ትሁን፡ የእግዚአብሔር መልአክ
ያሳድዳቸው፡፡ 7 በከንቱ ያጠፉኝ ዘንድ ወጥመዳቸውን በስውር



ዘርግተውብኛልና ነፍሴን በከንቱ አበሳጭተዋታል፡፡ 8 ያላወቋት
ወጥመድ ትምጣባቸው፡ በስውር የዘረጓት ወጥመድ ትያዛቸው፡
በዚህችም ወጥመድ ይውደቁ፡፡ 9 ነፍሴ ግን በእግዚአብሔር ደስ
ይላታል፡ በማዳኑም ሐሤት ታደርጋለች፡፡ 10 አጥንቶቼ ሁሉ
እንዲህ ይሉሃል፡-"አቤቱ እንዳንተ ማነው? ድሃውን ከሚቀማው
እጅ፡ ችግረኛውንም ከሚነጥቀው እጅ ታድነዋለህና"፡፡11-የሐሰት
ምስክሮች ተነሡብኝ፡ የማላውቀውንም ሁሉ ተናገሩ፡፡ 12 ስለ
በጐ ነገር ፈንታ ክፉ መለሱልኝ፡ ለሰውነቴም ልጆችን አሳጡአት
*(ልጆች አልባ አደረጓት)*፡፡ 13 እኔስ ባሠቃዩኝ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፡
ነፍሴንም በጾም አደከምኋት ፡ ጸሎቴም ወደ ብብቴ ተመለሰ፡፡
13-ለወዳጆቼና-ለወንድሞቼ-እንደማደርገው-አደረግሁ፡ 14 ለወን
ድሞቹ እንደሚታለቅስና እንደሚተክዝ ራሴን ዝቅ፡ ዝቅ
አደረግሁ፡፡ 15 በእኔ ላይ ተሰበሰቡ፡ ደስም አላቸው. ሲገርፉኝም
ተማከሩ ፡ እኔ ግን ይህን ሁሉ አላወቅሁም፡፡ ተሰበሩ፡ ግን
አልደነገጡም፡፡16 ፈተኑኝ፡ በእኔ ላይም በመዘባበት ሣቁብኝ ፡፡
ጥርሳቸውንም በእኔ ላይ አፋጩ ፡፡ 17 አቤቱ የምትፈርድልኝ
እስከ መቼ ነው? ነፍሴን ከክፉ ሥራቸው፡ ብቸኝነቴንም
ከአንበሶች አድናት፡፡ 18 አቤቱ በታላቅ ጉባኤ መሐል
አገዛልሃለሁ፡ በብዙ ሕዝብ ጉባኤ መሐልም አመሰግንሃለሁ፡፡
19--በግፍ-የሚጠሉኝ፡-በከንቱ-የሚጠሉኝና-በዓይናቸውም የሚጠ
ቃቀሱብኝ ሁሉ በእኔ ላይ ደስ አይበላቸው፡፡ 20 እኔን በሰላም-
እያነጋገሩኝ፡-በግርፋት-ያጠፉኝ-ዘንድ-ይመክራሉ፡፡21-አፋቸውንም
በእኔ ላይ አላቀቁ፡ እሰይ፡ እሰይ1 በዓይናችን አየነው ይባባላሉ፡፡
22 አቤቱ አንተ እይ፡ ዝምም አትበል፡ አቤቱ ከእኔ አትራቅ፡፡
23 ተነሥ፡ ፍርዴንም አድምጥ፡አምላኬ፡ ጌታዬም ስለ እኔ
ለመከራከር-ተነሥ፡፡ 24 አቤቱ አምላኬ እንደ ጽድቅህ ፍረድልኝ፡
ጠላቶቼም በእኔ ላይ ደስ አይበላቸው፡፡ 25 በልባቸውም
በሰውነቴ ላይ "እሰይ፡ እሰይ! ዋጥነው" አይበሉ፡፡ 26 በመከራዬ
ደስ የሚላቸው ሁሉ ይፈሩ፡ በአንድነትም ይጐስቊሉ፡ በእኔ ላይ
የሚታበዩ እፍረትንና ጐስቊልናን ይልበሱ፡፡ 27 ጽድቄን
የሚወዷት ግን ደስ ይበላቸው፡ ሐሤትም ያድርጉ፡፡ ዘወትርም



www.ethiopianorthodox.org

"የአገልጋዩን ሰላም የሚወድ እግዚአብሔር ታላቅ-ይሁን"-ይበሉ።
-28-አንደበቴ-ሁልጊዜ-ጽድቅህንና ምስጋናህን ይናገራል።

## መዝ ፴፭/35፡ የኃጥአን ክፋት፡የእግዚአብሔር-ቸርነት

1 ይነብብ ኃጥእ በዘያስሕት ርእሶ=ኃጢአተኛ ሰው ራሱን
የሚያስትበትን ነገር ይናገራል። የእግዚአብሔርም ፍርሃት
በዓይኖቹ ፊት የለም። 2 በአንደበቱ ሽንግሎአልና፡ ኃጢአቱ
ባገኘችው ጊዜ ይጠላታል። 3 የአፉ ቃል ዓመፅና ሽነንገላ ናት።
በጐ ሥራን ይሠራ ዘንድ ማስተዋልን አልወደደም። 4 በመኝ
ታው ዓመፅን እሰበ፡ በሁሉ ነገር መልካም ባልሆነች መንገድ
ቆሞአል፡ ክፉትንም አይሰለቻትም። 5 አቤቱ ምሕረትህ በሰማይ
ነው፡ እውነትህም እስከ ደመናት ትደርሳለች። 6 ጽድቅህም
እንደ እግዚአብሔር ተራሮች ናት፡ ፍርድህ እጅግ ጥልቅ ናት።

_7 አቤቱ ሰውንና እንስሳን ታድናለህ ።አቤቱ ምሕረትህን እንደ
አበዛህ የሰው ልጆች በክንፎችህ ጥላ ይታመናሉ። 8 ከቤትህ
ጠል ይረካሉ። ከደስታህም ፈሳሽ ታጠጣቸዋለህ ። 9 የሕይወት
ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን ።
10 ምሕረትህን በሚያወቁህ ላይ፡ ጽድቅህንም በልበ ቅኖች ላይ
ዘርጋ 11 የትዕቢት እግር አይምጣብኝ፡ የኃጢአተኛም እጅ
አያውከኝ። 12 ዓመፃን የሚያደርጉ ሁሉ በዚያ ይወድቃሉ።
ይሰደዳሉ፡ መቆምመም አይችሉም።

## መዝ ፴፮/36፡ የጻድቅ ሰው ዕጣ ፈንታና የክፉ ሰው መጨረሻ

1 ኢትቅናእ ላዕለ እኩያን=በክፉዎች ላይ አትቅና ዓመፃንም
በሚያደርጉ ላይ አትቅና 2 እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና
እንደለመለመ ቅጠልም ፈጥነው ይረግፋሉ። 3 በእግዚአብሔር
ታመን፡ መልካምንም አድርግ፡ በምድር ላይም ያሳድርሃል፡
በሀብትዋም ያሠመራሃል። 4 በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፡
የልብህንም መሻት ይሰጥሃል። 5 መንገድህን ለእግዚአብሔር
ግለጥ፡ በእርሱም ታመን፡ እርሱም የምትወደውን ያደርግልሃል።
6 ጽድቅህን እንደ በርሃን ፍርድህንም እንደ ቀትር ያመጣታል ፡
7 ለእግዚአብሔር ተገዛ፡ አገልግለውም። በሕይወቱ ደስ ባለውና
ዓመፃን በሚያደርግ ሰው ላይ አትቅና። 8 መዓትን ተዋት፡
ቁጣንም ጣላት፡ እንዳትበድልም አትቅና። 9 ክፉ አድራጊዎች
ይጠፋሉና፡ እግዚአብሑርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን እነርሱ
ምድርን ይወርሳሉ። 10 ኃጢአተኛም ገና ጥቂት እንኳ
አይኖርም፡ ትፈልገዋለህ፡ ቦታውንም አታገኝም።11 የዋሆች ግን
ምድርን ይወርሳሉ፡ በብዙም ሰላም ደስ ይላቸዋል። 12 ኃጢአ
ተኛ ጻድቁን ይመለከተዋል፡ ጥርሱንም በእርሱ ላይ ያፋጫል።
13 እግዚአብሔር ግን ይሥቅበታል፡ የጥፋቱ ቀን እንደሚደርስ
አስቀድሞ አውቋልና። 14 ኃጥአን ድሃውንና ችግረኛውን ሰው
ይገድሉ ዘንድ ሰይፋቸውን መዘዙ ፡ ቀስታቸውንም ገተሩ።
15 ሰይፋቸው ወደ ልባቸው ይገባ፡ ቀስታቸውም ይሰበር።
16 በእውነት የሚገኝ ጥቂቱ ከብዙ የኃጥኣን ሀብት ይበልጣል።
17 የኃጥአን ኃይላቸው ይሰበራልና፡ እግዚአብሔር ጻድቃንን
ይደግፋቸዋል። 18 የንጹሓንን መንገድ እግዚአብሔር ያውቃል።
ርስታቸውም ለዘለዓለም ነው። 19 በክፉ ዘመንም አያፍሩም
በራብ ዘመንም ይጠግባሉ። 20 ኃጥአን ግን ይጠፋሉ፡
የእግዝያብሔር ጠላቶች በከበሩና ከፍ ፡ከፍ ባሉ ጊዜ እንደ ጢስ
ፈጥነው ይጠፋሉ። 21 ኃቲአተኛ ይበደራል፡ አይከፈልም፡ ጻድቅ
ግን ይራራል፡ ይሰጣልም። 22 እርሱን የሚባርኩት ምድርን
ይወርሳሉና። የሚረግሙት ግን ይጠፋሉ። 23 የሰው አካሔዱ
ከእግዚአብሔር ዘንድ ይፀናል፡ መንገዱንም እጅግ ይወድለታል።
24 ቢወድቅም አይደነግጥም፡ እግዚአበሔር እጁን ይዞ
ይደግፈዋልና። 25 ጐለመስሁ፡ አረጀሁም። ጻድቅ ግን ሲጠፋ
አላየሁም፡ ዘሩም እህልን አጥቶ አይቸገርም። 26 ሁልገዜ
ይራራል፡ ያበድራልም ዘሩም በበረከት ይኖራል ። 27 ከክፉ
መልካምንም አድርግ፡ ለዘለአለምም ትኖራለህ። 28--እግዚአብ
ሔር ጽድቅን ይወድዳልና ጻድቃኑንም አይጥላቸውምና፡
ለዘለአለመምም ይጠብቃቸዋል፡ ለንጹሐንም ይበቀልላቸዋል፡
የኀጥአንን ዘር ግን ያጠፋል። 29 ጻድቃን ምድርን-ይወርሳሉ፡
በእርስዋም ለዘለዓለም ይኖራል። 30 የጻድቅአፈ-ጥበብን-
ይማራል፡-አንደበቱ-ጽድቅን ይናገራል። 31 የአምላኩ-ሕግ በልቡ


www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ ነው፡ ሰኮናውም አይሰናከልም።32 ኃጢአተኛ ጻድቁን-
ይመለከተዋል፡-ሊገድለውም-ይወድዳል።-33 እግዜአብሐር ግን
አይተወውም *(በእጁ አሳልፎ አይሰጠውም)።* በተፋረደውም ጊዜ
አያሸንፈውም።-34 እግዚአብሔር ደጅ ጥናው፡ መንገዱንም
ጠብቅ፡ ምድርን ትወርስ ዘንድ ከፍ ፡ከፍ ያደርግሀል፡ ኃጥአንም
ሲጠፉ ታያለህ። 35 ኃጢአተኛን ከፍ፡ከፍ ብሎ እንደ ሊባኖስ
ዛፍም ረዝሞ አየሁት። 36 ብመለስ ግን አጣሁት፡ ፈለግሁት
ቦታውንም *( ዱካውን )* አላገኘሁትም ። 37 ቅንነትን ጠብቅ፡
ጽድቅንም እይ፡ ለሰላም ሰው ቅሬት *(ቀሪ ዘር)* አለውና።
ዐመፀኞች ግን በአንድነት ይጠፋሉ፡ የኀጥአንም ቅሬቶች
ይጠፋሉ። 39 የጻድቃን መድኃኒታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ-
ነው።በመከራቸው-ጊዜ ጠባቂያቸው እርሱ ነውና።40 እግዚአብ
ሔር ይረዳቸዋል፡ ያድናቸዋልም፡ ከኃጥአን እጅ ያወጣቸዋል፡
በእርሱም ታምነዋልና ያድናቸዋል ።

መዝ ፴፯ /37፡ <u>ባስጨናቂ ጊዜ የሚቀርብ ጸሎት</u>

1-እግዚኦ-በመዓትከ-ኢትቅሥፈኒ=-አቤቱ-በመዓተትህ አትቅሠ
ፈኝ -በመቅሰፈትህ አትገሥፀኝ ። 2 ፍላጾችህ ወግተውኛልና
እጅህንም-በእኔ-ላይ-አክብደህብኛልና።3 ከቁጣህ ፊት የተነሣ
ለሥጋዬ ድኅነት የለውም፡ ከኃጢአቴም ፊት የተነሣ ለአጥንቶቼ
ሰላም የላችውም ።4 ኃጢአቴ ከራሴ ጠጉር በዝቷልና እንደ
ከባድ ሸክምም በላዬ ከብዶአልና 5 ከስንፍናዬም ፊት የተነሣ
አጥንቶቼ ሸተቱ፡ በሰበሱም። 6 እጅግ ጎሰቈልሁ፡ጎበጥሁም-
ሁልጊዜም-በትካዜ-እመላለሳለው። 7 ነፍሴ ስድብን ጠግባለችና
ለሥጋዬም ድኅነትን አጣሁ ። 8-ታመምሁ፡ እጅግም ተሰቃየሁ፡
ከልቤም ኀዘን የተነሣ እጮኻለሁ። 9 አቤቱ ፈቃዴ-ሁሉ
በፊትህ--ነው፡ ጩኸቴ ከአንተ አይሰወርም።10-ልቤ ደነገጠብኝ
ኃይሌም ተወኝ፡ የአይኖቼም ብርሃን ፈዘዘብኝ። 11 ወዳጆቼና
ባልንጀሮቼም ባላጋራ ሆኑኝ፡ ከበውም ደበደቡኝ፡ ዘመዶቼም
ተስፋ ቈርጠው ተለዩኝ።12 ነፍሴንም የሚሿት በረቱብኝ፡
መከራዩንም የሚፈልጉ ከንቱን ተናገሩ፡ ሁልጊዜም ያጠፉኝ
ዘንድ በሽንገላ ይመክራሉ። 13 እኔ ግን እንደማይሰማ ደንቆሮ፡



አፉንም እንደማይከፍት ዲዳ ሆንሁ።14 እንደማይሰማ ሰው፡
በአፋም መናገር እንደማይችል ሰው ሆንሁ። 15 አቤቱ
አምላኬ አንተ ስማኝ ።16 "የጠላቶቼ መዘባበቻ አታድርገኝ"
ብያለሁና እግሬም ቢሰናከል በእኔ ላይ ብዙ ነገርን ይናገራሉ።
17 እኔንስ ይገርፉኝ ዘንድ አቁዩኝ፡ ቁስሌ ሁል ጊዜ በፊቴ
ነውና።18 በደሌን እናገራለሁና ስለ ኃጢአቴም እተክዛለሁ።
19 ጠላቶቼ ሕያዋን ናቸው፡ ይበረቱብኛልም፡ በዓመፃ የሚጠ
ሉኝ በዙ ናቸው።20 በበጎ ፋንታ ክፉን የሚመልሱልኝ ጽድቅን
ስለ ተከተልሁ-ይከሰሱኛ። እንደ ርኵስ በድን ወንድማቸውን
ጣሉ። 21 አቤቱ አንተ አትጣለኝ፡ አምላኬ ከእኔ አትራቅ።22
አቤቱ የመድኀኒቴ አምላክ ሆይ እኔንለ መርዳት ፍጠን።

መዝ ፴8 /38፡ <u>የጭንቀት ጊዜ</u> ጸሎት -------

1 እቤ አዐቅብ አፉየ ከመ ኢይስሐት በልሳን=="በአንደበቴ
እንዳልስት አፌን እጠብቃለሁ፡ ኃጥኣን በፊቴ በተቃወመኝ ጊዜ
በአፌ ላይ ጠባቂ አኖራለሁ" አልሁ። 2 ዝም አልሁ፡ ራሴንም
አዋረደሁ፡ ለበጐ ነገርም እንኳ ዝም አልሁ፡ቁስሌም ታደሰብኝ።
3 ልቤ በውስጤ ተቃጠለ፡ ከመናገሬም የተነሣ እሳት ነደደ፡
በአንደበቴም ተናገርሁ፡ 4 አቤቱ "ፍጻሜዩን አስታውቀኝ"
አልሁ። የዘመኔ ቁጥሮች ምን ያህል ናቸው? ዐውቅ ዘንድስ
ለምን ወደ ኋላ እላለሁ? 5 እንሆ ዘመኖቼን አስረጀሃቸው።
አካሌም በፊትህ እንደ ኢምንት ነው። ነገር ግን የሰው ልጅ
ሁሉ ከንቱ ነው። 6 ሰው ሁሉ እንደ ጥላ ይመስላል፡ ነገር ግን
በከንቱ ይታወካሉ።ያከማቻሉ የሚሰበስብትም ለማን እንደሚሆን
አያውቁም። 7 አሁንስ ተስፋዩ ማን ነው? እግዚአብሔር
አይደለምን? ትዕግሥቴም ከአንተ ዘንድ ነው።8 ከኃጢአቴ ሁሉ
አዳንኸኝ፡-ለሰነፎች ስድብ አደረግኸኝ። 9 ዝም አልሁ፡ አፌንም
አልከፈትሁም ።አንተ ፈጥረኸኛልና። 10 መቅሠፍትህን ከእኔ
አርቅ፡-ከእጅህ-ብርታት-የተነሣ አልቋለሁና።11-በተግሣፅህ- ስለ
ኃጢአቱ ሰውን ዘለፍኸው፡ ሰውነቱንም እንደ ሸረሪት
አቀለጥኻት። ነገር ግን ሰዎች ሁሉ በከንቱ የታወካሉ።12 አቤቱ
ጸሎቴን ስማ፡ ልመናዩንና ለቅሲዩን አድምጥ፡ ቸልም አትበለኝ።



www.ethiopianorthodox.org

እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና እንደ አባቶችም ሁሉ እንግዳ
ነኝና13 ወደማልመለስበት ሳልሔድ ዕርፍ ዘንድ ተወኝ፡

## መዝ ፴፱/39፡ <u>እግዚአብሔርን ደጅ መጥናት</u>

1 እግዚአብሔር በትዕግሥት ደጅ ጠናሁት፡ እርሱም ተመልሶ
ሰማኝ፡ የልመናዬንም ቃል ሰማኝ።2 ከጥፋት ጉድጓድ ከረግረግ
ጭቃም አወጣኝ፡ እግሮቼንም በዓለት ላይ አቆመማቸው፡
አረማመዴንም አፀና። 3 አዲስ ምስጋናን በአፌ ጨመረ፡ ይህም
የአምላካችን ምስጋናው ነው፡ ብዙዎች አይተው ይፍሩ፡
በእግዚአብሔርም ይታመኑ። 4 መታመኛው የእግዚአብሔር
ስም የሆነና፡ ወደ ከንቱ ነገር ወደ ቁጣና ወደ ሐሰትም
ያልተመለከተ ሰው በፁዕ ነው። 5 አቤቱ አምላኬ ብዙ
ታምራትህን አደረግህ፡ አሳብህንም ምንም የሚመስለው የለም፡
አወራሁ፡ ተናገርሁ፡ ከቁጥርም በዛ። 6 መሥዋዕትንና ቁርባንን
አልወደድሁም፡ ሥጋህን አንጻልኝ፡ የሚቃጠለውንና ስለ
ኃጢአት-የሚቀርበውንም-መሥዋዕት-አልፈለግሁትም።7 በዚያን
ጊዜ አልሁ ‹‹እንሆ መጣሁ፡ ስለ እኔ በመጽሐፍ ራስ ተጽፎ
አል"። 8 አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ መከርሁ፡ ሕግህም
በልቤ ውስጥ ነው። 9 በታላቅ ጉባኤ ጽድቅህን አወራሁ፡ እንሆ
ከንፈሮችን አልከለክልም፡ አቤቱ አንተ ጽድቁን ታውቃለህና።
10 ቅንነትህን በልቤ ውስጥ አልሰወርሁም፡ ማዳንህንም
ተናገርሁ፡ ይቅርታህንና ምሕረትህን ከታላቅ ጉባኤ አልሰወር
ሁም። 11 አቤቱ አንተ ይቅርታህን ከእኔ አታርቅ፡ ቸርነትህና
እውነትህ ዘወትር ያግኙኝ።12 ቁጥር የሌላት ክፋት
አግኝታኛለችና፡ ኃጢአቶቼ ተገናኙኝ፡ ማየትም ተስኖኛል፡
የሠራሁት በደል ከራሴ-ጠጉር-ይልቅ በዛ፡ ልቤም-ተወኝ *(ከዳኝ)*፡
13 አቤቱ ታድነኝ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን። አቤቱ እኔን
ለመርዳት ተመልከት። 14 ነፍሴን ለማጥፋት የሚወድዱ
ይፈሩ፡ በአንድነትም ይጐስቁሉ። በእኔ ላይ ክፋትን ለማድረግ
የሚወድዱ ወደ ኋላቸው ይመለሱ፡ ይፈሩም።15 እሰይ፡ እሰይ
የሚሉኝ፡-እፍረታቸውን-ወዲያውኑ ይቀበሉ። 16 አቤቱ የሚፈል



ጉህ ሁሉ በአንተ ደስ ይበላቸው፡ ሐሤትንም ያደርጉ፡ ሁልጊዜ
ማዳንኅን የሚወዱ ዘወትር እግዚአብሔር ታላቅ ነው" ይበሉ።
17 እኔ ምስኪን /ድሃ ነኝ፡ እግዚአብሔር ግን ያስብልኛል፡ አንተ
ረዳቴና መድኃኒቴ ነህ፡አሁንም አምላኬ ሆይ አትዘግይ።

## መዝ ፵/40፡ <u>ከዝማሬ ጋር የሚቀርብ ጸሎትና ምስጋና</u>

1-ብፁዕ-ዘይሌቡ-ላዕለ-ነዳይ-ወምስኪን=ለድሃና-ለምስኪን የሚያ
ስብ ሰው ብፁዕ ነው፡ እግዚአብሐር ከክፉ ቀን ያድነዋል ።2
እግዚአብሐር ይጠብቀዋል፡ ሕያውም ያድርገዋል፡ በምድርም
ላይ ያስመሰግነዋል፡ በጠላቶቹ እጅ አሳልፎ-አየሰጠውም። 3 በደ
ዌው አልጋ ላይ ሳለ እግዚአብሔር ይረዳዋል፡ መኝታውንም
ምቹ ያደርግለታል። 4 እኔስ ‹‹አቤቱ ይቅር በለኝ፡ አንተን
በድያለሁና ለነፍሴ አስተስርይላት››አልሁ። 5 ጠላቶቼም በእኔ
ላይ ክፋትን ይናገራሉ ‹‹መቼ ይሞታል? ስሙስ መቼ ይሻር
ይሆን?›› ይላሉ። 6 ከንቱን የሚናገር ሁሉ ይግባና ይይ፡ ልቡ
በላዩ ላይ ኃጢአትን ሰበሰበ፡ ወደ ሜዳ ይወጣል፡ ይናገራልም፡
በእኔም ላይ ይተባበራል።7 ጠላቶቼ ሁሉ ይጠቃቀሱብኛል፡ በእኔ
ላይም ክፋትን ይመከራሉ። 8 የበደልን ነገር በእኔ አወጡ።
የተኛ ሰው ከእንግዲህ ወዲያ አይነሳምን ? ደግሞ የሰላሜ ሰው
የታመንሁበት እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን *(ሠኮናውን )*
አነሣ። 10 አንተ ግን አቤቱ ይቅር በለኝ፡ እመልስላቸውም
ዘንድ አስነሣኝ።11 ስለዚህ እንደ ወደድኸኝ አወቅሁ፡ ፡ ጠላቶቼ
በእኔ ደስ አላላቸውም ።12 እኔን ግን ስለ የዋህነቴ ተቀበልኸኝ፡
በፊትህም ለዘለዓለም አፀናኸኝ */አበረታኸኝ* ፡13 የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም
ይሁን፡ ይሁን ( ለይኩን፡ ለይኩን ) ።

## መዝ ፵፩ /41፡ <u>የአምላክን ፍቅር የተጠማች ነፍስ</u>

1 ከመ ያፈቅር ኅየል ኀበ አንቅዕተ ማያት ከማሁ ታፈቅር
ነፍስየ ኀበ እግዚአብሔር=ዋሊያ ወደ ውኃ ምንጮች
እንደሚናፍቅ፡ እንዲሁ ነፍሴ ወደ እግዚአብሔር ትናፍቃለች።
2 ነፍሴ ወደ ሕያው አምላኬ ተጠማች፡ መቼ ተነሥቼ ፡ መቼ
እደርሳለሁ? የአምላኬንስ ፊት መቼ አያለሁ? 3 ዘወትር

www.ethiopianorthodox.org

‹‹አምላክህ ወዴት ነው ?' ያሉኛልና እንባዩ በቀንና በሌሊት
ምግብ ሆነኝ። 4 ይህን ሳስብ ነፍሴ በእኔ ውስጥ ፈሰሰች፡ ወደ
እግዚአብሔር ቤት ወደ ምስጋናው መደሪያ ስፍራ እገባለሁና
በዓልን የሚያደርጉ ሰዎች በምስጋናና በደስታ ቃል ሲያመሰግኑ
ይሰማሉ።5 ነፍሴ ሆይ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ?
የፊቴን-መድኀኒት-አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔርታ
ታመኚ ።6 ነፍሴ በእኔ ውስጥ ትታወካለች። ስለዚህ አቤቱ
በዩርዳኖስ-ምድር።-በአርሞንኤምም-በታናሹ ተራራ- አስብሃለሁ፡
7-በፏፏቴህ ድምፅ ቀላይ-ቀላይን ትጠራዋለች፡-ማዕበልህና-
ሞገድህ ሁሉ በላዩ አለፈ። 8 እግዚአብሔር በቀን ይቅርታውን
ያዝዛል፡ በለሊትም እርሱን ይናገራል። ከእኔ ዘንድ የሕይወቴ
ብፅዓት ለእግዚአብሔር ነው።9 እግዚአብሔርን አልሁት-‹‹አንተ
አምላኬ-ነህ፡ ለምን-ተውኸኝ? ለምንስ አዝኜ እመለሳለሁ?
ጠላቶቼ-ሁሉ-አጥንቶቼን እየቀለጣጠሙ-ሰደቡኝ።10 ሁልጊዜ
‹‹አምላክህ ወዴት ነው?" ይሉኛልና።11 ነፍሴ ሆይ! ለምን
ታዝኛለሽ ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኀኒት አምላኬን
አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሐሔር ታመኚ።

## መዝ ፵፪/42፡ <u>የብቸኛ ሰው ጸሎት በስደት ጊዜ</u>

1 ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ=አቤቱ-ፍረድልኝ፡
ከጽድቅ ከወጡ ሕዝብም በቀሌን ተበቀል። ከአመፀኛና ከሽንጋይ
ሰው አድነኝ። 2 አንተ አምላኬ ኃይሌም ነህና ለምን
ትተወኛለህ? ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመለሳለሁ?
3 ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክ፡ እነርሱም ይምሩኝ። አቤቱ ወደ
መቅደስህ ተራራና ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ። 4 ወደ
እግዚአብሔር መሠዊያ፡ ጉልማስነቴንም ደስ ወዳሰኛት ወደ
አምላኬ እገባለሁ፡ አቤቱ አምላኬ በመሰንቆ አመሰግንሃለሁ።
5 ነፍሴ ሆይ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን
መድኀኒት አምላኬን አመሰግነው-ዘንድ-በእግዚአብሔር-ታመኚ ።

## መዝ-፵፫/43፡ የእግዚአብሔር-ረድኤት-ሲርቅ-የሰቆቃ ብዛት

1-እግዚኦ-ሰማዕነ በዕዘኒነ፡ ወአበዊነሂ ዜነውነ= አቤቱ በጆሮአችን
ሰማን አባቶቻችን በዘመናቸው በቀድሞ ዘመን የሠራኸውን



ሥራ ነገሩን። 2 እጅህ ጠላትን አጠፋች፡ እነርሱንም ተከልህ፡
አሕዛብን-አሠቃየኻቸው፡-አሳደድኻቸውም።3-በጦራቸው-ምድርን-
አልወረሱም፡-ክንዳቸውም-አላዳናቸውም።-ቀኝህና-ክንድህ የፊት
ህም ብርሃን ነው እንጂ። ይቅር ብለሃቸዋል።- 4 አምላኬና
ንጉሤ አንተ ነህ ለያዕቆብ መድኀኒትን ያዘዝህ።5 በአንተ
ጠላቶቻችንን ሁሉ እንወጋቸዋለን፡ በስምህ በላያችን የቆሙትን
እናዋርዳቸዋለን ።6 በቀስቴ የምታመን አይደለሁም፡ ጦሬም
አያድነኝም። 7 አንተ ግን ከከበቡን ጠላቶቻችን ሁሉ አዳንኸን።
የሚጠሉትንን ሁሉ አሳፈርሃቸው፡ 8 ሁልጊዜ በእግዚአብሔር
እንከብራለን፡ ስምህንም ለዘለዓለም እናመሰግናለን። 9 አሁን ግን
ጣልኸን፡-አሳፈርኸንም።-አምላካችን-ከሠራዊታችንም-ጋር አትወ
ጣም።10--በጠላቶቻችን-ዘንድ-ወደ-ኋላችን--መለስኸን፡ ጠላቶቻች
ንም ተነጣጠቁን።11 እንደ በጎች ሊበሉን አሳልፈህ ሰጠኸን፡
ወደ አሕዛብም በተንኸን። 12 ሕዝብህን ያለ ዋጋ ሸጥኸን፡
ለእልልታችንም ብዛት የለውም፡ በዙሪያችን ላሉ ጠላቶቻችን
ሁሉ መሣቂያና መዘበቻ አደረግኸን። 14 ለአሕዛብ መተረቻ፡
ለሕዝቡም የራስ መነቀነቀያ አደረግኸን። 15 እፍረቴ ሁልጊዜ
በፊቶ ነው፡ እፍረት ፊቴን ሸፈነችኝ። 16 ከሚሳደብና ከሚላገድ
ቃል የተነሣ፡ ከሚከብብ፡ ጠላትም ፊት የተነሣ።7 ይህ ሁሉ
በእኛ-ላይ-ደረሰ።-እኛ-ግን-አልረሳንህም፡-ቃል-ኪዳንህንም አላፈረስ
ንም።-18 ልባችንም ወደ ኋላው አልተመለሰም። ፍለጋችን-
ከመንገድህ-ፈቀቅ-አላለም። 19 በክፉ አገር አዋርደኸናልና የሞት
ጥላም ሰውሮናል። 20 የአምላካችንን ስም ረስተንስ ቢሆን ኖሮ፡
21 እግዚአበሔር ይህን ሁሉ በተመራመረው ነበር። እርሱ
በልባችን የሰወረውን ያውቃልና። 22 ስለ እርሱ ሁልግዜ
ይገድሉናል፡ እንደሚታረዱም በጎች ሆነናል ። 23 አቤቱ ንቃ1
ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ <u>! ለዘወትርም አትጣለን። 24 ለምንስ</u>
<u>ፊትህን ከእኛ ትመልሳለህ?</u> መከራችንንና ችግራችንንስ ለምን
ትረሳለህ? 25 ነፍሳችን በመሬት ላይ ተጕሳቊላለችና፡ ሆዳችንም
ወደ ምድር ተጣብቃለች። 26 አቤቱ ተነሥና እርዳን፡ ስለ
ስምህም ስትል ታደገን።

www.ethiopianorthodox.org

## መዝ-፵፬/44፡ ፍቅር የሞላበት የንጉሣዊ ሠርግ ዝማሬ

1 ጕሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ=ልቤ መልካም ነገርን ተናገረ፡
እኔም ሥራዩን ለንጉሥ እናገራለሁ፡ አንደበቴ እንደ ፈጣን
ጸሓፊ ብርዕ ነው፡፡ 2 ውበቱ ከሰው ልጆች ይልቅ ያምራል፡
ሞገስ ከከንፈሮችህ ፈሰሰ፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ለዘለዓለም
ባረከህ ፡፡3 ኃያል ሆይ በደም ግባትህና በውበትህ ሰይፍህን
በወገብህ ታጠቅ፡፡4 ስለ ቅንነትና ስለ የዋህነት፡ ስለ ጽድቅም
አቅና፡ ተከናወን፡ ንገሥም፡ ቀኝህ በክብር ይመራሃል፡፡ 5-ኃያል
ሆይ1 የተሳሉ ፍላጻዎችህ በንጉሥ ጠላቶች ልብ ውስጥ
ይገባሉ፡፡አሕዛብ በእግርህ ሥር ይወድቃሉ፡፡ 6 አምላክ ሆይ
ዙፋንህ ለዘለዓም ነው፡፡በትረ መንግሥትህ የጽድቅ በትር ነው፡፡
7 ጽድቅን ወዳድህ፡ ዓመፃንም ጠላህ፡፡ ስለዚህ ከባልንጀሮችህ
ይልቅ እግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይትን ቀባህ፡፡-8 ከርቤና
ሽቱ ዝባድም-በልብሶችህ ናቸው፡፡9 የንግሥት ሴቶች ልጆች
ለከብርህ ናቸው፡ በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸልማ ንግሥቲቱ
በቀኝህ ትቆማለች ፡፡10 ልጄ ሆይ ስሚ! እዩም፡ ጆሮሽንም
አዘንብዪ፡ ወገንሽንና ያባትሽንም ቤት እርሺ፡፡11 ንጉሥ
ውበትሽን ወዷልና፡፡እርሱ ጌታሽ ነው፡፡2 የጢሮስ ሴቶች ልጆች
እጅ መንሻን ይዘው ይስግድለታል፡፡የምድር ባለጠጎች አሕዛብ
ሁሉ በፊትሽ የማልላሉ፡፡13 ለሐሴቦን ንጉሥ ሴት ልጅ ሁሉ
ክብርዋ ነው፡ በወርቅ ዘቦ ልብስ የተጎናጸፈች ናት፡፡14 በኊላዋ
ደናግሉን አስከትለው ለንጉሡ ይወስዳሉ፡ ባልጀሮችዋንም ወደ
አንተ ያቀርባሉ፡ 15 በደስታና በሐሤት ይወስዱአቸዋል፡፡ወደ
ንጉሥ እልፍኝም-ያስገቡአቸዋል፡፡ 16 በአባቶችሽ--ፈንታ-ልጆች-
ተወለዱልሽ፡-በምደርም ሁሉ ላይ ገዥዎች አድርገሽ-ትሾሚያቸ
ዋለሽ፡፡-7-ስልጅ-ልጅ-ሁሉ-ስምሽን-ያሳስባሉ፡፡-አቤቱ-ስለዚህ-ለዓለ
ምና-ለዘላለም-አሕዛብ-በማመስገን ይገዙልሃል፡፡

## መዝ ፵፭ /45፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለመሆኑ

1-አምላክነሰ-ኃይልነ-ወጸወነነ=አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን
ነው፡ ባገኘን በታላቅ መከራም ጊዜ ረዳታችን ነው፡፡ 2 ስለዚህ
ምድር ብትነዋወጥ፡ ተረሮችም ፈልሰው ወደ ባሕር ልብ



ቢወሰዱ አንፈራም፡፡ 3 ውኃዎቻቸው ጮኹ፡ ደፈረሱም፡፡
ተረሮችም ከኃይሉ የተነሣ ተናወጡ፡፡ 4 የወንዝ ፈሳሽ ውኃ
የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኛል፡፡ ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ፡
5-እንዳትታወክም እግዚያብሔር በመካከልዋ ነው፡፡ እግዚያብሔ
ርም ፊት ለፊት ይረዳታል፡፡ 6 አሕዛብ ደነገጡ፡ ነገሥታትም
ተመለሱ፡፡ ልዑል ቃሉን ሰጠ፡ ምድርም ተንቀጠቀጠች፡፡ 7 የሠ
ራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው፡ የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው፡፡
8 የእግዚያብሔርን ሥራ በምድር ያደረገውንም ተአምራት
አንድታዩ ኑ፡፡ 9 እስከ ምድር ዳርቻ ጦርነትን ይሽራል፡ ቀስትን
ይሰብራል፡ ጋሻንም ይቀጠቅጣል፡ በእሳትም የጦር መሣሪያን
ያቃጥላል፡፡10 ልብ አድርጉ፡ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ ዕወቁ፡
በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ፡ከፍ እላለሁ፡ በምድርም ላይ ከፍ ፡ከፍ
እላለው፡፡ 11 የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው የያዕቆብ አምላክ
መጠጊያችን ነው፡፡

## መዝ ፵፮ /46፡ እግዚአብሔር የዓለማት ሁሉ ንጉሥ

1 ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ= አሕዛብ ሁላችሁ
በእጆቻችሁ አጨብጭቡ፡ በደስታ ቃልም ለእግዚአብሔር እልል
በሉ፡፡ 2 እግዚአብሔር ልዑል ግሩምም ነውና፡ በምድር ሁሉ
ላይ ታላቅ ንጉሥ ነውና፡፡ 3 አሕዛብን ከእኛ በታች አስገዛልን ፡፡
4 ለርስቱ እኛን መረጠን፡ የያዕብን ውበት የወደደ፡፡ 5 እግዚአ
ብሔርን-በእልልታ፡ ጌታም-በመመለከት-ድምፅ ዐረገ፡፡ 6 ዘምሩ
ለአምላካችን ዘምሩ፡ ለንጉሣችን ዘምሩ፡፡ 7 እግዚአብሔር
የምድር ሁሉ ንጉሥ መሆኑን፡ በማስተዋል ዘምሩ፡፡ 8 እግዚ
አብሔር በአሕዛብ ላይ ነገሠ፡ እግዚአብሔር በቅዱስ ዙፋኑ ላይ
ይቀመጣል፡፡ 9 የአሕዛብ አለቆች ከአብርሃም አምላክ ጋር
ተሰበሰቡ፡የምድር-ኃያላን-ለእግዚአብሔር-እጅግ-ከፍ፡-ከፍ አሉ፡፡

## መዝ-፵፯/47፡ የታላቁ ንጉሥ-የእግዚአብሔር-ከተማ

1 ዐቢይ እግዚአብሔር ወብዙኅ አኰቴቱ= እግዚአብሔር ታላቅ
ነው፡ በአምላካችን ከተማ በመቅደሱ ተራራ ምስጋናው ብዙ
ነው፡፡2 ለምድር ሁሉ ደስታን የሚያዝዝ የጽዮን ተራራዎች
በሰሜን በኩል ናችው፡፡ ጽዮን የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናት፡፡



www.ethiopianorthodox.org

3 በተቀበሏት ጊዜ-እግዚአብሔር በረከትዋን ያውቃል። 4 እነሆ
የምድር-ነገሥታት-ተሰብስበው-በአንድነት-መጥተዋል።5 እነርሱስ
ይህን አይተው አደነቁ፡ ስለፈሩም ደነገጠው ፡ 6 እንደ ወላድም
የሚያንቀጠቅጥ ምጥ ያዛቸው። 7 በኃይለኛ ነፋስ የተርሴስን
መርከቦች ትቀጠቅጣቸዋለህ። 8 እንደሰማን እንዲሁ አየን፡
የሠራዊት ጌታ የሆነ አምላካችን እግዚአብሔር ይህችን ከተማ
ለዘለዓለም ያፀናታል። 9 አምላክ ሆይ! በሕዝብ መካከልል
ይቅርታህን ተቀበልን።10 አምላክ ሆይ! እንደ ስምህ እንዲሁም
እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስጋናህ ነው።ቀኝህ ጽድቅን የተመላ
ነው።11 አቤቱ ስለ ፍርድህ የጽዩን ተራሮች ደስ ይላቸዋል፡
የይሁዳም ሴቶች ልጆች ሐሤት ያደርጋሉ።12 ጽዩንን
ክበቡአት፡ ዕቀፋአትም። በቅጥሮችዋም ተናገሩ።13-በብርታቷ
ልባችሁን አኑሩ፡ በረከቷንም ትካፈላላችሁ። ለሚመጣውም-
ትውልድ፡14 ለዓለምና ለዘለዓለም ይህ አምላካችን እንደ ሆነ
ትነግራላችሁ። እርሱም ለዘለዓለም ይጠብቀናል።

መዝ-፵፰/48፡ **<u>በምድራዊ ሀብት የመተማመን ከንቱነት</u>**

1 ስምዑ ዘንተ ኵልክሙ አሕዛብ= አሕዛብ ሁላችሁ ይህን
ስሙ፡ በዓለም የምትኖሩም ሁላችሁ አድምጡ። 2 የሰው ልጆች
ባለጠጎችና ደሆች በየሀገራችሁ በአንድነት። 3 አፌ ጥበብን
ይናገራል፡ የልቤም አሳብ ምክርን። 4 በጆሮዬ ምሳሌን አደምጣ
ለሁ፡ በበገናም ነገሬን እገልጣለሁ። 5 ከክፉ ቀን ለምን
እፈራለሁ? ኃጢአት ተረከዜን ከበበኝ። 6 በኃይላቸው
የሚታመኑ፡ በባለጠግነታቸውም ብዛት የሚኮሩ አይድኑም፡
ወንድም-ወንድሙን አያድንም፡ ሰውም-ሰውን-አያድንም፡--7 ለነ
ፍሱ ቤዛ የሚሆን ምንም ነገር ለእግዚአብሔር መስጠት
አይቻለውም፡ 8 የነፍሱንም ዋጋ ለውጥ መስጠት አይችልም።
9--በዚህ-ዓለም-የደከመ-ግን--ለዘለዓለም-ይድናል፡-ጥፋትን አያይ
ምና። 10 ጠቢባንን ሲሞቱ ባየሃቸው ጊዜ እንደዚሁ ልብ
የሌላቸው ሰነፎችም ይጠፋሉ፡ የደከሙበትን-ሀብታቸውን
ለሌሎች-ትተዉት-ይሄዳሉ።-11-መቃብራቸው-የዘላለም ቤታቸው
ይሆናል። ማደሪያቸውም ለልጅ ልጅ ነው። በየሀገራቸው



ስማቸው ይጠራል። 12 ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም፡
ልብ እንደሌላቸው እንደ እንስሶች ሆነ፡ መሰላቸውም፡ 13 በአፋ
ቸው ሲወዱ መንገዳቸው ራስዋ መሰናክያቸው-ናት።14 እንደ
በጎች-ሞት-በሲኦል-ይጠብቃቸዋል።ቅኖች-በማለዳ ይገዙአቸዋል።
ረድኤታቸውም ከክብራቸው ተለይታ በሲኦል ትጠፋለች።
15 ነገር ግን በሚውስዱኝ ጊዜ እግዚአብሔር ነፍሴን ከሲኦል
እጅ ያድናታል።6 በበለጸገ ጊዜ የቤቱም ክብር በበዛ ጊዜ ሰውን
አትፍራው።17 በሚሞት ግዜ ከእርሱ ጋር ይዞት የሚሄድ
ምንም ነገር የለምና። የቤቱም ክብር ሁሉ ከእርሱ ጋር
አይወርድምና። 18 በሕይወቱ ሳለ ሰውነቱ ደስ ብሎአታልና ።
ስው መልካም ብታደርግለት ያመሰግንሀል ። 19 ወደ አባቶቹም
ዓለም ይወርዳል፡ ከእንግዲህ ወዲህ ለዘለዓለም ብርሃንን
አያይም። 20 ሰው ግን ክቡር ሲሆን አላወቀም። ልብ
እንደሌላቸው እንስሶችም ሆነ፡ መሰላቸውም።

መዝ ፵፱ /49፡ *<u>የምስጋና መሥዋዕት</u>*

1 አምላከ አማልክት እግዚአብሔር ነበበ ወጸውዐ ለምድር=
የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ተናገረ፡ ምድርንም ጠራት።
ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ። 2 ከክብሩ
ውበት ከጽዮንም፡ 3 እግዚአብሔር በግልጥ ይመጣል።
አምላካችንም--ዝም-አይልም፡እሳት በፊቱ ይነድዳል፡ በዙሪያውም
ብዙ አውሎ አለ። 4 በላይ ያለውን ሰማይንና ምድርንም
በሕዝቡ ለመፍረድ ይጠራል። 5 እንደ ሕጉ መሥዋዕትን
የሚያቀርቡትን ጻድቃኑን ሰብስቡለት። 6 ሰማያት ጽድቁን
ይናገራሉ፡ እግዚአብሔር ፈራጅ ነውና። 7 ሕዝቤ ስማኝ፡
ልንገርህ ፡እስራኤልም እመሰክርብሃለሁ፡ አምላክስ ካልህ፡ እኔ
አምላክህ ነኝ። 8 ስለ መሥዋዕትህ የምዘልፍህ አይደለሁም፡
የሚቃጠል ቁርባንህም ሁልጊዜ በፊቴ ነው። 9 ከቤትህ ፍሪዳን፡
ከመንጋህም ጊደርን አልወስድም። 10 የዱር አራዊት ሁሉ፡
የምድረ በዳ እንስሶችና ላሞች ሁሉ የእኔ ናቸውና። 11 የሰማ
ይን አዕዋፍ ሁሉ አውቃለሁ፡ የዱር ውበትም በእኔ ዘንድ አለ።
12 ብራብም አብላኝ ብዬ አልጠይቅህም፡ ዓለም ሁሉ በመላው

www.ethiopianorthodox.org

የእኔ ነውና። 13 የፍሪዳውን ሥጋ አልበላም፡ የፍየሉንም ደም
አልጠጣም። 14 ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ሠዋ፡
ለልዑልም ጸሎትህን ስጥ፡ 15 በመከራህ ቀን ትጠራኛለህ፡-
አድንህማለሁ። አንተም ታከብረኛለህ። 16 ኃጢአተኛውን ግን
እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል፡ "ለምን አንተ ሕጌን-ትናገራለህ?
ኪዳኔን-በአፍህ-ለምን-ታነሣለህ?-17-አንተስ-ተግሣጼን ጠልተሃል፡
ቃሌንም ወደ ኋላህ መለስህ። 18 ሌባውን ባየህ ጊዜ ከእርሱ
ጋር ትሮጣለህ፡ ዕድል ፋንታህንም ከአመንዝሮች ጋር አደረግህ።
19- አፍህ ክፋትን አበዛች ። አንደበትህም ሽንገላን ተበተበ ።
20-ተቀምጠህ- ወንድምህን-ታማዋለህ፡-ለእናትህም-ልጅ እንቅፋ
ትን አኖርህ።21 ይህንም ሁሉ አድርገህ ዝም አልሁህ።
ኃጢአት አማረችህን? እኔም እንዳንተ-እሆን-ዘንድ-ጠረጠርህን?
በፊትህ ቆሜ ልዘለፍህን ? 22 እግዚአብሔርን የምትረሱ
እናንተ ይህን አስተውሉ፡ አለዚያ ግን=እርሱ-ይነጥቃል፡-
የሚያድን-የለም።23-ክብርት-መሥዋዕት-ታከብረኛለች፡እግዚአብ
ሔር-ማዳኑን-ያሳየባት-መንገድ-በዚያ-አለች።

## መዝ ፶ /50፡ <u>የበደልን ይቅርታ መጠየቂያ ጸሎት</u>

1 ተሠሃለኒ እግዚኦ በከመ ዕበየ ሣህልከ= አቤቱ እንደ ቸርነትህ
መጠን ማረኝ፡ እንደምሕረትህም ብዛት ኀጢአቴን ደምስስ።
2 ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፡ ከኃጢአቴም አንጻኝ። 3 እኔ በደሌን
አውቃለሁና ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና። 4 አንተን ብቻ
በደልሁ፡ በፊትህም ክፉ ነገርን አደረግሁ። በነገርህ ትጸድቅ
ዘንድ፡-በፍርድህም-ታሸንፍ-ዘንድ። 5 እነሆ በኀጢአት ተፀነስሁ፡
እናቴም-በዓመፃ-ወለደችኝ።-6-እነሆ-እውነትን-ወደድህ፡ የማይነገር
ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ። 7 በሂሶጵ እርጨኝ፡ እነጻማለሁ።
እጠበኝ ከበረዶ ይልቅ ነጭ እሆናለሁ። 8-ሐሤትንና ደስታን
አሰማኝ፡ የጸድቃን አጥንቶች ደስ ይላቸዋል። 9 ከኃጢአቴ
ፊትህን መልስ፡ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ ። 10 አቤቱ ንጹሕ
ልብ ፍጠርልኝ፡ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።
11 ከፊትህ አትጣለኝ፡ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ
አትውሰድብኝ። 12 ደስታንና ማዳንህን ስጠኝ፡ በፅኑ መንፈስም



አፅናኝ። 13 መንገድህን ለኃጥአን አስተምራቸው ዘንድ፡
ዝንጉዎችም ወደ አንተ ይመለሱ ዘንድ። 14 የመድኃኒቴ
አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ከደም አድነኝ። አንደበቴም በአንተ
ጽድቅ ደስ ይለዋል። 15 አቤቱ ከንፈሮቼን ክፈት፡ አፌም
ምስጋናህን ያውራ። 16 መስዋዕትን ብትወድስ በሰጠሁህ ነበር፡
የሚቃጠለውንም መስዋዕት አትወድም። 17- የእግዚአብሔር
መስዋዕት የዋህ መንፈስ ነው፡ የተዋረደውንና የዋሁን ልብ
እግዚአብሔር አይንቅም። 18 አቤቱ በውዴታህ ጽዮንን
አሰማምራት፡ የኢየሩሣሌምም ቅጽሮች እንዲታነፁ አድርግ።
19 የጽድቁን መስዋዕት፡ መባውንም የሚቃጠለውንም መስዋዕት
በወደድህ ጊዜ፡ ያን ጊዜ በመሰዊያህ ላይ ፍሪዳዎች መሥዋዕት
ሆነው ይቀርባሉ።

## መዝ ፶1 /51፡ <u>የክፉዎች መጨረሻ ዕድል ፈንታ</u>

1 ለምንት ይዜኀር ኃያል በእከዩ፡ወይዔምፅ ኵሎ አሚረ ?=
ኀያል ሆይ በክፋት ለምንት ትታበያለህ? ሁልጊዜስ ለምን
ትበድላለህ? 2 ልብህ ኃጢያትን ያስባል፡ እንደ ተሣለ ምላጭ
ሽንገላን ተናገርህ፡ 3 ከመልካም ይልቅ ክፋትን፡ ጽድቅንም
ከመናገር ይልቅ ዓመፃን ወደድህ። 4 የሚያስጥም የምላስ ነገርን
ሁሉ ወደድህ ። 5 ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘለዓለም ያፈርስሃል፡
ከቤትህም-ይነቅልሃል፡-ያፈልስህማል።-ሥርህን-ከሕያዋን ምድር
ይነቅላል። 6 ጻድቃንም አይተው ይፈሩ፡ በእርሱም ይሣቁ።
እንዲህም-ይበሉ-7-"እግዚአብሔርን-ረዳቱ-ያላደረገ፡ በባለጠግነቱም
ብዛት የታመነ፡ በከንቱ ነገርም የበረታ፡ ያ ሰው እነሆ! " 8 እኔስ
በእግዚአብሔር ቤት እንደለመለመ ወይራ ዛፍ ነኝ፡ ለዓለምና
ለዘለዓለም በእግዚአብሔር ምሕረት ታመንሁ።9-መልካም ነገር
አድርገህልኛልና ለዘለዓለም አመሰግንሃለሁ በጻድቃንህም ዘንድ
ምሕረትህን ተስፋ አደርጋለሁ ።

## መዝ ፶2 /52፡ <u>የአምላክን ህልውና የካዱ ሰነፎች</u>

1 ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር=ሰነፍ በልቡ "እግዚ
አብሔር የለም" ይላል። ረከሱ በበደላቸውም ጎሰቀሉ፡ በጎ ነገርን
የሚያደርጋት የለም 2 እግዚአብሔርን የሚፈልግ አስተዋይ

www.ethiopianorthodox.org

መኖሩን ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን
ተመለከተ። 3 ሁሉ ተካክሎ በአንድት በደለ፡ አንድም እንኳ በጐ
ነገርን የሚያደርጋት የለም። 4 እንጀራን እንደ መብላት
ብሕዝቤን-የሚበሉ-ግፍ-አድራጊዎች-ሁሉ-አያውቁም እግዚአብ
ሔ
ርንም-አይጠሩትም።5-እግዚአብሔር-የግብዞችን አጥንቶች በትኖአ
ልና። በዚያ የማያስፈራ እርሱ አስፈሪ ሆነባቸው። እጅግም ፈሩ፡
እግዚአብሔር አዋርዶአቸዋልና አፈሩ። 6 መድኃኒትን ከጽዮን
ለእስራኤል-ማን-ይሰጣል?-እግዚአብሔር-የሕዝቡን ምርኮ በመለሰ
ጊዜ ያዕቆብ ደስ ይለዋል፡ እስራኤልም ሐሤትን ያደርጋል ።

## መዝ-፶3/53፡ <u>የእግዚአብሔርን ረድኤት መማፀኛ ጸሎት</u>

1 እግዚኦ በስምከ አድኅነኒ፡ወበኃይልከ ፍታሕ ሊተ እግዚኦ=
አቤቱ በስምህ አድነኝ፡ በኃይልህም ፍረድልኝ። 2 አቤቱ ጸሎቴን
ስማኝ፡-የአፌንም-ቃል-አድምጥ። 3 ባዕዳን በእኔ ላይ ቆመዋልና።
ኃያላንም-ነፍሴን-ሽታዋታልና።እግዚአብሔርን--በፊታቸው-አላደረ
ጉትም። 4 እነሆ እግዚአብሔር ይረዳኛል፡ ጌታዬም ነፍሴንም
ያድናታል። 5 ክፋትን ወደ ጠላቶቼ ይመልሳታል። በእውነትም
አጥፋቸው። 6 ከፈቃዴ የተነሣ እሠዋልሃለሁ፡ አቤቱ መልካም
ነውና ስምህን አመሰግናለሁ።7 ከመከራ-ሁሉ-አድነሽኛልና-
ዓይኔ-የበጠላቶቼን ውድቀት አይታለችና።

## መዝ ፶፬ /54፡ <u>ከብዙ መከራ ለመዳን የሚቀርብ ጸሎት-</u>

1 አፅምዕኒ እግዚኦ ጸሎትየ፡ ወኢትትሐየየኒ ስእለትየ=አቤቱ
ጸሎቴን-አድምጠኝ፥ ልመናዬንም ቸል አትበል። 2. ተመልከተኝ፡
ስማኝም፤ በማዘን ደነገጥሁ፥ ተናወጥሁም፤ 3. ከጠላት ድምፅ፡
ከኀጢያተኛም ማሠቃየት የተነሣ፥ ዓመፃን በእኔ ላይ መልሰውብ
ኛልና፥-ሊያጠፋኝም-ተነሥተውብኛልና። 4-ልቤ-በውስጤ ደነገጠ
ብኝ፥ የሞት ድንጋጤም መጣብኝ ። 5. ፍርሃትና መንቀጥቀጥ
ያዙኝ፥ ጨለማም ሸፈነኝ። 6. "በርሬ ዐርፍ ዘንድ እንደ ርግብ
ክንፍን ማን በሰጠኝ?" አልሁ፥ 7.እነሆ ኮብልዬ በራቅሁና፥
በምድረ በዳም በኖርሁ። 8. እንደ አውሎ ነፋስ ከሆነው ከነፍሴ
መቅበዝበዝ የሚያድነኝን ተስፋ አደርገዋለሁ። 9. አቤቱ!



ዓመፃንና ጠብን በከተማ ውስጥ አይችአለሁና አስጥማቸው፥
አንደበታቸውንም-ቁረጥ። 10.-በቀንና-በሌሊት-በቅጥርዋ-ይከብቡአ
ታል፤ ዓመፃና ድካም ፡ኀጢአትም በመካከልዋ ነው፤11 ሽንገላ
ከአደባባይዋ አይርቅም። 12-ጠላትስ ቢሰድበኝ ፥ በታገሥሁ
ነበር፤የሚጠላኝም አፉን በላዬ ከፍ፡ ከፍ ቢያደርግ ፥ ከእርሱ
በተሸሸግሁ ነበር። 13. አንተ ሰው፥ አንተ ግን እንደራሴ ነበርህ፥
ባልንጀራዬና የማውቅህ ወዳጄም ነበርህ፤ 14. መብልን ከእኔ
ጋር በአንድነት ያጣፈጥህ ነበርህ፤ በአንድ ልብ ወደ እግዚአብ
ሔር-ቤት-አብረን-ተራመድን። 15.-ሞት-ይምጣባቸው በሕይወት
ሳሉ ወደ ሲኦል ይውረዱ፤ክፋት በማደሪያቸውና በመካከላቸው
ነውና።16.-እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥ እግዚአብሔርም
ሰማኝ። 17. በማታና በጠዋት በቀትርም እናገራለሁ አስረዳለሁ፥
ቃሌንም-አይሰሙኝም።18.-ከእኔ-ጋር-ካሉት-ይበዛሉና ከሚከታተ
ሉኝ-ነፍሴን-በሰላም-አድናት።19.-ቤዛ-የላቸውምና፥ እግዚአብሔ
ርንም አልፈሩትምና፡ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ እግዚአብሔር
ሰምቶ ያጐስቁላቸዋል። 20.ፍዳን ለማምጣት እጁን ዘረጋ፡ ቃል
ኪዳኑንም አረከሱ። 21. ከፊቱም ቁጣ የተነሣ ተለያዩ፥ ልቡም
ለዘበ፤ቃሉም-ከቅቤ-ይልቅ-ለሰለሰ፤-እነርሱ ግን እንደሚያስጥም
ማዕበል-ናቸው።22.-ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፥ እርሱም
ይመግብሃል፤-ጻድቁንም ለዘለዓለም ሁከት አሳልፎ አይሰጠውም፡
23. አንተ ግን ፥ አቤቱ ፥ ወደ ሞት ጉድጓድ አውረድሃቸው፤
የደም-ሰዎችና-ሸንጋዮች-የዘመናቸውን እኩሌታ መኖር አችሉም።
እኔ ግን አቤቱ በአንተ እታመናለሁ።

## መዝ ፶፭/55፡ <u>በስደት ላይ ከሚደርስ ጥቃት ለመዳን</u>

1 ተሣሃለኒ እግዚኦ እስመ ኬደኒ ሰብእ=አቤቱ ሰው ረግጦኛልና
ይቅር በለኝ፤ ሁልጊዜም ሠልፍ አስጨንቆኛል።2 ሁልጊዜ ቀኑን
ሁሉ ጠላቶች ረገጡኝ። የሚዋጉኝ በዝተዋልና ፈራሁ። 3 እኔ
ግን አቤቱ በአንተ ታመንሁ። 4 በእግዚአብሔር ታመንሁ፡
አልፈራም። ሰው-ምን-ያደርገኛል?- 5-ሁልግዜ-ቃሎችን ይጸየፉብ
ኛል፤-በእኔ ላይም የሚመክሩት ሁሉ ለክፉ ነው። 6-ይሸምቁብ
ኛል፡-እንዳላያቸውም-ይሸሽጉብኛል።- እነርሱም-ተረከዜን ይመለ



www.ethiopianorthodox.org

ካከታሉ፡ ሁልግዜም ነፍሴን ይሸምቁባታል። 7-በምንም ምን
አታድናቸው። 8. አሕዛብን በመዓትህ ትጥላቸዋለህ። 9--በጠራ
ሁህ -ጊዜ ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሱ፤አንተ አምላኬ እንደ
ሆንህ እነሆ ዐወቅሁ። 10-በእግዚአብሔር ቃሌን አከብራለሁ፡
የተናገርሁትም በእግዚአብሔር ዘንድ ይከብራል። 11-በእግዚአ
ብሔር ታምኛለሁ፡ አልፈራም፡ ሰው ምን ያደርገኛል። 12-አቤቱ
የምሰጥህ የምስጋና ስእለት በእኔ ዘንድ ነው።13 ነፍሴን ከሞት፡
ዓይኖቼን ከእንባ፡ እግሮቼን ከድጥ -አድነሃልና፡በሕያዋን-ምድር-
እግዚአብሔርን-አሰኘው-ዘንድ።

## መዝ ፶፮ /56፡ በእግዚአብሔር ረድኤት መታመን

1 ተሣሃለኒ እግዚኦ ተሣሃለኒ፡ እስመ ኪያከ ተወከለት
ነፍስየ= ይቅር በለኝ፡ አቤቱ ይቅር በለኝ፡ ነፍሴ አንተን
ታምናለችና ፤ኀጢአት እስክታልፍ ድረስ በክንፎችህ ጥላ
እታመናለሁ። 2.-ወደ ልዑል እግዚአብሔር ወደሚረዳኝ ወደ
እግዚአብሔር-እጮኻለሁ። 3. ከሰማይ ልኮ አዳነኝ፡ ለረገጡኝም
ውርደትን ሰጣቸው። እግዚአብሔር ቸርነቱንና ጽድቁን ላከ።
4-ነፍሴን-ከአንበሶች-መካከል-አዳናት። ደንግጬም ተኛሁ። የሰው
ልጆች ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ ነው። አንደበታቸውም የተሳለ
ሾተል ነው። 5. እግዚአብሔር በሰማያት ላይ ከፍ ፡ከፍ አለ፡
ክብሩም በምድር ሁሉ ላይ ነው። 6. ለእግሮቼ ወጥመድ
አዘጋጁ፡ ሰውነቴምንም አጎበጡአት። ጉድጓድን በፊቴ ቆፈሩ፡
በውስጡም ወደቁ። 7. ልቤ ፅኑዕ ነው፡ አቤቱ ልቤ ፅኑዕ ነው።
አመሰግናለሁ፡ እዘምራለሁም። 8. ክብሬ ይነሣ፡ በበገና እና፡
በመሰንቆ፡ ይነሣ፡ እኔም ማልጄ እነሣለሁ። 9. አቤቱ በአሕዛብ
ዘንድ አመሰግንሃለሁ ፡ በወገኖችም ዘንድ እዘምርልሃለሁ።10
ምሕረትሕ እስከ ሰማይ ደረስ ከፍ ብላለችና፡ ጽድቅህም እስከ
ደመናት ድረስ ። 11. እግዚአብሔር በሰማያት ላይ ከፍ፡ ከፍ
አለ፡ ክብሩም በምድር ሁሉ ላይ ነው።

## መዝ-፶፯/57፡ በችግር የተከበበ ሰው ጸሎት

1. እመሰ አማን ጽድቀ ትነቡ ወርትዐ ትኩንኑ፡ ደቂቀ ዕጓለ
እመሕያው==የሰው ልጆች ሆይ1 በእውነት ጽድቅን ብትናገሩስ



በቅን ትፈርዳላችሁ፤2. በልባችሁም በምድር ላይ ኃጢአትን
ትሠራላችሁና፡ እጆቻችሁም ሸንገላን ይታታሉ። 3.ኃጥአን
ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ፤ ከሆድም ጀምረው ሳቱ፡ ሐሰትንም
ተናገሩ። 4. ቁጣቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፡ ጆሮዋም እንደ
ደንቆረ እባብ።5. መተት ዐዋቂ ሲደግምባት የአስማተኛውን ቃል
እንደማትሰማ።--6.-እግዚአብሔር-የአንበሶቹን-መንጋጋቸውን
ያደቅቃል። 7.እንደሚፈስ ውኃ ይቀልጣሉ ፤እስከሚያደክማቸው
ድረስ ፍላጻቹን ይገትራል። 8.እንደሚቀልጥ ሠም ያልቃሉ።
እሳት ወደቀች፡ ፀሐይንም አላየኋትም። 9. እሾኻችሁ ሳይታወቅ
በትር ሆነ። ሕያዋን ሳላችሁ በመዓቱ ይውጣችኋል።10. ጻድቅ
በቀልን ባየ ጊዜ ደስ ይለዋል ፤ በኃጢአተኛውም ደም እጁን
ይታጠባል። 11. ሰውም "በእውነት ለጻድቅ ፍሬ አለው፤
በእውነት በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ" ይላል።

## መዝ ፶፰/58፡ በኃያላንን ላይ ፍርድ ሰጭ አምላክ

1 አድኅነኒ እግዚኦ እምፀርየ=አምላኬ-ሆይ1 ከጠላቶች አድነኝ ፤
በላዬም ከቆሙት አስጥለኝ። 2. ከዓመፅ አድራጊዎች ታደገኝ፡
ከደም ሰዎችም አድነኝ ። 3. እነሆ ነፍሴን በማደን ላይ ናቸው፡
ብርቱዎችም በላዬ ተነሡ። አቤቱ በበደሌም አይደለም፡
በኀጢአቴም አይደለም። 4. ያለ በደል ሮጥሁ፡ ተዘጋጀሁም፤
ተነሥ፡ ተቀበለኝ እይም። 5. አንተም አቤቱ የኃያላን አምላክ፡
የእስራኤል ንጉሥ አሕዛብን ጐብኛቸው፡ ይቅር በላቸው ዓመፅ-
የሚያደርጉትን-ሁሉ=ግን አትማራቸው። 6. ሲመሽ ማታ
ይመለሱ፡ እንደ ውሾችም ተርበው በከተማም ይዞሩ። 7 እነሆ
በአፋቸው ይናገራሉ፤ ሰይፍም በከንፈሮቻቸው አለ። 8. የምት
ሰማቸው አንተ ግን አቤቱ ትሥቅባቸዋለህ፡ 9. ኃይሌን ወደ
አንተ አስጠጋለሁ፡ አንተ አምላኬና መጠጊያዬ ነህና። 10. የአ
ምላኬ ይቅርታው ይድረሰኝ፡ አምላኬ በጠላቶቼ ላይ አሳየኝ።
11. ሕግህን እንዳይረሱ፡ አትግደላቸው። አቤቱ አምላኬና ረዳቴ
በኃይልህ በትናቸው፡ አዋርዳቸውም።12.-ስለ አፋቸው ኃጢአት፡
ስለ-ከንፈራቸውም-ቃል-በትዕቢታቸው-ይጠመዱ። ከመርገማቸ

www.ethiopianorthodox.org

ውና ከሐሰታቸው የተነሣ ፍጻሜያቸው ይታወቃል፡፡ 13.ኋላ በሚመጣ መቅሠፍት ያልቃሉ፤ የያዕቆብም አምላክ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንደሚገዛ ይወቁ፡፡ 14. ሲመሽ ማታ ይመለሱ እንደ ውሾችም ተርበው በከተማ ይዞሩ ፡፡ 15-.እነርሱም መብል ለመፈለግ ይበተኑ ፤በጠገቡም ጊዜ ያንጐራጕራሉ፡፡ 16. እኔ ግን ለኃይልህ እቀኛለሁ፤ በምሕረትህም በማለዳ ደስ ይለኛል፤ በመከራዬ ቀን መጠጊያዬና አምባዬ ሆነኸልኛልና፡17. አንተ ረዳቴ ነህ፡ ለአንተም ለአምላኬ እዘምራለሁ፤ አንተ አምላኬ መጠጊያዬ ነህና፡ አምላኪዬና ምሕረቴም ነህና፡፡

## መዝ-፶፱/59፡ ጠላት ሲበረታ የሚቀርብ ጸሎት

1 እግዚአ ገደፍከነ ወነሠትከነ፡ ቀሠፍከነኒ ወተሣሃልከነ=አቤቱ ጣልኸን፡ አፈረስኸን፤ገረፍኸን፡ ይቅርም-አልኸን፡፡ 2. ምድርን አናወጥሃት፡ አወከሐትም፡፡ ተናውጣለችና ቁስልዋን ፈወስኻት፡፡ 3. ለሕዝብህ ጭንቅ ነገርን አሳየሃቸው፡ አስደንጋጩንም ወይን አጠጣኸን፡፡4.ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው፡ ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ፡፡ 5 ወዳጆችህም ይድኑ ዘንድ በቀኝህ አድን፡ ስማኝም፡፡ 6 እግዚአብሔር በመቅደሱ ተናገረ፡ ደስ ይለኛል፡ ምርኮንም እካፈላለሁ፡፡ የሸለቆ ቦታዎችን እሠፍራለሁ፡፡7 ገለዓድ የእኔ ነው፡ ምናሴም የእኔ ነው፤ ኤፍሬም የራሴ መጠጊያ ነው፡፡ ይሁዳ ንጉሤ ነው፤ 8. ካህን ሞአብም ተስፋዬ ነው፡ በኤዶምያስ ላይ-ጫማዬን እዘረጋለሁ፤ ፍልስጥኤምም ይገዙልኛል፡፡ 9.ቅጥር ወደ አለባት ወደ ጽኑ ከተማ ማን ይወስደኛል? ማንስ እስከ ኤዶምያስ ይመራኛል? 10. አቤቱ የጣልኸን አንተ አይደለህምን ? አምላካችን ሆይ ከሠራዊታችን ጋር አት ወጣም፡፡11 በመከራችን ረድኤትን ስጠን፡ በሰውም መታመን ከንቱ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ኀይልን እናደርጋለን፤ እርሱም የሚያስጨንቁንን ያዋርዳቸዋል፡፡

## መዝ ፷/60፡ እግዚአብሔርን መጠጊያ የማድረግ ጸሎት

1 ስምዐኒ አምላኪየ ስእለትየ፡ ወአፅምዐኒ ጸሎትየ=አምላኬ ሆይ ልመናዬን ስማኝ፡ ጸሎቴንም አድምጠኝ፡፡ 2. ልቤ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤ በድንጋይ (ዐለት)



ላይ ከፍ፡ ከፍ አደረግኸኝ፡፡ 3 .በጠላት ፊት ዕኑ ግንብ ነህ፤ ተስፋዬም-ሆነህ መራኸኝ፡፡ 4. በድንኳንህ ለዘለአለም እኖራለሁ፤ በክንፎችህ-ጥላም-እጋረዳለሁ፤5.-አምላኬ-አንተ-ጸሎቴን ሰምተሃልና፤ስማፈሩህ ርስትን ሰጠሃቸው፡፡6.ለንጉሥ ከቀን በላይ ቀንን *(ዘመንን)* ትጨምራለህ፡ ዓመታቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ-ይሆናሉ፡፡7. በእግዚብሔር ፊት ለዘለዓለም-ይኖራል፤ ይቅርታውንና-ጽድቁን-ግን ማን ይፈልጋል? 8. እንዲሁም ለስምህ ለዘለዓለም እዘምራለሁ፡ ምኞቴን ሁልጊዜ ፈጽምልኝ ፡፡

## መዝ ፷፩/61፡ ተስፋን በእግዚአብሔር ላይ-ማድረግ

1 አኮኑ ለእግዚአብሒር ትገኒ ነፍስየ እስመ ኀቤሁ መድኃኒትየ= ነፍሴ ለእግዚአብሔረ የምትገዛ አይደለችምን? መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና፡፡ 2.እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና፤ እርሱ እረዳቴ ነው፡ ሁልጊዜም አልታወክም፡፡ 3 እስከ መቼ በሰው ላይ ትቆማላችሁ? እናንተ ሁላችሁ እንዳዘነበለ ግዳግዳ፡ እንደ ፈረሰም ቅጥር ትገድሉታላችሁ፡፡ 4. ነገር ግን ክብሬን ይሽሩ ዘንድ መከሩ፡ በጥሜም ሮጥሁ፤ በአፋቸው ይመርቃሉ፡ በልባቸውም ይረግማሉ፡፡ 5. ነገር ግን ነፍሴ ለእግዚአብሔር ትገዛለች፡ ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ናትና፡፡ 6. እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም-ነውና፤-እርሱ-ረዳቴ-ነውና-አልታወክም፡፡7. መድኃኒቴ-በእግዚአብሔር-ነው፤-ክብሬም-በእግዚአብሔር-ነው፡፡የረድኤቴ አምላክ፡ ተስፋዬም እግዚአብሔር ነው፡፡ 8 የአሕዛብ ማኅበር ሁላችሁ-በእርሱ-ታመኑ፡-ልባችሁንም- በፊቱ -አፍስሱ፡ እግዚአብሔር ረዳታችን ነው፡፡9.ነገር ግን የሰው ልጆች ሁሉ ከንቱ ናቸው፡ የሰው ልጆችም ሐሰተኞች ናቸው፤ በሚዛንም ይበድላሉ፡ እነርሱስ በፍጹም ከንቱ ናቸው፡፡10. ዓመፃን ተስፋ አታድርጉ፡ ቅሚያንም አትተማመኑብት ፤ ባለጠግነት ሲበዛ አይታችሁ ልባችሁ አይታበይ፡፡ 11. እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፡ እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ፤ ይቅርታ የእግዚአብሔር ነውና፡ 12.አቤቱ ኃይልም ያንተ ነው፤ አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ትከፍለዋለህና፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## መዝ ፷፪ /62 **እግዚአብሔርን በጸሎት መሻት**

1-አምላኪየ፡-አምላኪየ-እገይሥ-ኀቤከ፡-ጸምዐት-ነፍስየ-ለከ፡ አም
ላኬ፡አምላኬ-ወደ-አንተ-እገሠግሣለሁ፤ነፍሴ-አንተን-ተጠማች፡
እንጨትናውኃበሌለበት-ምድረ-በዳ-ሥጋዬን-ላንተ-እጼት ልዘርጋ
ልህ? ኃይልህንና ክብርህን አውቅ ዘንድ እንዲሁ በመቅደስህ
ውስጥ-ተመለከትሁህ፡፡- 3- ምሕረትህ-ከሕይወት-ይሻላልና-ከንፈ
ሮቼ ያመሰግኑሃል፡፡4.እንዲህ በሕይወቴ ዘመን አመሰግንሃለሁ፡
በአንተም-ስም-እጆችን-አነሣለሁ፡፡5-ነፍሴ-በቅቤና-በስብ እንደሚጠ
ግቡ ትጠግባለች፡ ደስተኞች ከንፈሮቼም ስምህን ያመሰግናሉ፡፡
6 በመኝታዬም አስብሃለሁ፡ በማለዳም እናገርልሃለሁ፡፡ 7 ረዳቴ
ሆነኸልኛልና በክንፎችህም ጥላ እታመናለሁ፡፡ 8. ነፍሴ በኋላህ
ተከታተለች፡ እኔንም ቀኝህ ተቀበለችኝ፡፡ 9 እነርሱ ግን ነፍሴን
ለከንቱ ፈለጓት፤ ወደ ምድር ጥልቅ ይግቡ፡፡ 10. በሰይፍ እጅ
አልፈው ይሰጡ፡ የቀበሮዎችም ዕድል ፈንታ ይሁኑ፡፡ 11 ንጉሥ
ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል፤ በእርሱም የሚምል ሁሉ
ይከብራል፡ ዓመፅን የሚናገር አፍ ይዘጋልና፡፡

## መዝ ፷፫ /63፡ **ተስፋችንን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ**

1.ስምዐኒ-እግዚኦ-ጸሎትየ-ዘሰአልኩ-ኀቤከ=-አቤቱ-ወደአንተ-የለመ
ንሁትን ጸሎቴን ስማ፡ ከጠላትም ትዝብት *(ጥርጥር)* ነፍሴን
አድናት ፡፡ 2. ከክፉዎች ሴራ ከብዙዎችም ዐመፅ አድራጊዎች
ሰውረኝ፡፡ 3-.እንደ እባብ ምላሳቸውን አሰሉ፤ መራራ ነገርን
ለማድረግ-፡-4-ንጹሕንም-በስውር ለመግደል-ቀስትን--ገተሩ፤ በድ
ንገት ይነድፏቸዋል፡ አይፈሩምም፡፡5 ለእነርሱም ለራሳቸው ክፉ
ነገርን አፀኑ፤-የሚያየንም-የለም"-ይላሉ፡፡6.-ዓመፃን ፈለጓት፡
ሲፈትኑም፡ ሲጀምሩም-አለቁ፤-ሰው-በጥልቅ-ልብ-ውስጥ-ይገባል፡፡
7-እግዚአብሔርም-ከፍ-፡ከፍ-ይላል-መቅሠፍታቸው እንደ ልጆች
ሕንፃ ሆነ፤ 8 አንደበታቸው በላያቸው ደከመ፡ የሚያዩአቸውም
ሁሉ ደነገጡ፡፡ 9. ሰው ሁሉ ፈራ፡ የእግዚአብሔርንም ሥራ
ተናገሩ፡ ሥራውንም ዐወቁ፡ 10 ጻድቅ በእግዚአብሔር ደስ
ይለዋል፡ በእርሱም ይታመናል፡፡ ልባቸው የቀና ሁሉ ይከብራሉ፡



## መዝ ፷፬/64፡ **ለምድር በረከትን የሚሰጥ አምላክ**

1 ለከ ይደሉ-እግዚኦ ስብሐት በጽዮን=አቤቱ በጽዮን ለአንተ
ምስጋና ይገባል ለአንተም በኢየሩሳሌም ጸሎት ይቀርባል ፡፡
2. ወደ አንተ የሚመጣ የሰውን ሁሉ ጸሎት ስማ 3. የዐመፀ
ኞች ነገር በረታብን፤ ኃጢአታችንንስ አንተ ይቅር ትለናለህ፡፡
4. አንተ የመረጥኸው ብፁዕ ነው፤ አቤቱ ከቤትህ በረከት
ጠገብን፡፡ 5. ቤተ መቅደስህ ቅዱስ ነው በጽድቅም ድንቅ ነው፡፡
በምድር-ዳርቻ-ሁሉና-በሩቅ ባሕር ውስጥ ላሉ ተስፋቸው የሆንህ
አምላካችንና መድኃኒታችን ሆይ ስማን፡፡6. በኃይልህ ተራሮችን
አፀናሃቸው፡ እነርሱም በኃይል ታጥቀዋል፡፡7 የባሕሩን ዓሣ
አነበሪ--የሚያውከው--እርሱ-ነው፡-የሞገድዋንም-ድምፅ የሚቃወ
መው ማን ነው? 8. ከተአምራትህ የተነሣ አሕዛብ ይደነግጣሉ፡-
በምድር-ዳርቻም-የሚኖሩ -ይፈራሉ፤ በጥዋት ይወጣሉ፡ ማታም
ይደሰታሉ፡፡9. ምድርን ጐበኘሃት፡ አረካሃትም፡ ብልጽግናዋንም
እጅግ አበዛህ፤ የእግዚአብሔር ወንዝ ውሆችን የተመላ ነው፤
ምግባቸውን አዘጋጀህ እንዲሁም ታሰናዳለህና ፡፡ 10.-ትልምዋን
አርካው መከሯንም አሣምረው፤ በነጠብጣብህም ደስ ብሏት
ትበቅላለች 11. የምሕረትህን ዓመት እክሊል-ትባርካለህ፡-ምድረ-
በዳዎችም-ጠልን-ይጠግባሉ፡፡ 12- የምድረ በዳዎች-ተራሮችም-
ይረካሉ፡ኮረብቶችም በደስታ-ይታጠቃሉ፡፡ 13- የበጎች አውራዎች
ስብን ይለብሳሉ፡ ሸለቆዎችም ስንዴን ይመላሉ፡ ድምፃቸውንም
ከፍ አድርገው ያመሰግናሉ፡፡

## መዝ ፷፭/65፡ **በእልልታ-ለእግዚአብሔር ዘምሩ**

1-የብቡ ለእግዚአብሔር በኵሉ ምድር፡ ወዘምሩ ለስሙ=በምድር
ያላችሁ ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፡ 2. ለስሙም ዘምሩ፡
ለክብሩም ምስጋናን አቅርቡ፡፡ 3 እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
"ሥራህ ግሩም ነው፤ኀይልህ ብዙ ሲሆን ጠላቶችህ ዋሹብህ"፡፡
3. ምድር በመላዋ ለአንተ ትሰግዳለች፡፡ ለአንተም ትገዛለች፡
ለስምህም ትዘምራለች ፡፡ 5 የእግዚአብሔርን ሥራ ታዩ ዘንድ
ኑ፡፡ ምክሩ ከሰው ልጆች ይልቅ ግሩም ነው፡፡ 6. ባሕርን የብስ
አደረጋት፡ ወንዙንም በእግር ተሻገሩ፡፡ እዚያም በእርሱ ደስ



www.ethiopianorthodox.org

ይሰናል። 7 በኃይሉ ለዘለዓለም ይገዛል፡ ዐይኖቹ ወደ አሕዛብ
ይመለከታሉ። ራሳችሁን ከፍ፡ ከፍ አታድርጉ። 8. አሕዛብ ሆይ
አምላካችንን አመስግኑ! የምስጋናውንም-ቃል አድምጡ። 9.-ነፍ
ሴን-በሕይወት-ያኖራታል፡-ለእግሮቼም-ሁከትን-አልሰጠም።
10.አቤቱ-ፈትነኸናልና፡-ብርን እንደሚያነጥሩት አንጥረኸናልና።
11. ወደ ወጥመድም አገባኸን፡ በፊታችንም መከራን አመጣህ።
12. በራሳችን ላይ ሰውን አስጫንህ *(ሰውን አሠለጠንህብን)*፤
በእሳትና በውኃ መካከል አሳለፍኸን፡ ወደ ዕረፍትም አወጣኸን።
13 መባዬን ይዤ ወደ ቤትህ እገባለሁ፤ 14. በመከራዬ ጊዜ
በአፌ የተናገርሁትን፡ በከንፈሮቼም እሰጣለሁ ብዬ የተሳልኩትን
ለአንተ-እሰጣለሁ።15-ዕእጣንና ከሙክቶች ጋር ነውር የሌለበትን
ንጹሕ-መሥዋዕትን-አቀርብልሃለሁ፤ላሞችንና-ፍየሎችንም እሠዋ
ልሃለሁ።16-እግዚአብሔርን-የምትፈሩት-ሁሉ-ኑ-ስሙኝ፤ለነፍሴ-
ያደረገላትን-ልንገራችሁ፡ 17. በአፌ-ወደ-እርሱ-ጮኽሁ፡ በአንደበ
ቴም ከፍ ፡ ከፍ አደረግሁት ። 18. በልቤ በደልን አይቶ ቢሆን
ኖሮ፡ እግዚአብሔር አይሰማኝም ነበር፤ስለዚህ የልመናዬን ድምፅ
አደመጠ።-ጸሎቴን-ያልከለከለኝ-ምሕረቱንም-ከእኔ-ያላራቀ እግዘአ
ብሔር ይክበር /ይመስገን።

## መዝ ፷፮/66፡ ስለ ምድር በረከት የሚቀርብ ምስጋና

1 እግዚአብሔር-ይባርከነ ወይሣሃለነ=እግዚአብሔር ይማረን፡
ይባርከንም፡ ፊቱንም በላያችን ያብራ፤ እኛም በሕይወት
እንኑር። 2 መንገድህን በምድር በአሕዛብም ሁሉ ዘንድ ማዳን
ህን እናውቅ ዘንድ። 3 አቤቱ አሕዛብ ያመሰግኑሃል፡ አሕዛብ
ሁሉ ያከብሩሃል። አሕዛብ ደስ ይላቸዋል፡ ሐሤትም ያደርጋሉ።
4. ለአሕዛብ ቅን ፍርድን ትሰጣለህት፡ አሕዛብንም በምድር ላይ
ትመራለህና። 5 አቤቱ አሕዛብ ያመሰግኑሃል።6 ምድር ፍሬዋን
ሰጠች፤ እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል፡ የምድርም
ዳርቻ ሁሉ ይፈሩታል። 7 እግዚአብሔር ይባርከናል፡ የምድርም
ዳርቻዎች ሁሉ ያከብሩታል።



## መዝ ፷፯/67፡ የብሔራዊ ድል መዝሙር

1 ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረዉ ፀሩ=እግዚአብሔር ይነሣ፡
ጠላቶቹም-ይበተኑ፡-የሚጠሉትም-ከፊቱ-ይሸሹ።2.-ጢስ እንደሚ
በንን-እንዲሁ-ይብነኑ፤ሠም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፡ እንዲሁ
ኃጥአን ከእግዚአብሔር ፊት ይጥፉ። 3. ጻድቃን ግን ደስ
ይበላቸው፡ በእግዚአብሔር ፊትም ሐሴትን ያድርጉ፡ በደስታም
ደስ ይበላቸው ። 4 እግዚአብሔርን አመስግኑ፡ ለስሙም
ዘምሩ። ወደ ምዕራብ ለወጣው መንገድን አብጁ፤ ስሙ
እግዚአብሔር ነው፡ በፊቱም ደስ ይበላችሁ። ከፊቱም የተነሣ
ይደነግጣሉ።5. እግዚአብሔር-በቅዱስ-ቦታው-ለድሃ-አደጎች-አባት፡
ለባልቴቶችም-ዳኛ-ነው።6 እግዚአብሔር ብቸኞችን *(ባሕታውያንን)*
በኃይሉ-ያወጣቸዋል፤በመቃብር-የሚኖሩ-ጎዘንተኞችንም እንዲሁ፡
7 አቤቱ በሕዝብህ ፊት በወጣህ ጊዜ፡ በምድረ በዳም ባለፍህ
ጊዜ፡ 8 ከሲና አምላክ ፊት፡ ከእስራኤል አምላክ ፊት ምድር
ተናወጠች፡ ሰማያትም ነጠብጣብን አወረዱ።9 አቤቱ በፈቃድህ
ዝናብን ለርስትህ ለየህ፡ በደከመም ጊዜ አንተ ታፀናዋለህ።
10. እንስሶችህ በውስጡ ያድራሉ፤ አቤቱ-በቸርነትህ-ለድሆች-
ሁሉን አዘጋጀህ። 11 በብዙ ኃይል ለሚናገሩ እግዚብሔር
ቃሉን ሰጠ፤ 12 ነገሥታት ከነሠራዊታቸው-ፈጥነው ይሸሻሉ፡
በቤት የምትኖርም ምርኮን ተካፈለች። 13 በርስቶች መካከል
ብታድሩ-ከብር እንደተሠሩ እንደርግብ ክንፎች፡በቅጠልያ ወርቅም
አንደተለበጡ-ላባዎችዋ-ትሆናላችሁ።14. ሰማያዊ ንጉሥ በላይዋ
ባዘዘ ጊዜ በሰልሞን *(ተራራ)* ላይ በረዶ ይዘንማል። 15.-የእግዚአ
ብሔር ተራራ ልምላሜ የሞላበት ነው።ከልምላሜውም ጋር
የፀና ተራራ ነው። 16 የፀኑ ተራራዎች ለምን ይነሣሉ?
እግዚአብሔር ያድርበት ዘንድ የወደደው ተራራ ይህ ነው፤
እግዚአብሔር ለዘለዓለም ያድርባቸዋልና። 17.የብዙ ብዙ ሺህ
የሆኑ የእግዚአብሔር ሠረገላዎች ደስተኞች ናቸው። እግዚአብ
ሔር--በመቅደሱ-በሲና-በመካከላቸው ነው።18. ምርኮን ማርከህ፡
ወደ ሰማይ ወጣህ፡ ስጦታህንም ለሰዎች ሰጠህ፡ ያድሩ-ዘንድ-

www.ethiopianorthodox.org

(ለመኖር-ሲሉ)ይክዱ-ነበርና፡፡19.-እግዚአብሔር አምላክ ቡሩክ
ነው፤ እግዚአብሔር በየዕለቱ ቡሩክ ነው፤ አምላካችንና መድኃኒ
ታችን ይረዳናል፡፡ 20. አምላካችንስ የማዳን አምላክ ነው፤
የሞት መንገድ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር
የጠላቶቹን ራስ ይሰብራል፡ በጠጉራቸው ጫፍም በደላቸው
ይሄዳል፡፡ 22 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡- ወጥቼ-እመለሳለሁ-
በባሕሩም፡-ጥልቅ-እመላለሳለሁ-፡፡23 እግሮች በደም ይነከሩ ዘንድ
የውሾችህ ምላስ በጠላቶችህ ላይ ነው፡፡ 24. አቤቱ መንገድህ
ተገለጠ፡፡ የአምላካችን የንጉሡ መንገድ በመቅደሱ ነው፡ 25-አለ
ቆች ደረሱ፡ ከበሮን በሚመቱ ደናግል መካከል መዘምራንም-
አሏቸው፡-26.-እግዚአብሔርን-በጉባኤ አምላካችንንም በእስራኤል
ምንጮች አመስገኑት፡፡ 27. ወጣቱ ብንያም በጉልበቱ በዚያ አለ፡
የይሁዳ አለቆች፡ የዛብሎን አለቆችና የንፍታሌምም አለቆች
ገገሮቻቸው ናቸው፡ ፡28. አቤቱ በኃይልህ እዘዝ፤-አቤቱ-ይህን-
ለእኛ-የሠራኸውን-አፅናው፡፡ 29--በኢየሩሳሌም-ባለው-መቅደስህ
ነገሥታት እጅ መንሻን ለአንተ ያመጣሉ፡፡ 30 በጉሸ መቃ
ውስጥ ያሉትን አራዊት፡ በሕዝብ ጥጆች-መካከል-የኮርማ-
በሬዎችን-ጉባኤ-ገሥፅ፡-እንደ-ብር የተፈተኑት አሕዛብ እንዳይዘጉ
ሠልፍን የሚወድዱትን አሕዛብን በትናቸው፡፡ 31.-መልእክተ
ኞች-ከግብፅ-ይምጡ፤ኢትዮጵያ-እጆችዋን-ወደ-እግዚአብሔር-ትዘረ
ጋለች፡፡32-የምድር-ነገሥታት-እግዚአብሔርን-አመስግኑት፡ለአም
ላካችንም-ዘምሩ፡፡-33-በምሥራቅ በኩል ወደ ሰማየ ሰማያት
ለወጣ-(ሳረገ)-ለእግዚአብሔር-ዘምሩ፤የኃይል-መገለጫ-የሆነ ቃሉን-
እነሆ-ይሰጣል፡-34.-ለእግዚአብሔር-ምስጋናን-ስጡ፤ግርማው-በእስ
ራኤል-ላይ-ኃይሉም-እስከ-ደመናት-ነው፡፡35-እግዚአብሔር በቅዱ
ሳኑ-ላይ-ድንቅ-ነው፤የእስራኤል-አምላክ-እርሱ-ኃይልንና-ብርታትን
ለሕዝቡ ይሰጣል፤ ስለዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

## መዝ ፷፰/68፡ <u>በጨካኞች ጠላቶች ላይ የተነገረ ተግሣፅ</u>

(ስለ ክርስቶስም የተነገረ ትንቢት ያለበት ነው ) ------------

1.አድኅነኒ እግዚኦ እስመ በጽሐኒ ማይ እስከ ነፍስየ፡ አቤቱ
ውኃ እስከ ነፍሴ ሊያሰጥመኝ ደርሶብኛልና አድነኝ፡፡ 2. በጥልቅ



ረግረግ ጠለቅሁ፡ ኃይልም የለኝም፤ ወደ ጥልቁ ባሕርም ደረስሁ
ማዕበሉም አሰጠመኝ፡፡ 3 በጩኸት ደከምሁ፡ ጉሮሮዬም ሻከረ፤
አምላኬን ተስፋ ሳደርግ ዓይኖቼ ፈዘዙ፡፡ 4. በከንቱ የሚጠሉኝ
ከራሴ ጠጉር ብዙ፤ ያልወሰድሁትን ያስከፍሉኛል፡፡ 5 አቤቱ
አንተ ስንፍናዬን ታውቃለህ፡ ኃጢአቴንም ከአንተ አልተሰወርም፡
6. አቤቱ የኃያላን አምላክ የሚሹህ በእኔ አይፈሩ፤ የእስራኤል
አምላክ ሆይ ተስፋ የማያደርጉህ በእኔ አይነወሩ፡፡ 7. ስለ አንተ
ስድብን-ታግሻለሁና እፍረትም-ፊቴን ሸፍኖኛልና፡፡8 ለወንድሞቼ
እንደ ባዕድ፡ ለአባቴና ለእናቴም ልጆች እንግዳ ሆንሁባቸው፡፡
9. ለቤትህ የቀናሁት ቅንዓት በልቶኛልና፡ የሚሰድቡህም ስድብ
በላዬ ወድቆአል፡፡ 10. ሰውነቴን በጾም አደከምኋት፡ ይህም
መሰደቢያ ሆነብኝ፡፡11. ማቅ ለበስሁ መተረቻም ሆንሁላቸው፡፡
12. በደጅ የሚቀመጡ በእኔ ይጫወታሉ፤ወይን የሚጠጡም
በእኔ-ይዘፍናሉ፡፡13.-እኔስ-በጸሎቴ-ወደ-እግዚአብሔር-አመለከትሁ
.የእግዚአብሔር ይቅርታው የሚገለጥ በጊዜው ነው፤ ይቅርታህ
ብዙ ስለሆነ መድኃኒቴ ሆይ በእውነት አድነኝ ፡፡ 14.
እንዳይውጠኝ ከረግረግ አውጣኝ ፤ ከጠላቶችና ከጥልቅ ውኃ
አስጥለኝ፡፡ 15. የውኃ ማዕበል አያስጥመኝ፡ ጥልቁም አይዋጠኝ፡
ጉድጓዶችም አፋቸውን በኔ ለይ አይክፈቱ፡፡ 16.-አቤቱ
ምሕረትህ መልካም ናትና ስማኝ፤ እንደ ይቅርታህም ብዛት-
ወደ-እኔ-ተመልከት፤17.-ከአገልጋይህ-ፊትህን-አትመልስ-ተጨንቄ
አለሁና ፈጥነህ ስማኝ፡ 18. ነፍሴን ተመልክተህ ተቤዠት
(ታደጋት) ፤ ስለ ጠላቶቼም አድነኝ፡፡ 19. በሚያስጨንቁኝ ሁሉ
ፊት አንተ ስድቤን ፡ እፍረቴንና ነውሬንም ታውቃለ ህና ፡፡
20- ሰውነቴ- ስድብንና ውርደትን ታገሠች፤አዝኜ-ተቀመጥሁ፡፡
የሚያጽናናኝም-አጣሁ፡ 21.-በመብሌ-ውስጥ-ሐሞትን-ጨመሩ፡
በተጠማሁም-ጊዜ-ሆምጣጤን-አጠጡኝ፡፡-22.-ማዕዳቸው በፊታ
ቸው ለወጥመድ፡ ለፍዳና ለዕንቅፋት ትሁንባቸው፤ 23.-ዓይኖ
ቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ ፡-ጀርባቸውም ዘወትር- ይጉበጥ፡፡
24-መዓትህን-በላያቸው-አፍስስ፡-የቁጣህ-መቅሠፍት-ያግኛቸው፡፡
25.ከተማቸው-በረሃ-ትሁን፡-በድንኳኖቻቸው የሚቀመጥ አይገኝ፤
26. አንተ የቀሠፍኸውን እነርሱ ተከትለዋልና በቁስሌም ቁስልን



www.ethiopianorthodox.org

ጨመሩብኝ፡፡ 27. በኃጢታታቸው ላይ ኃጢአትን ጨምርባቸው፡
ወደ ጽድቅህም አይግቡ፡፡ 28. ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፡
ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ፡፡ 29. እኔ ድሃና ቁስለኛ ነኝ፤ የፊቴ
መድኃኒት የሆንህ እግዚአብሔር ተቀበለኝ፡፡ 30 የእግዚአብሔ
ርን--ስም-በዝማሬ-አመሰግናለሁ፡-በምስጋናም-ከፍ፡-ከፍ አደርገ
ዋለሁ፡፡31.-ቀንድና-ጥፍር-ካላቀበለ-ከእምቦሳ-ይልቅ እግዚአብሔ
ርን ደስ አሰኘዋለሁ፡፡ 32. ድሆች ይዩ፡ ደስም ይበላቸው፡፡
እግዚአብሔርን-ፈልጉት፡-ነፍሳችሁም-ትድናለች፡፡-33-እግዚአብ
ሔር-ድሆችን-ሰምቶአቸዋልና -እስረኞችንም አልናቃቸውምና፡፡-
34 ሰማይና ምድር ባሕርም በእርስዋም የሚንቀሳቀሱ ሁሉ
ያመሰግኑታል፡፡35.-እግዚአብሔር-ጽዮንን-አድኗታልና፡ የይሁዳ-
ከተሞች-ይሠራሉና፤-በዚያም-ይቀመጣሉ፡ይወርሷታል፡-36-የአገል
ጋዮችህ-ዘሮች-ይኖሩባታል፡ስምህን-የሚወድዱ-በውስጧ ይኖራሉ፡፡

## መዝ ፷፱/69፡ <u>በጭንቀት ጊዜ ተሚቀርብ ጸሎት</u>

1 እግዚኦ ነጽር ውስተ ረዲኦትየ=አቤቱ እኔን ለማዳን
ተመልከት፤ አቤቱ እኔን ለመርዳትም ፍጠን፡፡ 2 ነፍሴን
የሚሹአት ይፈሩ፡ ይጐስቍሉም፡፡ ክፉንም የሚመከሩብኝ
አፍረው ወደኋላቸው ይመለሱ፡፡ 3 "እሰይ! እሰይ " ! የሚሉ
ተዋርደው ወደ ኋላቸው ይመለሱ፡፡ 4. አቤቱ የሚሹህ ሁሉ
በአንተ ሐሤት ያድርጉ፡ ደስም ይበላቸው፡፡ ሁልጊዜ ማዳንኅን
የሚወድዱ ዘወትር "እግዚአብሔር ታላቅ ነው" ይበሉ ፡፡ 5. እኔ
ድሃና ምስኪን ነኝ፤ እግዚአብሔርም ይረዳኛል፤ ረዳቴም
መጠጊያዬም አንተ ነህ፡ አቤቱ አምላኬ አትዘግይ፡፡

## መዝ ፸/70፡ <u>እስከ ሽምግልና ዘምን የምንደገፍበት ጸሎት——</u>

1-ኪያከ ተወከልኩ እግዚኦ ወኢይትኀፈር ለዓለም=አቤቱ አንተን
ታመኛለሁናI ለዘለአለም አልፈር። 2. በጽድቅህ አድነኝ፡
ታደገኝም I ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፡ ፈጥነህም አድነኝ። 3.
በጠንካራ ቦታ ታድነኝ ዘንድ አምላኬና መድኀኒቴ አንተ ነህና።
4. አምላኬ ከኃጥአን እጅ፡ ከዓመፀኛናጌታዬ ሆይ ከታናሽነቴ
ጀምሬ ተስፋ አደረግሁህ። 6. በእናቴ ማኅፀን ከግፈኛም እጅ
አድነኝ። 5 አቤቱ አንተ ተስፋዬ ነህና ውስጥም አንተ ሸሸግኸኝI



-ሁልግዜም-ስም-አጠራሬ-አንተ-ነህ።7-.ለብዙዎች እንደ ጥንግ-
ሆይ፤-አ`ንተ ግን ረዳቴና ኀይሌ-ነህ፡፡8 አፌን
በምስጋና ሙላ፡ ሁልግዜ ምስጋናህንና የክብርህን ገናናነት
አመስግን ዘንድ፡ 9.-በሽምግልናዬ ዘመን አትጣለኝ።
ጉልበቴም ባለቀ ጊዜ አምላኬ አትተወኝ፡፡ 10.-ጠላቶቼ
በእኔ ላይ ተናግረዋልና፡ ነፍሴንም የሚሹአት በአንድነት
ተማክረዋልና፡ እንዲህም አሉ 11. እግዚአብሔር ትቶታል ፤
የሚያድነው የለምና ተከትላችሁ ያዙት ፡፡ 12. አምላኬ ሆይ
ከእኔ አትራቅ ፤ አምላኬ ሆይ! እኔን ለመርዳት ተመልከት፡፡
13.-ነፍሴን-የሚያጣኗት-ይፈሩ፡ይዋረዱም፡-ጉዳቴንም የሚፈ
ልጉ-እፍረትንና-ኃሣርን-ይልበሱ።14.-እኔ ግን አቤቱ ሁልግዜ
ተስፋ አደርግሃለሁ። በምስጋናህም ሁሉ ላይ እጨምራለሁ።15.-
አፌ-ጽድቅህንና-ሁልግዜም-ማዳንህን-ይናገራል፡ የክፋትን ሥራ
አላውቅምና፡ 16. በእግዚአብሔር ኃይል እገባለሁI አቤቱ
ጽድቅህን ብቻ አስባለሁ። 17. አምላኬ ከታናሽነቴ ጀምረህ
አስተማርኸኝI እስከ ዛሬም ክብርህን እናገራለሁ።18.-አምላኬ-
ሆይ1-እስከሽመግል ድረስ ለሚመጣ ትውልድም ሁሉ ክንድህንና
ኃይልህንም፡ ጽድቅህንም እስከነግር ድረስ አትተወኝ። 19. አቤቱ
እስከ አርያም ታላላቅ ነገሮችን አደረግህ I አምላክ ሆይ እንዳንተ
ያለ-ማን-ነው?-20.-ብዙ ጭንቀትንና መከራን አሳይተኸኛልና-
ተመልሰህም-ሕያው-አደረግኸኝIከምድር-ጥልቅም-እንደገና-
አወጣኸኝ፡21 .ጽድቅህንም አብዝተህ ደስ ታሰኘኝም ዘንድ
ተመለስህ።ከምድር ጥልቅም እንደ ገና አወጣኸኝ። 22. እኔም
በመዝሙር መሣሪያ ስለ እውነትህ አመሰግንሃለሁI የእስራአል-
ቅዱስ-አምላክ ሆይ በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ። 23 ዝማሬን
ባቀረብሁልህ ግዜ ከንፈሮቼን ደስ ይላቸዋል፡ ነፍሴንም አንተ
አዳንሃትII 24 ክፋትን ለእኔ የሚመኙ ባፈሩና-በተነወሩ-ጊዜ-
አንደበቴ ሁልግዜ-ጽድቅህን-ይናገራል።



www.ethiopianorthodox.org

መዝ ፸፩/71፡ <u>በተስፋ ስለሚጠበቀው ንጉሥ የቀረበ ጸሎት</u>

*(ፍጻሜው ግን ስለ ክርስቶስ መንግሥት የተነገረ ትንቢት)*

1 እግዚኦ ሆነኔከ ሀቦ ለንጉሥ ፤ ወጽድቀከኒ ለወልደ ንግሥ=
ለ ወለልደ ንጉሥ= አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጠው፡ ጽድቅህንም
ለንጉሥ ልጅ 2. ሕዝብህን በጽድቅ ድሆችህንም በፍርድ ይዳኝ
ዘንድ። 3. ተራሮችና ኮረብቶች የሕዝብህን ሰላም ይቀበሉ። 4
ለድሆች ሕዝብህ በጽድቅ ፍረድ፡ የድሆችንም ልጆች
አድናቸው። ትዕቢተኛውንም አዋርደው። 5. ፀሐይ በሚኖርበት
ዘመን ሁሉ በጨረቃም ፊት ለልጅ ልጅ ይኑር። 6. በባዘቶ ላይና
በምድርም ላይ እንደሚወርድ የጠል ነጠብጣብ ( ጠብታ) ሆኖ
ይወርዳል። 7 በዘመኑም ጽድቅ ይበቅላል። ጨረቃም
እስኪያልፍ ድረስ የርሱ ሰላም ብዙ ነው። 8. ከባሕርም እስከ
ባሕርና እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ይገዛል። 9. በፊቱም ኢትዮጵያ
( ኢትዮጵያውያን ) ይሰግዳሉ፡ ጠላቶቹም አፈርን ይልስሉ።
10 የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት እጅ መንሻን ያመጣሉ።
11. የምድር ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል፡ አሕዛብም ሁሉ
ይገዙለታል።12. ድሃውን ከሚቀማው-እጅ፡-ረዳት-የሌለውንም-
ምስኪን--ከሞት-እጅ ያድነዋልና። 13 ለድሃና ለምስኪን ይራራል፡
የድሆችንም ነፍስ ያድናል። 14. ከግፍና ከቅሚያ ነፍሳቸውን
ያድናታል። ስሙም በፊታቸው ክቡር ነው። 15. እርሱ ይኖራል ፤
የዓረብን ወርቅን ይሰጡታል። ሁልግዜም ስለ እርሱ ይጸልያሉ፡
ዘወትርም ይመርቁታል። 16 በተራሮች ራስ ላይ ለምድር ሁሉ
መጠጊያ ይሆናል። ፍሬውም ከሊባኖስ ዛፍ ይልቅ ከፍ፡ ከፍ
ይላል። እንደ ምድር ሥር ከከተማ ይበቅላል። 17 ስሙ
ለዘለዓለም ቡሩክ ነው። ከፀሐይም አስቀድሞ ስሙ ነበረ።
የምድርም አሕዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ ፤ ሕዝቡ ሁሉ
ያመሰግኑታል።18-ብቻውን- ተአምራትን -የሚያደርግ የእስራ



ኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን ። 19 የምስጋናው ስም
ለዓለምና ለዘለአለም ይባረክ። ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይሙላ፡
፡ ይሁን። ይሁን (ለይኩን፡ ለይኩን )።

መዝ ፸፪/72፡ <u>ልባቸው ለቀና ሰዎች የእግዚአብሔር ቸርነት</u>

1 ጥቀ ኄር እግዚአብሔር ለእስራኤል፡ ለርቱዓነ ልብ=ልባቸው
ለቀና ለእስራኤል እግዚአብሔር እጅግ ቸር ነው።2. እኔ ግን
እግሮቼ- ሊሰናከሉ፡- አረማመዴ- ሊወድቅ- ጥቂት-ቀረ።3. የዓመፀ
ኞችን ሰላም አይቼ በኃጥአን ላይ ቀንቼ ነበርና። 4. ለሞታቸው
እረፍት የለውም ፤ለመቅሠፍታቸውም ኃይል የለውምና፡ 5. በድ
ካምም ጠላት አልሆኑም። ከሰው ጋርም አልተገረፉም። 6. ስለዚህ
ትዕቢት ያዛቸው፤ ኃጢያታቸውንና በደላቸውን ተጐናፉአት።
7. መቅን /ስብ ከቅልጥም እንደሚወጣ ኃጢአታቸው ከውስጣቸው
ይወጣል።ልባቸው ከትዕቢት አለፈ። 8. አስበው ከንቱ ነገርን
ተናገሩ። በአርያምም ዓመፃን ተናገሩ። 9. አፋቸውንም በሰማይ ላይ
አኖሩ፡ አንደበታቸውም በምድር ላይ ተመላለሰ። 10 ስለዚህ ሕዝቤ
ወደዚህ ይመለሳሉ፤ ለነርሱም መልካም ዘመን ይሆናል።11 "እግዚ
አብሔር እንዴት ያውቃል? በአርያምስ በውኑ የሚያውቅ አለን?"
ይላሉ። 12. እነሆ እነዚህ ኃጥአን ደስ ይላቸዋል፤ ሁልግዜም
ባለጠግነታቸውን ያፀኗታል ፤ 13. እንዲህም አልሁ በውኑ ልቤን
በከንቱ አጸደቅኊትን? እጆቼንም በንጽሕና አጠብሁ።14. ሁልግዜም
የተገረፍሁ ሆንሁ፡ መሰደቤም በየማለዳም እሰደባለሁ ። 15. እንደ
ዚህ ብዬ ብናገር ኖሮ እነሆ የልጆችህን ትውልድ በበደልሁ ነበር።
16. አውቅም ዘንድ ተቀበልሁኝ ። ይህ ግን በፊቴ ድካም ነው።
17 ፍጻሜያቸውን አውቅ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስክገባ
ድረስ። 18 ነገር ግን ስለ ሽንገላቸው አቆየሃቸው ፡ በመነሣታቸውም
ወዲያውኑ ጣልሃኻቸው። 19. እንዴት ለጥፋት ሆኑ? እንዴትስ
በድንገት-አለቁ?-ስለ-ኀጢአታቸውም-ጠፉ።20.-ከእንቅልፍ እንደሚ



www.ethiopianorthodox.org

ነቃ አቤቱ በከተማህ ምልክታቸወን ታስነውራለህ። 21 ልቤ
ነዷል፡-ኩላሊቴም-ቀልጧልና።22.-እኔ-የተናቅሁ-ነኝ፡ አሉወቅሁም፡
በአንተ ዘንድ እንደ እንሰሳ ሆንሁ። 23. እኔ ግን ዘወትር ከአንተ ጋር
ነኝ፡ ቀኝ እጀንም ያዝኸኝ። 24. በአንተ ምክር መራኸኝ ፤ በክብርም
ተቀበልኸኝ። 25. በሰማይ ያለኝ ምንድን ነው? በምድርስ ውስጥ
ከአንተ በቀር ምን እሻለሁ? 26 የመድኃኒቴ አምላክ ሆይ! ልቤና
ሥጋዬ አለቀ፡ እግዚአብሔር ግን ለዘለዓለም ዕድል ፈንታዬ ነው።
26 ለእኔ እግዚአብሔርን መከተል ይሻለኛል፡ መታመኛዬ አንተ
ነህና። በጽዮን ልጅ በሮች አመሰግንሃለሁ።

መዝ ፸፫/73፡ <u>ሀገር ክጥፋት እንድትድን መማፀኛ ጸሎት</u> -

1 ለምንት ገደፍከነ እግዚኦ ስገዘሉፉ=አምላክ ሆይ፤ ለዘለዓለም
ስለምን ጣልኸን? በማሰማሪያህ ባሉ በጎችህስ ላይ ቍጣህ ለምን
ነደደ? 2 ጥንት ገንዘብህ ያደረግሃትን ጉባኤ፣ የዋጀሃትን
የርስትህን ነገድ፣ መኖሪያህ ያደረግሃትን የጽዮን ተራራ አስብ።
3 እርምጃህን ለዘላለሙ ባድማ ወደ ሆነው አቅና፤ ጠላት
በመቅደስህ ውስጥ ያለውን ሁሉ አበላሽቶአል። 4 ጠላቶችህ
በመገናኛ ስፍራህ መካከል ደነፉ፤ የራሳቸውንም ዓርማ ምልክት
አድርገው በዚያ አቆሙ።5 በጫካ መካከል ዛፎችን ለመቍረጥ፣
መጥረቢያ የሚያነሣ ሰው መሰሉ። 6 በእደ ጥበብ ያጌጠውን
ሥራ ሁሉ፣ በመጥረቢያና በመዶሻሰባበሩት። 7 መቅደስህን
አቃጥለው አወደሙት፤ የስምህንም ማደሪያ አረከሱ። 8 በልባቸ
ውም፣ ፈጽሞ እንጨቍናቸዋለን አሉ፤ እግዚአብሔር በምድሪቱ
ላይ የተመለከበትን ስፍራ ሁሉ አቃጠሉ። 9 የምናየው ምልክት
የለም፤ ከእንግዲህ የሚነሣ አንድም ነቢይ የለም፤ ይህ እስከ
መቼ እንደሚቀጥል የሚያውቅ በእኛ ዘንድ የለም። 10 አምላክ
ሆይ፤ ጠላት የሚያሾፈው እስከ መቼ ነው? ባላንጣስ ለዘላለም
በስምህ ያላግጣልን? 11 እጅህን ለምን ትሰበስባለህ? ቀኝ
እጅህን ለምን በብብትህ ሥር ታቆያለህ? 12 አምላክ ሆይ፤



አንተ ከጥንት ጀምሮ ንጉሤ ነህ፤ በምድር ላይ ማዳንን
አደረግህ። 13 ባሕርን በኀይልህ የከፈልህ አንተ ነህ፤ የባሕሩንም
አውሬ ራሶች በውሃ ውስጥ ቀጠቀጥህ። 14 የሌዋታንን ራሶች
አደቀቅህ፤ ለምድረ በዳ ፍጥረታትም ምግብ አድርገህ ሰጠ
ሃቸው፣ 15 ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ አንተ ነህ፤
ሳያቋርጡ የሚፈሱትንም ወንዞች አደረቅህ። 16 ቀኑ የአንተ
ነው፤ ሌሊቱም የአንተ ነው፤ ጨረቃንና ፀሓይን አንተ
አፀናሃቸው። 17 የምድርን ዳርቻ ሁሉ የወሰንህ አንተ ነህ፤
በጋውንም ክረምቱንም አንተ ሠራህ። 18 እግዚአብሔር ሆይ፤
ጠላት እንዴት እንደሚያሾፍ፣ ከንቱ ሕዝብም ስምህን እንዴት
እንዳቃለለ አስብ። 19 የርግብህን ነፍስ አሳልፈህ ለዱር አራዊት
አትስጥ፤ የችግረኞች ሕዝብህን ሕይወት ለዘላለሙ አትርሳ።
20 ኪዳንህን አስብ፤ የዓመፅ መናኸሪያ በምድሪቱ ጨለማ
ስፍራዎች ሞልተዋልና። 21 የተጨቈኑት አፍረው አይመለሱ፤
ድኾችና ችግረኞች ስምህን ያመስግኑ። 22 አምላክ ሆይ፤
ተነሥ፤-ለክብርህ-ተሟገት፤-ከንቱ-ሰው ቀኑን ሙሉ እንደሚያላግጥ
አስብ።23-ዘወትር-የሚነሣውን-የባላጋራዎችህን ድንፋታ አትርሳ።

መዝ &4/74፡ <u>ስለ አምላካዊ ፍትሕ የቀረበ ተማኅፅኖ</u> -------1

እገኒ ለከ እግዚኦ እገኒ ለከ=አምላክ ሆይ፤ እገዛልሃለሁ፡
ምስጋናም እቀርብልሃለሁ፤ ስምህ ቅርብ ነውና ምስጋና
እቀርብልሃለሁ፤ሰዎችም ድንቅ ሥራህን ይናገራሉ። 2 አንተም
እንዲህ አልህ፤ ኝለይቼ በወሰንኋት ሰዓት፣ በቅን የምፈርድ እኔ
ነኝ።3 ምድርና ሕዝቦችዋ ሁሉ በሚናወጡበት ጊዜ፣ ምሰሶችዋን
አፅንቼ የምይዝ እኔ ነኝ። 4 ዕብሪተኛውን ኝአትደንፉ፤
ክፉውንም ቀንድህን ከፍ ፡ከፍ አታድርግ እለዋለሁ፤ 5 ቀንድህን
ወደ ሰማይ አታንሣ፤ አንገትህንም መዝዘህ አትናገር። 6 ክብር
ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ፣ ወይም ከምድረ በዳ
አይመጣምና፤ 7 ነገር ግን የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ
አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ ያደርጋል። 8 በእግዚአብሔር እጅ



www.ethiopianorthodox.org

ጽዋ አለ፤ በሚገባ የተቀመመና ዐረፋ የሚወጣው የወይን ጠጅ
ሞልቶበታል፤ ይህን ከውስጡ ወደ ውጭ ገለበጠው፤ የምድር
ዐመፀኞችም አተላው ሳይቀር ይጨልጡታል። 9 እኔ ግን ይህን
ለዘላለም ዐውጃለሁ፤ ለያዕቆብ አምላክ ዝማሬ አቀርባለሁ።
10 እርሱ የክፉዎችን ቀንድ- እሰብራለሁ፤ የጻድቃን ቀንድ ግን
ከፍ ይላል ብሏልና።

## መዝ ፸፭ /75፡ የእግዚአብሔርን ግርማ የሚገልጥ ቅኔ

1 ተዐውቀ እግዚአብሔር በይሁዳ= እግዚአብሔር በይሁዳ
ታወቀ፤ ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው። 2 ድንኳኑ በመረጣት
አገር፣ ማደሪያውም በጽዮን ነው። 3 በዚያም ተወርዋሪውን
ፍላጻ፣ ጋሻንና ሰይፍን፣ ጦርንም ሰበረ። 4 አንተ አንጸባራቂ
የሆነውን ብርሃን ተላብሰህ ደምቀሃል፤ ግርማህም ከዘላለም
ተራሮች ይልቃል።5 ልበ ሰነፎች ሁሉ ደነገጡ፡ ሕልምን
አለሙ ። የሰው ሁሉ አሳብ ስለ እጁ ብልጽግና ብቻ ነው።
6 የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ከተግሣፅህ የተነሣ፣ ፈረስና
ፈረሰኛው ዝለው ተኝተዋል።7 መፈራት ያለብህ አንተ ብቻ
ነህ፤ በተቈጣህ ጊዜ ማን በፊትህ መቆም ይችላል? 8 አንተ
ፍርድን ከሰማይ አሰማህ ፤ ምድርም ፈርታ ጸጥ አለች ፤
9 አምላክ ሆይ፤ ይህም የሆነው አንተ ልበ ቅኖችን ለማዳን፣
ለፍርድ በተነሣህ ጊዜ ነው። 10 ሰው በፊቃዱ ያመሰግንሃል።
ከኀሊናቸው ትርፍም በዓልህን ያደርጋሉ። ለአምላካችን
ለእግዚአብሔር-ስእለትን-ስጡ።-በእርሱ-ዙሪያ-ያሉ-ሁሉ መፈራት
/መከበር ለሚገባው ለርሱ እጅ መንሻን ያገባሉ።፡መፈራት
/መከበር ለሚገባው ለርሱ እጅ መንሻ ያምጡ።12 እርሱ
የገገሮችን ነፍስ ያወጣል።በምድር ነገሥታትም ዘንድ ይከብራል።



## መዝ ፸፮ /76፡ እግዚአብሔር ለዘለዓለም ይጥላልን ?

1 ቃልየ ኀበ እግዚአብሔር ጸራሕኩ፡ =በቃሌ ወደ እግዚአብሔር
ጮኽሁ፡ እርሱም አደመጠኝ /ሰማኝ። 2 በመከራዬ ቀን እግዚአ
ብሔርን ፈለግሁት፡እጆቼም በሌሊት ወደ እርሱ የተዘረጉ
ናቸው። ስለዚህም ጠላቶቼ አልረገጡኝም። ነፍሴ ግን ደስታን
አጣች። 3 እግዚአብሔርን አሰብሁት፡ ደስ አለኝም። ተናገርሁ፡
ነፍሴም ፈዘዘች። የጠላቶቼን ሰዓቶች አወቅኋቸው፡ 4 ደነገጥሁ፡
ምንም አልተናገርሁም።5-የድሮውን-ዘመን-አሰብሁ፡የዘለዓለምንም
ዓመታት-አሰብሁ፡-አነበብሁም፡-6-በሌሊት-ከልቤ-ጋር ተጫወትሁ፡
መንፈሴንም አነቃቃኋት። 7 እግዚአብሔር በውኑ ለዘለዓለም
ይጥላልን? ከእንግዲህስ ወዲህ ይቅርታውን አይጨምርምን?-
ለዘለዓለምስ-ምሕረቱን-ለልጅ-ልጅ-ይቈርጣልን? 8 እግዚአብሔር
ይቅርታን ይረሳልን? በቍጣውስ ምሕረቱን ዘጋውን?-10-እነሆ-
ዛሬ-ጀመርሁአልሁ፡-ልዑል-ቀኙን-እንደሚያፈራርቅ።11 የእግዚአ
ብሔርን-ሥራ-አስታወስሁ፡-የቀድሞውን-ታምራትህን አስታውሳለ
ሁና፡-12-በምግባርህ-ሁሉ-እናገራለሁ፡በድንቅ=ሥራህም-እጫወታ
ለሁ። 13 አቤቱ መንገድህ በመቅደስህ ውስጥ ነው፡ እንደ
አምልክችን ያለ ታላቅ አምላክ ማነው? ታምራትን የምታደርግ
አምላክ አንተ ብቻ ነህ፡ ለሕዝብህ ኃይልህን አሳየሃቸው።
15- የያዕቆብንና -የዮሴፍን-ልጆች፡-ሕዝብህንም-በክንድህ አዳንሃ
ቸው። 16 አቤቱ ውኆች አዩ፡ ውኆች አይተውህ ፈሩ፡
የውኆች ጥልቆች ሁሉ ተነዋወጡ፡ ውኆቻቸውም ጮሁ።
17 ደመናት ድምፅን ሰጡ፡ ፍላጻዎችህም ድምፅን ሰጡ።
ፍላጻዎፕችህም ወጡ። 18 የነጐድጓህ ድምፅ በሠረገላ ነበር፡
መብረቆች ለዓለም አበሩ፡ ምድር-ተናወጠች፡ ተንቀጠቀጠችም።
19 መገድህ በባሕር ውስት ነው፡ ፍለጋህም በብዙ ውኆች



www.ethiopianorthodox.org

ስለሆነ ነው፡ አይታወቅም። 20 በሙሴና በአሮን እጅ ሕዝብህን
እንደ በጎች መራሓቸው።

መዝ ፸፯/77፡ <u>የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንንዳይረሳ ማሰብ</u>

1 አፅምዑ ሕዝብየ ሕግየ ወጽልዉ ዕዝነክሙ ኀበ ቃለ አፉየ=
ሕዝቤ ሆይ1 ሕጌን አድምጡ፡ ጆሮአችሁንም ወደ አፌ ቃል
አዘብሉ።2-አፌን-በምሳሌ-እከፍታለሁ፡-ከቀድሞ-ጀምሮ የተሰወረ
ውን ምሳሌ እናገራለሁ፡ የሰማነውንና ያየነውን፡ አባቶቻችንም
የነገሩንን፡ ለሚመጣው ትውልድ ከልጆቻቸው አልሰወሩም።
4 የእግዚአብሔርን ምስጋና ተናገሩ፡ ኃይሉንና ያደረገውንም-
ታምራት። 5-ለያዕቆብ-ያቆመውን-ምስክር፡-ለእስራኤል-የሠራውን
ሕግ፡ ለአባቶቻችን ያዘዘውን ለልጆቻቸው ይነግሩ ዘንድ፡6 -የሚ
መጣ ትውልድ፡ የሚወለዱም ልጆች-ያውቁ-ዘንድ፡ተነሥተው -
ለልጆቻቸው=ይናገራሉ።7-ተስፋቸውን-በእግዚአብሔር-ላይ ማድ
ረግ እንዲችሉ፡ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድይረሱ፡ ትእዛዙንም
እንዲፈልጉ እንጂ፡ 8 እንደ አባቶቻቸው እንድይሆኑ፡ ጠማማና
የምታስመርር ትውልድ፡ ልብዋን ያላቀናች ትውልድ፡ ነፍስዋ
በእግዚአብሔር ዘንድ ያልታመነች። 9 የኤፍሬም ልጆች
ለሠልፍ ታጥቀው ቀሥስትን ገተሩ፡ በሠልፍ ቀን ግን ወደ
ኋላቸው-ተመለሱ።10-የእግዚአብሔርን-ቃል-ኪዳን አልጠበቁምና፡
በሕጉም መመላለስን እምቢ አሉ፡ 11-ረድኤቱንና-ያሳያቸውን-
ታምራቱን-ሁሉ-ረሱ፡ 12 በግብጽ አገርና በጣኔዎስ በረሃ፡
በአባቶቻቸው ፊት የሠራውን ታምራት፡ 13 ባሕርን ከፍሎ
አሳለፋቸው፡ ውኆችንም እንደ ክምር አቆመ። 14 ቀን በደመና
መራቸው፡ ሌሊቱንም ሁሉ በኣሳት ብርሃን። 15 ዐለቱን
በምድረ በዳ ሰነጠቀ፡ ከጥልቅ እንደሚገኝ ያህል ውኃን አብዝቶ
አጠጣቸው። 16 ከጭንጫ አፍልቆ ውኃን እንደ ወንዞች
አፈሰሰ። 17 ነገር ግን እርሱን መበደልን እንደገና-ደገሙ፡-



ልዑልንም-በምድረ-በዳ-አስመረሩት። 18- ለነፍሳቸው ምግብን-
ፈልገው፡19-እግዚአብሔርን እንዲህ-ብለው -አሙት፡-"እግዚአብ
ብሔር-በምድረ- በዳ-ማዕድን መሥራት ይችላልን? 20 ዐለቱንስ
በመምታት ውኃን ማፍለቅ ይቻለዋልን? እንጀራን መስጠትና
ለሕዝቡስ ማዕድ መሥራት ይችላልን?" 21 እግዚአብሔርም
ይህን ሰምቶ-ተቈጣ፡ በያዕቆብም ላይ እሳት ነደደ፡ መቅሠፍት
በእስራኤል-ላይ-መጣ።22 በእግዚአብሔር አላመኑም፡ በማዳኑም
አልተማመኑምና።23 ደመናውን ከላይ አዘዘ፡ የሰማይንም ደጆች
ከፈተ፡ 24-ይበሉ ዘንድ-መና-አዘነመላቸው፡የሰማይን-እንጀራ-
ሰጣቸው።25 የመላእትንም እንጀራ የሰው ልጆች በሉ።
የሚበቃቸውን ስንቅ ላከላቸው። 26 ከሰማይ የደቡብን ነፋስ
አስነሣ። በኃይሉም፡ የሰሜንን ነፋስ አመጣ፡ 27 ሥጋንም እንደ
አፈር፡ የሚበሩ ወፎችንም እንደ ባሕር አሸዋ አዘነመላቸው፡
28--በሠፈራቸውመሐል፡ በድንኳናቸውም ዙሪያ ወደቀ።29 በሉ፡
እጅግም-ጠገቡ፡-የተመኙትን-ሰጣቸው።-30--ከተመኙትም-ሁሉ-
ምንም አላሳጣቸውም። ምግባቸውም ገና በአፋቸው ላይ ሳለ፡
የእግዚአብሔር-መቅሠፍት-/ቍጣ-በላያቸው-ላይ-መጣ።31-የእግዚ
አብሔርም መቅሠፍት ከእነርሱ ብዙዎችን ገደለ፤ የእስራኤልንም
ምርጦች አሰናከለ። 32 ከዚህም ሁሉ ጋር እንደገና እርሱን በደሉ።
ተአምራቱንም-አላመኑም፤-33-ቀኖቻቸው-በከንቱ--አለቁ-ዓመቶቻ
ቸውም በችኮላ አለፉ። 34 በገደላቸውም ጊዜ ወዲያው ፈለጉት፤-
ተመልሰው፤ወደ-እግዜአብሔር-ገሠገሡ።-35-ረዳታቸውም-እግዜአ
ብሔር፡መድኃኒታቸው ልዑል እግዘአብሔር እንደሆነ አስቡ። 36
በአፋቸው ብቻ ወደዱት፤ በአንደበታቸው ዋሹበት፤ 37 ልባቸውም
ከእርሱ ጋር አልቀናም፤ በቃል ኪዳንም አልተማመኑበትም። 38
እርሱ ግን መሐሪ ነው፤ ኃጢያታቸውን ሁሉ ይቅር አላቸው፡
አላጠፋቸውምም፤ ቁጣውን መመለስን--አበዛ፤ መዓቱም ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲቃጠል አላዳረገም። 39 ሥጋም እንደሆኑ አሰበ። መንፈስ
ከወጣ በኃላ አይመለስምና ፤ 40 በምድረበዳ ያን ያህል አስቆጡት፤
በበረሃም አሳዘኑት። 41-ተመልሰው፡ እግዚአብሔርን ፈተኑት፤
የእስራኤልንም ቅዱስ አሳዘኑት 42 እነርሱም እጁን አላሰቡም፤
ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳነበትን፤ 43 በግብፅ ያደረገውን ተአምራቱን፡
በጣኔዎስም በረሃ ያደረገውን ድንቅ ሥራውን ረሱ። 44 -ወንዞቻች
ውን ወደ ደም ለወጠ፤ ምንጮቻቸውንም ደግም እንዳይጠጡ
45 ተቆናጣጭ ዝንቦችንም በላያቸው ሰደደባቸው፡ በሉአቸውም፤
ጓጉንቸሮችን ሰደደ፤ አረከሷቸውም። 46 ፍሬያቸውንም ለኩብኩባ፤
የእጃቸውንም ሥራ ለአንበጣ ሰጠ፡፡፡ 47 ወይናቸውንም በበረዶ፤
በለሳቸውንም በውርጭ አጠፋ። 48 እንስሶቻቸውንም ለበረዶ፤
ሀብታቸውንም ለእሳት ሰጠ። 49 የመዓቱን መቅሠፍት በላያቸው
ሰደደ፤ 50 ለቁጣውም መንገድን ጠረገ፤ ነፍሳቸውንም ከሞት
አላዳናትም፤እንሶቻቸውንም በሞት ውስጥ ዘጋ፤ 51 በኵር ሆኖ
የተወለደላቸውን የሰውንና የእንስሳት አራዊት ዘር ሁሉ በግብፅ
ምድር-ገደለ።-52-ሕዝቡን-ግን-እንደበጎች-አሠማራቸው፤ እንደመን
ጋም ወደ ምድረ በዳ አወጣቸው ። 53 በተስፋም መራቸው፡
አልፈሩምም፤ ጠላቶቻቸውንም ባሕር ደፈናቸው። 54 -ወደ-
መቅደሱም-ተራራ-ወሰዳቸው፤ቀኙ-ወደ ፈጠራቸው ተራራ፤ 55-ከፊ
ታቸውም አሕዛብን አባረረ፤ርስታቸውንም በገመድ አካፈላቸው፤
የእስራኤልንም ነገደ ሕዝብ በቤታቸው አኖረ፡ 56 -ሕዝቡ ግን
ልዑል እግዚአብሔርን ፈተኑት፤ አሳዘኑትም፤ ምስክሩንም-
አልጠበቁም፤57-ተመልሰው፤እንደአባቶቻቸው-ከዱ፤-እንደ ጠምማ
ቀስት-ሆኑ፤58-በኮረብቶቻቸው-አስቆጡት።-በተቀረጹ ምስሎቻቸው
"አስቀኑት። 59 እግዚአብሔር ይህን ሰምቶ ተቆጣ። እስራኤልንም
እጅግ ናቃቸው። 60 የሴሎምን ድንኳኑን ተዋት፤ በሰዎች መካከል
ያደረባትን ድንኳኑን። 61 ኃይላቸውንም ለምርኮ፤ ጌጣቸውንም



ለጠላት እጅ አሳልፎ ሰጠ። 62 ሕዝቡንም በጦር ውስጥ ዘጋቸው፤
እነርሱንም ቸል አላቸው። 63 ጎልማሶቻቸውን እሳት በላቻቸው፤
ቆነጃጅቶቻቸውንም አላለቀሱም። 64 ካህናቶቻቸውም በሰይፍ
ተመትተው-አላለቀሱላቸውም።--65-እግዚአብሔርም-ጐልማሳ
ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ተነሣ፡-የወይን ስካር እንደተው እንደ
ኃያልም ሰው ፤ 66 ጠላቶቹንም በኋላው ገደለ ፤ የዘላለምንም
ነሳር ሰጣቸው። 67 የዮሴፍንም ድንኳን ተዋት፤ የኤፍሬምንም
ወገን አልመረጠውም፤ 68 የይሁዳን ወገን ግን መረጠ፤ የወደደውን
የጽዮንን ተራራ፡ 69--መቅዱሱን እንደ አርያም፤ ሠራ፡ ለዘላለምም
በምድር ውስጥ መሠረታት። 70 አገልጋዩን ዳዊትንም መረጠው፡
ከበጎቹ መንጋ ውስጥ ወሰደው፤ 71-ከሚያጠቡ በጎኖችም በኋላ
አገልጋዩን -ያቆብንና ርስቱን እስራኤልን ይጠብቅ ዘንድ
ወሰደው፡፡72 በልቡ ቅንነት ጠበቃቸው፤ በእጁ ጥበብም መራቸው።

## መዝ ፸8 /78፡ እናት አገር በጠላት እጅ ስትወድቅ

1 እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ= አቤቱ አሕዛብ ወደ ርስትህ
ገቡ፤ ቤተ መቅደስህንም አረከሱ፤ ኢየሩሳሌምንም እንደ ተክል ጠባቂ
ጎጆ አደረጓት። 2 የአገልጋዮችህንም በድኖች ለሰማይ ወፎች መብል
አደረጉ፤ የጻድቃንህንም ሥጋ ለምድር አራዊት ፤ 3 ደማቸውንም
በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ውኃ አፈሰሱ፤ የሚቀብራቸውም አጡ ።
4 ለጎረቤቶቻችንም ስድብ ሆንን ፤ በዙሪያችንም ላሉት ሁሉ
መሣቂያና መዘበቻ። 5 አቤቱ፤ እስከ መቼ ለዘለዓለም ትቈጣለህ?
ቅንዓትህም እንደ እሳት ይነድዳል? 6 በማያውቁህም አሕዛብ ላይ፡
ስምህንም በማትጠራ መንግሥት-ላይ መዓትህን አፍስስ፤ 7 ያዕቆ
ብን በልተውታልና፤ መኖሪያውንም ባድማ አድርገዋልና፡ 8 የቀደ
መውን--በደላችንን--አታስብብን፤-አቤቱ-ምሕረትህ-ፈጥኖ ይድረ
ስልን፡ እጅግ ተቸግረናልና። 9 አምላካችንና መድኀኒታችን ሆይ፤
እርዳን፤-ስለስምህ -ክብር- አቤቱ፤-ታደገን፤-ስለ-ስምህም ኃጢአታ



www.ethiopianorthodox.org

ችንን አስተሰርይልን፡ 10 አሕዛብ፤ "አምላካችው ወዴት ነው?"
እንዳይሉን፤ የፈሰሰውን የአገልጋዮችህን ደም በቀል ስትመልስ
በዓይኖቻችን ፊት አሕዛብ ይዩ። 11 የእስረኞች ጩኸት ወደ ፊትህ
ይገባ፤ እንደ ክንድህም ታላቅነት የተገደሉትን ሰዎች ልጆች
ጠብቃቸው። 12 አቤቱ የተገዳደሩህን ሁሉ ለጎረቤቶቻችን ሰባት
እጥፍ ክፈላቸው። 13 እኛ ሕዝብህና የማሰማሪያህም በጎች ግን
ለዘለዓለም እናመሰግንሃለን፤ ለልጅ ልጅም ምስጋናህን እንናገራለን።

## መዝ-፸፱/79፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት መማጸኛ

1-ኖላዊሆሙ-ለእስራኤል-አፅምዕ=ዮሴፍን-እንደ-በግ-መንጋ የምት
መራው፤ የእስራኤልን ጠባቂ ሆይ፤ አድምጥ፤ በኩሩቤል ላይ
የምትቀጥ፤ ተገለጥ፡2 በኤፍሬምና በብንያም፡ በምናሴም ፊት እኛን
ለማዳን ኃይልህን አንሣ፤ ፡ 3 የኃያላን አምላክ አቤቱ መልሰን፤
ፊትህንም አብራ፡ እኛም እንድናለን። 4 የኃያላን አምላክ አቤቱ፤
በአገልጋይህ ጸሎት ላይ እስከ መቼ ትቈጣለህ?5-የእንባችንን
እንጀራ-ትመግበናለህ፤-እንባችንንም-በስፍር-ታጠጣናለህ።6 ለጎረቤ
ቶቻችንም-መነጋገሪያ-አደረግኸን፤-ጠላቶቻችንም-በላያችን ተሳለቁ
ብን። 7 የኃያላን አምላክ አቤቱ መልሰን፤ ፊትህንም አብራ፡ እኛም
እንድናለን። 8 ከግብጽ የወይንን ግንድ አመጣህ፤ አሕዛብን
አባረርህ፤ እርስዋን በነርሱ ቦታ ተከልህ። 9 በፊቷ መንገድህን
ጠረግህ፤ ሥሮችዋንም ተከልህ፤ ምድርንም ሞላች። 10 ጥላዋ
ተራሮችን ከደነ፤ ጫፎችዋ እንደ እግዚዘአብሔር ዝግባ ሆኑ። 11 ቅር
ንጫፎችዋን እስከ ባሕር፡ ቡቃያዋንም እስከ ወንዙ ዘረጋች።
12 አጥርዋን ለምን አፈረስህ? መንገድ አላፊም ሁሉ ይበላታል።
13 የበረሃ አርእያ አረከሳት፤ የዱር አውሬም መሠማሪታ አደረጋት፡
14 የኃያላን አምላክ ሆይ፤ እባክህ ተመለስ፤ ከሰማይ ተመልከት፤
እይም፤ ይህችንም የወይን ግንድ ይቅር በላት። 15 ለአንተ
ያጸናሃትንና፡ ቀኝህ የተከላትን ይህችን ወይን አፅንተህ አነሣሣት።



16 በእሳት ተቃጥላ ተነቅላማለችና፡ ከፊትህ ተግሣፅም የተነሣ
ይጠፋሉ።17 አንተ ባፀናኸው በሰው ልጅ ላይ፤ በቀኝህ ሰው ላይ
እጅህ- ይሁን። 18--ከአንተም-አንራቅ፤-አድነን፤-ስምህንም እንጠራ
ለን። 19 አቤቱ መልሰን፤ ፊትህንም አብራልን እኛም እንድናለን።

## /መዝ ፸፱ 79፡ አገርን ከውድቀት ለማንሣት

1 ኖላዊሆሙ ልእስራኤል አፅምዕ= ዮሴፍን እንደ በግ መንጋ
የምትመራ፤ የእስራኤልን ጠባቂ ሆይ፤ አድምጥ፤ በኩሩቤል
ላይ የምትቀጥ፤ ተገለጥ። 2 በኤፍሬምና በብንያም በምናሴም
ፊት ኃይልህን አንሣ፤ እኛንም ለማዳን ና። 3 የኃያላን አምላክ
አቤቱ መልሰን፤ ፊትህንም አብራ፡ እኛም እንድናለን፡ 4 የኃያላን
አምላክ አቤቱ፤ በባሪያህ ጸሎት ላይ እስከ መቼ ትቈጣለህ?
5 የእንባችንን እንጀራ ትመግበናለህ፤ እንባችንንም በስፍር
ታጠጣናለህ።-6-ለጎረቤቶቻችንም-መነጋገሪያ-አደረግኸን፤ ጠላቶቻ
ችንም በላያችን ተሳለቁብልን። 7 የኃያላን አምላክ አቤቱ
መልሰን፤ ፊትህንም አብራ፡ እኛም እንድናለን። 8 ከግብፅ
የወይንን ግንድ አመጣህ፤ አሕዛብህን አባረርህ፤ እርስዋንም
ተከልህ።9 በፊቷ መንገድህን ጠረግህ፤ ሥሮችዋንም ተከልህ፤
ምድርንም ሞላች። 10 ጥላዋ ተራሮችን ከደኑ፤ጫፎችዋም
እንደ እግዚዘአብሔር ዝግባ ሆኑ። 11 ቅርንጫፎችዋንም እስከ
ባሕር ቡቃያዋንም እስከ ወንዙ ዘረጋች። 12 አጥርዋን ለምን
አፈረስህ? መንገድ አላፊም ሁሉ ይበላታል። 13 የበረሃ አርእያ
አረከሳት፤ የዱር አውሬም ተሰማራበት። 14 የኃያላን አምላክ
ሆይ፤ እባክህ ተመለስ፤ ከሰማይ ተመልከት፤ እይም፤ ይህችንም
የወይንን ግንድ ይቅር በላት።15 በሰው ልጅ ለአንተ
ያፀናሃትንና ቀኝህ የተከላትን አፅንተህ አነሣሣት። 16 በእሳት
ተቃጥላለች፤ ተጕሣቍላለች፡ ከፊትህ ተግሣፅም የተነሣ
ይጠፋሉ።17 ለአንተ ባፀናኸው በሰው ልጅ ላይ፤ በቀኝህ ሰው
ላይ እጅህ ይሁን። 18 ከአንተ አንራቅ፤ አድነን፤ ስምህን
እንጠራለን። 19-የኃያላን አምላክ አቤቱ መልሰን፤ ፊትህንም
አብራ እኛም እንድናለን።



www.ethiopianorthodox.org

### መዝ ፹/80፡ የክብረ በዓል ቅኔያዊ መዝሙር

1-ተፈሥሑ-በእግዚአብሔር-ዘረድአነ፡-ወየብቡ-ለአምላከ-ያዕቆብ
በረዳታችን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ፤ ለያዕቆብ አምላክ
እልል በሉ። 2 ዝማሬውን ስጡ፡-ከበሮንም አንሡ፤ ደስ የሚያሰኘውን
በገና ከመሰንቆ ጋር፡-3 በታወቀችው በመባቻ በዓላችን ቀን
መለከትን ንፉ፤ 4 ለእስራኤል ሥርዐቱ ነውና፡ የያዕቆብም አምላክ
ፍርድ ነውና። 5 ወደ ግብፅ ሀገር በሄደ ጊዜ ለዮሴፍ ምስክርን አቆመ፡
የማያውቀውን ቋንቋ ሰማ። 6 ጀርባውን ከመስገጃቸው መለሰ።
እጆቹም-በቅርጫት እህል በመሥፈር አገልግሎት ሰጡ። 7 በመከ
ራህ ጊዜ ጠራኸኝ፤-አዳንሁህ፤በተሰወረ አውሎ ነፋስ መለስሁልህ፤
በክርክር ውኃ ዘንድም ፈተንሁህ። 8 ሕዝቤ ሆይ 1 ስማኝ፡
አነግርሃለሁም፤ እስራኤል ሆይ እመሰክርልሃለሁ። 9 አንተስ
ብትሰማኝ የድንገት አምላክ አልሆንህም፤ ለሌላ አምላክም አትስገድ፡
10 ከግብጽ ምድር ያወጣሁህ እኔ እግዜአብሔር አምላክህ ነኝና፤-
አፍህን-አስፋ፤-እሞላዋለሁም።11-ሕዝቤ-ግን-ቃሌን አልሰሙኝም፡-
እስራኤልም-አላዳመጡኝም።-12=ስለዚህ-እንደ-ሥራቸው ላክሁባ
ቸው፤ በልባቸውም ዐሳብ ሄዱ። 13 ሕዝቤስ ቃሌን ሰምተውኝ
ቢሆን-ኖሮ፤-እስራኤል-በመንገዴ-ሄድው-ቢሆን-ኖሮ፡-14-ጠላቶቻቸ
ውን--ፈጥኜ-ባዋረድሁቸው-ነበር፤ በሚያስጨንቋቸውም ላይ- እጄን
በጫንሁ ነበር፤15 የእግዚአብሔር ጠላቶችስ ዋሽተዋል፡ ሕዝቡ
የሚኖሩበት ዘመን ለዘለዓለም ይሆናል፤ 16 ከስንዴም ስብ
መገባቸው፤ ከዓለቱም የማር ወለላን አጠገባቸው።

### መዝ ፹፩ /81፡ እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ

1-እግዚአብሔር ቆመ ውስተ ማኅበረ አማልክት=እግዚአብሔር
በአማልክት ማኅበር መሐል ይፈርዳል። 2 እስከ መቼ ዓመፃን
ትፈርዳላችሁ? 3 ለድሆችና ለድሃ - አደጎች ፍረዱ፤ ለተገፋውና
ለምስኪኑ ጽድቅን አድርጉ፤4 ብቸኛውንና ችግረኛውን አድኑ፤



ከኃጥአንም እጅ አስጥሉአቸው።5 አያውቁም፤ አያስተውሉምም፤
በጨለማ ውስጥም ይመላለሳሉ፤ የምድር መሠረቶች ሁሉ
ተናወጡ። 6 እኔ ፤ "አማልክት ናችሁ፤ሁላችሁም የልዑል ልጆች
ናችሁ"-እልሁ፡7 እናንተ ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ፤ ከአለቆችም
እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ። 8 አቤቱ ተነሥ፤ በምድር ላይም
ፍረድ፤ አንተ አሕዛብን ሁሉ ትወርሳለህና።

### መዝ ፹፪/82፡ የሕዝብ ጠላቶችን የሚመለከት ጸሎት ---

1 እግዚኦ መኑ ከማከ፡ ኢታርምም ወኢትጸመም እግዚኦ=አቤቱ
እንደ አንተ ማን ነው? አቤቱ ዝም አትበል፤ ቸልም አትበል። 2 እነሆ
ጠላቶችህ--ጮኸዋልና። ጠላቶችህ -ራሳቸውን -አንሥተዋልና ።
3 ሕዝብህን በምክር ሸነገሏቸው፤በቅዱሳንህም ላይ ተማከሩ 4 "ኑ
ከአሕዛብ ለይተን እናጥፋቸው። ከእንግዲህ ወዲያ የእስራአልን
ስም አይጥሩ /አያስቡ " አሉ 5 በአንድነት ተካክለው ተማክረዋልና፤
በአንተ ላይ ሤራ ቈረጡ፤ ቃል ኪዳንም አደረጉ፤ 6 የኤዶሚያስ
ወገኖች፤ እስማኤላውያንና ሞባውያንም፡ አጋራውያንም፤ 7 ጌባል፤
አሞንና አማሌቅም፤ፍልስጤማውያንም ከጢሮስ ሰዎች ጋር፤
8 አሦርም ከእነርሱ ጋር ተባበረ፤ ለሎጥ ልጆችም ረዳት ሆኑአቸው።
9 እንደ ምድያምና እንደ ሲሣራ፤ በቂሶንም ወንዝ እንደ ኢያቢስ
አድርግባቸው። 10 አለቆቻቸውን እንደ ሔሬብና እንደ ዜብ፤
ታላላቆቻቸውን-ሁሉ እንደ-ዛብሄልና-እንደ ሰልማና- አድርጋቸው፡
12 የእግዚአብሔርን መሠዊያ እንወርሳለን የሚሉትን። 13 አምላኬ
ሆይ-እንደ--መንኰራኵር።-በእሳት-ፊትም-እንደገኝ-ገለባ አድርጋ
ቸው። 14 እሳት ዱሩን እንደሚያቃጥል፤ ነበልባልም ተራሮችን
እንደሚያነድ፤ 15 እንዲሁ በቁጣህ አሳድዳቸው። በመቅሠፍትህም
አስደንግጣቸው። 16 በፊታቸውም ላይ እፍረትን ሙላ፤ አቤቱ
ስምህን ይወቁ። 17 ይፈሩ፡ ለዘለዓለሙም ይታወኩ፤ ይጐስቆሉ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይጥፋም። 18 ስምህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ ፤ በምድር ሁሉ ላይም አንተ ብቻ ልዑል እንደ ሆንህ ይወቁ።

## መዝ ፹፫/83፡ <u>ከቤተ እግዚአብሔር ሳይለዩ ስለመኖር</u>

1 ጥቀ ፍቁር አብያቲከ እግዚኦ እግዚአ ኃያላን=የኃያላን አምላክ ሆይ! ማደሪያዎችህ እጅግ የተወደዱ ናቸው። 2 አቤቱ ነፍሴ አደባባዮችህን በመውደድ ደስ አላት፤ ልቤም፡ ሥጋዬም በሕያው እግዚአብሔር ደስ አላቸው። 3 ወፍ ለእርስዋ ቤትን አገኘች፤ ዋኖስም ጫጩቶችዋን የምታኖርበት ቤት አገኘች፤ የኃያላን አምላክ፡ ንጉሤም፡ አምላኬም ሆይ፤ እርሱ መሠዊያህ ነው። 4 በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ ብፁዓን ናቸው፤ ለዓለምና ለዘለዓለም ያመሰግኑሃል። 5 አቤቱ እርዳታው ከአንተ ዘንድ የሆነለት፤ በልቡም የላይኛውን መንገድ የሚያስብ ሰው ብፁዕ ነው። 6 በልቅሶው ሸለቆ ውስጥ በወሰንህላቸው ስፍራ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና።7 ከኃይል ወደ ኃይልም ይሄዳል። የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል ። የኃያላን አምላክ አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ፤ የያዕቆብ አምላክ ሆይ! አድምጠኝ። 9 አቤቱ መታመኔን -እይልኝ፤ ወደ ቀባኸውም ፊት ተመለከት።10--ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች፤ በኃጥአን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ በእግዜአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ። 11-እግዚአብሔር አምላክ ምጽዋትና መስጠትንና እውነትን ይወድዳልና፤ እግዜአብሔር ክብርና ሞገስን ይሰጣል፤ እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከበረከቱ አያሳጣቸውም። 12 አቤቱ የኀያላን አምላክ ሆይ፤ በአንተ የታመነ ሰው ብፁዕ ነው።

## መዝ ፹፬/84፡ <u>ስለ ሰላምና ፍቅር የሚቀርብ ጸሎት</u>

1 ተሣሃልከ እግዚኦ ምድረከ ወሜጥከ ዜዋሁ ለያዕቆብ=አቤቱ፡ ምድርህን ይቅር አልሃት። የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ። 2 የሕዝብህን ኀጢአት ይቅር አልህ፡ አበሳቸውንም ሁሉ ሰወርህ። 3 መዓትህንም ሁሉ-አስወገድህ፡ ከቁጣህ መቅሠፍት ተመለስህ። 4 አምላካችንና መድኀኒታችን ሆይ! አሁንም መልስን፤ ቁጣህንም ከእኛ መልስ። 5 ለዘላለም አትቆጣን፤ ቁጣህንም ለልጅ ልጅ አታስረዝም። 6 አንተ አምላካችን ሆይ! ተመለስልን፡ አድነንም፤ ሕዝብህም በአንተ-ደስ ይበላቸው።-7 አቤቱ ምሕረትህን አሳየን፤ አቤቱ ማዳንኅን-ስጠን።-8-እግዚአብሔር-አምላኬ-የሚናገረኝን አደምጣለሁ፤ ሰላምን ለሕዝቡና ለጻድኀቃኑ፡ ልባቸውንም ወደ እርሱ ለሚመልሱ ይናገራልና ።9 ነገር ግን ክብር በምድራችን ያድር ዘንድ ማዳኑ ለሚፈሩት ቅርብ ነው። 10 ይቅርታና ቅንነት ተገናኙ፤ ጽድቅና ሰለም ተስማሙ።11 ቅንነት -ከምድር በቀለች፤ ጽድቅንም ከሰማይ-ጐበኘች-/ተመለከተች። 12 ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፤ ፍለጋውንም በመንገድ ውስጥ ይተዋል።

## መዝ ፹፭/85 <u>እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ ስለ ማመስገን</u>

1 አፅምዕ እግዚኦ ዕዝነከ ኀቤየ ወስምዐኒ ። አቤቱ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፡ ስማኝም፤ ድሃና ምስኪን ነኝና። 2 እኔ የዋህ ነኝና-ነፍሴን ጠብቃት፤ አምላኬ ሆይ አንተን የታመነውን አገልጋይህን አድነው። 3 አቤቱ ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና ይቅር በለኝ። 4 የእኔን የአገልጋይህን ነፍስ ደስ አሰኛት፤ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁና። 5 አቤቱ አንተ መሐሪና ይቅር ባይ ነህና፤ ይቅርታህም ለሚጠሩህ ሁሉ ብዙ ነውና። 6 አቤቱ ጸሎቴን አድምጥ፡ የልመናዬንም ቃል ስማ።7 ትሰማኛለህና በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጮኻለሁ። 8 አቤቱ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፤ በድንቅ ሥራም አንተን የሚመስል ማንም የለም። 9 የፈጠርሃቸው አሕዛብ ሁሉ ይምጡ፡ አቤቱ በፊትህ ይስገዱ፤ ስምህንም ያከብሩ፤ 10 አቤቱ ድንቅን የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህና፤ አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና 11 አቤቱ መንገድህን ምራኝ፡ በእውነትህም እሄዳለሁ፤ ስምህንም በመፍራት ልቤን ደስ ይለዋል። 12 አቤቱ





www.ethiopianorthodox.org

አምላኬ ሆይ! በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፡፡ ለዘለዓለምም ስምህን
አከብራለሁ፤ 13 ምሕረትህ በእኔ ላይ ታላቅ ናትና፤ነፍሴንም
ከታችኛይቱ ሲኦል አድነሃታልና፡፡ 14 አምላኬ ሆይ! ዓመፀኞች
በእኔ ላይ ተነሥተዋል፤ የክፉዎችም ማኅበር ነፍሴን ፈለጉአት፤
አንተንም በፊታቸው አላደረጉህም ፡፡ 15 ወደ እኔ ተመልከት፤
ይቅርም በለኝ፤ ለእኔ ለአገልጋይህ ኃይልን ስጠኝ፡ የሴት
አገልጋይህንም ልጅ አድን፡፡ 16 ምልክትንም ለመልካም ከእኛ ጋር
አድርግ፤ ጠላቶቻችንም ይዩ፤ይፈሩም፤አቤቱ አንተ ረድተኸኛል፤
ደስም አሰኝተኸኛልና፡፡

## መዝ ፹፮ /86፡ ስለ እናት አገር የሚቀርብ ጸሎት

1 መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን=መሠረቶችዋ በተቀደሱ
ተራሮች ናቸው፤ 2 ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ፤ እግዚአብሔር
የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል፡፡ 3 የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፤ ስለ
አንቺ የተነገረው ነገር ድንቅ ነው፡፡ 4 የሚያውቁኝን ረዓብንና፡
ባቢሎንን አስባቸዋለሁ፤ እነሆ፤ ፍልስጤማውያን፤ ጢሮስ፡
የኢትዮጵያም ሕዝብ፤ እነዚህ በዚያ ተወለዱ፡፡ 5 ሰው እናታችን
ጽዮን ይላል፤ በውስጥዋም ሰው ተወለደ፤ እርሱ ራሱም ልዑል
መሠረታት፡፡ 6 እግዚአብሔር ለሕዝቡ፤ በውስጥዋም ለተወለዱት
አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል፡፡ 7 በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ ደስ
እንደሚላቸው ይነግራቸዋል፡

## መዝ ፹፯/87፡ ሐዘንና ትካዜን የሚገልጥ ጸሎት

1 እግዚኦ አምላከ መድኃኒትየ፡ ዕለትየ ጸራሕኩ ኀቤከ ወሌሊት
የኒ ቅድሜከ= የመድኃኒቴ አምላክ እግአብሔር ሆይ!፤ በቀንና
በሌሊት በፊትህ ጮኽሁ፤ 2 ጽሎቴ ወደ ፊትህ ትግባ፤ ጆሮህንም
ወደ ልመናዬ አዘንብል፤ 3 ነፍሴ መከራን-ጠግባለችና፡ ሕይወቴም
ለሞት ቀርባለች፡፡ 4 ወደ ጉድጓድ ከሚወርዱ ጋር ተቈጠርሁ፤
ረዳትም እንደሌለው ሰው ሆንሁ፡፡ 5 እንደተገደሉና በመቃብር



ውስጥ እንደ ተጣሉ፤ ለዘለዓለም እንደማታስባቸ በሙታን መካከል
የተጣልሁ ሆንሁ፤ እነርሱ ከእጅህ ርቀዋልና፡፡6-በጨለማ በሞት
ጥላ ውስጥ፤ በታችኛው ጉድጓድ አስቀመጡኝ፡፡ 7 በእኔ ላይ ቁጣህ
በረታ፤ መቅሠፍትህን ሁሉ በእኔ ላይ አመጣህ፡፡ 8 የሚያውቁኝን
ከእኔ አራቅህ፡፡ በእነርሱ ዘንድ ርኩስ አደረግኸኝ፤ ያዙኝ፤ መውጫም
የለኝም፡፡ 9 ዓይኖቼም በችግር ፈዘዙ፤ አቤቱ! ሁልጊዜ ወደ አንተ
ጮህሁ፤ እጆቼንም ወደ አንተ ዘረጋሁ፡፡ 10 በውኑ ለሙታን ድንቅ
ነገርን ታደርጋለህን? ወይስ ያመሰግኑህ ዘንድ ባለ መድኀኒቶች
ያስነሡአቸዋልን? 11 በመቃብርስ ውስጥ ያሉት ቸርነትህን፤
እውነትህንስ በሞት ስፍራ ይናገራሉን? 12 ተአምራትህ በጨለማ
ይታወቃልን? ቅንነትህስ በምድር ተረሳን? 13 አቤቱ እኔ ግን ወደ
አንተ ጮኽሁ፤ በጥዋት ጸሎቴ ወደ አንተ ትድረስ፡፡ 14 አቤቱ
ጸሎቴን ለምን ትጥላለህ? ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትመልሳለህ፡፡ 15 እኔ
ድሃ ነኝ፤ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ደከምሁ፡፡ ከፍ ፡ከፍ ካልሁ በኋላ
ተዋረድሁ፡ ተናቅሁም፡16 መቅሠፍትህ በላዬ አለፈ፤ ግርማህም
አስደነገጠኝ፡፡ 17 ሁልጊዜ እንደ ውኃ ከበቡኝ፡ በአንድነትም ያዙኝ´፡፡
18 ወዳጆቼንና ባልጀሮቼን፡ ዘመዶቼንም ሁሉ ከችግሬ የተነሣ
ከእኔ አራቅህ፡፡

## መዝ ፹፰/ /88፡ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በማሰብ

1 ምሕረተከ እሴብሕ እግዚኦ ለዓለም=አቤቱ ምሕረትህን ለዘለዓለም
እዘምራለሁ፡፡ጽድቅህንም በአፌ ለልጅ ልጅ እናገራለሁ፡፡ 2
"ምሕረትን- ለዘለዓለም አንፃለሁ " ብለሃልና፤ ጽድቅህ በሰማይ ፀና፡፡
3 ከመረጥኋቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ፤ለአገልጋዬም ለዳዊት
ማልሁ፤ 4 ዘርህን ለዘለዓለም አዘጋጃለሁ፤5 ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ
አፀናለሁ፡፡ 5 አቤቱ ሰማያት ክብርህን፤ ጽድቅህንም ደግሞ በቅዱሳን
ማኅበር-ያመሰግናሉ፡፡ 6 እግዚአብሔርን በደመናት ማን ይተካከለ
ዋል ?ከአማልክትስ ልጆች እግዚአብሔርን ማን ይመስለዋል?



www.ethiopianorthodox.org

7 እግዚአብሔር በቅዱሳን ምክር ክቡር ነው፤ በዙሪያው ባሉት ሁሉ
ላይ ታላቅና ግሩም ነው፡፡ 8 አቤቱ የኃያላን አምላክ እንደ አንተ ያለ
ማን ነው? 9 የባሕርን ኃይል አንተ ትገዛለህ፤ የሞገዱንም መናወጥ
አንተ ዝም ታሰኘዋለህ፤፤10 አንተ ትዕቢተኛውን እንደ ተገደሉ
አዋረድኸው፤ በኃያል ክንድህም ጠላቶችህን በተንሃቸው፡፡ ዓለምን
በሙሉ አንተ መሠረትህ፡፡ 12 ደቡብንና ሰሜንን አንተ ፈጠርህ፤
ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ደስ ይላቸዋል፡፡ ስምህንም ያመሰግናሉ፡
፡ 13 ክንድህን ከኃይል ጋር ነው፤ እጅህ በረታች፤ ቀኝህም ከፍ፡ ከፍ
አለች፡፡ 14 የዙፋንህ መሠረት ፍትሕና ርትዕ ነው፤ ምሕረትህና
እውነትህ በፊትህ ይሄዳሉ፡፡ 15 እልልታን የሚየውቅ ሕዝብ ብፅዕ
ነው፤ አቤቱ በፊትህ ብርሃን ይሄዳሉ፡፡ 16 በስምህ ቀኑን ሁሉ ደስ
ይላቸዋል፤ በጽድቅህም-ከፍ፡ከፍ ይላሉ፤17-የኃይላቸው ትምክሕት
አንተ ነህ፡ በይቅርታህም ቀንዳችን ከፍ፡ ከፍ ይላልና፡፡ 18 ረድኤታ
ችን ከእግዚአብሔር ነውና፡፡ ንጉሣችንም የእስራኤል ቅዱስ ነው፡፡
19 በዚያን ጊዜ ለልጆችህ በራእይ ተናገርህ፡፡ እንዲህም አልህ
"ረድኤትን በኃይል ላይ አኖርሁ፤ ከሕዝቤ የመረጥሁትን ከፍ፡ ከፍ
አደረግሁ"፡፡ 20 አገልጋዬን ዳዊትን አገኘሁ፤ የተቀደሰ ዘይትንም
ቀባሁት፡፡21-እጄም-ትረዳዋለች ፤22- ጠላት-እርሱን መጠቀሚያ
ማድረግ አይችልም፡፡ የዓመፃ ልጅም መከራ አይጨምርበትም ፡፡
23 ጠላቶቹን ከፊቱ አጠፋለሁ፤ የሚጠሉትንም አዋርዳቸዋለሁ፡፡
24 እውነቴና ምሕረቴም ከእርሱ ጋር ነው፤ በስሜም ቀንዱ
(ሥልጣኑ) ከፍ፡ ከፍ ይላል፡፡ 25 እጁን በባሕር ላይ ፡ቀኙንም
በወንዞች ላይ አኖራለሁ፡፡ 26 እርሱ " አባቴ አንተ ነህ፤ አምላኬ
ረዳቴና መድኃኒቴም ነህ " ይላል፡፡ 27 እኔም ደግሞ በኵሬ
አደርገዋለሁ፤ከምድር ነገሥታት በላይ-ከፍ-ይላል፡፡ 28 ለዘላለም
ይቅርታዬን ለእርሱ እጠብቃለሁ፤ ለኪዳኔም እርሱ የታመነ ነው፡፡



29 ዘሩንም ለዓለምና ለዘለዓለም፤ ዙፋኑንም እንደ ሰማይ ዘመን
አደርጋለሁ፡፡ 30 "ልጆቹ ግን ሕጌን ቢተዉ፤ በፍርዴም ባይሄዱ፤
1 ሥርዐቴንም ቢያረክሱ፤ ትእዛዜንም ባይቀበሉ፤ 32 ኀጢያታቸ
ውን በበትር፡ በደላቸውንም በመቅሠፍት እጐበኛለሁ፡፡ 33 ይቅርታ
ዬን ግን ከእርሱ አላርቅም፤ በእውነቴም አልበድልም፤ 34 ኪዳኔንም
አላረክስም፤ ካፌም የወጣውን አልለውጥም፡፡ 35 ዳዊትን እንዳልዋ
ሽው አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ፡፡ 36 ዘሩ ለዘለዓለም ዙፋኑም
በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል፡፡ 37 ለዘለዓለም እንደ ጨረቃ ይፀናል፡፡
ምስክርነቱም በሰማይ የታመነ ነው"፡፡
38 አንተ ግን ናቅኸው፤ ጠላኸውም፤ የቀባኸውንም-አቃለልኸው፡፡
39 የአገልጋይህን ቃል- ኪዳን አፈረስህ ፤ መቅደሱንም በምድር
አረከስህ፡፡40-ቅጥሩን ሁሉ አፈራረስህ፤ አምባዎቹንም የሚየስፈሩ
አደረግህ፡፡-41-መንገድ-አላፊውንም-ሁሉ ተናጠቀው፤ ለጎረቤቶችም
ስድብ ሆነ፡፡ 42 የጠላቶችንም ቀኝ ከፍ፡ ከፍ አደረግህ፡፡ ጠላቶቹንም
ሁሉ ደስ አሰኘህ፡ 44 የሰይፋንም ረድኤት መለስህ ፤ በሠልፉም
ውስጥ አልደገፍከውም፡፡ 45 ከንጽሕናውም ሻርኸው ፡ዙፋኑንም
በምድር ጣልኸው፡፡ 46 የዙፋኑንም ዘመን አሳነስህ፤ በላዩም
እፍረትን ጨመርህ፡፡ 47 አቤቱ፤ እስከ መቼ ለዘለዓለም ፊትህን
ትመልሳለህ? እስከ መቼስ ቁጣህ እንደ እሳት ይነድዳል? 48 ኃይሌ
ምን እንደሆነ አስብ፤ በውኑ የሰውን ልጅ ሁሉ በከንቱ ፈጠረኸውን ?
49 ሕያው ሆኖ የሚኖርና ሞትንስ የማያይ ሰው ማን ነው? ነፍሱን
ከሲኦል እጅ የሚያድናት ማን ነው? 50 አቤቱ የቀድሞው ይቅርታህ
ወዴት ነው? ለአገልጋይህ ለዳዊት በእውነት የማልህ፤ 51 አቤቱ፤
አገልጋዮችህን የሰደቡዋቸውን ስደብ፤ በብብቴ ብዙ አሕዛብን
የተከቀበልሁትን፤ 52 አቤቱ፤ ጠላቶችህ የሰደቡትን ፡ በቀባኸው
ዘመን የሰደቡትን ስድብ አስብ፡፡ 53 እግዜአብሔር ለዘለዓለም
ይመስገን ፡፡ ይሁን፡ ይሁን ! 9ለይኩን፡፡ ለይኩን ) ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

**መዝ-፹፱/89፡ ዓለማዊ ሀብት ኃላፊነና-ጠፊ ስለመሆኑ-**

1 እግዚኦ ጸወነ ኮንከነ ለትውልደ ትውልድ= አቤቱ፤ አንተ ለልጅ
ልጅ ሁሉ መጠጊያ ሆንህልን፤፤ 2 ተራሮች ሳይወለዱ፡ ምድርና
ሌሎች ዓለማትም ሳይሠሩ፡ ለዘለዓለም እስከ ዘላለም ድረስ መቼም
መች አንተ ነህ። 3 ሰውን ወደ ኀሳር አትመልሰው፤ "የሰው ልጆች
ሆይ፤ ተመለሱ" ትላለህ፤ 4 ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ
ትላንት ቀን ናት፤ እንደ ሌሊትም ሰዓት ነውና፤፤ 5 ዘመኖቻችን
በፊትህ የተናቁ ናቸው፤ በማለዳም እንደ ሣር ያልፋሉ። 6 ማልዶ
ይበቅላል፡ ያልፋልም፤ በሰርክም ጠውልጎና ደርቆ ይወድቃል። 7 እኛ
በቁጣህ-አልቀናልና፤-በመቅሰፋትህም-ደንግጠናልና።8 ኃጢአታችን
ንም በፊትህ አስቀመጥህ ፤ ዓለማችንም በፊትህ ብርኀን ነው ።
9 ዘመናችን ሁሉ አልፎአልና፤ እኛም በመቅሰፍትህ አልቀናልና
ዘመናቶቻችንም እንደ ሸረሪት ድር ይሆናሉ። 10 የዘመኖቻችንም
ዕድሜ ሰባ ዓመት ነው፤ ቢበዛም ሰማንያ ዓመት ነው፤ ከዚህ ቢበዛ
ግን ድካምና መከራ ነው፤ የዋህነት ከእኛ አልፋለችና፤ እኛም
ተገሥፀናል። 11 የመቅሠፍትን ኃይል ማን ያወቃል? ከቁጣህ ግርማ
የተነሣ አለቁ። 12 ጥበብን በልብ ለተማሩ፤ ቀኝህ እንዲግለጥ።
13 አቤቱ ተመለስ፤ እስከ መቼስ ነው? ስለ አገልጋዮችህም ተሟገት፡
14 በማለዳ ምሕረትህን እንጠግባለንና፤በዘመናችን-ሁሉ-ደስ-
ይለናል፤ 15 መከራን ባሳየኸን ፈንታ፤ ሐሴትን እናደርጋለን፡

**መዝ ፺ /90፡ <u>የእግዚአብሔር ጠባቂነትና የማዳን ኃይል</u>**

1 ዘየኀድር በረድኤተ ልዑል ፡ ወይነብር ውስተ ጽላሎቱ
ለአምላከ ሰማይ= በልዑል ረድኤት የሚያድር በሰማይ አምላክ ጥላ
ውስጥ የሚያርፍ፡ 2 እግዚአብሔርን "አንተ መጠጊያዬና አምባዬ
"ነህ፡ አምላኬና ረዳቴ ነው በእርሱም እታመናለሁ ይለዋል። 3 እርሱ
ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድነኛልና 4 በላባዎቹ



ይጋርድሃል በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፡ እውነት እንደ ጋሻ
ይከብብሃል። 5 ከሌሊት ግርማ፡ በመዓልትም ከሚበርር ፍላጻ፡
6 በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ሥራ፡ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።
7 በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም ዐሥር ሺህ ይወድቃሉ፡ ወደ አንተ ግን
አይቀርቡም። 8 በዐይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ ፡የኃጥአንንም ፍዳ
ታያለህ። 9 አቤቱ አንተ ተስፋዬ ነህና ልዑልን መጊያህ አደረግህ።
10 ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፡ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ
አየገባም። 11 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ
አንተ-ያዝዛቸዋልና፡12-እግርህም-በድንጋይ-እንዳትሰናከል በእጆቻ
ቸው ያነሡሃል። 13 በተኩላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፡ አንበሳውንና
ዘንዶውን-ትረግጣለህ።14-በእኔ-ተማምኖአልና-አድነዋለሁ፡ ስሜን
አውቋልና-እጋርደዋለሁ።15-ይጠራኛል፡-እመልስለትማለሁ፡-በመከ
ራው-ጊዜ- ከእርሱ-ጋር -እሆናለሁ፡-አድነዋለሁ፡ አከብረውማለሁ።
16 ረዥም ዕድሜን አጠግበዋለሁ፡ ማዳኔንም አሳየዋለሁ።

**መዝ ፺፩ /91፡ <u>በእግዚአብሔር የመታመን ጸሎት-----</u>**

1- ይሄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር፡ ወዘምሮ ለስምከ ልዑል=
በእግዚአብሔር-መታመን ከሁሉ የተሻለ ነው። ልዑል ሆይ ለስምህ
መዘመርና 2 በማለዳም ምሕረትሕን ፡ በሌሊትም እውነትህን
መናገር፡ 3 ዐሥር አውታር ባለው በበገና ከምስጋና ጋርም በመሰንቆ
መዘመር መልካም ነው። 4 አቤቱ በሥራህ ደስ ይለኛል።5 አቤቱ
ሥራህ እጅግ ጥልቅ ነው 6 ሰነፍ ሰው ይህን አያውቅም ልብ
የሌለውም ይህን አያስተውለውም። 7 ኃጥአን እንደ ሣር በበቀሉ ጊዜ
ዓመፃን የሚያደርጉም ሁሉ በስመለሙ ጊዜ፡ ለዘለዓለም ዓለም
ተነቃቅለው ይጠፋሉ። 8 አቤቱ አንተ ግን ለዘለዓለም ልዑል ነህ፤
9 አቤቱ እነሆ ጠላቶችህ ይጠፋሉና ዓመፃንም የሚሠሩ ይበተናሉና።
10 ቀንዴ አንድ ቀንድ እንዳለው ከፍ፡ ከፍ ይላል፡ ሽምግልናዬም
በዘይት ይለመልማል 11 ዓይኔም በጠላቶቼ ላይ በቆሙ በክፉዎች



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ሰማች፡፡ 12 ጻድቅ ግን እንደ ዘንባባ ያፈራል ፡እንደ ሊባኖስ
ዝግባም ይበዛል 13 በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የተተከሉ ናቸው
በአምላካችንም አደባባይ ውስጥ ይበቅላሉ፡፡ 14 ያን ጊዜ በመልካም
ሽምግልና ይበዛሉ፡ ዕረፍት ያላቸውም ሆነው ይኖራሉ፡፡ 15 አምላካ
ችን እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ ይናገራሉ፡ በእርሱም ዘንድ
ዓመፃ የለም፡፡

## መዝ-፺፪/92፡ <u>የእግዚአብሔር-ንጉሣዊ-ግርማ</u> --------

<u>1-</u>እግዚአብሔር ነግሠ፡ ስብሐቲሁ ለብሰ=እግዚአብሔር ነገሠ-
<u>ክብሩንም ለበሰ፡፡ እግዚአብሔር ኃይልን ለበሰ፡ታጠቀም ዓለምንም</u>
እንዳትናወጥ አፀናት፡፡ 2 አቤቱ ዙፋነህ ከጥንት ጀምሮ የተዘጋጀ
ነው ፡፡አንተም መቼም መች እስከ ዘለዓለም ነህ፡፡ 3 አቤቱ ወንዞች
ከፍ፡ ከፍ አደረጉ፡ ወንዞች ቃላቸቸውን ከፍ፡ ከፍ አደረጉ፡፡ 4 ከብዙ
ውኖች ድምፅ የተነሣ የባሕር እንቅስቃሴዋ ድንቅ ነው፡፡ ድንቅስ
በልዕልና የሚኖር እግዚአብሔር ነው፡፡ 5 ምስክርህ እጅግ የታመነ
ነው፡ አቤቱ በዘመናት ሁሉ ለቤትህ ምስጋና ይገባል፡፡

## መዝ ፺፫ /93፡ <u>በቀልን የሚመልስ አምላክ</u> -----------

1 እግዚአብሔር እግዚእ መስተበቅል፡=ጌታ እግዚአብሔር ተበቃይ
ነው፡ እግዚአብሔር በግልጥ ተበቃይ ነው፡፡ 2 የምድር ፈራጅ ከፍ ፡
ከፍ አለ፡ ለትዕቢተኞች ፍዳቸውን ክፈላቸው፡፡ 3 አቤቱ ኃጥአን እስከ
መቼ እየታበያዩ ይከራከራሉ፡ 4 ዓመፃንም ይናገራሉ? ዓመፃንም
የሚያደርጉ ሁሉ ይናገራሉ፡፡5 አቤቱ ሕዝብህን -አዋረዱ፡ ርስትህን
አሠቃዩ፡፡ 6 ባልቴቲቱንና-ድሃ-አደጉግ ስደተኛውንም ገደሉ ፡፡
7 -"እግዚአብሔር አያይም ፡ የያዕቆብ አምላክ አያውቅም" አሉ፡፡
8 ሰነፎች ሕዝብ ሆይ! ልብ አድርጉ፡ ሰነፎችም መቼ ይጠበባሉ?
<u>9</u> ጆሮን የተከለው እርሱ አይሰማምን? ዓይንን የሠራውስ
አያይምን? 10 አሕዛብንስ የሚገሥፅ፡ ለሰዎችም ዕውቀትን
የሚያስተምር እርሱ አይዘልፍምን? 11 የጠቢባን አሳብ ከንቱ



እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ 12 አቤቱ አንተ የገሠፅኸውና
ሕግህንም ያስተማርኸው ሰው ብፁዕ ነው፡፡13 ከክፉዎች ዘመናት
ይርቅ ዘንድ ለኃጥአን ጕድጓድ እስኪቆፈር ድረስ፡ 13 እግዚአብሔር
ሕዝቡን አይጥላቸውምና ርስቱንም አይተዋቸውምና፡፡
_15 ፍርድ ለእውነተኛ እስኪመለስ ድረስ ልበ ቅኖች ሁሉ
ይከተሏታል፡፡ 16 ስለ ክፉዎች ማን ይከራከርልኛል? ዓመፃንስ
ስለሚያደርጉ ማን ይቆምልኛል? 17 እግዚአብሔር የረዳኝ ባይሆን
ኖሮ ነፍሴ ለጥቂት ጊዜ በሲኦል ባደረች ነበር፡፡ 18 "እግሮቼ
ተሰናከሉ" ባልሁ ጊዜ አቤቱ ምሕረትህ ረዳኝ፡፡ 19 አቤቱ ለልቤ እንደ
መከራዋ ብዛት ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኛት፡፡ 20 በሕግ ላይ
ድካምን የሚፈጥር የዓመፃ ዙፋን አይቃወምህም፡፡ 21 የጻድቅን ነፍስ
ያድናታል፡ በንጹሕ ደምም ይፈርዳል፡፡ 22 እግዚአብሔር መጠጊያዬ
ሆነኝ፡ አምላኬ የተስፋዬም ረዳት ነው፡፡ 23 እንደ ክፋታቸው
ፍዳቸውን ይከፍላቸዋል፡ አምላካችን እግዚአብሔርም ያጠፋቸዋል፡፡

## መዝ ፺፬ //94፡ <u>የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ</u>

1-ንዑ ንትፌሣሕ በእግዚአብሔር ወንየብብ ለአምላክነ ወመድኅኒነ
ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን፡ ለአምላካችንና ለመድኀኒታችንም
እልል እንበል፡ 2 በእምነት ወደ ፊቱ እንድረስ፡ በዝማሬም ለእርሱ
እልል እንበል፡፡ 3 አምላካችን እግዚአብሔር ታላቅ ነውና፡
በአማልክትም ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ ነውና፡፡ 4 እግዚአብሔር
ሕዝቡን አይጥላቸውም፡ የምድር ዳርቻዎችም ሁሉ በእጁ ውስጥ
ናቸውና፡ ረገኘርም ተራሮች የእርሱ ናቸውና ፡ 5 ባሕር የእርሱ
ናት፡ እርሱም ፈጥሯታልና፡ የብስንም በእጁ ፈጥሯታልና፡፡
6 ኑ እንስገድ፡ ለእርሱም እንገዛ፡ በእርሱ በፈጠረን በእግዚአብሔር
ፊት እናልቅስ፡ 7 እርሱ አምላካችን ነውና እኛ ግን ሕዝቡ
የማሰማርያውበጎች ነን፡፡ 8 በምድረ በዳ እንደ ተፈታተኑትና
እንዳስቆጡት ጊዜ ዛሬ ድምፁን-ብትሰሙ-ልባችሁን-አታጽኑ፡፡9



www.ethiopianorthodox.org

የተፈታተኑኝ አባቶቻችሁ ፈተኑኝ ፡ ሥራዬንም እዩ። 10 ያችን
ትውልድ ዐርባ ዓመታት ተቈጥቻት ነበር፡ ሁልጊዜ ልባቸው
ይስታል። እነርሱም መንገዴን አላወቁም" አልሁ 11 ወደ ዕረፍቴም
እንዳይገቡ በቁጣዬ ማልሁ።

መዝ ፺፭ //95፡ **የደስታ መዝሙርና ጸሎት** --------------

1 ሰብሆ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ=ለእግዚአብሔር አዲስ
ምስጋናን አቅርቡ፡ ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑት። 2 እግ
ዚአብሔርን አመስግኑት፡ ስሙንም ባርኩ፡ ዕለት ዕለትም ማዳኑን
አውሩ። 3 ክብሩንም ለአሕዛብ፡ ተአምራቱንም ለወገኖች ሁሉ ንገሩ።
4 እግዚአብሔር ታላቅ፡ ምስጋናውም ብዙ ነውና፡ በአማልክትም
ሁሉ ላይ የተፈራ ነውና። 5 የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት
ናቸውና፡ እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ፈጠረ። 6 እምነትና በጎነት
በፊቱ፡ ቅድስናብ እና የክብር ገናናነት በመቅደሱ ውስጥ ናቸው።
7 የአሕዛብ ወገኖች ለእግዚአብሔር አምጡ፡ ክብርንና ምስጋናን
ለእግዚአብሐር አቅርቡ። 8 ለእግዚአብሔርም ስም ክብርን ስጡ፡
መሥዋዕትን ይዛችሁ ወደ አደባባዮች ግቡ፡ 9 ለእግአብሔር
በቅድስናው ቦታ ስገዱ፡ ምድር በመላዋ ከእግዚአብሔር ፊት የተነሣ
ትነዋወጣለች። እግዚአብሐር-ነገሠ:-ለአሕዛብ-ንገሩአቸው። እንዳይ
ናወጥም ዓለሙን ሁሉ አፀናው፡ አሕዛብንም በቅንነት ይገዛል ።
11 ሰማያት ደስ ይላቸዋል፡ ምድርም ሐሤትን ታደርጋለች። ባሕር
በመላዋ ትናወጣለች፡ 12 በረሃና በእርስዋም ያሉ ሁሉ ሐሤትን
ያደርጋሉ፡ የዱር ዛፎች ሁሉ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ደስ
ይላቸዋል። 13 ይመጣልና በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣልና።
እርሱም ዓለምን በጽድቅ፡ አሕዛብንም በቅንነት ይገዛል።

መዝ ፺፮ /96፡ **እግዚአብሔር የድል ባለቤት**

1 እግዚአብሔር ነገሠ፡ ምድር ሐሤትን ታደርጋለች፡ ብዙ
ደሴቶችም ደስ ይላቸዋል። 2 ደመናና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው፡



ፍትሕና ርትዕ የዙፋኑ መሠረት ናቸው። 3 እሳት በፊቱ ይሄዳል፡
ነበልባሉም ጠላቶቹን ይከብባቸዋል። 4 መብረቆቹ ለዓለም አበሩ፡
ምድር ተንቀጠቀጠች፡ ተናወጠችም ። 5 ተራሮችም ከእግዚአብሔር
ፊት የተነሣ እንደ ሠም ቀለጡ፡ ምድር ሁሉ ከእግዚአብሔር ፊት
የተነሣ ቀለጠች። 6 ሰማያት የእርሱን ጽድቅ አወሩ፡ አሕዛብም ሁሉ
ክብሩን አዩ ። 7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ ሁሉ በጣዖቶቻቸውም
የሚመኩ ይፈሩ፡ መላእክቱም ሁሉ ይሰግዱለታል። 8 አቤቱ ስለ
ፍርድህ ጽዮን ሰምታ ደስ አላት፡ የይሁዳም ሴቶች ሐሤት አደረጉ።
9 አንተ እግዚአብሐር በምድር ላይ ሁሉ ብቻህን ልዑል ነህና፡
በአማልክት ሁሉ ላይ እጅግ ከፍ፡ ከፍ ብለሃልና። 10 እግዚአብሔር
የጻድቃኑን ነፍሶች ይጠብቃል፡ ከኃጥአንም እጅ ያድናቸዋል። 11 ለጻ
ድቃን-ደስታ-የሆነ-ብርሃን-ለልበ-ቅኖች-ወጣ።12-ጻድቃን በእግዚአ
ብሔር ደስ ይላቸዋል፡ ለቅድስናውም መታሰቢያ ምስጋና ያቀርባሉ፡

መዝ ፺፯ /97፡ **የምድር ሁሉ ፈራጅ የሆነ አምላክ**----

1 ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ=ለእግዚአብሐር አዲስ
ምስጋናን አቅርቡ፡ የእግዚአብሐር ሥራ፡ የቀኙም ማዳን፡ የተቀደሰ
ክንዱም ድንቅ ነውና 2 እግዚአብሐር ማዳኑን አሳየ። በአሕዛብም
ፊት ቃል ኪዳኑን ገለጠ። ለያዕቆብ ይቅርታውን፡ ለእስራኤልም ቤት
እውነቱን አሰበ። የምድር ዳርቻዎች ሁሉ የአምላካችንን ማዳን እዩ።
4 በምድር ሁሉ ለእግዚአብሐር እልል በሉ፡ አመስግኑ፡ ደስም
ይበላችሁ፡ ዘምሩም። 5 ለእግዚአብሔር በመሰንቆና በዝማሬ ድምፅ
ዘምሩ። 6 በነጋሪትና በመለከት ድምጽ በንጉሡ በእግዚአብሔር ፊት
እልል በሉ ።7 ባሕር በሞላዋ፡ ዓለምና በእርስዋ የሚኖሩ ሁሉ
ይናወጡ። 8 ወንዞችም በአንድነት በእጅ ያጨብጭቡ፡ ተራሮች ደስ
ይበላቸው፡ 9 ለምድር በዚያ ይፈርድላታልና ለዓለምም በእውነት
ይፈረድላታልና ለአሕዛብም በቅንነት ይፈርዳል።



www.ethiopianorthodox.org

## መዝ ፺፰ /98፡ <u>የእግዚአብሔር ጽድቅና ቅድስናው</u> -----

1-እግዚአብሔር ነግሠ ደንገፁ አሕዛብ=እግዚአብሔር ነገሠ፡ አሕዛብ-ደነገጡ፡፡-በኪሩቤል-ላይ-የተቀመጠ-እርሱ-ምድርን አነዋወጣት፡ 2 እግዚአብሐር በጽዮን ታላቅ ፡ እርሱም በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ፡ ከፍ አለ፡፡ 3 ሁሉም ታላቅ ስምህን ያመስግናል፡፡ ግሩምና ቅዱስ ነውና፡፡ 4 ክቡር ንጉሥ ፍርድን ይወድዳል፡፡ አንተ በኃይልህ ጽድቅን አጸናህ፡ ለያዕቆብ ፍርድንና ጽድቅን አንተ አደረግህ፡፡ 5-ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ከፍ፡ ከፍ አለ፡፡ ከእግሩ መረገጫ በታችም ይሰግዱለታል፡፡ 6 ሙሴና አሮን በክህነታቸው ቅዱሳን ናቸውና፡ ሳሙኤልም ስሙን ከሚጠሩት ጋር ነው፡ እግዚአብሐርን ጠሩት፡ እርሱም መለሰላቸው፡፡7 በደመና ዓምድም ተናገራቸው ፡፡ ምስክሩንና የሰጣቸውን ትእዛዝ ጠበቁ፡፡ 8 አቤቱ አምላካችን ሆይ! አንተ ሰማሃቸው፡ አቤቱ አንተ ማርሃቸው፡ በክፉ ሥራቸው ሁሉ ግን ትበቀላቸዋለህ፡፡9-አምላካችን-እግዚአብሔር-ከፍ፡-ከፍ-አለ፡፡ በተቀደሰው ተራራ ይሰግዱለታል፡ አምላካችን እግዚአብሐር ቅዱስ ነውና፡፡

## መዝ ፺፱ /99፡ <u>እግዚአብሔርን ማመስገኛ ጸሎት</u>

1 የብቡ ለእግዚአብሔር በኵሉ ምድር= በምድር ሁሉ ለእግዚአብሐር እልል በሉ፡፡ 2 በደስታም ለእግዚአብሐር ተገዙ፡ በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ፡፡ 3 እግዚአብሐር እርሱ አምላካችን እንደሆነ እወቁ፡ እርሱ ፈጠረን፡ እኛም አይደለንም፡፡ እኛስ ሕዝቡና የመሠማርያውም በጎች ነን፡፡ 4 ወደ ደጆቹ በመገዛት፡ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ፡፡ አመስግኑት ስሙንም አክብሩ 5 እግዚአብሔር ቸር ምሕረቱም ለዘለዓለም እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና፡፡

## መዝ ፻/ 100፡ <u>ክፉትን ተሚጠላ አምላክ</u>

1 ምሕረት ወፍትሐ አኀሊ ለከ=አቤቱ ምሕረትህንና ፍርድህን በማሰብ-እዘምርልሃለሁ፡፡2-እዘምራለሁ-ንጹሕ-መንገድንም አስተውላለሁ፡ ወደ እኔ መቼ ትመጣለህ? በቤቴ መካከል በልቤ ቅንነት እሄዳለሁ፡፡3--በዓይኔ-ፊት-ክፉ-ነገርን-አላኖርሁም፡-ዓመፃ የሚያደርጉትን ጠላሁ፡፡ 4 ጠማማ ልብም አልተከተለኝም፡ ክፉ ከእኔ በራቀ ጊዜ አላወቅሁም፡፡5 ባልንጀራውን በስውር የሚያማን እርሱን አሳደድሁ፡ ዓይኑ ትዕቢተኛ የሆነና ልቡ የሚሳሳ ከእኔ ጋር አይተባበርም፡፡ 6 ከእኔ ጋር አኖራቸው ዘንድ ዓይኖቼ ወደ ምድር ምእመናን ናቸው፡፡ በንጹሕ መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል፡፡ 7 ትዕቢትን የሚያደርግ በቤቴ መካከል አይኖርም፡ ዓመጽን የሚናገር በፊቴ አይፀናም፡፡ 10 የምድርን ኃጢአተኞች ሁሉ ለማዳን ዓመፃን የሚያደርጉትን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተማ አጠፋቸው ዘንድ እገድላቸዋለሁ፡፡

## መዝ-፻፩/101፡ <u>መክራ ሲያጋጥም ያስጨናቂ ጊዜ ጸሎት</u>

1 ስምዐኒ እግዚኦ ጸሎትየ ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዐርየ= =አቤቱ ጸሎቴን ስማኝ፡ ጩኸቴም ወደ ፊትህ ይድረስ ፡፡ 2 በመከራዬ ቀን ፊትህን ከእኔ አትመልስ፡ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፡ በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ ስማኝ፡፡ 3 ዘመኔ እንደጢስ አልቋልና፡ አጥንቶቼም እንደሣር ደርቀዋልና፡፡ 4 ተቀሠፍሁ፡ ልቤ እንደ ሣር ደረቀ፡ እህል መብላት ተረስቶኛልና፡፡ 5 ከጩኸቴ ድምፅ የተነሣ ሥጋዬ በአጥንቶቼ ላይ ተጣበቀ፡፡ 6 እንደ ሜዳ አህያ ሆንሁ፡፡ ሌሊት በወና ቤት እንዳለ እንደ ጉጉት ሆንሁ፡፡ 7 ተጋሁ በሰገነትም እንደሚኖር ብቸኛ ወፍ ሆንሁ፡ 8 ጠላቶቼ ሁልጊዜ ይሰድቡኛል፡ የሚያሳድዱኝም ተማማሉብኝ፡፡ 9 አመድን እንደ እህል ቅሜአለሁና፡ መጠጤንም ከእንባዬ ጋር ጠጥቻለሁና፡፡ 10 ከቁጣህ መቅሠፍት የተነሣ አንስተህ ጥለኸኛልና፡፡ 11 ዘመኔም እንደ ጥላ አለፈ፡ እኔም እንደሣር ደርቄአለሁ፡፡ 12 አንተ ግን አቤቱ ለዘለዓለም ትኖራለህ ፡መታሰቢያህም ለልጅ ልጅ ነው፡፡ 13 አንተ ተነሥ፡ ጽዮንንም ይቅር በላት፡ ይቅር ትላት ዘንድ ጊዜዋ ነው፡ ዘመኗም ደርሶአልና፡፡ 14 አግልግዮችህ ድንጋዮችዋን





www.ethiopianorthodox.org

ወድደዋል፡ መሬቷንም አክብረውታል። 15 አቤቱ አሕዛብ ስምህን፡
ነገሥታትም ሁሉ ክብርህን ይፍሩ። 16 እግዚአብሔር ጽዮንን
ይሠራታል፡-በክብሩም-ይገለጣልና።17-ወደ-ድሆች-ጸሎት ተመለ
ከተ፡ ልመናቸውንም አልናቀም።18 ይህችም ለሚመጣ ትውለድ
ተጻፈች፡ የሚፈጠርም ሕዝብ እግዚአብሔርን ያመሰግነዋል።
19 ከሰማይ ሆኖ መቅደሱን ተመልክቶአል፡ እግዚአብሔር ከሰማይ
ሆኖ ምድርን ጐብኝቶአልና። 20 የእስረኞችንም ጩኸት ይሰማ
ዘንድ፡-የተገደልትንም-ሰዎች-ልጆች-ያድን-ዘንድ።-21 የእግዚአብሔ
ርን ስም በጽዮን፡ ምስጋናውንም በኢየሩሳሌም ይነግሩ ዘንድ፡
22 አሕዛብ በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ ነገሥታት ለእግዚአብሔር
ይገዙ ዘንድ፡ 23 በኃይሉ ጎዳና መለሳቸው። የዘመኔን ማነስ ንገረኝ።
24 በዘመኔም እኩሌታ አትውሰደኝ፡ ዓመቶችህ ለልጅ ልጅ ናቸው።
25 አቤቱ አንተ አስቀድመህ፡ ምድርን መሠረትህ፡ ሰማያትም የእጅህ
ሥራ ናቸው። 26 እነርሱ ይጠፋሉ፡ አንተ ግን ትኖራለህ። ሁሉ እንደ
ልብስ ያረጃል፡ እንደ መጐናጸፊያ ትለውጣቸዋለህ፡ ይለወጡማል።
27 አንተ ግን ምን ጊዜም-ያው-አንተ-ነህ፡-ዓመታትህም-ከቶ-
አያልቁም።28 የተአገልጋዮችህም ልጆች ይኖራሉ፡ ዘራቸውም
ለዘለዓለም ፀንቶ ይኖራል።

## መዝ ፻፪ /102፡ <u>የፍቅር አምላክ እግዚአብሔር</u>

1 ትባርኮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ወኵሉ አዕፅምትየ ለስሙ
ቅዱስ=ነፍሴ እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች። አጥንቶቼም ሁሉ
የተቀደሰ ስሙን። 2፣ ነፍሴ እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች፡
ምስጋናውንም ሁሉ አትረሳም። 3 ኃጢአትሽንም ሁሉ ይቅር
የሚልልሽ፡ ደዌየሽንም ሁሉ የሚፈውስሽ፡ 4 ሕይወትሽን ከጥፋት
የሚያድናት፡ በይቅርታውና በምሕረቱ የሚከልልሽ፡ 5 ምኞትሽን
ከበረከቱ የሚያጠግባት፡ ጐልማስነትሽንም እንደ ንስር የሚያድሳት፡
6 እግዚአብሔር ይቅርታ አድርጊ ነው። ለተበደሉ ሁሉ ይፈርዳል ።



7 ለሙሴ መንገዱን አሳየ፡ ለእስራኤልም ልጆች ፈቃዱን ። 8 እግዚ
አብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው፡ ከቁጣው የራቀና ምሕረቱም የበዛ
ጻድቅ ነው። 9 ሁልጊዜም አይቀሥፍም፡ ለዘለዓለምም አይቈጣም።
10 እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፡ እንደ በደላችንም አልከፈለንም፡
11 ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፡ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱ
በሚፈሩት ላይ አፀና። 12 አባት ለልጆቹ እንደሚራራ፡እንዲሁም
እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራላቸዋል። 14 ተፈጥሯችንን እርሱ
ያውቃልና፡ አቤቱ እኛ አፈር /ትቢያ እንደ ሆንን አስብ። 15 ሰውስ
በዘመኑ እንደ ሣር ነው ፡ እንደ ዱር አበባ ደምቆ በማበብ ይታያል፡
16 ነፍሱ ከእርሱ ትወጣለችና ከእንግዲህም በሕወት አይኖርም፡
ስፍራውንም ደግሞ አያውቀውም። 17 የእግዚአብሐር ይቅርታ ግን
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሚፈሩት ላይ፡ ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ
ነው።18 ሕጉን በሚጠብቁና ትእዛዙንም ያደርጉ ዘንድ በሚያስቡ ላይ
ነው። 19 እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፡ በመንግሥቱም
ሁሉን ይገዛል። 20 ቃሉን የምትፈጽሙ ብርቱዎችና ኃያላን፡
የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን
አመስግኑት። 21 ሠራዊቱ ሁሉ ፈቃዱን የሚያደርጉ፡ አገልጋዮቹ
እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ናቸው።22 ፍጥረቶቹ ሁሉ በግዛቱ
ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፡ ነፍሴ እግዚአብሔርን
ታመሰግነዋለች።

## መዝ ፻፫ /103፡ <u>እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ መጋቢ</u>

1 ትባርኮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፡ እግዚኦ አምላኪየ ጥቀ ዐበይከ
ፈድፋደ= ነፍሴ እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች፡ አቤቱ አምላኬ ሆይ
አንተ እጅግ ታላቅ ነህ፡ መታመንንና የጌትነትን ክብር ለበስህ።
2 ብርሃንን እንደ ልብስ ተጐናጸፍህ፡ ሰማይንም እንደ መጋረጃ
ዘረጋህ ።3 እልፍኙን በውሃ የሚሠራ፡ ደመናን መሄጃው
የሚያደርግ፡ በነፋስ ክንፍም የሚሄድ፡ 4 መላእክቱን መንፈስ፡



www.ethiopianorthodox.org

አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸ 5 ለዘለዓለም
እንዳትናወጥ ምድርን መሠረታት፡ ዐፀናትም። 6 ጥልቁንም እንደ
ልብስ ክዳኗ ነው፡ በተራሮችም ላይ ውኖች ይቆማሉ።
7 ከተግሣፅህም የተነሣ ይሸሻሉ፡ ከነጐድጓድህም ድመፅ የተነሣ
ይደነግጣሉ። 8 ወደ ተራሮች ይወጣሉ፡ ወደ ሜዳ ወዳዘጋጀህላቸው
ስፍራም ይወርዳሉ። 9 እንዳያልፉትም ድንበር አደረግህላቸው፡
ምድርን ይከድኑ ዘንድ እንዳይመለሱ። 10 ምንጮችን ወደ ቆላዎች
የሚልክ፡ በተራሮች መካከል ውኖች ያልፋሉ። 11 የሰማይ ወፎችም
በዚያ ይኖራሉ፡ በዋሻው መካከልም ይጮኻሉ። 13 ተራሮችን
ከውስጣቸው የሚያጠጣቸው :ከሥራህ ፍሬ ምድር ትጠግባለች።
14 እህልን ከምድር ያወጣ ዘንድ ለምለሙን ለሰው ልጆች
አገልግሎት ሣርንም ለእንስሳ ያበቅላል። 15 ወይን የሰውን ልብ ደስ
ያሰኛል፡ ዘይትም ፊትን ለማብራት የተዘጋጀ ነው፡ እህልም የሰውን
ኃይል ያጠነክራል። 16 የዱር ዛፎች ሁሉ፡ የተከልኸው የሊባኖስ
ዝግባም ይጠግባሉ። 17 በዚያም ምሮች ይዋለዳሉ፡ የሽመላ ቤትም
ጐረቤታቸው ይሆናል።: 18 ረጃጅም ተራራዎች ለዋሊያዎች፡
ድንጋዮችም ለአሽኮኮዎች መሸሸ ናቸው። 19 ጨረቃን በጊዜው
ፈጠርህ፡ ፀሐይም መግቢያውን ያውቃል። 20 ጨለማን ታመጣለህ፡
ሌሊትም ይሆናል፡ በእርሱም የዱር አራዊት ሁሉ ይወጡበታል፡
21 የአንበሶች ግልገሎች ያገሣሉ፡ ይነጥቃሉ ። ከእግዚአሔርም
ምግባቸውን ይሻሉ። 22 ፀሐይ ስተወጣ ይገባሉ፡ በየዋሻቸውም
ይውላሉ። 23 ሰው ወደ ተግባሩ ይሠማራል፡ እስኪመሽም ድረስ
ሲሠራ ይውላል። 24 አቤቱ ሥራህ እጅግ ታላቅ ነው፡ ሁሉን በጥበበ
አደረግህ፡ የፈጠርኸውም ፍጥረት ምድርን ሞላ። 25 ይህች ባሕር
ታላቅና ሰፊ ናት፡ በዚያ ስፍር ቁጥር የሌለው ተንቀሳቃሽ፡ ታላላቆችና
ታናናሾች እንስሶች አሉ፡26 በዚያ ላይ መርከቦች ይሄዳሉ፡ በዚያም



ላይ የፈጠርኸው ዘንዶ ይጫወታል። 27 ምግባቸውን በየጊዜው
ትሰጣቸው ዘንድ እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ። 28 በሰጠሃ
ቸውም ጊዜ ይሰበስባሉ፡ እጅህን ፈትተህ ከቸርነትህ የተነሣ ሁሉን
ታጠግባለህ። 29 ፊትህን ብትመልስ ግን ይደነግጣሉ፡ ነፍሳቸውንም
ታወጣለህ፡ ይሞታሉ፡ ወደ አፈርነታቸውም ይመለሳሉ። 30 መንፈ
ስህን ትልካለህ፡ ይፈጠራሉም፡ የምድርንም ፊት ታድሳለህ። 31 የእግ
ዚአብሔር ክብር ለዘለዓለም ይሁን፡ እግዚአብሔር በሥራው ደስ ይለዋል።
32 ምድርን ያያል፡ እንድትንቀጠቀጥም ያደርጋል። ተራሮችን ይዳስሳል፡
ይጤሳሉም።33-በሕይወቴ-ሳለሁ-እግዚአብሔርን-አመሰግነዋለሁ፡በምኖር
በትም ዘመን ሁሉ ለአምላኬ እዘምራለሁ ። 34 በቃሌም ደስ አሰኘዋለሁ፡
እኔም በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል። 35- ኃጥአን ከምድር ይጠፋሉ፡
ዓመፀኞችም እንግዲህ አይኖሩም፡ ነፍሴ እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች።

## መዝ-፻፬/104፡ <u>እግዚእብሔር ለሕዝቡ የገለጠው ድንቅ ሥራ</u>

1-ግነዩ-ለእግዚአብሔር-ወጸውዑ-ስሞ=እግዚአብሔርን-አመስግኑ ስሙ
ንም ጥሩ፡ ለአሕዛብም ሥራውን ንገሩ። 2 ተቀኙለት፡ ዘምሩለት፡
ተአምራቱንም ሁሉ ተናገሩ። 3 በቅዱስ ስሙም ትከብራላችሁ 4 እግዚአ
ብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው። እግዚአብሔርን ፈልጉት፡
ትፀኑማላችሁ፡ ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ። 5 የሠራውንም ድንቅ ነገር ዐስቡ፡
ተአምራቱንና የአፉንም ፍርድ። 6 አገልግይቹ የአብርሃም ዘር፡ ለእርሱም
የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች ሆይ 7 እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን
ነው፡ ፍርዱ በምድር ሁሉ ነው። 8 ለዘለዓለም የሚኖር ቃል ኪዳኑን እስከ
ሺህ ትውልድ ያዘዘውን ቃሉን አስበ። 9 ለአብርሃም የሠራለትን፡
ለይሥሐቅም የማለውን፡ 10 ለያዕቆብ ምስክርነትን አጸና። 11 ለእስራኤል
ለዘለዓለም የሚኖር ኪዳኑን። እንዲህም አለው "ለአንተ የከነዓንን ምድር
የርስታችሁ ገመድ ትሆናችሁ ዘንድ እሰጣለሁ። 12 እነርሱ በቁጥር እጅግ
ጥቂቶችና በውስጧ ስደተኞች ሲሆኑ 13 ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ከነገሥታት
ወደ ሌላ ሕዝብ አለፉ። 14 ሰው ግፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፡ ስለ
እነርሱም ነገሥታቱን ገሠጸ። 15 እንዲህ ሲል "የቀባኋቸውን አትዳስሱ
በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ"። 16 በምድር ላይም ራብን አመጣ፡



www.ethiopianorthodox.org

የእህልንም ኃይል ሁሉ አጠፋ። 17 በፊታቸው ሰውን ላከ፡ ዮሴፍ ተሸጠ
አገልጋይ ሆነ። 18 እግሮቹም በእግር ብረት ሰለሰሉ፡ ሰውነቱም ከጦር
አመለጠች።19 ቃሉ ሳይደርስ የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው። 20 ንጉሡ
ልኮ ፈታው፡ የሕዝብም አለቃ አድርጎ ሾመው። 21 የቤቱም አዛዥ
አደረገው፡ በገንዘቡ ላይ ገዢ አድርጎ ሾመው። 22 አለቆቹንም እንደ እርሱ
ጥበበኞች ያደርጋቸው ዘንድ፡ 23 እስራኤልም ወደ ግብጽ ገባ፡ ያዕቆብም
በካም ምድር ተቀመጠ። 24 ሕዝቡንም እጅግ አበዛቸው። 25 ሕዝቡንም
ይጠሉ ዘንድ፡ በባሪያዎቹም ላይ ይተነኰሉ ዘንድ ልባቸውን ለወጠ። 26 አገ
ልግዮቹ ሙሴን፡ የመረጠውንም አሮንን ላከ። 27 የተአምራቱን ቃል
በላያቸው፡ ድንቁንም በካም ምድር አደረገ። 28 ጨለማንም ላከ፡
አጨለመባቸውም፡ ቃሉንም መራራ አደረጉት፡ 29 ውኃቸውን ደም አደረገ፡
ዓሦዎቻቸውንም ገደለ። 30 ምድራቸው በንጉሦቻቸው ቤተ መንግሥት
ጓጉንቸሮችን አወጣች። 31 እርሱ ተናገረ፡ የውሻ ዝንብ፡ ትንኝም
በምድራቸው ሁሉ መጡ። 32 ዝናባቸውን በረዶ አደረገው፡ እሳትም
በምድራቸው ነደደ። 33 ወይናቸውንና በለሳቸውን መታ፡ የሀገራቸውንም
ዛፍ ሁሉ ሰባበረ፡ 34 ተናገረ አንበጣማ ስፍር ቁጥር የሌለውም ኩብኩባ
መጣ 35-የምድራቸውንም ፍሬ ሁሉ በላ፡ የተግባራቸውን መጀመሪያ ሁሉ
በላ፡ 36 ከወርቅና ከብር ጋርም አወጣቸው፡ በወገናቸውም ውስጥ ደዌ
አልነበረም ፡38 ፈርተዋቸው ነበርና ግብፅ በመውጣታቸው ደስ አላቸው።
39 ደመናን ጋርዶ ሰወራቸው። እሳትንም በሌሊት ያበራላቸው ዘንድ ዘረጋ፡
40 ለመኑ፡ ድርጭትም መጣ፡የሰማይንም እንጀራ አጠገባቸው። 41 ዐለቱን
ሰነጠቀ፡ ውኃንም አመነጨ፡ በበረሃ ወንዞች ውስጥ ሄዱ፡ 42 ለአገልጋዩ
ለአብርሃም የነገረውን ቅዱስ ቃሉን አስቦአልና። 43 ሕዝቡን በደስታ፡
የመረጣቸውንም በሐሤት አወጣ ። 44 የአሕዛብንም ሀገሮች አወረሳቸው።
ባዕዳን የደከሙበትን ሁሉ ወረሱ ።45 ሕጉን ይጠብቁ ዘንድ ሥርዓቱንም
ይፈልጉ ዘንድ አዘዘ።

## መዝ /105፡ <u>የአባቶችን በደል መናዘዝ</u>

1 ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘለዓለም ነውና እግዚአብሔርን
አመስግኑ። 2 የእግዚአብሐርን ኃይል ማን ይናገራል? ምስጋናውንስ



ሁሉ ይሰማ ዘንድ ማን ይችላል? 3 ፍርድን የሚጠብቁ፡ ጽድቅንም
ሁልጊዜ የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው። 4 አቤቱ ሕዝብህን በይቅርታህ
አስበን፡ በማዳንህም ይቅር በለን። 5 የመረጥሃቸውን ሕዝብ በጎነት
እናይ ዘንድ፡ በሕዝብህም ደስታ ደስ ይለን ዘንድ፡ ከርስትህም ጋር
እንከብር ዘንድ።6 ከአባቶቻችን ጋር ኃጢአትን ሠራን፡ ዓመፅን፡
በደልንም። 7 አባቶቻችን በግብጽ ሀገር ሳሉ ተአምራትህን
አላስተዋሉም። የምሕረትህንም ብዛት አላሰቡም፡ በኤርትራ ባሕር
ባለፉ ጊዜ አስመረሩህ። 8 ኃይሉን ያሳያቸው ዘንድ ስለ ስሙ
አዳናቸው ። 9 የኤርትራን ባሕር ገሠጻት፡ ደረቀችም። እንደ ምድረ
በዳ በጥልቅ መራቸው፡ 10 ከጠላቶቻቸውም እጅ ተቤገሮቸው
(*አዳናቸው*)። 11 ያሳደዱአቸውንም ውኃ ደፈናቸው፡ ከእነርሱም
አንድ ስንኳ አልቀረም። 12 ያንጊዜም በቃሉ አመኑ፡ በምስጋናውም
አመሰገኑት። 13 ፈጥነው ግን ሥራውን ረሱ፡ በምክሩም አልፀኑም።
14 በምድረ በዳም ምኞትን ተመኙ፡ በበረሃም እግዚአብሔርን
አሳዘኑት፡ 15 የለመኑትንም ሰጣቸው፡ ለነፈሳቸውም ጥጋብን ላከ፡
16-ሙሴንም-እግዚአብሔር-የቀደሰውን-አሮንንም-በሠፈር አስቈጧ
ቸው። 17 ምድር ተከፈተች፡ ዳታንንም ዋጠችው፡ የአቤሮንንም ወገን
ደፈነች፡ 18 በማኅበራቸው እሳት ነደደች፡ ነበልባልም ኃጥአንን
አቃጠላቸው፡ 19 በኮሬብም ጥጃን ሠሩ፡ ቀልጦ ለተሠራ ምስልም
ሰገዱ። 20 ሣርንም በሚበላ በበሬ ምሳሌ ክብራቸውን ለወጡ።
21 ያዳናቸውን እግዚአብሐር ረሱ፡ ታላቅ ነገርንም በግብጽ፡
22 ድንቅንም በካም ምድር፡ ግሩም ነገርንም በኤርትራ ባሕር
ያደረገውን አላስተዋሉም። 23 እንዳያጠፋው የቁጣውን መቅሠፍት
ሁልጊዜ ይመልስ ዘንድ የመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት-ጊዜ በፊቱ
ባይቆም ኖሮ፡ ባጠፋቸው ነበር ። 24--የተወደደችውንም-ምድር ናቁ፡-
በቃሉም-አልታመኑም።25 በድንኳኖቻቸውም ውስጥ አንጐራጐሩ፡



www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔርንም ቃል አልሰሙም፡ 26 በምድረ በዳ ይጥላቸው
ዘንድ እጁን አነሣባቸው፡ በየሀገሩም ይበትናቸው ዘንድ አሰበ።
28 በብዔል ፌጎርም አለቁ፡ የሞተ መሥዋዕትንም በሉ፡
29 በሥራቸውም አነሣሡት፡ ቸነፈርም በላያቸው በዛ። 30 ፊንሐ
ስም ተነሥቶ አዳናቸው፡ ቸነፈሩም ተወ።31-በክርክር-ውኃ-ዘንድም-
አስቈጡት፡-ስለእነርሱም-ሙሴ-ተበሳጨ፡ 33-መንፈሱን አስመርረ
ዋታልና በከንፈሮቹም አዘዘ። 34 እግዚአብሔርም እንዳዘዛቸው
አሕዛብን አላጠፉም። 35 ከአሕዛብ ጋር ተደባለቁ፡ ሥራቸውንም
ተማሩ፡ 36 ለጣዖቶቻቸውም ተገዙ፡ በደልም ሆነባቸው። 37 ወንዶች
ልጆቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት መሥዋዕት አድርገው
አቀረቡ። 38 ንጹሕ ደምንም አፈሰሱ፡ የወንዶች ልጆቻቸውንና
የሴቶች ልጆቻቸውን ደም ለከነዓን ጣዖቶች ሠዉ፡ ምድርም በደም
ተበከለች፡ 39 በሥራቸውም ረከሰች፡ በጣዖቶቻቸውም አመነዘሩ።
40 እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ቁጣን ተቈጣ፡ ርስቱንም ተጸየፈ፡
41 በጠላቶቻቸውም እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፡-የሚጠሉአቸውም-
ገዙአቸው። 42- ጠላቶቻቸው አሠቃዩአቸው፡ ከእጃቸውም በታች
ተዋረዱ። 43 ብዙ ጊዜ አዳናቸው፡ እነርሱ ግን በምክራቸው አስመረሩት፡
በኃጢአታቸውም መከራ ተቀበሉ፡ 44 እንደ ተጨነቁም ተመለከታቸው፡
ጸሎታቸውንም ሰማቸው፡ 45--ለእነርሱም ቃል ኪዳኑን አሰበ፡
እንደምሕረቱ ብዛት አዘነላቸው። 46 በማረኩአቸውም ሁሉ ፊት
ይቅርታን ሰጣቸው፡ 47 አምላካችን እግዚአብሐር ሆይ! አድነን፡ ቅዱስ
ስምህን እናመሠግን ዘንድ፡ በምስጋናህም እንመካ ዘንድ ከአሕዛብ መካከል
ሰብስበን። 48 ከዘላለም እስከ ዘለዓለም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር
ይመስገን፡ ሕዝቡም ሁሉ "ይሁን፡ ይሁን ይበሉ ።

## መዝ ፻፮ /106፡ ከመከራ ሁሉ የሚታደግ አምላክ

1 ግነይ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር እስመ ለዓለም ምሕረቱ=
እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና
2 እግዚአብሔር ያዳናቸው፡ ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳናቸው ይናገሩ።



3 ከምሥራቅና ከምዕራብ፡ ከሰሜንና ከደቡብ፡ ከየሀገሩ ሰበሰባቸው።
4 ውኃ በሌለበት ምድረ በዳ ተቅበዘበዙ፡ የሚኖሩበትንም ከተማ
መንገድ አላገኙም 5 ተራቡ፡ ተጠሙም ሰውነታቸውም በላያቸው
አለቀች። 6 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡ ከመከራቸውም
አዳናቸው። 7 ወደሚኖሩበትም ሀገር ይሄዱ ዘንድ የቀና መንገድን
መራቸው። 8 የእግዚአብሔር ምሕረትን ለሰው ልጆችም ያደረገውን
ድንቅ ሥራውን ንገሩ 9 የተራበችን ነፍስ አጥግቦአልና
የተራቈተችንም ነፍስ በበረከት ሞልቶአልና 10 በጨለማና በሞትም
ጥላ የተቀመጡ በችግር በእግር ብረትም የታሰሩ 11 የእግዚአብሔር
ቃል ስላማረሩ የልዑልንም ምክር ስላስቆጡ፡ 12 ልባቸው በመከራ
ደከመ፡ ታመሙ፡ የሚረዳቸውንም አጡ 13 በተጨነቁ ጊዜ ወደ
እግዚአብሔር ጮሁ፡ ከመከራቸውም አዳናቸው 14 ከጨለማና
ከሞት ጥላ አወጣቸው፡ እግር ብረታቸውንም ሰበረ 15 የእግዚአብሔ
ርን ምህረት ለሰው ልጆችም ያደረገውን ድንቁን ንገሩ 16 የናሱን
ደጆች-ሰብሮአልና።-የብረቱን-መወርወሪያ-ከጥቅጦአልና። 17 ከበደ
ላቸው ኀዳና ተቀበላቸው፡ በኃጢያታቸውም ተሰቃይተዋልና፡
18 ሰውነታቸውም መብልን ሁሉ ተጸየፈች፡ ወደ ሞትም ደጆች
ቀረቡ ። 19 በተጨነቁም ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡ ከመከራቸ
ውም አዳናቸው። 20 ቃሉን ልኮ ፈወሳቸው፡ ከጥፋታቸውም
አዳናቸው 21 የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሰው ልጆችም ያደረገውን
ድንቁን ንገሩ 22 የምስጋና መስዕዋትንም ይሰውለት በደስታም
ሥራውን ይንገሩ 23 በመርከቦቹ ወደ ባሕር የሚወርዱ በብዙ ውኃ
ላይ ሥራቸውን የሚሠሩ 24 እነርሱ የእግዚአብሔርን ሥራ
በጥልቅም ያለችውን ድንቁን አወቁ። 25 ተናገረ አውሎ ነፋስም
ተነሳሣ፡ ሞገድም ከፍ፡ ከፍ አለ። 26 ወደ ሰማይ ይወጣሉ ፡
ወደጥልቅም ይወርዳሉ።ሰውነታቸው በመከራ ቀለጠ፡ 27 ደነገጡ፡
እንደሰካራም ተንገዳገዱ፡ ጥበባቸውም ሁሉ ተዋጠ። 28 በተጨነቁ



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡ ከመከራቸውም አዳናቸው፡ አውሎ
ነፋሱንም ጸጥ አደረገ። ባሕሩም ዝም አለ፡ 30 ማዕበሉም ዝም አለ፡
አርፈዋልና ደስ አላቸው። ወደ ፈለጉትም ማረፊትያ ወደብ
መራቸው፡ 31 የእግዚአብሔርን ምሕረትና ለሰው ልጆችም ያለውን
ድንቁን ንገሩ 32 በአህዛብ ጉባዔ ከፍ፡ ከፍ ያደርጉታል በሽማግሌዎ
ችም ሸንጎ ያመሰግኑታል። 33 ወንዞችንም በምድረ በዳ አደረገ፡
የውኃውንም ምንጮች ደረቅ አደረጋቸው 34 በተቀመጡባት ሰዎች
ክፋት ፍሬያማዋን ምድር ጨው አደረጋት። 35 ምድረ በዳውን
ለውሃ መውረጃ፡ ደረቁንም ምድር የውሃ ምንጮች አደረገ። 36 በዚ
ያም ረሀብተኞችን አስቀመጠ። የሚኖሩባቸውን ከተሞች ሠሩ ።
37 እርሻዎችንም ዘሩ፡ ወይኖችንም ተከሉ፡ የእህልንም ሰብል
አደረጉ።-38 ባረካቸውም እጅግ በዙ እንስሶቻቸውንም አላሳነሰባቸ
ውም። 39 እነርሱ በክፉ መከራና በጭንቀት ተሠቃዩ ።እያነሱም
ሄዱ፡ 40 በአለቆችም ላይ ኅሳር ፈሰሰ፡ መንገድም በሌለበት በምድረ
በዳ--አሳታቸው።41-ችግረኛውንም-በችግሩ-እረዳው፡-በሀገር እንደተ
ሠማገሩ በጎች አደረገው፡ 42 ቅኖች አይተው ደስ ይበላቸው፡ ዓመፃ
ሁሉ አፏን ትዘጋለች። 43 ይህን የሚጠብቅ ጥበበኛ ማን ነው? እርሱ
እግዚአብሔር ይቅር ባይ እንደሆነ ያውቃል።

መዝ ፻፯ /107፡ <u>የማለዳ ጸሎትና ውዳሴ</u>

1 ጥቡዕ ልብየ እግዚእ ጥቡዕ ልብየ=ልቤ ጽኑ ነው፡ አቤቱ ልቤ ጽኑ
ነው፡ አመሰግናለሁ እዘምራለሁም፡ 2 ክብሬም ይመስለኛል፡
በበገናና በመሰንቆ እነሣለሁ፡ ማልጄም እነሣለሁ፡ 3 አቤቱ በአሕዛብ
መካከል አመሰግንሃለሁ፡ በወገኖችም መካከል እዘምርልሃለሁ፡
4 ምሕረትህ በሰማይ ታላቅ ናትና፡ እውነትህም እስከ ደመና ድረስ
ነው፡ 5 እግዚአብሔር በሰማይ ከፍ ፡ ከፍ አለ ክብሩም በምድር
ሁሉ ላይ ነው። 6 ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ በቀኝህ አድን ፡
አድምጠኝም ፡ 7 እግዚአብሔር በመቅደሱ ተናገረ፡ ደስ ይለኛል፡



ሴኬምንም አካፈላለሁ፡ የሸለቆ ቦታዎችንም አሠፍለሁ፡ 8 ገለአድ
የእኔ ነው፡ ምናሤም የእኔ ነው፡ ኤፍሬምም የራሴ መጠጊያ ነው፡
ይሁዳ ንጉሤ ነው፡ 9 ካህን ሞዐብም ተስፋዬ ነው፡ በኤዶምያስ ላይም
ጫማዬን እዘረጋለሁ፡ ፍልስጤምም ይገዙልኛል ፡10 ወደ ፅኑ ከተማ
ማን ይወስደኛል? ማንስ እስከ ኤዶምያስ ይመራኛል? 11 አቤቱ
የጣልኸኝን አንተ አይደለህምን? አምላካችን ሆይ! ከሠራዊታችን
ጋር አትወጣም፡ 12 በመከራችን ጊዜ ረድኤትን ስጠን፡ በሰውም
መታመን ከንቱ ነው፡ 13 በእግዚአብሔር ኀይልን እናደርጋለን
እርሱም የሚያስጨንቁንን ያዋርዳቸዋል ።

መዝ-፻፰ /108፡ <u>በጨካኝ ጠላት ላይ የቀረበ ጸሎት</u>

1 እግዚኦ ኢትጸመመኒ ስእለትየ=አቤቱ ልመናዬን ቸል አትበል፡
2 የአመፀኛ አፍና የኃጢያተኛ አፍ በላዬ ተላቅቀዋልና፡ በሽምግልና
አንደበትም በላዬ ተናገሩ ፡3 በጥል ከበቡኝ፡ በከንቱም ተዋጉኝ፡
4 በወደድሃቸው ፈነታ ጠሉኝ፡ እኔ ግን እጸልይላቸዋለሁ፡-
5-በመልካም-ፈንታ-ክፉ-ከፈሉኝ ፡በወደድኂቸውም ፋንታ ጠሉኝ።
6 በላዩ ኃጢያተኛን ሹም፡ ሰይጣንም በቀኙ ይቁም፡ 7 በሚከራከርም
ጊዜ ተረትቶት ይውጣ፡ ጸሎቱም በደል ትሁንበት፡ 8 ዘመኖቹም
ጥቂት ይሁኑ፡ ሹመቱንም ሌላ ሰው ይውሰዳት፡ 9 ልጆቹም ድሃ
አደጎች ይሁኑ፡ ሚስቱም መበለት ትሁን፡ 10 ልጆቹም ታውከው
በመሰደድ ይለምኑ። ከቤታቸውም ያባሯቸው 11 ባለዕዳም ገንዘቡን
ሁሉ ይበርብረው፡የደከመበትንም ሁሉ ባዕድ ይበዝብዘው፡ 12-የሚ
ረዳውንም አያግኝ፡ ለድሃ አደግ ልጆቹ የሚራራላቸው አይኑር፡
13-ልጆቹም ይጥፉ፡ በአንዲት ትውልድ የስሙ መታሰቢታ ትጥፋ፡
14 የአባቱ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ትታሰብ፡ የእናቱም
ኃጢአት አይደምሰስ፡ 15 በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ ይኑር፡
መታሰቢያውም ከምድር ይጥፋ። 16 ምጽዋትን ያደርግ ዘንድ
አላሰበምና፡ ድሃንና ምስኪንንም ሰው አሳዷልና፡ ልቡም ሰውን



www.ethiopianorthodox.org

ስመግደል የጨከነ ነውና። 17 መርገምንም መረጣት፡ ወደእርሱም
ትምጣ፡ በረከትንም አልመረጣትምና፡ ከእርሱ ትራቅ ።18 መርገምን
እንደልብስ ለበሰ፡ እንደውሃም ወደ አንጀቱ፡ እንደቅባትም ወደ
አጥንቱ ገባች፡ 19 እንደሚለብሰው ልብስ፡ ሁልጊዜም እንደሚታጠቀ
ውም ትጥቅ ትሁንበት፡ 20 ይህ ድርጊት በእግዚአብሔር ዘንድ
በሚያጣሉኝና በነፍሴም ላይ ክፉ በሚናገሩ ላይ ነው። 21 አንተ ግን
አቤቱ ጌታዬ ስለ ስምህ ምሕረትህን በእኔ ላይ አድርግ፡ ምሕረትህ
መልካም ናትና፡ አድነኝ ፡ 22 እኔ ድሃና ምስኪን ነኝና፡ ልቤ በውስጤ
ደነገጠብኝ። 23 እንዳለፈ ጥላ አለቅሁ፡ እንደ አንበጣም እረገፍሁ።
24 ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ፡ ሥጋዬም ቅባት በማጣት ከሣ፡ 25 እኔ
በእነርሱ ዘንድ ተሰደብኩ፡ ባዩኝ ጊዜ እራሳቸውን ነቀነቁ። 26 አቤቱ
አምላኬ እርዳኝ፡ ስለምሕረትህም አድነኝ ። 27 አቤቱ እጅህ ይህቺ
እንደሆነች፡ አንተም ይህችን እንዳደረግህ ይወቁ። 28 እነርሱ
ይራገማሉ፡ አንተ ግን ባርክ፡ በእኔ ላይ የሚነሡ ይፈሩ፡ አገልጋህን
ደስ ይበለው፡ 29 የሚያጣሉኝ እፍረትንና ውርደትን ይልበሱ፡
ኃጢአታቸውን እንደመጐናጸፊያ ይልበሷት። 30 እግዚአብሔርን
በአፌ እጅግ አመሰግነዋለሁ፡ በብዙዎችም መካከል አከብረዋለሁ፡
31 ነፍሴን ከሚከባት ያድን ዘንድ በእኔ በድሃው ቀኝ ቆሞአልና።

## መዝ ፻፱ /109፡ የእግዝይአብሔር ካህንና መሲሕ

1 ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ=ጌታ ጌታዬን 'ጠላቶችህን
ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ' አለው 2
እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል፡ በጠላቶችህም
መካከል ገዢ ትሆናለህ፡ 3 ቀዳማዊ በኃይል ቀን፡ በቅዱሳን ብርሃን
ካንተ ጋር ነበር፡ ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ፡ 4
"እንደመልከ ጻድቅ ሹመት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ" ብሎ
እግዚአብሔር ማለ፡ አይፀፀትም።5 እግዚአብሐር በቀኝህ ነው፡
ነገሥታትን በቁጣ ቀን ይቀጠቅጣቸዋል። 6 በአሕዛብ መካከል



ይፈርዳል፡ እሬሳቸውንም ያበዛል ፡ በምድር ላይ የብዙዎችን
እራሶች ይቀጠቅጣል ፡ 7 በመንገድ ከፈሳሽ ውሃ ጠጡ።ስለዚህም ራስ
ከፍ፡ ከፍ ይላል።

## መዝ-፻፲/110፡ የእግዚአብሔር-ታላቅነት-

1 እገኒ ለከ እግዚኦ በኵሉ ልብየ=አቤቱ በቅኖች ሸንጎ በጉባዔም
በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ 2 የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ ናት፡
በፈቃዱም ሁሉ የተፈለገች ናት፡ 3 ሥራውም ምስጋናና የጌትነት
ክብር ነው፡ ጽድቁም ለዘለዓለም ይኖራል፡ 4 ለጌትነቱ መታሰቢያን
አደረገ፡ እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው፡ ለሚፈሩት ምግብን
ሰጣቸው፡ቃል ኪዳኑንም ለዘለዓለም ያስባል።6 የአሕዛብን ርስት
ይሰጣቸው ዘንድ፡ ለሕዝቡም የሥራውን ብርታት አሳየ፡ 7 የእጆቹ
ሥራ እውነትና ቅን ነው፡ ትእዛዙም የታመነ ነው፡ 8 ለዘለዓለም የፀና
ነው፡ በእውነትና በቅንም የተሠራ ነው፡ 9 እግዚአብሔርም
መድኃኒትን ለሕዝቡ ላከ፡ ቃል ኪዳኑንም ለዘለዓለም አዘዘ፡ ስሙ
የተቀደሰና የተፈራ ነው። 10 የጥበብ-መጀመሪያ እግዚአብሔርን
መፍራት ነው፡ ለሚያደርጋትም ሁሉ ምክር መልካም ናት፡
ምስጋናውም ለዘለዓለም ይኖራል።

## መዝ ፻፲፩ /111. የጻድቅ ሰው በረከት ዘለዓለማዊነት

1 ብፁዕ ብእሲ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር=እግዚአብሔርን
የሚፈራ፡ ትእዛዙንም የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው። ዘሩ በምድር
ላይ-ኃያል-ይሆናል፡-የጻድቃን-ትውልዶች-ይባረካሉ።3 ባለጸግነትና
ክብር በቤቱ ነው፡ ጽድቁም ለዘለዓለም ይኖራል። 4 ለቅኖች
በጨለማ ብርሃን ወጣላቸው፡ እግዚአብሒአአር መሐሪና ይቅር
ባይ ነው። አምላካችን ጻድቅ ነው።5 ርኅሩኅ፡ ይቅር ባይና ቸር
ነው። ነገሩን በፍርድ ይፈጽማል።6 ለዘለዓለም አይታወክም።
የጻድቅ ሰው መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል። 7 ከክፉ ነገርም
አይፈራም፡ ባእግዚአብሔር ለመታመን ልቡ7 የፅ4አና ነው። 8
የጠላቶቹን አወዳደቅ እስኪያይ ድረስ ልቡ ፅን ነው፡ ለዘለዓለም



www.ethiopianorthodox.org

አይታወክም። ያለውን ሁሉ በተነ፡ ለድሆችም ሰጠ፡ ዝድቁ
ለዘለዓለም ዓለም ይኖራል። ቀንዱም *(ሥልጣኑ)* በክብር ከፍ፡ ከፍ
ይላል። 10 ኃጢአተኛ ይህን አቶ ይቈጣል፡ ትርሱንም
ታፋጫል፡ ይቀልጣልም፡ የኃጥአንም ምኞት ትጠፋለች

## መዝ፻፲፪ /112፡ ለመሐሪ አምላክ የሚቀርብ ምስጋና

1--ሰብሕዎ አግብርቲሁ ለእግዚአብሔር=የእግዚአብሐር አገልጋ
ዮች ሆይ! አመስግኑት፡-የእግዚአብሔርን-ስም-አመስግኑ፡ 2-ከዛሬ
ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ የእግዙአብሐር ስም ቡሩክ ይሁን፡
3 ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ የእግዚአብ
ሐር ስሙ ይመስገን። 4 እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ
ልዑል ነው፡ ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው። 5 እንደ አምላካችን
እንደ እግዚአብሔር በልዕልና የሚኖር ማነው?6--በሰማይና
በምድር የተዋረዱትን የሚያይ፡ 7 ድሃውን ከምድር የሚያነሣ፡
ምስኪኑንም ከመሬት ከፍ፡ ከፍ የሚያደርግ፡ 8 ከአለቆች ጋርና
ከሕዝቡም አለቆች-ጋይ ያኖረው ዘንድ። 9 መካኒቱን በቤቱ
የሚያኖራትና ደስ የተሰኘችም የልጆች እናት ያደርጋታል።

## መዝ-፻፲፫ /113፡ ምድርን የሚያናውጥ ድንቅ ሥራ

1 አመ ይወፅኡ እስራኤል እምግብጽ=እስራኤል ከግብጽ፡
የያዕቆብም፡ ወገን ከጠላት ሕዝብ አምልጠው በወጡ ጊዜ፡
2 ይሁዳ መመስገኛው፡ እስራኤልም ግዛቱ ሆነ፡ 3 ባሕር አየች፡
ሸሸችም፡ ዮርዳኖስም ወደ ኋላ ተመለሰ። 4 ተራሮች እንደ
ኮርማዎች፡ ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ። 5 አንቺ ባሕር
የሸሸሽ፡ አንተም ዮርዳኖስ ወደ ኋላ የተመለስህ ምን ሆናችሁ
ነው ? 6 እናተም ተራሮች እንደ ኮርማዎች፡ ኮረብቶችስ እንደ
በጎች ጠቦቶች ስለምን ዘለላችሁ? 7 ከያዕቆብ አምላክ ፊት፡
ከእግዚአብሔር ፊት የተነሣ ምድር ተናወጠች፡ 8 ዐለቱን ወደ
ውኃ ምንጭ፡ ጢንጫውንም፡ ወድ ውኃ ኩሬ የለወጣ። 9 ለእኛ፡
አይደለም-አቤቱ-ለእኛ-አይደለም፡ነገር ግን ለስምህ ስለምሕረትህና
ስለእውነትህም ምስጋናን እንስጥ፡ 10 አሕዛብ "አምላካችን
ወዴት ነው? አይበሉ 11 አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው።
በሰማይም በምድርም እግዚአብሐር የፈቀደውን ሁሉ አደረገ ።



12 የአሕዛብም ጣዖቶች የወርቅና የብር የሰው እጅ ሥራ
ናቸው፡ 13 አፍ አላቸው ግን አይናገሩም፡ አይን አላቸው
አያዩም፡ 14 ጆሮ አላቸው፡ አይሰሙም፡ አፍንጫ አላቸው ፡
አያሸቱም፡ 15 እጅ አላቸው፡ አይዳስሱም፡ እግረ አላቸው፡
አይሄዱም፡ በጉሮሮአቸውም አይናገሩም፡ 16 በአፋቸው ትንፋሽ
የለም። የሚሠሯቸውና የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደእነርሱ
ይሁኑ፡ 17 የእስራኤል ወገኖች ሆይ በእግዚአብሔር ታመኑ፡
እረዳታችሁና መታመኛችሁ እርሱ ነው። 18 የአሮን ወገኖች
ሆይ! በእግዚአብሐር ታመኑ፡ ረዳታችሁና መታመኛችሁ እርሱ
ነው።19-እግዚአብሔርን-የምትፈሩ ሆይ! በእግዚአብሐር ታመኑ፡
እረዳታችሁና መታመኛችሁ እርሱ ነውና። 2 እግዚአብሐር
ሆይ!--አስበን፡-ባርከንም፡-የእስራኤልንም-ወገኖች-ባርክ፡ የአሮንንም
ወገኖች ባርክ፡ 21 እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ትንንሾችንና
ትልልቆችን ሁሉ ባርካቸው። 22 እግዚአብሔር ባላያችሁና
በልጆቻችሁ ላይ ይጨምር፡ 23 እናንተ ሰማይና ምድርን
ለሠራው ለእግዚአብሔር የተባረካችሁ ናችሁ፡ 24 የሰማዮች
ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው፡ ምድር ግን ለሰው ልጆች ሰጠ። 25
አቤቱ ሙታን የሚያመሰግኑህ አይደሉም፡ ወደ ሲኦልም
የሚወርዱ ሁሉ፡ 26 እኛ ሕያዋን ግን ከዛሬ ጀምሮ እስከ
ዘለዓለም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

## መዝ-፻፲፬/114፡ የእግዚአብሐር ምሕረትና ይቅርባይነት

1 አፍቀርኩ-እስመ-ሰምዐኒ-እግዚአብሔር-ቃለ ስእለትየ= እግዚአ
ብሐር የልመናዬን ቃል በማድመድዕ ሰምቶአልና ወደድሁት፡
2 ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና በዘመኔ ሁሉ እጠራዋለሁ።
3 የሞት ጣር ያዘኝ፡ የሲኦልም ሕማም አገኘኝ፡ ጭንቀትና
መከራ አገኘኝ፡ 4 የእግዚአብሔርን ስም ጠራሁ፡ አቤቱ ነፍሴን
አድናት። 5 እግዚአብሔር መሐሪና ጻድቅ ነው፡ አምላካችን
ይቅር ባይ ነው። 6 እግዚአብሔር ሕፃናትን ይጠብቃል፡
ተቸገርርኩ፡ እርሱም አዳነኝ ።7 ነፍሴ ሆይ! ወደ ዕረፍትሽ
ተመለሺ፡ እግዚአብሔር ረዳትሽ ነውና። 8 ነፍሴን ከሞት፡



www.ethiopianorthodox.org

ዓይኔን ከእንባ፡ እግሬንም ከድጥ አድኖአልና በሕያዋን ምድር
ላይ እግዚአብሐርን ደስ አሰኘዋለሁ።

መዝ 15/115፡ <u>የእግዚአብሔር በረከት</u>

1 አመንኩ በዘ ነበብኩ እስመ ብዙኀ ሐመምኩ=በተናገርሁት
አመንሁ፡ እኔ እጅግ ታምሜአለሁና። 2 እኔም "ከራሴ ጀምሮ
ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው" አልሁ።3 ስላደረገልኝ መልካም ነገር
ሁሉ ለእግዚአብሔር ምንን እከፍለዋለሁ? 4 የሕይወትን ጽዋ
እቀበላለሁ፡ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ። 5 በሕዝቡ
ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሔር እሰጣለሁ። 6 የጻድቅ ሞት
በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው፡ 7 አቤቱ እኔ አገልጋይህ ነኝ፡
የሴት አገልጋይህም ልጅ ነኝ፡ ሰንሰለቴን ሰበርሃልና፡ 8 ለአንተ
የምስጋና መሥዋዕትን እሠዋለሁ፡ የእግዚአብሐርንም ስም
እጠራለሁ፡ 9 በሕዝቡም ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሐር
እሰጣለሁ።10 በእግዚአብሐር ቤት አደባባይ ኢየሩሳሌም ሆይ!
በመካከልሽም፡ ሃሌ ሉያ !

መዝ-፻፲፮/116፡ <u>የአሕዛብ ሁሉ ምስጋና ለእግዚአብሔር</u>

1 ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ አሕዛብ= አሕዛብ ሁላችሁ
እግዚአብሔርን አመስግኑ ፡ ወገኖችም ሁሉ ያመስግኑት
2 ምሕረቱ በእኛ ላይ ፀንታለችና፡ የእግዚአብሔርም እውነት
ለዘለዓለም ትኖራለች፡ ሃሌ ሉያ።

መዝ ፻፲፯ /117፡ <u>በእግዚአብሔር ከንድ ተማምኖ መኖር</u>

1 ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር= እግዚአብሔርን አመስግኑ
ቸር ነውና ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና 2 ቸር እንደሆነ ምሕረቱ
ለዘለዓለም እንደሆነ የእስራኤልን ወገኖች ንገሩ፡ 3 ቸር እንደሆነ
ምሕረቱ ለዘለዓለም እንደሆነ የአሮን ወገኖች ንገሩ፡ 4 ቸር
እንደሆነ ምሕረቱ ለዘለዓለም እንደሆነ እግዚአብሔርን የምትፈሩ
ሁሉ ንገሩ። 5 በተጨነቅህ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፡
ሰማኝ፡ አስፋልኝም። 6 እግዚአብሐር ረዳቴ ነው። አልፈራም፡
ሰው ምን ያደርገኛል ? 7 እግዚአብሔር እረዳቴ ነው።
የጠላቶቼን ውድቀት አይለሁ፡ 8 በሰው ከመታመን
በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል፡ 9 በአለቆች ተስፋ ከማድረግ



ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል። 10 አሕዛብ
ሁሉ ከበቡን፡ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው፡ 12 ንብ
ማርን እንደሚከብብ ከበቡኝ፡ እሳትም በእሾህ እንደሚነድድ
ነደዱ። በእግዚአብሔርም ስም አሸንፍኳቸው ።13 ለመውደቅም
ተንገዳገድሁ፡ እግዚአብሐር ግን አነሣኝ፡ 14 ኃይሌም፡ ስም
አጠራሬም እግዚአብሔር ነው፡ እርሱ አዳኜ ሆነኝ፡ 15 የደስታ
ድምፅ በጻድቃን ማደሪያዎች ነው። የእግዚአብሔርም ቀኝ
ኃይልን አደረገች፡ 16 የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ፡ከፍ አደረገችኝ፡
የእግዚአብሔር-ቀኝ ኃይልን አደረገች። 17 አልሞትም፡
በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፡ የእግዚአብሔርንም ሥራ
እናገራለሁ፡ 18 መገሠፁን እግዚአብሔር ገሰሠፀኝ፡ ለሞት ግን
አሳልፎ አልሰጠኝም። 19 ወደ እነርሱም ገብቼ እግዚአብሔርን
አመሰግን ዘንድ የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ፡ 20 ይህቺ
የእግዚአብሔር ደጅ ናት፡ ወደ እርሷም ጻድቃን ይገባሉ።
21 ሰምተኸኛልና፡ አዳኜ፡ ሆነኸኛልና አቤቱ አመሰግንሃለሁ።
22 ግንበኞኖችን የናቋት ድንጋይ እርሷ የማዕዘን እራስ ሆነች፡
23 ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፡ ለዓይኖቻችንም ድንቅ
ናት። 24 እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፡ በእርሷ ደስ
ይበለን፡ ሐሴትንም እናድርግባት። 25 አቤቱ እባክህ አሁን
አድን፡ አቤቱ እባክህ አሁን አቅና፡ 26 በእግዚአብሔር ስም
የሚመጣ ብሩክ ነው።ከእግዚአብሐር ቤት መረቅናችሁ፡ 27 ጌታ
እግዚአብሔር ተገለጠልን፡ እስከ መሠዊያው ቀንዶች ድረስ
የሚያስተነትኑበት በደስታ በዓለን አድርጉ። 28 አንተ አምላኬ
ነህ፡ አመሰግንሃለሁ አንተ አምላኬ ነህ፡ ከፍ ፡ከፍ አደርግሃለሁ፡
ሰምተኸኛልና፡ አዳኜ ሆነህህልኛልና አመሰግንሃለሁ። 29 እግዚ
አብሔርን አመስግኑ። ቸር ነውና፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና።

መዝ ፻፲፰/118. <u>*አሌፍ ብሂል አብ ፈጣሬ ኵሉ ዓለም=*</u>
<u>*አሌፍ-አብ-የዓለማት-ፈጣሪ-ማለት-ነው።*</u> 1 በመንገዳቸው-ንጹ
ሐን የሆኑና በእግዚአብሔር ሕግ የሚሄዱ ብፁዓን ናቸው፡ 2
ምስክሩን የሚፈልጉ በፍጹም ልብ የሚሹት ብፁዓን-ናቸው።3
ዓመፃን የሚያደርጉ ግን በመንገዱ አይሄዱም፡ 4 ትእዛዝህን



www.ethiopianorthodox.org

እጅግ እንጠብቅ ዘንድ አንተ አዘዝህ ፡5 ሥርዓትህንም እንጠብቅ
ዘንድ፡፡የሚቀና ከሆነ መንገዴ ይቅና፡፡ 6-ትእዛዝህን ሁሉ
ስመለከት በዚያን ጊዜ አላፍርም፡፡ 7 አቤቱ የጽድቅህን ፍርድ
ስማር-በቅን ልብ አመሰግንሃለሁ፡ 8 ሥርዓትህንም እጠብቃለሁ፡
ለዘለዓለም አትጣለኝ፡፡
*ቤት-ብሂል ባዕል እግዚአብሔር=እግዚአብሔር ባለጸጋ ማለት*
*ነው።* 9 ጐልማሳ መንገዱን በምን ያቀናል? ቃልህን በመጠበቅ
ነው፡፡10-በፍጹም-ልቤ-ፈለግሁህ፡-ከትእዛዝህ-አታርቀኝ፡፡11-አን
ተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ፡፡ 12 አቤቱ አንተ
ቡሩክ ነህ፡ ሥርዓትህንም አስተምረኝ፡፡ 13 የአፍህን ፍርድ
ሁሉ በከንፈሬ ነገርሁ፡፡ 14 ብልጽግናን እንዳገኘ ሁሉ፡ በምስክ
ርህ-መንገድ-ደስ አለኝ፡፡15-ትእዛዛትህን-አሰላስልሁ፡ መንገድህንም
እፈልጋለሁ፡፡ 16 ትእዛዛትህን አነብባለሁ፡ ቃልህንም አልረሳም፡፡
*ጋሜል ብሂል ሕያው እግዚአብሔር= ሕያው እግዚአብሔር*
*ማለት ነው።* 17 ሕያው እንዲሆንና ቃልህንም እንዲጠብቅ
ለአገልጋይህ ስጠው፡፡18 ዓይኖቼን ክፈት፡ ከሕግህም ድንቅ
ነገርን አያለሁ፡፡ 19 እኔ በምድር ደስተኛ ነኝ፡ ትእዛዛትህን ከእኔ
አትሰውር፡፡ 20 ነፍሴ ሁልጊዜ ፍርድህን እጅግ ናፈቀች፡
ትዕቢተኞችን ገሠፅሃቸው፡፡ 21 ከትዕዛዝህ የሚርቁ ርጉማን
ናቸው፡፡ 22 ትዕዛዝህን ፈልጌአለሁና ስድብንና ነውርን ከእኔ
አርቅ፡፡ 23 አለቆች ደገሞ ተቀምጠው እኔን አሙኝ፡ አገልጋይህ
ግን ፍርድህን ያሰላስላል፡፡ 24 ምስክርህም ትምህርቴ ነው፡
ሥርዓትህም መካሪዬ ነው፡፡
*ዳሌጥ ብሂል ድልው እግዚአብሔር።* 25 ሰውነቴ ወደ
ምድር ተጣበቀች፡ እንደ ቃልህ ሕያው አድርገኝ፡፡ 26 መንገድ
ህንና ምስክርህን ነገርሁ፡ ፍርድህን አስተምረኝ፡፡ 27-የእውነት
ህን-መንገድ-እንዳስተውል-አድርገኝ፡-ተአምራትህንም አሰላስላ
ለሁ፡፡28 ከሐዘን የተነሣ ሰውነቴ አንቀላፋች፡ በቃልህ አበርታኝ፡፡
29-የዓመፃን መንገድ-ከእኔ-አርቅ፡ በሕግህ-ይቅር-በለኝ፡፡ 30-የእ
ውነትህን-መንገድ-መረጫለሁ፡-ፍርድህን-አልረሳሁም፡፡ 31-አቤቱ



አቤቱ-ምስክርህን-ተከትያለሁና-ልሁና አታሳፍረኝ፡፡ 32-ልቤን-
ባሰፋኸው-ጊዜ-በትእዛዝህ መንገድ ሮጥሁ፡፡
*ሄ ብሂል ህልው እግዚአብሔር= እግዚአብሔር የሚኖር /ኑዋሪ*
*ማለት ነው።* 33 አቤቱ የእውነትህን መንገድ አስተምረኝ፡
ሁልጊዜም እፈልጋታለሁና፡ 34 እንዳስተውል አድርገኝ፡
ሕግህንም-እፈልጋለሁ፡በፍጹም ልቤም-እጠብቀዋለሁ፡፡ 35 እርስ
ዋን ወድጃለሁና የትእዛዝህን መንገድ ምራኝ፡፡ 36 ልቤን
ወደ ምስክርህ መልስ፡ ወደ ቅሚያም አይሁን ፡፡ 37 ከንቱ
ነገርን እንዳያዩ ዓይኖቼን መልስ፡ በመንገድህ ሕያው አድርገኝ፡፡
38-ለአገልጋይህ በቃልህ የተናገርኸውን አፅና፡፡ 39 ፍርድህ
መልካም-ነውና-የተጠራጠርሁትን-ስድብ ከእኔ አርቅ፡፡ 40 እነሆ
ትእዛዝህን ናፈቅሁ፡ በጽድቅህም ሕያው አድርገኝ፡፡
*ዋው-ብሂል-ዋሕድ እግዚአብሔር=አንድ-እግዚኣአብሔር ማለት*
*ነው።* 41 አቤቱ ምሕረትህ ይምጣልኝ፡ አቤቱ ማዳንህ እንደ
ቃልህ ነው፡፡ 42 በቃልህ ታምኛለሁና ለሚሰድቡኝ በቃል
እመልስላቸዋለሁ፡፡ 43 በፍርድህም ታምኛለሁና፡ የእውነትን
ቃል ከአፌ ፈጽመህ አታርቅ፡፡ 44 ለዘለዓለም ዓለም ሁልጊዜ
ሕግህን እጠብቃለሁና፡ 45 ትእዛዝህንም ፈልጌአለሁና አስፍቼ
እሄዳለሁ፡፡ 46 በነገሥታት ፊት ምስክርህን እናገራለሁ፡ አላፍር
ምም፡፡ 47 -እጅግም -የወደድኊቸውን ትእዛዛትህን እንገራለሁ፡
48 እጆቼንም ወደ-ወድድኊቸው ትእዛዛትህ አነሣለሁ፡፡
ፍርድህንም አሰላስላለሁ፡፡
*ዛይ-ብሂል-ዝኩር-እግዚአብሔር=መታወስ-የሚገባው-ማለት-ነው፡፡*
49 ላገልጋይህ ተስፋ ያስደረግኸውን ቃልህን አስብ፡ 50 ቃልህ
ሕያው አድርጎኛልና፡ ይህች በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ፡፡ 51 ትዕቢ
ተኞች እጅግ ዓመፁ፡ እኔ ግን ከሕግህ አልራቅሁም፡፡ 52 ከጥ
ንት-የነበረውን-ፍርድህን አሰብሁ፡-አቤቱ ደስ አለኝ፡፡53 ሕግህን
ከረሱ ኃጥአን የተነሣ ኃዘን ያዘኝ ፡ 54 በተሰደድሁበት ሀገር
ፍርድህ መዝሙር ሆነኝ፡፡ 55 አቤቱ በሌሊት ስምህን አሰብሁ፡
ሕግህንም ጠበቅሁ፡ 56 ትእዛዛትህንም ፈልጌአለሁና ይህች
መመሪያ ሆነችልኝ ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

*ሔት ብሂል ሕያው እግዚአብሔር=* 57 እግዚአብሔር ክፍሌ ነው፡ "ሕግህን ይጠብቁ" አልሁ። 58 አቤቱ በፍጹም ልቤ ወደ ፊትህ ለመንሁ፡ እንደ ቃልህ ይቅር በለኝ። 59 ስለ መንገዶችህ አሰብሁ፡ እግሬንም ወደ ምስክርህ መለስሁ።60-ትእዛዝህን ለመጠበቅ-ጨከንሁ፡ አልተጠራጠርሁምም። 61 -የኃጥአን ገመዶች ተተበተቡብኝ፡ሕግህን ግን አልረሳሁም። 62 ስለ ጽድቅህ ፍርድ አመሰግንህ ዘንድ በእኩለ ሌሊት እነሣለሁ።63 እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ ትእዛዝህንምለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ። 64 አቤቱ ይቅርታህ በምድር ሁሉ ሞላች።

*ጤት ብሂል ጠቢብ እግዚአብሔር= እግዚአብሔር ጠቢብ ማለት ነው።* 65 አቤቱ እንደ ቃልህ ለአገልጋይህ መልካም አደረግህ። 66 በትእዛዛትህ ታምኛለሁና መልካም ምክርንና ጥበብን አስተምረኝ። 67 እኔ ሳልጨነቅ ተፀፀትሁ፡ ስለዚህም ቃልህን ጠበቅሁ። 68 አቤቱ አንተ ቸር ነህ። በቸርነትህም ፍርድህን አስተምረኝ። 69 የትዕቢተኞች ዓመፃ በላዬ በዛ፡ እኔ ግን በፍጹም ልቤ ትእዛዝህን እፈልጋለሁ። 70 ልባቸው እንደ ወተት ረጋ፡ እኔ ግን ሕግህን አነብባለሁ። 71 ፍርድህን አውቅ ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።72 ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል።

*ዮድ ብሂል የማነ እግዚአብሔር=የእግዚአብሔር ቀኝ ማለት ነው።* 73 እጆችህ ሠሩኝ፡ አበጁኝም። እንዳስተውል አድርገኝ። ትእዛዝህንም እማራለሁ። 74 በቃልህ ታምኛለሁና የሚፈሩህ እኔን አይተው ደስ ይላቸዋል። 75 አቤቱ ፍርድህ ጽድቅ እንደሆነችና በሚገባም እንዳስጨነቅኸኝ አወቅሁ።76 ምሕረትህ ለደስታዬ ይሁነኝ፡ እንደቃልህም ለአገልጋይህ ይሁንለት። ሕግህ ትምህርት ሆኖልኛልና፡ 77 ሕግህ ትምህርቴ ነውና፡ ቸርነትህ ይምጣልኝ፡ በሕይወትም ልኑር። 78 ትዕቢተኞች ዓመፃን መክረውብኛልና ይፈሩ ። እኔ ግን ትእዛዝህን አሰላስላለሁ። 79 የሚፈሩህና ምስክሮችህን የሚያውቁ ወደ እኔ ይመለሱ። 80 እንዳላፍር ልቤ በፍርድህ ንጹሕ ይሁን።



*ካፍ ብሂል ከሃሊ እግዚአብሔር= ሁሉን ማድረግ የሚችል ማለት ነው።* 81 ነፍሴ ወደ ማዳንህ አለፈች፡ በቃልህም ታመንሁ። 82 'መቼ ታጽናናኛለህ?' እያልሁ ዓይኖኖቼ ትድግናህን በመጠበቅ ፈዘዙ። 83 በውርጭ እንዳለ አቁማዳ ሆኛለሁና። ፍርድህን ግን አልረሳሁም። 84 የአገልጋይህ ዘመኖች ምን ያህል ናቸው? በሚያሳድዱኝስ ላይ መቼ ትፈርድልኛለህ? 85 ኃጥአን ዋዛ ፈዛዛን ነገሩኝ፡ አቤቱ እንደ ሕግህ ግን አይደለም። 86-ትእዛዝህ ሁሉ እውነት ብቻ ናቸው። በአመፃ አሳደውኛልና ርዳኝ። 87 ከምድር ሊያጠፉኝ ጥቂት ቀርቶአቸው ነበር። እኔ ግን ትእዛዝህን አልተውሁም። 88 እንደ ምሕረትህ ሕያው አድርገኝ፡ የአፍህንም ምስክር እጠብቃለሁ። 89 አቤቱ ቃልህ በሰማይ ለዘለዓለም ይኖራል። 90 እውነትህ ለልጅ ልጅ ናት። ምድርን መሰረትሃት፡ እርሷም ትኖራለች። 91 ሁሉን ገዝተሃልና ቀኑ በትዕዛዝህ ይኖራል። 92 ሕግህ ትምህርቴ ባይሆን ኖሮ በጉስቁልናዬ በጠፋሁ ነበር። 93 በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና ፍርድህን ለዘለዓለም አልረሳም። 94 እኔ የአንተ ነኝ፡ ፍርድህን ፈልጌአለሁና አድነኝ። 95 ኃጥአን ያጠፉኝ ዘንድ ጠበቁኝ፡ ምስክርህን አስተውያለሁና።

*ሜም-ብሂል-ምዑዝ-እግዚአብሔር= መዓዛ ያለው ማለት ነው።* 96 የሥራውን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ፡ ትእዛዘህ ግን እጅግ ሰፊ ነው። 97 አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትምህርቴ ነው። 98 ለዘለዓለም ለእኔ ነውና ትእዛዝህ፡ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ። 99 ትእዛዝህ ትምህርቴ ነውና ካስተማሩኝ ሁሉ ይልቅ አዋቂ አደረገኝ።-100 ትእዛዝህን ፈልጌአለሁና-ከሽማግሌዎች-ይልቅ-አስተዋይ-ሆንሁ።101-ቃልህን እጠብቅ-ዘንድ ከክፉ-መንገድ-ሁሉ-እግሬን-ከለከልሁ፡-102 አንተ አስተምረኸኛልና ከፍርድህ አልራቅሁም። 103 ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፡ ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ ሆነልኝ። 104 ከትእዛዝህ የተነሣ አስተዋልሁ። የዓመፃን መንገድ ጠላሁ።

*ኖን-ብሂል-ንጉሥ እግዚአብሔር=*-105 ሕግህ ለእግሬ መብራት፡ ለመንገዴ ብርሀን ነው። 106 የጽድቅህን ፍርድ እጠብቅ ዘንድ



www.ethiopianorthodox.org

ማልሁ፡ አፀናሁም። 107 እጅግ መከራ ተቀበልሁ፡ አቤቱ እንደቃልህ ሕያው አድርገኝ። 108 አቤቱ ከአፌ የሚወጣውን ቃል ውደድ፡ ፍርድህንም አስተምረኝ።109 ነፍሴ ሁልጊዜ በእጅህ ውስጥ ናት፡ ሕግህንም አልረሣሁም።110 ኃጥአን ወጥመድን ዘረጉብኝ። ከትእዛዝህ ግን አልራቅሁም። 111 የልቤ ደስታ ነውና ምስክርህን ለዘለዓለም ወረስሁ፡ 112 ለዘለዓለም ያለ ነቀፋ ትእዛዝህን አደርግ ዘንደ ልቤን መለስሁ።

*ሳምኬት ብሂል ሰፋኒ እግዚአብሔር=ገዢ እግዚአብሔር ማለት ነው።*

113 ዓመፀኞችን ጠላሁ፡ ሕግህን ግን ወደድሁ ።114 አንተ ረዳቴና መጠጊያዬ ነህ፡ በቃልህም ተማመንሁ። 115 እናንተ አመፀኞች-ከእኔ-ራቁ፡ የአምላኬንም-ትእዛዝ-ልፈልግ። 116 እንደ ቃልህ ተቀበለኝ፡ ሕያውም እሆናለሁ፡ ከተስፋዬም አታሳፍረኝ። እርዳኝ፡-አድነኝም።-ሁልጊዜም-ፍርድህን-አነብባለሁ።118 ምኞታ ቸው ዓመፃ ነውና ከሥርዓትህ የሚርቁትን ሁሉ አጐሳቈልሃ ቸው። 119 የምድር ኃጥአን ሁሉ-ወንጀለኞች-ናቸው፡ስለዚህ ምስክርህን-ወደድሁ።-120-መፈራትህን-በሥጋዬ-ውስጥ-እንዲስ ማማ፡ አድርግ፡ ከፍርድህ የተነሣ ፈርቻለሁና፡

ዔ ብሂል ዐቢይ እግዚአብሔር=ታላቅ የሆነ እግዚአብሔር ማለት ነው።

121 ፍርድንና ጻድቅን ሠራህ፡ ለሚያስጨንቁኝ አሳልፈህ አትስጠኝ። 122 አገልጋይህን በመልካም ጠብቀው። ትዕቢተኞ ችም አይጋፉኝ፡ 123 ዐይኖቼ ለማዳንህና ለጽድቅ ቃልህም ፈዘዙ፡ 124 ለባሪያህ እንደ ምሕረትህ አድርግ፡ ፍርድህንም አስተምረኝ። 125 እኔ አገልጋይህ ነኝ፡ እንዳስተውል አድርገኝ፡ ምስክርህንም አውቃለሁ፡ 126 ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ አለው፡ ሕግህንም ሻሩት። 127 ከወርቅና ከዕንቁ ይልቅ ትእዛዝትህን ወደድሁ። 128 ስለዚህ ወደ ትእዛዝህ ሁሉ አቀናሁ፡ የዓመፃንም መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

*ፌ ብሂል ፍቁር እግዚአብሔር=የሚወደድ አምላክ ማለት ነው።*

129-ምስክርህ-ድንቅ-ነው፡-ስለዚህ-ነፍሴ-ፈለገችው።130- የቃልህ ነገር ያበራል፡ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል። 131 አፌን ከፈትሁ፡ልቡናዬን-አስፋሁ፡ትእዛዝህን-ወድጃለሁና። 132 ስምህን



ለሚወድዱ-እንደምታደርገው-ፍርድ-ወደ-እኔ ተመልከት፡ ይቅርም በለኝ።133 መንገዴንና አካሄዴን እንደ ቃልህ አቅና፡ ኀጢአትም ሁሉ ድል አይንሳኝ። 134 ከሰው ቅሚያ አድነኝ ፡ትእዛዝህንም እጠብቃለሁ። 135 ባገልጋይህ ላይ ፊትህን አብራ፡ ፍርድህንም አስተምረኝ። 136 ሕግህን አልጠበቅሁምና፡ የውኃ ፈሳሽ ከዓይኖቼ ወረደ ።

*ጻዴ ብሂል ጻድቅ እግዝይአብሔር=*137 አቤቱ አንተ ጻድቅ ነህ፡ ፍርድህም ቅን ነው። 138 ምስክርህን በጽድቅ አዘዝህ፡ እጅግም ቅን ነው። 139 ጠላቶቼ ትእዛዝህን ረስተዋልና የቤትህ ቅንዓት አቀለጠኝ። 140 ቃልህ እጅግ የጋለ ነው። አገልጋይህ ህ ግን ወደደው። 141 እኔ ታናሽና የተናቅሁ ነኝ፡ ሕግህን ግን አልረሳሁም። 142 ጽድቅህም የዘለዓለም ጽድቅ ነው፡ ቃልህም የታመነ ነው። 143 መከራና ችግር አገኙኝ፡ ትእዛዝህ ግን ትምህርቴ ነው። 144 ምስክርህ ለዘለዓለም እውነት ነው፡ እንዳስተውል አድርገኝ፡ በሕይወትም አኑረኝ።

*ቆፍ ብሂል ቅሩብ እግዚአብሔር (ኤር 23፣ 23)=*145 በፍጹም ልቤ ጮኽሁ፡ አቤቱ ስማኝ፡ ፍርድህንም ፈለግሁ። 146 ወደ አንተ ጮኽሁ ስማኝ አድንኝም፡ ምስክርህንም ልጠብቅ። 146 ወደ ተራሮች ደረስሁ፡ ጮኽሁም። ቃልህን ተስፋ አድርጌአለሁና ። 148 ዓይኖቼ ለመገሥገሥ ደረሱ ፡ ቃልህን እናገር ዘንድ፡ 149 አቤቱ እንደ ይቅርታህ ቃሌን ስማ፡ እንደ ፍርድህ ሕያው አድርገኝ። 150 በዐመፃ የከበቡኝ ቀረቡ፡ ከሕግህ ግን ራቁ። 151 አቤቱ አንተ ቅርብ ነህ፡ መንገዶችህም ሁሉ የቀኑ ናቸው። 152--ምስክሮችህን-ከቀድሞ-ጀምሮ-ለዘለዓለም-እንደ መሠረትሃ ቸው ዐወቅሁ።

*ሬስ ብሂል ርእስ እግዚአብሔር=የሁሉ ራስ እንደማለት ነው።*

153 ሕግህን አልረሳሁምና ችግሬን ተመልከት፡ አድነኝም።
154 ፍርዴን ፍረድ፡ አድነኝም ስለ ቃልህም ሕያው አድርገኝ።
155 ሕይወት ከኃጥአን የራቀ ነው፡ ፍርድህን አልፈለጉምና ።
156 አቤቱ ይቅርታህ እጅግ የበዛ ነው፡ እንደ ፍርድህም ሕያው አድርገኝ። 157 የከበቡኝና ያስጨነቁኝ ብዙዎች ናቸው፡

www.ethiopianorthodox.org

ከምስክርህ ግን ፈቀቅ አላልሁም። 158 ቃልህን አልጠበቁምና፡ ሰነፎችን-አይቼ-አዘንሁ። 159- ትእዛዝህን-እንደ-ወደድሁ ተመልከት፡-አቤቱ-በይቅርታህ-ሕያው-አድርገኝ። 160-የቃልህም መጀመሪያ-እውነት-ነው፡-ፍርድህ- ሁሉ ለዘለዓለም እውነት ነው።

*ሳን ብሂል ሰዑሕ **እ**ግዚአብሔር*=161 አለቆች በከንቱ አሳደዱኝ ፡ ከቃልህ የተነሣ ግን ልቤ ደንገጠብኝ። 162 ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ። 163 ዓመፃን ጠላሁ፡ ተጸየፍሁም፡ ሕግህን ግን ወደድሁ። 164 ስለእውነት ፍርድህ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ። 165 ስምህን ለሚወድዱ ብዙ ሰላም ነው፡ ዕንቅፋት የለባቸውም። 166 አቤቱ ማዳንህን ተስፋ አደረግሁ፡ ትእዛዝህንም ጠበቅሁ። 167 ነፍሴ ምስክርህን ጠበቀች፡ እጅግም ወደደችው። 168 አቤቱ መንገዶችህ ሁሉ በፊትህ ናቸው፡ ትእዛዛህንና ምስክርህን ጠበቅሁ ።

*ታው ብሂል ትጉህ **እ**ግዚአብሔር*=169 አቤቱ ልመናዬ ወደ አንተ ትቅረብ፡ እንደ ቃልህም አስተዋይ አድርገኝ። 170 አቤቱ ምልጃዬ-ወደ-ፊትህ-ትድረስ፡-እንደ-ቃልህም-አድነኝ።171 ፍርድህን አስተምረሽኛልና፡ከንፈሮች-ምስጋናህን-ይናገራሉ።172 ትእዛዝትህ-ሁሉ-ጽድቅ-ናቸውና፡-አንደበቴ-ቃልህን-ተናገረ።173 ትእዛዝህን ወድጃለሁና፡ ቀኝህ የሚያድነኝ ይሁን። 174 አቤቱ ማዳንህን ናፈቅሁ፡ ሕግህም ትምህርቴ ነው። 175 ነፍሴ በሕይወት-ትኑርልኝ፡-ላመስግንህ፡-ፍርድህም-ይርዳኝ። 176 እንደ ጠፋ-በግ-ተዘነጋሁ፡-ትእዛዛትህን- አልረሳሁምና፡- አገልጋይህን- ፈልገው።

**መዝ ፻፲፱ /119፡ ከክፉ ሰዎች የምንጠበቅበት ጸሎት**

1 ኀቤከ እግዚኦ ጸራሕኩ ሶበ ተመንደብኩ=አቤቱ በተጨነቅሁ ጊዜ ወደ አንተ ጮኽሁ፡ ሰማኸኝም ። 2 ከዓመፀኛ ከንፈር፡ ከሸንጋይም አንደበት አቤቱ ነፍሴን አድናት። 3 ስለ ሽንገላ አንደበት ምንን ይሰጡሃል? ምንስ ይጨምሩልሃል? 4 እንደ በረሃ ቋያ የኃያል ፍላጻች የተሳሉ ናቸው። 5 መኖሪያዬ የራቀ



እኔ ወዮልኝ፡ በዘላን ድንኳኖች አደርሁ። 6 ሰላምን ከሚጠሉ ጋር ነፍሴ ብዙ ጊዜ ታገሠች። 7 እኔ ሰላማዊ ስሆን፡ በተናገርኋቸው ጊዜ በከንቱ ይጠሉኛል።

**መዝ ፻፳ /120፡ የእግዚአብሔር ጠባቂነት**

1 አንሣእኩ አዕይንትየ መንገለ አድባር=አይኖቼን ወደ ተራራ አነሣሁ ረድኤቴ ከወዴት ይምጣ 2 ረድኤቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። 3 ለእግሮቼም ሁከትን አይሰጣቸውም፡-የሚጠብቅህም አይተኛም ። 4 እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ-አይተኛም፡-አያንቀላፋምም። 5- እግዚአብሔር ይጠብቅህ፡ እግዚአብሔርም በቀኝ እጅ ይጋርድህ። 6 ፀሐይ በቀን አያቃጥልህ ጨረቃም በሌሊት-በርሃኗን አትከልክልህ። 7-እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅህ፡ እግዚአብሐር ነፍስህንም ይጠብቃት። 8 ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቅ።

**መዝ ፻፳፩ /121፡ ከክፉ ሰዎች የምንጠበቅበት ጸሎት**

1 ተፈሣሕኩ እስመ ይቤሉኒ ቤተ እግዚአብሔር ነሐውር= ወደ እግዚአብሐር-ቤት እንሂድ ስላሉኝ ደስ አለኝ። 2-ኢየሩሳሌም ሆይ! እግሮቻችን በአደባባዮችሽ ቆሙ። 3 ኢየሩሳሌምስ እንደ ከተማ የታነጸች ናት። 4 እንደ እርሷ ያሉት በአንድነት ከእርሷ ጋር ናቸው። አቤቱ ለስምህ ይገዙ ዘንድ ለእስራኤል ምስክር የሚሆኑ የእግዚአብሐር ወገኖች አሕዛብ ወደዚያ ይወጣሉና። 5 ለመፍረድ ዙፋኖቻቸውን በዚያ አስቀምጠዋልና የዳዊት ቤት ዙፋኖችም-ባዚያው አሉ።6 ስለኢየሩሳሌም ድኅነትዋን ተነጋገሩ። ስምህን ለሚወድዱ ደስታቸው ነው ። 7 በኃይልህም ሰላም ይሁን፡ በክብርህ ቦታ ደስታ አለ። 8 ስለ ወንድሞቼና ስለ ባልንጀሮቼ ስለአንቺም ሰላምን ይናገራሉ። 9 ስለ አምላኬ ስለ እግዚአብሐር ቤት ደኅንነትሽን ፈለግሁ።

**መዝ ፻፳፪ /122፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማግኘት**

1 ኀቤከ አንቃዕደዉ አዕይንቲነ ዘትነብር ውስተ ሰማይ= በሰማይ የምትኖር ሆይ! ዓይኖቻችንን ወደ አንተ አነሣን።


www.ethiopianorthodox.org

2 እነሆ ያገልጋዮችች ዓይኖች ወደ ጌቶቻቸው እጅ እንደ ሆኑ፡ የሴት አገልጋይም ዓይን ወደ እመቤቷ እጅ እንደሆነ፡ እንዲሁም ይቅር እስከሚለን ድረስ ዓይኖቻችን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ናቸው። 3 ማረን። አቤቱ ማረን፡ ስድብን እጅግ ጠግበናልና፡-የባለጠጎችን- ስድብና- ከትዕቢተኞች የመጣብንን - ውርደት ነፍሳችንን እጅግ ጠገበች።

## መዝ ፻፳3 /123፡ እግዚአብሔር የሕዝቡ አዳኝ

1 ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ=እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን እስራኤል እንዲህ ይበል 2 እግዚአብሐር ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ 3 የመዓት ቁጣቸውን በላያችን ባነሡ ጊዜ፡ "ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር" ብዬ በተጠራጠርሁ ነበር 4 በውኃም ባሰጠሙን ነበር 5- ነፍሳ ችንም ከጐርፍ አመለጠች፡ ነፍሳችን ከክርክር ውኃ አመለጠች። 6 ወደ ከባቢ ወጥመዳቸው ያላገባን እግዚአብሐር ይመስገን። 7 ሰውነታችን ግን እንደ ወፍ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች፡ ወጥመድ ተሰበረች፡ እኛ ግን ዳን። 8- ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሐር ስም ነው።

## መዝ ፻፳ /124፡ የሚታመኑበትን የሚጠብቅ አምላክ

1 እለ ተወከሉ በእግዚአብሔር ከመ ደብረ ጽዮን= በእግዚአብ ሐር የታመኑ እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው፡ በኢየሩሳሌም የሚኖር የዘለዓለም አይታወክም። 2 ተራሮች ይከቧታል፡ ከዛሬ ጀምሮ ለዘለዓለም እግዚአብሐር ሕዝቡን ይመግባል። 3 ጻድቃን እጃቸውን በዓመፃ እንዳይዘረጉ እግዚአብሐር የኃጥአንን በትር በጻድቃን ዕጣ ላይ አይተውምና። 4 አቤቱ ለቸሮች ልባቸውም ለቀና መልካምን አድርግ። 5 ወደ ጠማማነት የሚመለሱትን ግን ዓመፃን ከሚሠሩት ጋር እግዚአብሐር ይወስዳቸዋል። ሰላም በእስራኤል ላይ ይሁን።

## መዝ ፻፳፭ /125፡ ከስደት መልስ የቀረበ ጸሎት

1 አመ ሜጠ እግዚአ3ብሔር ፄዋ ጽዮን=እግዚአብሐር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ፡ እጅግ ደስተኞች ሆንን። 2 በዚያን ጊዜ



አፋችን ደስታን ተሞላ፡ አንደበታችንም ሐሤትን አደገ፡ በዚያን ጊዜ አሕዛብ "እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገላቸው" አሉ። 3 ደስተኞችም ሆን። 4 አቤቱ በደቡብ እንዳሉ ፈሳሾች ምርኮአችንን መልስ። 5 በልቅሶ የሚዘሩ፡ በደስታ ይሰበስባሉ። 6--በሄዱ-ጊዜ-ዘራቸውን-ተሸክመው-እያለቀሱ-ተሠማሩ፡ ሲመለሱ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ።

## መዝ ፻፳፮ /126፡ በእግዚአብሔር የመታመን ጸሎት

1-እመ-እግዚአብሔር-ኢሐነፀ-ሀገረ=እግዚአብሐር ቤትን ካልሠራ፡ ቤትን የሚሠሩ በከንቱ ይደክማሉ፡ እግዚአብሐር ከተማን ካልጠበቀ፡ የሚጠብቁ በከንቱ ይተጋሉ ። 2 በማለዳ መገሥገሣ ችሁም ከንቱ ነው። ለወዳጆቹ እንቅልፍን በሰጠ ጊዜ እናንተ የመከራን እንጀራ የምትበሉ ከተቀመጣችሁበት ተነሡ። 3 እነሆ ልጆች የእግዚአብሐር ስጦታ ናቸው፡ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው። 4 በኃያል እጅ እንዳሉ ፍላጾች ተጥለው በነበሩ ሰዎች ልጆች እንዲሁ ናቸው። 5 ከእነርሱ ዘንድ ተጥለው በነበሩ ምኞቱን የሚፈጽም ሰው ብፁዕ ነው፣ ጠላቶቹን በአደባባይ በተናገራቸው ጊዜ እርሱ አያፍርም።

## መዝ ፻፳፯/127፡ ለእግዚአብሔር መታዘዝ

1ብፁዓን ኵሎሙ እለ ይፈርህዎ ለእግዚአብሔር=እግዚአብ ሔርን-የሚፈሩትና በመንገዶቹም የሚሄዱ ሁሉ ብፁዓን ናቸው፡ ፡ 2 የድካምህን ፍሬ ትመገባለህ፡ ብፁዕ ነህና፡ መልካምም ይሆንልሃል። 3 ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ትሆናለች፡ ልጆችህም በማዕድህ ዙሪያ እንደ አዲስ የወይራ ተክል ይሆናሉ። 4 እነሆ እግዚአብሐርን የሚፈራ ሰው እንደዚህ ይባረካል። 5 እግዚአብሐር ከጽዮን ይባርክህ፡ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የኢየሩሳሌምን መልካምነት ታያለህ። 6 የልጆችህንም ልጆች ታያለህ፡ በእስራኤል ላይ ሰላም ይሁን።

## መዝ ፻፳፰/128፡ በጽዮን ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት

1 ዘልፈ ይጽዘኡኒ ይብል እስራኤል= እስራኤል እንዲህ ይበል፡ ከትንሽነቴ ጀምሮ ሁልጊዜ ተሰለፉብኝ፡ 2 ከትንሽነቴ ጀምሮ



www.ethiopianorthodox.org

ሁልጊዜ ተዋጉኝ፡ ነገር ግን ሊያሸንፉኝ አልቻሉም። 3 ኃጥአን
በጀርባዬ ላይ መቱኝ፡ ኃጢያአቸውንም አበዙአት። 4 እግዚአብ
ሐር ጻድቅ ነው፡ የኃጥአንን አንገታቸውን ቁረጠ። 5 ጽዮንን
የሚጠሉ ሁሉ አፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ። 6 በሰገነት ላይ
እንደ በቀለ ሣር ሳይነቀል እንደሚደርቅ ፡7-ለሚያጭደው
እጁን፡ ነዶዎቹን ለሚሰበስብም እቅፉን እንደማይሞላ ሣር
ይሁኑ። 8 በመንገድም የሚያልፉ በመዘባበት የእግዚአብሐር
በረከት-በእናንተ-ላይ-ይሁን፡-በእግዚአብሐር-ስም እንመርቃችኋ
ለን፡ በማለት አይዘብቱብን ።

## መዝ ፻፳/129፡ የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት የቀረብ ጸሎት

1 እማዕምቅ ጸዋዕኩከ እግዚኦ፡ ስምዐኒ ቃልየ=አቤቱ አንተን
ከጥልቅ ጠራሁህ፡ 2 አቤቱ ቃሌን ስማኝ፡ ጆሮህም የልመናዬን
ቃል የሚያደምጥ ይሁን። 3 አቤቱ ኀጢያትንስ-ብትጠባበቅ
በፊትህ ማን-መቆም ይችላል? 4 ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና።
5 አቤቱ ስለ ስምህ ተስፋ አደረግሁህ፡ ነፍሴ በሕግህ ታገሠች።
6 ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፍሴ በእግዚአብሐር
ታመነች ፡ ከማለዳ ጀምሮ እስራኤል በእግዚአብሐር ታመነ።
7 ከእግዚአብሐር ዘንድ ይቅርታ፡ በእርሱም ዘንድ ብዙ ማዳን
አለና 8 እርሱም እስራኤልን ከኃጢያቱ ሁሉ ያድነዋል።

## መዝ ፻፴ /130፡ በእግዚአብሔር የመታመን ጸሎት

1 እግዚኦ ኢይትዔበየኒ ልብየ= አቤቱ ልቤ አይታበይብኝ
ዓይኖቼም ከፍ ፡ ከፍ አይበሉብኝ፡ ከትልልቆች ጋር። ከእኔም
ይልቅ ከሚከብሩ ጋር አልሄድሁም፡ 2 ራሴን አዋረድሁ እንጂ።
ለነፍሴ ዋጋዋን ትሰጣት ዘንድ የእናቱን ጡት እንዳስጣሉት
ልጅ በቃሌ ጮኽሁ። 3 ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እስራኤል
በእግዚአብሔር ይታመናል።



## መዝ-፻፴፩/131፡--የእግዚአሔርን ቤት የመሥራት ብፅዓት

1 ተዘከሮ እግዚኦ ለዳዊት ወለኵሉ የዋሃቱ=አቤቱ ዳዊትን፡
ገርነቱነም ሁሉ አስብ። 2 ለእግዚአብሐር እንደማለና ለያዕቆብም
አምላክ እንደተሳለ፡ "ወደ ቤቴ እንኳን አልገባም፡ ወደ
መኝታዬም አልጋ አልወጣም፡ 4 ለዐይኖቼም መኝታ፡
ለቅንድቦቼም እንቅልፍን፡ ለጉንጮቼም ዕረፍትን አልሰጥም።
5 የእግዚአብሐርን ቦታ የያዕቆብ አምላክን ማደሪያ እስካገኝ-
ድረስ" ብሎ እንደ ተሳለ አስብ። 6 እነሆ በኤፍራታ ሰማነዉ፡
ዛፍ በበዛበትም ቦታ አገኘነው። 7 እንግዲህስ ወደ እግዚአብሐር
ማደሪያዎች እንገባለን። የጌታችን እግሮቹ በሚቆሙበት ቦታ
እንሰግዳለን። 8 አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፡ አንተና የመቅደስህ
ታቦት። 9 ካህናትህ ጽድቅን ይለብሳሉ፡ ጻድቃንህም ደስ
ይላቸዋል።10 ቀብተህ ካነገሥኸው ከአገልጋይህ ከዳዊት ፊትህን
አትመልስ፡ 11 እግዚአብሐር ለዳዊት እንዲህ ሲል በእውነት
ማለ: -አይጸጸትምም።- "ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለ
ሁና።12 ልጆችህ ኪዳኔኔና ይህንም የማስተምራቸውን ምስክሬን
ቢጠብቁ ልጆቻቸውም በዙፋንህ ላይ ለዘለዓለም ይነግሣሉ።
እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፡ ማደሪያውም ትሆነው
ዘንድ ወድዶአታልና። 14 ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት፡
መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ። 15 ባልቴቶችዋን እጅግ
እባርካቸዋለሁ፡ ድሆችዋንም እህልን አጠግባቸዋለሁ።
16 ለካህናቷም ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ፡ ጻድቃኖችዋም እጅግ
ደስ ይላቸዋል። 17 በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ *(ሥልጣኑን
ከፍ፡ ከፍ አደርጋለሁ)*፡ ቀብቼ ላነገሥሁትም መብራትን አዘጋጃለሁ፡
18-ጠላቶቹን -እፍረትን -አለብሳቸዋለሁ፡-በእርሱም-ቅድስናዬ-
ያፈራል" ብለሃልና

## ማዝ ፻፴፪ /132፡ የወንድሞች በኅብረት መኖር

1 ናሁ-ሠናይ-ወናሁ-አዳም-ሶበ-ይሄልዉ አኃው ኅቡረ=ወንድሞች
በኅብረት ቢኖሩ እነሆ መልካም ነው፡ እነሆም ያማረ ነው።
2 ከራሱ ጀምሮ እስከ ጢሙ በልብሱ መደረቢያ ላይ
እስከሚወርደው እስከ አሮን ጢም ድረስ እንደሚፈስ ሽቱ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

3 በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንኤምም ጠል
ነው። በዚያ እግዚአብሔር በረከቱንና ሕይወትንም ከዛሬ ጀመሮ
ለዘለዓለም አዝዞአልና።

### መዝ ፻፫ /133፡ <u>የሌሊት ጸሎት አገልግሎት</u>

1 ናሁ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር ኵሎሙ አግብርተ እግዚአብ
ሔር= በእግዚአብሔር ቤት በአምላካችን ቤት በአደባባዮች
የምትቆሙ እናንተ የእግዚአብሐር አገልጋዮች ሁላችሁ እነሆ
እግዚአብሔርን-አመስግኑ።-2-በሌሊት-በቤተ መቅደስ እጆቻችሁን
አንሡ፡ እግዚአብሔርንም አመስግኑት። 3 ሰማይንና ምድርን
የሠራ እግዚአብሐር ከጽዮን ይባርክህ።

### መዝ ፻፴፬ /134፡ <u>የእግዚአብሔር አገልጋዮች ምስጋና</u>

1 ሰብሑ ለስመ እግዚአብሔር= እናንተ የእግዚአብሔር
አገልጋዮች ሆይ! የእግዚአብሐርን ስም አመስግኑ። እናንተ
አገልጋዮቹ ሆይ! እግዚአብሔርን አመስግኑት። 2 በእግዚአብ
ሐር ቤት ውስጥ በአምላካችን ቤት አደባባይ የምትቆሙ።
3 እግዚአብሔር ቸር ነውና፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ፡ ለስሙ
ዘምሩ፡-መልካም ነውና። 4 እግዚአብሐር ያዕቆብን ለራሱ
እስራኤልንም ርስቱ እንዲሆን መርጦታልና ። 5 እግዚአብሐር
ታላቅ እንደ ሆነ፡ አምላካችንም ከአማልክት-ሁሉ እንደሚበልጥ
አውቃለሁና፡ 6 በሰማይና በምድር፡ በባሕርና በጥልቆችም ሁሉ
እግዚአብሔር የወደደውን አደረገ። 7 ከምድር ዳርቻ ደመናትን
ያወጣል። ለዝናም ጊዜም መብረቅን አደረገ፡ ነፋሳትንም
ከመዛግብቱ ያወጣል። 8 የግብጽን በኲር ልጆች ሁሉ ከሰው
ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ገደለ። 9 ግብጽ ሆይ! በመካከልሽ
በፈርዖንና በባሪያዎቹ ሁሉ ላይ ተአምራትንና ድንቅን ሰደደ።
10 ብዙ አሕዛብን መታ፡ ብርቱዎችንም ነገሥታት ገደለ።
11 የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፡ የባሳንንም ንጉሥ ዐግን፡
የከነዓንንም ነገሥታት ሁሉ ገደለ። 12 ምድራቸውንም ሁሉ
ለሕዝቡ ለእስራኤል ርስት አድርጎ ሰጠ።13 አቤቱ ስምህ
ለዘለዓለም ነው፡ መታሰቢያህም ለልጅ ልጅ ነው። 14 እግዚአብ



ሔር ለሕዝቡ ይፈርዳልና አገልጋዮቹን ያጽናናል። 15 የአሕዛብ
ጣዖታት ከብርና ከወርቅ-በሰው-እጅ የተሠሩ-ናቸው።16 አፍ
አላቸው፡ አይናገሩም፡ ዓይን አላቸው፡አያዩም፡ 17 ጆሮ አላቸው
አይሰሙም፡-አፍንጫ-አላቸው-አያሸቱም ፡-እጅ-አላቸው አይዳስ
ሱም፡-እግር-አላቸው፡-ግን አይሄዱም፡ በጉሮሮአቸው አይናገሩም፤
እስትንፋስ--በአፋቸው-የለምና ፤18-የሚሠሩአቸውና የሚታመኑ
ባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ።19 የእስራኤል ወገኖች
ሆይ1 እግዚአብሐርን አመስግኑት፡ የአሮን ወገኖች ሆይ!
እግዚአብሔርን አመስግኑት 20-የሌዊ-ወገኖች-ሆይ!-እግዚአብሐ
ርን-አመስግኑት-እግዚአብሐርን-የምትፈሩት ሆይ! እግዚአብሐርን
አመስግኑት 21 በኢየሩሳሌም የሚያድር እግዚአብሔር በጽዮን
የተመሰገነ ነው።

### መዝ-፻፴፭/135፡ <u>በመቀባበል-የሚቀርብ የምስጋና-ጸሎት</u>

1 ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር እስመ ለዓለም ምሕረቱ=
እግዚአብሐርን አመስግኑ፡ ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘለዓለም
ነውና።2 የአማልክትን አምላክ አመስግኑ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም
ነውና። 3 የጌቶችን ጌታ አመስግኑ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና።
4 እርሱ ብቻውን ታላቅ ተአምራትን ያደረገ፡ ምሕረቱ
ለዘለዓለም ነውና። 5 ሰማያትን በጥበብ የሠራ ምሕረቱ
ለዘለዓለም ነውና። 6 ምድርን በውሃ ላይ ያፀና፡ ምሕረቱ
ለዘለዓለም ነውና። 7 ብቻውን ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ፡
ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና። 8 ለፀሐይ ቀንን ያስገዛው፡ ምሕረቱ
ለዘለዓለም ነውና። 9 ለጨረቃና ለከዋክብት ሌሊትን ያስገዛቸው፡
ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና። 10 ከበኵራቸው ጋር ግብጽን
የገደለ፡-ምሕረቱ-ለዘለዓለም ነውና። 11 እስራኤልን ከመካከላቸው
ያወጣ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና። 12 በፀናች እጅ፡ በተዘረጋች
ክንድ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና። 13 የኤርትራን ባሕር
ፈጽሞ የከፈለ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና። 14 እስራኤልን
በመካከሉ ያሳለፈ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና። 15 ፈርዖንና
ሠራዊቱን በኤርትራ ባሕር ውስጥ የጣለ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም

www.ethiopianorthodox.org

ነውና ፡፡ 16 ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም
ነውና ፡፡ ከዓለት ውኃን ያፈለቀ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፡፡
17 ታላላቅ ነገሥታትን የገደለ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡
18 ፅኑዓን ነገሥታትን የገደለ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡
9 የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡
20 የባሳንን ንጉሥ ዐግን ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡
21-ምድራቸውን ርስት አድርጎ ለሕዝቡ የሰጠ፡ ምሕረቱ ለዘለዓ
ለም ነውና፡፡ ለአገልጋዩው ለእስራኤል ርስት አድርጎ የሰጠ
ምሕረቱ-ለዘለዓለም-ነውና፡፡-22 እግዚአብሔር እኛን በመዋረዳችን
ዐስቦናል፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡ ከጠላቶቻችንም እጅ
አድኖናልና ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡ 24 ለሥጋዊ
ፍጥረት ሁሉ ምግብን የሚሰጥ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡
25 የሰማይን አምላክ አመስግኑ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና፡፡

**መዝ ፻፴፮ /136፡ <u>የምርኮኞች ቅኒያዊ የምስጋና ጸሎት</u>**

1 ውስተ አፍላገ ባቢሎን ሀየ ነበርነ ወበከይነ=በባቢሎን ወንዞች
አጠገብ ተቀመጥን በዚያ ጽዮንን ባሰብናት ጊዜ አለቀስን፡፡
2 በአኻያ ዛሮች ላይ በገናዎቻችንን ሰቀልን፡፡ 3 የማረኩን በዚያ
የዝማሬ ቃል ጠይቀውናልና፡ የወሰዱንም "የጽዮንን ዝማሬ
ዘምሩልን" አሉን፡፡ 4 የእግዚአብሔርን ዝማሬ በባዕድ አገር
እንዴት እንዘምራለን? 5 ኢየሩሴም ሆይ! ብረሳሽ ቀኙ ትርሳኝ፡
6 ባላስብሽም ምላሴ በጉሮሮዬ ይጣበቅ፡ ከደስታዬ ሁሉ በላይ
ኢየሩሳሌምን ባልወድድ፡፡ 7 አቤቱ በኢየሩሳሌም ቀን እስከ
መሠረቷ ድረስ አፍርሱ ፡ አፍርሱ ያሉአትን የኤዶምን ልጆች
አስብ፡፡ 8 አንቺ የተዋረድሽ የባቢሎን ልጅ ሆይ! ስለ ተበቀልሽን
የሚበቀልሽ ብፁዕ ነው፡፡ 9 ሕፃናቶችሽን አንሥቶ በዓለት ላይ
የሚፈጠፍጣቸው ብፁዕ ነው፡፡

**መዝ ፻፫፯ /137፡ <u>በምስጋና መዝሙር የተቃኘ ጸሎት-----</u>**

1 እገኒ ለከ እግዚኦ በኵሉ ልብየ=አቤቱ በፍጹም ልቤ አመሰግን
ሃለሁ፡ የአፌን ነገር ሁሉ ሰምተኸኛልና፡ በመላእክት ፊት
እዘምርልሃለሁ፡፡ 2 በቤተ መቅደስህም እሰግዳለሁ፡፡ ስለ
ምሕረትህና ስለ እውነትህም ስምህን አመሰግናለሁ፡፡ በሁሉ ላይ



ቅዱስ ስምህን ከፍ ፡ ከፍ አድርገሃልና፡፡ 3 በጠራሁህ ቀን
በፍጥነት አድምጠኝ፡ ነፍሴን በኃይልህ በብዙ አጸናሃት፡ 4-አቤቱ
የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመሰግኑሃል፡ የአፍህን ቃል ሁሉ
ሰምተዋልና፡፡ 5 በእግዚአብሔርም ምስጋና ይዘምራሉ፡፡
የእግዚአብሔር ክብር ታላቅ ነውና፡፡ 6 እግዚአብሔር ከፍ ያለ
ነውና፡ የተዋረዱትንም ይመለከታልና፡፡ ትቢተኛውንም ከሩቁ
ያውቀዋል፡ 7 በመከራ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ታድነኛለህ፡
በጠላቶች-ቁጣ-ላይ- እጆችህን ትዘረጋለህ፡ ቀኝህም ያድነኛል ፡፡
8 እግዚአብሔርም ይበቀልልኛል፡ አቤቱ ምሕረትህ ለዘለዓለም
ነው፡ አቤቱ የእጅህን *ሥራ (ፍጥረትህን)* ቸል አትበል፡፡

**መዝ ፻፴፰ /138፡ ` <u>እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለመሆኑ</u>**

1 እግዚኦ አመከርከኒ ወአእመርከኒ=አቤቱ ፈተንኸኝ፡ ዐወቅኸ
ኝም፡፡ 2 አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ፡ የልቤን
አሳብ ሁሉ ከሩቁ ታስተውላለህ ፡፡3 ፍለጋዬንና መንገዴን አንተ
ትመረምራለህ፡መንገዶቼን-ሁሉ-አስቀድመህ ዐወቅህ፡፡ 4- የዓመፃ
መፃ ቃል በአንደበቴ እንደሌለ፡ 5 አቤቱ አንተ እነሆ
የቀድሞውንና የኋላውን ሁሉ ዐወቅህ፡፡ አንተ ፈጠርኸኝ፡
እጅህንም በላዬ አደረግህ፡ 6 ዕውቀትህ በእኔ ላይ ተደነቀ፡፡
በረታችብኝ፡ ወደ እርሷም ለመድረስ አልችልም፡፡ 7 ከመንፈስህ
ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ሸሽቼ ወዴት እሰወራለሁ? 8 ወደ
ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፡ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ
በዚያ-አለህ፡-9-እንደ-ንሥርም-ክንፍ-ብወስድ-እስከ-ባሕር መጨሻ
ብበርር ፡10 በዚያ እጅህ ትመራኛለች፡ ቀኝህም ታኖረኛለች፡፡
11 በእውነት "ጨለማ ይሸፍነኛል" ብል ሌሊቱ በደስታዬ
ብርሃን ይሆናል፡፡ 12 ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፡፡
ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና፡ እንደ ጨለማዋ እንዲሁ
ብርሃንዋ ነው፡፡ 13 አቤቱ አንተ ኩላሊቴን ፈጥረሃለና፡ ከእናቴ
ማሕፀን ጀምሮ ተቀበልኸኝ፡፡ 14 በመፈራት የተደነቅህ ነህና፡
አቤቱ አመሰግንሃለሁ፡፡ *ሥራህ ድንቅ* ነው፡ ነፍሴም እጅግ
ታስተውለዋለች፡፡፡15-በስውር-የሠራኸው-አጥንቴ-ከአንተ አልተሰ
ወረም፡16 አካሌንም ዓይኖችህ አዩ፡ ሁሉም በመጽሐፍህ የተጻፉ
ነው፡፡ በቀን ይፈጠራሉ ነገር ግን ከእንርሱ አንድ ስንኳ



www.ethiopianorthodox.org

አይኖርም ፡፡17 አቤቱ ወዳጆችህ በእኔ ዘንድ እጅግ የከበሩ ናቸው፡፡ ከቀደምቶቻቸውም እጅግ በረቱ፡፡18 እቈጥራቸዋለሁ፡ ከአሸዋም ይልቅ ይበዛሉ፡፡ ተነሣሁ፡ ገናም ከአንተ ጋር ነኝ፡፡ 19 አቤቱ አንተ ኃጥአንን የምትገድል ከሆንህስ የደም ሰዎች ሆይ! ከእኔ ፈቀቅ በሉ፡ 20 በአሳባቸው ይኰራሉና፡ ከተሞችህንም በከንቱ ይወስዷቸዋል፡፡ 21 አቤቱ የሚጠሉህን እኔ የጠላሁ አይደለሁምን? ስለ ጠላቶችህም አልጠፋሁምን? 22 ፍጹም ጥልን ጠላኋቸው፡ ጠላቶችም ሆኑኝ፡፡ 23 አቤቱ መርምረኝ፡ ልቤን ፈትን፡ ፈትነኝ፡ መንገዶቼም፡ ዕወቅ፡ 24 -በደልም በእኔ ላይ ቢገኝ እይ፡ የዘለዓለምነም መንገድ ምራኝ፡፡

መዝ ፻፴፱ /139፡ **ከክፉዎች ለመዳን የቀረበ ጸሎት**

1 አድኅነኒ እግዚኦ እምብእሲ እኩይ =አቤቱ ከክፉ ሰው አድነኝ፡ ከዓመፀኛ ሰውም ታደገኝ፡፡ 2 ሁልጊዜ በልባቸው ዓመፃን የሚመክሩ ይገድሉኝ ዘንድ ይከብቡኛል፡ 3 ምላሳቸውን እንደ እባብ ሳሉ፡ ከከንፈራቸው በታች የእባባ መርዝ አለ፡፡

4 አቤቱ ከኃጥአን እጅ ጠብቀኝ፡ እርምጃዬንም ሊያሰናክሉ ከመከሩ ከዓመፀኞች ሰዎች አድነኝ፡፡ 5 ትዕቢተኞች የወጥመድ ገመድን ዘረጉ፡ በመንገዴም ዕንቅፋትን አኖሩ፡፡ 6 እግዚአብሔርንም "አንተ አምላኬ ነህ፡ የልመናዬንም ቃል አቤቱ አድምጥ" አልሁት 7 አቤቱ ጌታዬ የደኅንነቴ ኃይል፡ በጦርነት ቀን ራሴን ሰወርኸኝ፡፡ 8 አቤቱ ጌታዬ ከምኞቴ የተነሣ ለኃጢአተኞች አትስጠኝ፡ በላዬ ተማከሩ፡ እንዳይታበዩም አትተወኝ፡፡ 9 የአሽክላቸው ራስና የከንፈራቸውም ክፋት ይድፈናቸው፡፡ 10 የእሳት ፍም ላይ በላያቸው ይውደቅ፡ መቆም እንዳይችሉ በችግር ወደ ምድር ይውደቁ 11 ተናጋሪ ሰው በምድር ውስጥ አይጸናምና ዐመፀኛ ሰውን ክፋት ለጥፋት-ታድነዋለች፡፡ 12 እግዚአብሐር ለድሆች ዳኝነትን፡ ለችግረኞችም ፍርድን እንደሚያድርግ ዐወቅሁ ፡፡ 13 ጻድቃንም ሁሉ በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ፡ ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ፡፡



መዝ ፻፵ /140፡ **ከክፉ አድራጊዎች ለመዳን** ----------

1 እግዚኦ ጸራሕኩ ኀቤከ ስምዐኒ=አቤቱ ወደ አንተ ጮኽሁ፡ ስማኝ፡ ወደ አንተ ስጮኽም የልመናዬን ቃል አድምጥ፡፡

2 ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን መዓዛ ተቀበልልኝ፡ እጆቼ የሠርክ መሥዋዕትን-አነሡ፡፡ 3 አቤቱ ለአፌ ጠባቂ፡ ለከንፈሮቼም ጽኑዕ መዝጊያን አኑር፡፡ 4 ልቤን ወደ ክፉ ነገር አትመልሰው፡ ዓመፃን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር ለኃጢአት ምክንያት እንዳልሰጥ፡ ከምርጦቻቸውም ጋር አልተባበርም፡፡

5 በጽድቅ ገሥጸኝ፡ በምሕረትም ዝለፈኝ፡ የኃጢአተኛ ዘይትን ግን ራሴን አልቀባም፡ ዳግመኛም ጸሎቴ ይቅር እንዳትላቸው ነውና፡፡ 6 ኃያላኖቻቸው በዓለት አጠገብ ተጣሉ፡ ተችሎኛልና ቃሌን ስሙኝ፡፡ 7 እንደ ጓል በምድር ላይ ተሰነጣጠቁ፡ እንዲሁ አጥንቶቻቸው በሲኦል ተበተኑ፡፡ 8 አቤቱ ጌታዬ ዓይኖቼ ወደ አንተ ናቸውና፡ በአንተ ታመንሁ፡ ነፍሴን አውጣት፡፡ 9 ከሰወሩብኝ ወጥመድና ዓመፃንም ከሚያደርጉ ሰዎች እንቅፋት ጠብቀኝ፡፡10 እኔ ብቻዬን እስካልፍ ድረስ ኃጥአን በወጥመዳቸው ይውደቁ፡፡

መዝ ፻፵፩ /141፡ **ጠላት በበዛበት ጊዜ የሚቀርብ ጸሎት**

1 ቃልየ ኀበ እግዚአብሔር ጸራሕኩ=በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፡ በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ለመንሁ፡፡ 2 ልመናዬን በፊቱ አፈስሳለሁ፡ መከራዬንም በፊቱ እናገራለሁ፡፡ 3 ሰውነቴ በላዬ ላይ ባለቀች ጊዜ አቤቱ መንገዴን አንተ ታውቃለህ፡ በምሄድባት በዚያች መንገድ ስውር ወጥመድን ዘረጉብኝ ፡፡

4 ወደ ቀኝም ተመልሼ አየሁ፡ የሚያውቀኝም አጣሁ፡ መሸሸጊያም የለኝም፡፡ ስለ ሰውነቴ የሚመራመር የለም፡ 5-አቤቱ ወደ አንተ ጮኽሁ፡ "አንተ ተስፋዬ ነህ፡ በሕያዋን ምድር አንተ ዕድል ፈንታዬ ነህ" አልሁ፡፡ 6 እጅግ ተዋርጃለሁና ወደ ልመናዬ ተመልከት በርትተውብኛልና፡ ከከበቡኝ አድነኝ፡፡7-አቤቱ ስምህን አመሰግን ዘንድ ሰውነቴን ከእስራት አውጣት፡ ዋጋዬን እስክትሰጠኝ ድረስ ጻድቃን እኔን ይጠብቃሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## መዝ ፻፵፪ /142፡ <u>የትሑት ሰው ጸሎት</u>

1 እግዚኦ ስምዐኒ ጸሎትየ=አቤቱ ጸሎቴን ስማ፡ በእውነት
ልመናዬን አድምጥ፡ በጽድቅህም መልስልኝ፡ 2 ሕያው ሁሉ
በፊትህ አይጸድቅምና-ከባሪያህ-ጋር-ወደ-ክርክር-አትግባ። 3-ጠላት
ነፍሴን ከብቦአታልና፡ ሕይወቴንም በምድር ውስጥ አዋርዷታል፡
ቀድሞ፡ እንደ ሞተ ሰው በጨለማ አኖሩኝ። 4 ሰውነቴ በላዬ
አለቀችብኝ።ልቤም በውስጤ ደነገጠብኝ። 5 የቀድሞውን ዘመን
አሰብሁ፡ ሥራህንም ሁሉ አነበብሁ፡ የእጅህንም ሥራ
አነብባለሁ። 6 እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ፡ ነፍሴም እንደ ምድረ
በዳ አንተን ተጠማች። 7 አቤቱ ፈጥነህ ስማኝ፡ ሰውነቴ
አልቃለች፡ ፊትህንም ከእኔ አትመልስ፡ ወደ ጉድጓድም
እንደሚወርዱ አልሁን። 8 አቤቱ አንተን ታምኛለሁና በማለዳ
ምሕረትህን አሰማኝ፡ አቤቱ ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና
የምሄድባትን መንገድ ምራኝ፡ 9 አቤቱ ወደ አንተ ተማጽኛለሁና
ከጠላቶቼ አድነኝ። 10 አቤቱ አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን
ለማድረግ አስተምረኝ። 11 አቤቱ ስለ ስምህ ሕያው አድርገኝ፡
ስለ ጽድቅህም ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት። 12 በፈቃድህ
ጠላቶቼን አጥፋቸው፡ እኔ አገልጋህ ነኝና ነፍሴን የሚያስጨን
ቋትን ሁሉ አጥፋቸው።

## መዝ ፻፵፫/143፡ <u>በጦርነት ጊዜ የእግዚአብሔር ትድግና</u>

1 ይትባረክ እግዚአብሔር ዘመሐሮን ፀብዐ ለእደውየ= ለእጆቼ
ጠብን> በጣቶቼም ላይ ሠልፍን ያስተማራቸው አምላኬ
እግዚአብሔር-ይመስገን። 2 የሚምረኝ መሸሸጊያዬ፡ መጠጊያዬና
አዳኜ መታመኛዬም እርሱ ነው። በርሱ ታመንሁ፡ ሕዝቡንም
ከእኔ በታች የሚያስገዛልኝ እርሱ ነው። 3 አቤቱ ለእርሱ
ትገለጥለት ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ታስበው ዘንድስ የሰው
ልጅ ምንድን ነው? 4 ሰው ከንቱ ነገርን ይመስላል፡ ዘመኑም
እንደ-ጥላ-ያልፋል፡፡5-አቤቱ-ሰማዮችህን ዝቅ ፡ ዝቅ አድርጋቸው፡
ውረድም፡ ተራሮችን ዳስሳቸው ይጢሱም፡ 6 የመብረቆችህንም
ብልጭ በማሳየት ጠላቶቼን በትናቸው፡ ፍላጾችህን በመላክ
አስደንግጣቸው። 7 እጅህን ከአርያም ላክ፡ ከብዙ ውኃም



አድነኝ። ከባዕድ ልጆችም እጅ፡ 8 አፋቸው ከንቱ ነገርን
ከሚናገር ቀኛቸውም፡ የዓመፃ ቀኝ ከሆነ አስጥለኝ። 9 አቤቱ
በአዲስ ምስጋና አመሰግንሃለሁ፡ ዐሥር አውታር ባለው በገናም
እዘምርልሃለሁ። 10 ለነገሥታት መድኀኒትን የሚሰጥ፡
አገልጋዩን-ዳዊትን-ከክፉ-ጦር-ያዳነው-እርሱ-ነው። 11 አፋቸውም
ከንቱ ነገርን ከሚናገር፡ ቀኛቸውም የዓመፃ ቀኝ ከሆነ ከባዕዳን
ልጆች እጅ አድነኝ፡ አስጥለኝም። 12 ልጆቻቸው በጕልማስነታ
ቸው እንደ አዲስ ተክል የሆኑ፡ ሴቶች ልጆቻቸውም እንደ
እልፍኝ ያማሩና ያጌጡ፡ 13 ግምጃ ቤቶቻቸውም ዓይነቱ በበዛ
ዕቃ የተሞሉ ናቸው፡ በጎቻቸውም ብዙ-የሚወልዱ። በየመስማ
ርያቸውም የሚበዙ 14 ላሞቻቸውም የሰቡ፡ ቅጥራቸውም
የማይፈርስ፡ መውጫና መግቢያው -የማይታወቅ፡ አደባባያ
ቸውም-የዋይታ-ጩኸት-ድምፅ-የማይሰማበት፡-ነው።15--እንደዚህ
ያለውን ሕዝብ አድንቋት፡እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ሕዝብ
ብፁዕ ነው።

## መዝ ፻፵፬ /144፡ <u>ድል በእግዚአብሔር ኃይል</u>

1 አሌዕለከ ንጉሥየ ወአምላኪየ=አምላኬ፡ ንጉሤ ሆይ ከፍ ፡ከፍ
አደርግሃለሁ፡ ስምህንም ለዘለዓለም ዓለም አመሰግናለሁ። 2
በየቀኑ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፡ ለስምህም ለዘለዓለም ዓለም
ምስጋና አቀርባለሁ። 3 እግዚአብሐር ታላቅ ነው፡ ምስጋናውም
እጅግ ብዙ ነው።ለታላቅነቱም ዳርቻ የለውም ። 4 የልጅ ልጆች
ሥራህን ያደንቃሉ፡ ኃይልህንም ይናገራሉ፡ 5 የቅድስናህንም
ክብር ታላቅነት ይናገራሉ፡ ተአምራትህንም ያስረዳሉ። 6
“ኃይልህ-ግሩም-ነው”-ይላሉ-ግርማህንም-ይናገራሉ፡ ብርታትህንም
ያስረዳሉ፡፡7-የቸርነትህን-ብዛት መታሰቢያ ይናገራሉ፡ በጽድቅህም
ሐሤትን ያደርጋሉ። -8 እግዚአብሔር ይቅር ባይና መሐሪ ነው፡
መዓቱ፡ የራቀ ምሕረቱም የበዛ እውተኛ ነው ። 9 እግዚአብሔር
ለሚታገሡት ሁሉ ቸር ነው፡ ይቅርታውም በሥራው ሁሉ ላይ
ነው። 10 አቤቱ ፍጥረታትህ ሁሉ ያመሰግኑሃል፡ ጻድቃንህም
ያከብሩሃል፡፡፡-11 “ለመንግሥትህ ክብር ይገባል” ይላሉ
ኃይልህንም-ይናገራሉ፡፡-12-ለሰው-ልጆች-ኃይልህንና የመንግሥት



www.ethiopianorthodox.org

ህንም-ክብር-ታላቅነትና-ዘለዓለዊነትን-ያበሥራሉ።13 መንግሥትህ የዘለዓለም ሁሉ መንግሥት ናት፡ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው ።14 እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉ የታመነ ነው። በሥራውም ሁሉ-ጻድቅ-ነው።-እግዚአብሔር-የተፍገመገሙትን-ሁሉ-ይደግፋቸዋል፡-እግዚአብሔር የወደቁትን ያነሣቸዋል። 15- የሰው ሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል። አንተም ምግባቸውን-በየጊዜው-ትሰጣቸዋለህ።16-ቀኝ እጅህን- በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው፡ በሥራውም ሁሉ ቸር ነው።19 ለሚፈሩት ሁሉ ፈቃዳቸውን ያደርጋል፡ ልመናቸውንም ይሰማል፡ ያድናቸዋልም። 20 እግዚአብሔር የሚወድዱትን ሁሉ ይጠብቃል፡ ኃጢአኞችንም ሁሉ ያጠፋል። 21 አፌ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል፡ ሥጋ ለባሽ -ሁሉ-ለዘለዓለም ዓለም የተቀደሰውን ስሙን ያመሰግናል።

መዝ ፻፵፭/145፡ <u>ምስጋና ረድኤቱን ለማያርቅ አምላክ</u>

**ሃሌ-ሉታ!**-፡1-ተአኵቶ--ነፍስየ-ለእግዚአብሔር=ነፍሴ-እግዚአአብሔርን ታመግነዋለች።2 በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን አመግነዋለሁ ። በምኖርበትም ዘመን መጠን ለአምላኬ እዘምራለሁ፡ 3 ማዳን በማይችሉ በአለቆችና በሰው ልጆች አትታመኑ።4 ነፍሳቸው ትወጣለች፡ ወደ መሬትም ይመለሳሉ። ያንጊዜም ምክራቸው ሁሉ ይጠፋል። 5 የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነ መታመኛውም በአምላኩ በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ብፁዕ ነው። 6 እርሱም ሰማይንና ምድርን፡ ባሕርንም፡ በእነርሱ ውስጥ ያለውንም ሁሉ የፈጠረና እውነትን ለዘለዓለም የሚጠብቅ ነው፡ 7 ለተበደሉትም የሚፈርድላቸው፡ ለተራቡ ምግብን የሚሰጥ ነው። እግዚአብሔር የታሰሩትን ይፈታቸዋል፡ 8 እግዚአብሔር የወደቁትን ያነሣቸዋል፡ እግዚአብሔር ዕውሮችን ጥበበኞች ያደርጋቸዋል።-እግዚአብሔር-ጻድቃንን-ይወድዳቸዋል። 9 እግዚአ ብሔር ስደተኞችን ይጠብቃቸዋል፡ ድሃ አደጎችንና ባልቴቶችን ይቀበላቸዋል፡ የኃጥአንንም መንገድ ያጠፋል። 10 እግዚአብሐር ለዘለዓለም ይነግሣልና ጽዮን ሆይ! አምላክሽ ለልጅ ልጅ ነው።



፻፵፮ /146፡ **ምስጋና ሁሉን ቻይ ልትሆነው አምላክ**

**ሃሌ-ሉያ!**-1-ሰብሕዎ-ለእግዚአብሔር-እስመ-ሠናይ መዝሙር =እግዚአብሔርን-አመስግኑ፡-መዝሙር-መልካም-ነውና፡ ለአምላካችንም-ምስጋና-ማቅረብ-ያማረ-ነው።2-እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይሠራታል፡ ከእስራኤልም የተበተኑትን ይሰበስባል። 3 ልባቸው የቈሰለውን ይፈውሳል፡ ቁስላቸውንም ያደርቅላቸዋል።4 ከዋክብትንም በሙሉ ይቈጥራቸዋል፡ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል። 5 እግዚአብሔር ታላቅ ነው፡ ኃይሉም ታላቅ ነው። ለጥበቡም ሥፍር፡ ቁጥር የለውም። 6 እግዚአብሔር የዋሃንን ያነሣቸዋል፡ ኃጥአንን ግን እስከ ምድር ድረስ ያዋርዳቸዋል።
7 ለእግዚአብሔር በምስጋና ዘምሩ፡ ለአምላካችንም በመሰንቆ ዘምሩ። 8 ሰማዩን በደመናት የሚሸፍን፡ ለምድርም ዝናምን የሚያዘጋጅ፡ ሣርን በተራሮች ላይ፡ ልምላሜውንም ለሰው ልጆች አገልግሎት የሚያበቅል። 9 ለእንስሶችና ለሚጠሩት ለቁራዎች ጫጩቶች ምግባቸውን የሚሰጣቸው እርሱ ነው።10 የፈረስን ኃይል አይወድድም፡ በሰውም ጉልበት ደስ አይለውም።11 እግዚ አብሔር በሚፈሩትና በምሕረቱም በሚታመኑ ደስ ይለዋል።

መዝ ፻፵፯ /147 <u>የድል መዝሙርና ጸሎት</u>

**ሃሌ ሉያ!**-1 ትሴብሖ ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር=ኢየሩሣሌም ሆይ1 እግዚአብሔርን አመስግኚ፡ 2 ጽዮንም ሆይ! አምላክሽን አመስግኚ፡ የደጆችሽን መወርወሪያ አፅንቷልና፡ ልጆችሽንም በውስጥሽ ባርኮአልና። 3 ለወሰኖችሽም ሰላምን አደረገ። የስንዴንም ስብ አጠገበሽ፡ 4 ቃሉን ወደ ምድር ይልካል፡ ነገሩም እጅግ ፈጥኖ ይሮጣል። 5 በረዶውን እንደ ባዘቶ ይሰጣል፡ ጉሙን እንደ አመድ ይበትነዋል።6 በረዶውን እንደ ፍርፋሪ ያወርዳል፡ ቅዝቃዜውንስ ማን ይቋቋማል? 7 ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል፡ ነፋሱን ያነፍሳል፡ ውኖችንም ያፈስሳል። 8 ቃሉን ለያዕቆብ፡ ሥርዕቱንና ፍርዱንም ለእስራኤል ይናገራል።
9 ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ-ግን እንዲህ አላደረገም፡ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም።



www.ethiopianorthodox.org

## መዝ ፻፵፰ /148፡ <u>የድል ምስጋና ለእግዚአብሔር</u>

ሃሌ-ሉያ!፡-1 ሰብሕዎ-ለእግዚአብሔር እምሰማያት=እግዚአብ
ሔርን ከሰማያት አመስግኑት፡ በአርያም ያመስግኑታል፡
2 መላእክቱ ሁሉ ያመስግኑታል፡ ሠራዊቱ ሁሉ ያመስግኑታል፡
3 ፀሐይና ጨረቃ ያመስግኑታል፡ ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ
ያመስግኑታል። 4 ሰማየ ሰማያትና ከሰማያት በላይ ያለ ውኃም
ያመስግኑታል። 5 የእግዚአብሔርንም ስም ያመስግናሉ፡ እርሱ
ብሎአልና ሆኑ፡ እርሱም አዝዞአልና ተፈጠሩ። 6 ለዘዓለም
አቆማቸው፡ ትእዛዝን ሰጣቸው አላለፉምም። 7 አባቦችና
ጥልቆች ሁሉ እግዚአብሔርን ከምድር አመስግኑት፡ 8 እሳትና
በረዶ አመዳይና ውርጭ ቃሉን የሚያደርግ ዐውሎ ነፋስም፡
9 ተራሮችና ኮረብቶችም ሁሉ የሚያፈራም ዛፍና ዝግባም ሁሉ
ተንቀሳቃሾችና የሚበሩ ወፎችም፡ 11 የምድር ነገሥታታ
አሕዛብ ሁሉ አለቆች የምድርም ፈራጆች ሁሉ፡ 12 ጐልማሶችና
ደናግል፡ ሽማግሌዎትና ልጆች 13 የእግዚአብሔርን ስም
ያመስግናሉ ስሙ ብቻውን ከፍ፡ ከፍ ብሎአልና በሰማይና
በምድር ያመስግኑታል። 14 የሕዝቡንም ቀንድ ከፍ፡ ከፍ
ያደርጋል የጻድቃኑም ሁሉ ምስጋና ወደ እርሱ ያቀረበ
እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች የሆኑ ሕዝቡን ከፍ ፡ ከፍ
ያደርጋል።

## መዝ ፻፵፱ /149፡ <u>የታላቅ ድል መዝሙር</u>

ሃሌ-ሉያ!-1-ሰብሕዎ-ለእግዚአሔር-ስብሐተ ሐዲሰ=እግዚአብ
ሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት፡ ምስጋናውም በጻድቃኑ
ጉባዔ ነው። 2 እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይለዋል፡ የጽዮንም
ልጆች በንጉሣቸው ሐሤትን ያደርጋሉ። 3 ስሙን በደስታ
ያመስግናሉ፡ በከበሮና በበገና ይዘምሩለታል። 4 እግዚአብሔር
በሕዝቡ ደስ ብሎታልና የዋሃንንም በማዳኑ ከፍ፡ ከፍ
ያደርጋልና ።5-ጻድቃን በክብሩ-ይመካሉ፡-በመኝታቸውም-ላይ-
ሐሤትን-ያደርጋሉ። 6-እግዚአብሔርን- በጉሮሮአቸው ያመስግኑ
ታል፡ ሁለት አፍ ያለውም ሰይፍ በእጁ ነው። 7 በአሕዛብ ላይ
በቀልን-በማድረግ-ሕዝቡን-ይዘልፋቸው-ዘንድ፡-8-ንጉሦቻቸውንም-
በእግር-ብረት፡ አለቆቻቸውንም በሰንሰለት ያስራቸው ዘንድ፡
9 የተጻፈውን ፍርድ በእነርሱ ላይ ያደርግ ዘንድ ይህች ክብር
ለጻድቃኑ ሁሉ ናት።

## መዝ ፻፶ /150፡ <u>ስለ ሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን</u>

ሃሌ-ሉያ!-1-ስብሕዎ-ለእግዚአብሔር-በቅዱሳኑ፡እግዚአብሔርን
በተቀደሱ ቦታዎች አመስግኑት፡ በኃይሉ ፅናት አመስግኑት፡
2-በሁሉን ቻይነቱ አመስግኑት፡ እንደ ታላቅነቱ ብዛት
አመስግኑት፡ 3 በመለከት-ድምፅ-አመስግኑት፡-በበገናና-በመሰንቆ-
አመስግኑት፡ 4 በከበሮና በሽብሸባ አመስግኑት፡ አውታር ባለው
መሣሪያና በእንዚራ አመስግኑት ። 5 ድምፁ መልካም በሆነ
ጸናጽል አመስግኑት። ሃሌ ሉያ ! 6 እስትንፋስ-ያለው-ሁሉ-
እግዚአብሔርን ያመስግነው፡ ሃሌ ሉያ!

www.ethiopianorthodox.org

# መክሥተ አርእስት


| | |
|---|---|
| የአዕማድጥቅሰችመዘከር | 3 |
| መግቢያ-- | 4-5 |
| ፩ /1 በአዲስ ዘመን መለወጫ ዕለት የሚቀርብ የምስጋና ጸሎት | 5 -6 |
| የንጹሐንን ደም የሚበቀል የፍትሕ-አምላክ | 6 -7 |
| ፬ /4. በክርስቶስ የተባረከ ቤተሰባዊ ሕይወት | 7-8 |
| ፭ /5. የእግዚአብሔር ቸር ጠባቂነት | 9-10 |
| ፮ /6. ስለ ምድር አበቦች የሚቀርብ የምስጋና ጸሎት (Thanksgiving ) | 10-11 |
| ፯ /7. ከሐዘን የምንፅናናበት የሕይወት ተስፋ | 11-12 |
| ፰ /8 .አምላካዊ ጠለ ምሕረት የሚገኝበት በረከት | 12-13 |
| ፱ /9. የእግዚአብሔርን ቃል ሁል ጊዜ በማንበብና የሚገኝ ታላቅ ድል | 13-14 |
| ፲ /10. ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚገኝ የሀገር ዕድገትና ብልጽግና | 14-15 |
| ፲፩ /11. በሽምግልና ዘመን የሚያስፈልግ አምላካዊ ጸጋና ኃይለ ረድኤት | 15-16 |
| ፲፪/12 አንደበትን ከክፉ ንግግር የመጠበቅ-ጥበብ | 16-17 |
| ፲፫ /13. እግዚአብሔር-አምላኩ የሆነለት ሕዝብ በረከትና ብልጽግና | 17-18 |
| ፲፬ /14. በእግዚአብሔር ላይ መተማመኛ ጸሎት | 18-19 |
| ፲፭/15- በደልን በመናዘዝ የሚቀርብ ጸሎት (ዳን፡9፡ 4-14)። | 19-20 |
| ፲፮ /16 """ የንስሐ ጸሎት """ (ዳን 9 :15-18) | 20-21 |
| ፲፯ /17. በእግዚአብሔር ላይ የሚተማመኑ የቤተሰብ መሪዎች ጸሎት፣ | 21-22 |
| ፲፰/18.- ከፈተና-ተጠብቆ በድል አድራጊነት የሚኖር ሰው ጸሎትና ምስጋና | 22-23 |
| ፲፱/19. የእግዚአብሔር ሰላም በልባችን ነግሦ እንዲኖር | 23-24 |
| ፳ /20. የእግዚአብሔርን ምሕረትና ትዕግሥት | 24-25 |
| ፳፩ /21. እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን እንዲገልጥልን | 25-26 |
| ፳፪/22፡ ለመላው ዓለም የክርስቶስ ሰላም-አስፈላጊነት | 26-27 |
| ፳፫/23፡ ከጠላት የምንጠበቅበት ጸሎት (መዝ. 30) | 27-28 |
| ፳፬ /24. የወንድሞችና እኅቶች በኅብረት መኖር | 28 |
| ፳፭ /25 ስለ ዝናመ ምሕረትና ጠለ በረከት መማፀኛ-ጸሎት - | 29 |
| ፳፮ /26.. መንፈሳዊ ኃይልና ብርታት የሚገኝበት | 29-30 |
| ፳፯ /27 በሞት ለተለዩ አማኞች ምሕረትን መማፀኛ ጸሎት | 30-31 |
| ፳፰ /28. የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁንም ስለመሻት | 31-32 |
| ፳፱ /29. የወንድሞችንና የእኅቶችን በደል ይቅር ባይ መሆን | 32-33 |
| ፴ /30. የመዳን ተስፋ በክርስቶስ ስም | 33-34 |
| ፴፩ /31. በደልን በመናዘዝ የሚቀርብ የንስሓ ጸሎት | 34 -35 |
| ፴፪/32. ለመንፈሳዊ ድል የሚያበቃ ኃይለ ጸሎት (ኤፌ 6፡ 10 -18) | 35-36 |
| ፴፫ /33 ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው | 36-37 |
| ፴፬ /34 የማኅበር ጾምና ጸሎት(ኢዮኤል 2፡-12-13) | 37-38 |
| ፴፭ /35 ብንወድቅም እንኳ በእግዚአብሔር ኃይል እንነሣለን | 38-39 |
| ፴፮/36. በእግዚአብሔር ኃይል ከድል ወደ ድል (መዝ 44፥1-10) | |
| ፴፯/37፡ የእግዚአብሔርን ቃል የመስማት ጥበብ የሚያስገኝልን ጸጋና ሞገስ | 39-40 |
| ፴፰ /38. መኑ ይክለነ ለእመ እግዚአብሔር ምስሌነ | 40-41 |
| ፴፱ /39. በአደጋ ጊዜ እግዚአብሔር ተረዳኢ መልአኩን እንዲልክን መማፀኛ ጸሎት (ኢዮብ 33፡ 23 -24) | 41-42 |
| ፵ /40. የበደልን ይቅርታ-መጠያቂያ ጸሎተ | 42-43 |
| ፵፩ /41 . ለንጉሥ ኢዮሳፍጥ ታላቅ ድልን ያቀዳጀ አስደናቂ ኃይለ ጸሎት | 43-44 |
| ፵፪ /42. ንጉሥ ሕዝቅያስን ከሞት አፋፍ የመለሰ ኃይለ ጸሎት | 45 |
| ፵፫/43. ዓለምን ያናወጠ የሥራ አጥነት ችግር ሲያጋጥም | 46-47 |
| ፵፬ /44. ልጅ መውለድ የሚፈልጉ መሐኖች በእምነት የሚያቀርቡት ጸሎት | 52 -53 |
| ፵፭ /45. የተማሪዎች አእምሮ መክፈቻ ጸሎት | 48-49 |
| ፵፮/46፡ የምልጃ ጥያቄ | 49-50 |
| ፵፯ /47፥ የማዕድ ጸሎትና ምስጋና | 51-52 |
| ፵፰ /48. በባዕድ አገር የስደት ኑሮ ከችግርና ከፈተና የምንጠበቅበት ጸሎት | 52-54 |
| ፵፱ /49. ከማናቸውም ደዌና ሕመም የምንጠበቅበት ጸሎት | 54-55 |
| ፶ /50፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ-የምትመራ ሕይወት | 55-57 |
| ፶፩ /51. ጻድቅ ብእሲ ይምሕር ነፍስ እንስሳሁ | 57-58 |
| ፶፪ /52. የስደት አገርን ፈተና በማሰብ የቀረበ ጸሎት ( ባሮክ 3፥ 1-12 ) | 58-59 |
| ክፍል- ሁለት፡- ከጸሎተ ቅዳሴያት መደምደሚያ/ -- (ሐዳፌ ነፍስ) | 60-62 |
| ፶፮ /56. የዘመነ ሐዋርያት ጸሎተ ማኅበር ( የሐዋት ሥራ 4 24 -32 ) | 62 -64 |
| ፩ /1. ከሰኞ ሊጠን ጋር የቀረበ የምስጋና ጸሎት፥ | 64-72 |
| ክፍል ዐራት፥ መዝሙረ ዳዊት | 72-193 |


www.ethiopianorthodox.org